# የቃየን መሥዋዕት



ሠርቅ ዳ.

ለ - ጋሼ አቤል አዳም

በምድር የፈሰሰ ደምህ በሰማይ ይጮሃል ...

ፍየል ወዲህ ...

# ክፍል ፩

በመጀመሪያ ... እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን
እንደምሳሌያችን እንፍጠር ... አለ።

*ኦሪት ዘፍጥረት ፩፡፳፮*

እሳርፍ ያለች ጣት ...

## ፩

አዲስ አበባ ...

ቅጭል ... ቅጭል ...

"... ቅጭል ... ቅጭል ..." ይላል ሰንሰለቱ ...

በመረጃው መሥሪያ ቤት፣ በፀረ ስለላ ክንፍ ከምድር በታች ወዳለው የምርመራ ክፍል በሚወስደው ጠባብ መተላለፊያ "...ቅጭል ... ቅጭል..." ይላል ሰንሰለቱ ... የእስረኛው ሰንሰለት ...

የግራውን አስቀድሞ የቀኙን ሲያስከትል ... "... ቅጭል ... ቅጭል ..."

እስረኛው እግሮቹን ባንሸራተተ ቁጥር በሁለት እግሮቹ መሀል ያለው የብረት ሰንሰለት ይወጠራል ... ወደኋላ ያስቀረዋል ... አንገትና ትከሻው በፋሻ የተጠቀለሉት እስረኛ እንዳቀረቀረ በዝግታ ወደፊት ይራመዳል ...

ጠባቡን መተላለፊያ አልፎ ከምርመራ ክፍሉ ሲደርስ በስተቀኝ ክንዱን ይዞት የነበረው የእስር ቤት ጠባቂ በሩን በእርጋታ ከፍቶ ወደ ውስጥ አስገባው ... የብረቱን በር ከውጭ ዘጋው::

አንድ የብረት ጠረጴዛና ሶስት ወንበሮች አሉ - ከውስጥ:: ፊት ለፊት የተቀመጡት ሁለት መርማሪዎች ምርመራውን ለመጀመር ትዕግስት አጥተው ሲጠባበቁ እንደቆዩ በሚያሳጣ መልክ ወንበሮቻቸውን ወደ ጠረጴዛው አስጠጉ::

"ቁጭ በል::"

እስረኛው በሰንሰለት የታሰሩትን ሁለት እጆቹን ዘርግቶ ወንበር ሳበና ተቀመጠ::

"ሻለቃ ፀጋዬ ..." አሉ ከፊት ለፊቱ የተቀመጠው መርማሪ አቤሰሎም "... ጠዋት ከቆምንበት እንቀጥላለን ... እ ... ስለመረቡ ዓላማ ጀምረህ ነበር ያቆምከው ..."

እስረኛው በተሰላቸ መልክ በረጅሙ ተነፈሰ ... በክፍሉ ውስጥ ብቻውን እንዳለ ሁሉ ሁለቱን መርማሪዎች ችላ ብሎ ባሻገር ባለው ነጭ የብረት ቀለም የተቀባው ግድግዳ ላይ አፈጠጠ::

"ሻለቃ ፀጋዬ ጊዜ ባናጠፋ ..." ሁለተኛው መርማሪ እዮብ አጣደፈው::

"ኢትዮጵያ ..." እስረኛው ወንበሩ ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠ ... በተዳከመ መልክ ጀመረ "... ላለፉት ሠላሳ ዓመታት ለዓለም አቀፍ የአደንዛዥ እፅ አቀባባዮች የመሸጋገሪያ ጣቢያ ሆና ነበር የቆየችው ... የወቅቱ፣ የዛሬው እቅድ ግን ኢትዮጵያን እራስዋን ወደ አደንዛዥ እፅ ማሳነት መቀየር ነው:: ኢትዮጵያን የአፍሪካ አፍጋንስታን፣ ፔሩና ኮሎምቢያ ማድረግ ነው! ኢትዮጵያን የኦፒየም፣ የኮካና የካናቢስ አምራችና ላኪ አድርጎ ዳግም መፍጠር ነው::"

"ለምን? ... ለምን ኢትዮጵያ? " ቀጠን ረዘም ያለው መርማሪ እዮብ ጭንቅላቱን ወደ አንድ ወገን ዘመም አድርጎ ጠየቀ::

"በየትኛውም አቅጣጫ ብትመለከቱት ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ለሕገወጥ የአደንዛዥ ዕጽ ማሳነት ምቹ ናት::" አለ ተመርማሪው በአንገቱ ዙሪያ የተጠመጠመውን የቁስል ፋሻ ዳበስ አድርጎ " ... የሕዝቧ ድህነት ... ተስፋ መቁረጥ፤ የወጣቱ ትውልድ ሥራ አጥነት፣ ግራ መጋባት፣ አላማ ማጣት፤ በተደላደለ የኑሮ ደረጃ ላይ ያለው ክፍል ሳይቀር ለተሻለና ለተቀማጠለ ኑሮ ያለው ጉጉት ... ሁሉንም በየአቅጣጫው ብታጤኑት ምናልባት ከመቼውም ጊዜ በላይ ለገንዘብ ያለንን ተገዢነት በቁርጠኛነት ያረጋገጥንበት ጊዜ ቢኖር ዛሬ ነው ያስብላል::"

ተመርማሪው ድንገት ፈገግ አለና በብረት ጠረጴዛው መሀል ተቀምጦ በእርጋታ "ስ ... ስ ... ስ" እያለ፣ እየተሽከረከረ ሦስቱ ሰዎች የሚመላለሱትን በሚቀዳው፣ በሚያጠነጥነው የድምፅ መቅጃ ላይ አይኖቹን ተከለ::

"... ትዝ ይላችሁ እንደሆን ባለፉት ጥቂት ዓመታት ጽላቶች ሳይቀሩ ከቅድስተ ቅዱሳን መጋረጃ ውስጥ እየተመነተፉ የወጡት፤ የተቸበቸቡት ለሌላ አልነበረም ... ለገንዘብ ነው:: በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም፤ ድህነት አንፈራጦ በቆመበት ሁሉ ለገንዘብ ሲሉ ማንኛውንም ለመፈጸም ፈቃደኛ የሆኑ ወንጀለኞችን ማግኘት ቀላል ጉዳይ ነው ... ሐይማኖት ሥር በሰደደበትና ሌላው ቀርቶ እያንዳንዷን ቀን "ልደታ ... በዓታ..." እያለ በሚቆጥር ሕብረተሰብ ውስጥ ታቦቱ እራሱ ገበያ ከወረደ ሌላ ለማድረግ የምንፈራውና የምንሰቀቀው ጉዳይ አለ ለማለት ይከብደኛል::"

"ይገባኛል ..." አለ አቤሰሎም መሀል ገብቶ " ... ግን ለድህነቱ ከሆን ሌሎች የአፍሪካ አገሮችም ... በእስያም ... በላቲን አሜሪካም ..." ድንገት እንደጀመረ ድንገት አቋረጠና ትክሻውን ሰበቅ አድርጎ " ... ኢትዮጵያ ውስጥ ምን የተለየ ነገር ተገኘ?"

"በመጀመሪያ ደረጃ የመሬቷ ለምነትና የአየር ንብረቷ አመቺነት ማንኛውንም የአደንዛዥ እፅ ተክል ሊታበቅልባት ያስችልሀል:: ሞቃትና እርጥበት አዘል የሆነ አየር ከሚፈልጉት ከኦፒየም ፖፒና የኮካ ቅጠል ጀምረህ እስከ ደረቁ ጂምሠን ዊድ ድረስ ለተለያዩ የእፅ ተክሎች ተስማሚ የሆነ የአየር ንብረት አላት::"

ቀጥሎ ካለው ክፍል ውስጥ የአንድ ሴት ተመርማሪ የስቃይ ጩኸት፣ ማንቋረር ሲሰማ ተመርማሪው አይኖቹን በግድግዳው ላይ ተክሎ ለአንድ አፍታ ዝም አለ:: ወድያው ሀሳቡን አሰባስቦ ቀጠለ::

"... ሌላው የደህንነት ጥያቄ ነው:: እያችሁ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ ወዲህ የምዕራቡም ሆነ የምሥራቁ አለም አትኩሮት በተለይ በአሸባሪዎችና በአደንዛዥ እፅ አምራቾችና አቀባባዮች ላይ ሆኗል:: እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በተለይ ከ1994 ወዲህ ጊዜው ለአደንዛዥ እፅ ከበርቴዎች ጨልሟል:: የ1994ቱን የሰላሳ አራት አገሮች የማያሚ ስምምነትን ተከትሎ የመጣው አደን ለታላላቅ የእፅ ከበርቴዎች ማብቂያ ነው የሆነው:: እነ ዲሚትሮ ቻቬዝ፣ ፔኔራራና ኤልያስ አልቫቲካኖ ከፔሩና ከኮሎምቢያ፣ የገልፉ ሰብሰብና የአሬላኖ ፌሊክስ ቡድን በሜክሲኮ፤ በታይላንድም የከሆን ሳ ሽፍቶች ... ሌሎችም አንድ በአንድ

የተሰቀሙት በጥቂት አመታት ውስጥ ነው:: በላቲን አሜሪካና በደቡብ ምሥራቅ እስያ ለአደንዛዥ እፅ ከበርቴዎች ዙሪያው ገደል ሆኖባቸዋል::"

ተመርማሪው ንግግሩን ገታና ማጅራቱን እያሻሸ " ... እባካችሁ ሲጋራ ካላችሁ ... " አለ::

አቤሰሎም ፈጠን ብሎ ከግራ የኮት ኪሱ አንድ ፓኬት ማርልቦሮ ሲጋራ እና ክብሪት ጠረጴዛው ላይ ወርወር አደረገለት:: ተመርማሪው በእርጋታ ሲጋራውን እያያዘና ቀጠለ:-

"አደጋው በከበርቴዎች ላይ ብቻ ያነጣጠረ አይደለም:: በእጹም ላይ ነው:: ለምሳሌ በ1990 አጋማሽ ላይ የኮሎምቢያ መንግሥት ዘጠኝ ሺህ ሔክታር የኮካና የኦፒየም ፖፒ ማሳ በአውሮፕላን አቃጥሏል:: በእስያም በ1994 ብቻ በበርማ፣ በፓኪስታንና በአፍጋኒስታን ወደ አምስት ሺህ ሔክታር የሚጠጋ የኦፒየም ፖፒ ማሳ አቃጥለዋል:: ይህ ቀላል እንዳይመስላችሁ:: በኦፒየም ፖፒ ምርታማነቷ ብዙም በማትጠቀሰው በላኦስ አቅም እንኳን ከአንድ ሔክታር በዓመት በአማካኝ 720 ኩንታል የኦፒየም ፖፒ ቅጠል ይታፈሳል:: ይህ እንግዲህ ከተጣራ በኋላ አንዷ ግራም አስቡት ... አንዷ ግራም በዩናይትድ ስቴትስና በአውሮፓ ገበያዎች እስከ 110 የአሜሪካ ዶላር ታወጣለች ... እንግዲህ አንዱ ኪሎ 110 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ተሸጠ ማለት ነው:: ይህንን በእኛው ቢላቢሎ ብር ብታሰሉት አንድ ኪሎ አንድ ሚሊየን ብር ማለት ነው:: በአመት ከአንድ ሔክታር የሚሰበሰብን 72 ሺህ ኪሎ ግራም አደንዛዥ እፅ የገበያ ዋጋ እናንተው አስሉት ... ንገረንም ካላቸሁ ... አንድ ግራም ኮኬይን ወይም ሔሮይን ከሰባት እስከ አስራ ሦስት ግራም ንፁህ ወርቅ ያወጣል:: እንግዲህ በላቲን አሜሪካና በደቡብ ምሥራቅ እስያ እሳት እየበላው ያለው ይህን ነው::

"እና? ... ይሔ በላቲን አሜሪካና በእስያ የሚቃጠል ቅጠል ከኢትዮጵያ ጋር ምን ያገናኘዋል?" እዮብ መሀል ገብቶ::

"በቀጥታ ይገናኛል::" አለ ተመርማሪው በወንበሩ ላይ ወደፊት ፎቀቅ ብሎ "... የኮሎምቢያን ኢኮኖሚ ያፋፋ ገበያ ኢትዮጵያን የሚያጫጫ ይመስላችኋል? በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ አንድ ድሀ ገበሬ ሩብ ሔክታር ብቻ ቢያለማና ያልተጣራውን አንድ ኪሎ አደንዛዥ እፅ የላቲን አሜሪካ ገበሬ በሚሸጥበት ሀያና ሀያ አምስት የአሜሪካን ዶላር መሸጡን ትቶ በግማሽ ዋጋ ኪሎውን በአስር የአሜሪካን ዶላር ቢሸጥ እንኳን አንድ ሚሊየን ሁለት መቶ ሺህ ብር ያገኛል:: ደፍሮ አንድ ሔክታር ያለማ በአመቱ በእጁ ላይ አምስት ሚሊየን ብር አለ:: ገበሬውን ተውት ሰፋፊ መሬት በእጁ ነው:: ከወር ወር በጥቂት መቶ ብሮች የሚንደፋደፍ የመንግሥት ሠራተኛ ለነፍሱ ቢያውቅላት፣ ያለችውን ጓሮ አደንዛዥ እፅ ቢያበቅልባት ከሁለት መቶ ካሬ ሜትር ላይ በአመት ከአስራ አራት ኩንታል በላይ ያልተጣራ አደንዛዥ እፅ ያገኛል ይህን ወደ ብር ብትለውጡት በአመት ግማሽ ሚሊየን ብር ማለት ነው::"

"ይሔ ሁሉ ገበሬ አደንዛዥ እፅ ሲያመርት መንግሥት ምን ይሰራል?" አለ አቤሰሎም ፈገግ ብሎ::

"መንግሥት?" አለ እስረኛው በተራው ፈገግ ብሎ ጥያቄውን ለእራሱ መልሶ እየደገመ "... መንግሥት ምንም ማድረግ አይችልም ... እየህ የኢትዮጵያ መልክዓ ምድር ወጣ ገባ ነው:: እንደ ላቲን አሜሪካና ደቡብ እስያ በአውሮፕላን እየተንሳፈፍክ ልታቃጥለው፣ የኬሚካል መርዝ ልትረጭበት የሚያስችልህ

አቀማመጥ የለውም፡፡ በሁለተኛ ደረጃም በሜክሲኮና በኮሎምቢያ እንደተደረገው በመሬት እየተንቀሳቀስክ የአደንዛዥ እፅ ማሳ ለማቃጠል ብትሞክር የመገናኛ ችግር ይገታሀል፡፡ ያንንም አልፈህ ወደ አደንዛዥ እጽ ማሳዎች መጠጋት ሞክረህ ቢሳካልህ እንኳ የሚበላውና የሚለብሰው የሌለው ድሀ የኢትዮጵያ ገበሬ አደንዛዥ እፅ እያመረተ በቀላሉ ሀብት ማካበት ከጀመረ ወዲያ፣ ገና በስምንትና በዘጠኝ አመቱ ነፍጥ እያንጠለጠለ ቆላ ደጋ የሚል የገበሬ ልጅ አውቶማቲክ ጠመንጃዎችና ላውንቸሮች ካነገበ ወዲያ ማሳውን ልታቃጠል ስትውተረተር እንደ ኮሎምቢያ የዋህ ገበሬ ህፃናት ልጆቹን ግራና ቀኝ አቅፎ ይዞ 'ሳንታ ማርያ!' እያለ ሰወሳዲተ አምላክ የሚያሳቅልህ ይመስልሀል? አይምሰልህ፡፡ መጀመሪያ ነገር ከደጃፉ አትደርስም፡፡ የኢትዮጵያ ገበሬ እጹን አምርቶ ጥቅሙን ካጣጣመ ወዲያ ማንም አያቆመውም ... ራሱን ተከላክሎ ምርቱን ለአቀባባዮች ያስረክባል ... ሽፍታነት ባህላችን ነው፡፡"

"ለአቀባባይ ያስረክባል!" አለ አቤሰሎም በመገረም ፈገግ ብሎ "...ማነው የሚያቀባብለው ... መንግሥት ዝም ብሎ ያያል እንዴ ...?"

"መንግሥት እራሱ ያቀባብላል!" አለ ተመርማሪው በተራው ስቆ ... እያየነው! ... መንግሥትኮ የጥቂት ግለሰቦች ጥርቅም ነው፡፡ ምን ነካችሁ? የትኛው የኢትዮጵያ ባለሥልጣን፣ የትኛው የአፍሪካ ባለሥልጣን ነው ለገበያ የማይቀርብ? እርግጥ ዋጋው ወደድ ሊል ይችላል ... ለዛውም የአንዳንዱ፡፡ እስቲ እንደው ማን ይሙት በጥቂት አስር ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላሮች ማነው የማይሸጥ የማይገዛ? ዛሬ ቅቤ ቀብተን ነገ የምንላጨው ፖለቲከኛ ነው?"

"እ ... ቢሆንም ሁሉም ለገንዘብ የሚንበረከክ ነው ለማለት ይቸግረኛል ... ለንጹህ ሕሊናቸው የታመኑ አሉ፡፡" አለ አቤሰሎም በስሱ ፈገግ ብሎ፡፡

"እነሱን ተዋቸው፡፡" አለ ተመርማሪው ቀኝ እጁን አወናጭፎ " ... እነሱ መንግሥታቸው እንደ እየሱስ በሰማይ ቤት ነው፡፡ በ1984 የኮሎምቢያውን የፍርድ ሚኒስትር በ1989 እና በ1993 ደግሞ አሁንም የኮሎምቢያውንና የሜክሲኮውን እጩ ፕሬዚዳንቶች በወጡበት ያስቀራቸው ኮሌራ ይመስልሀል ወይስ ጥላወጊ? አልሸጥም ያለን ዕፆ መጋዘን ታወርደዋለህ፡፡ እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ግን ዛሬ በዚህች ምድር፣ በኢትዮጵያ፣ ገዢያቸው ከበር ቆሞ ሳንቲሞች ሲያቃጭል ወደ ምድር ቤት፣ ወደ መጋዘን መውረድ የሚመርጡ አሉ ብትሉኝ ለማመን ያስቸግረኛል፡፡" አለ ተመርማሪው ፊት ለፊት የተቀመጡት መርማሪዎቹ ላይ አፍጥጦ፡፡

"ስለዚህ በአጭሩ ... ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ የአደንዛዥ እፅ ከበርቴዎች አይን ማረፊያ ሆናለች ነው የምትለን፡፡" አለ እዮብ በተቀመጠበት ወንበር ላይ ለጠጥ ብሎ እንደ ማሸፍ እየቃጣው፡፡

"አፍሪካ በጠቅላላው ..." አለ ተመርማሪው "... ሆኖም ይበልጥ ተመራጭነት ያላቸውና በቅድሚያ የተተኮረባቸው ደቡብ አፍሪካ፣ ኢትዮጵያና ናይጄሪያ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ የአደንዛዥ እፁን በማምረት፣ ናይጄሪያ ከዚህ ቀደምም ባላት የማቀባበልና የማዘዋወር፣ ደቡብ አፍሪካ ደግሞ ካላት የማምረት አቅሟ በተጨማሪ በግልፅና በስውር በተደራጀው የላቦራቶሪ ብቃቷ፡፡ እነዚህ መነሻ ናቸው፡፡ በሚቀጥሉት ጥቂት አስርተ ዓመታት ግን በዓለም አቀፍ ደረጃ ዋነኛ የአደንዛዥ እፅ ምንጭ የምትሆነው አፍሪካ ነች፡፡"

"ምናልባት ደቡብ አፍሪካና ናይጄሪያ በተለይ የቴክኒካዊ ብቃታቸው ተመራጭ አድርጓቸዋል እንበል? ኢትዮጵያ ግን ..." አለ እዮብ እንደ ማመንታት ብሎ " ... ማለቴ ተመሳሳይ የአየር ንብረት ያላቸው የአፍሪካ አገሮች እያሉ ... "

"የአየር ንብረት ብቻ አይደለም ..." አለ ተመርማሪው መሀል ገብቶ "... ጂኦግራፊካዊ አቀማመጧ በራሱ ለማምረት ብቻ ሳይሆን ለማሰራጨትም አመቺ ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ አምርተህ ቀጥታ የቀይ ባሕርን አሻግረህ የመካከለኛውን ምሥራቅ፣ ወደ ላይ የሜድትራንያንን አልፎም የአውሮፓን ገበያ፤ በታችም በባበል ሰርጥ እስያን ለማዳረስ ትችላለህ:: ከዛ በተረፈ ያላት የቆዳ ስፋት የኮንትሮባንድን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ፍጹም የማይሞከር ያደርገዋል:: የፈለግከውን የእፅ ክምችት ምንም ጥበቃ በማይደረግለት ዙሪያ ድንበሯ እንዳሻህ ወደ ውጭ ማውጣት ትችላለህ:: በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት በያዘው ዕቅድ ..."

አቤሰሎም አቋርጦት የድምፅ መቅጃውን አቁሞ ከመቀመጫው ተነሳ::

"ይቅርታ..." አለ በተቻለው መጠን ስሜቱን አፍኖ ይዞ "እዮብ አንድ ጊዜ ውጭ ባነጋግርህ::"

ሁለቱ መርማሪዎች ከምርመራ ክፍሉ እንደወጡ አቤሰሎም ሁለት እጆቹን ወደፊት ዘረጋና ቆመ::

"ምን ሆንክ?" እዮብ ግራ ተጋባ::

"ምን 'ምን ሆንክ' ትለኛለህ? ... " አለ አቤሰሎም "... እየቀለደብን ነው'ኮ ያለው::"

"ምን ማለትህ ነው?"

"ለሽፋን ያዘጋጀውን ተረት ነው'ኮ እየተረተረልህ ያለው!" አቤሰሎም በስጨት አለ "... መንግሥት ባለበት አገር ... "

"አቤሰሎም ..." አለ እዮብ እያመነታ "... መንግሥት ባለበት አገር' ብለን ለመደምደም ትንሽ የሚያሸቸግር ይመስለኛል ... የመንግሥት የመንግሥትማ አደንዛዥ እጽ በሚያመርቱና በሚያስተላልፉ አገሮች ውስጥስ መንግሥት መች ጠፋ? መንግሥት ውስጥ ያሉት'ኮ ያው ግለሰቦች ናቸው ... እርሱ እራሱን ውሰደው ... የመከላከያ አባል አይደል እንዴ? መንግሥት ማለት'ኮ ያው ... እሱ ... እኔ ... አንተ ማለት ነው::"

"ለነገሩ እዎ ... ግን ሰውየው ሳይጠየቅ ነው'ኮ የሚተረተረው ... ምንድነው ይሄ?"

"ለምን አናስጨርሰውም?"

"ምኑን ነው የምናስጨርሰው? ስለራሱ'ኮ አይደልም የሚያወራው!"

"ጥሩ ጥሩ ... " አለ እዮብ ባልደረባውን እያረጋጋ "... በተቻለ መጠን እያጠበበ እንዲሄድ እንሞክራለን::"

መርማሪዎቹ ተመልሰው ወደ ምርመራው ክፍል ገቡ::

"በአጭሩ ኢትዮጵያ ለአደንዛዥ እፅ ከበርቴዎች ገነት ነች ማለት ነው::" አቤሰሎም ቀጠለ::

"ትክክል ..." አለ ተመርማሪው የአቤሰሎምን ፌዝ ችላ ብሎ "... ዋና ዋና በሆኑት አቅጣጫዎች ብትመዘን ኢትዮጵያ በሚገባ ታዋጣለች:: አንደኛ የአየር ንብረቷ ተስማሚነት፤ ሁለተኛ የአደንዛዥ እፅ ከበርቴዎችን የሚገጥማቸው ዝቅተኛ የደህንነት ስጋት፤ ሶስተኛ የአምራቹና የአቀባባዩ ድህነትና ችግር የሚፈጥረው ሙሉ ፈቃደኝነትና ዝቅተኛ የማምረቻ ወጪ አራተኛ አገሪቷ ለገበያው ያላት ጂኦግራፊካዊ ቀረቤታ ... ኢትዮጵያ ሁሉንም በሚገባ ታሟላለች::"

"መቼ ነው ይህንን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚታሰበው? " እዮብ::

"ተግባራዊ ሆኗል:: " አለ ተመርማሪው ያለቀች ሲጋራውን ምጥጥ አድርጎ እግሩ ሥር ጥሎ እየደፈጠጣት " ... የወንጀሉ መረብ ላለፉት ሦስት ዓመታት ራሱን ሲያደራጅና መረቡን ሲዘረጋ ነው የቆየው:: አሁን ያለነው በማምረት ዝግጅት ላይ ነው::"

"ለሶስት ዓመታት ነበር ማለት ነው በዚህ የወንጀል መረብ ውስጥ የቆየኸው?" አቤሰሎም ፈርጠም ብሎ ጠየቀ::

"አይደለም::" አለ ተመርማሪው ወንጀሉን ለማቅለል ያሰበ ይመስል ቀኝ እጁን አንስቶ "... እኔ ባለፈው ዓመት ጥር ውስጥ ነው የተመለመልኩት::"

"ማነው የመለመለህ?"

"አለቃዬ::"

"ማነው አለቃህ?"

"ኮሎኔል ገዳሙ አደፍርስ::"

"የኃላፊነት ቦታቸው?"

"እስካለፈው የካቲት ድረስ ለስድስት ዓመታት በመከላከያ ሚኒስቴር የሎጂስቲክስ ክፍል ኃላፊ ነበሩ::",

"ያንተ የሥራ ድርሻ ምንድን ነበር?"

"ቀድሞ ... ማለቴ ከሁለት ዓመታት በፊት በመከላከያ ሚኒስቴር ሂሳብ ክፍል ውስጥ ነበርኩ:: ከዚያ ወዲህ ግን የኮሎኔሉ 'ልዩ ፀሐፊ' የሚል ነበር የኃላፊነት ደረጃዬ::"

"እንዴት ነው ኮሎኔሉ የመለመሉህ?"

"የመለመሉኝ ..." አለ ተመርማሪው በመዳከም መልክ በረጅሙ ተንፍሶ "... ባለፈው ዓመት ጥር ውስጥ ነበር ... ቀስ በቀስ ሳይታወቀኝ ነበር በወንጀል መረብ የተበተቡኝ:: አያችሁ እንደዚህ ባለ የወንጀለኞች እንቅስቃሴ ውስጥ ለእንቅስቃሴው መሠረት የሚሆን ፍልስፍና የለም:: የምትመለምለውን ሰው የምታስጠናው፣ እምነት ወይ አመለካከት የለም:: ብር ታቀምሰዋለህ፤ ወንጀል ታሰራዋለህ ሁለቱ ተጋግዘው ከማያመልጥበት መቀመቅ ይከቱታል::"

ተመርማሪው ከፊቱ የተቀመጠው የሲጋራ ፓኮ የራሱ የሆነ ይመስል አንድ ሲጋራ መዝዞ በእርጋታ ለኩሰና ቀጠለ፡-

"... የእኔ አመላመል ግን ትንሽ የተለየ ነበር:: ባለፈው ዓመት ጥቅምት አካባቢ ባልተጠበቀ የሒሳብ ማጣራት ሰላሳ ሺህ ብር ተመዘበረ ተባለ:: ገንዘቡን እንዳላጠፋሁ ባውቀውም ማስረጃዎች ሁሉ ወደ እኔ ነበር የሚጠቁሙት:: ለሳምንታት ከሥራ ታግጄ ቆየሁ:: ወዲያው ታህሳስ ውስጥ ወደ ሥራዬ እንድመለስ ተደረገ፤ ጠፋ የተባለውም የገንዘብ ጉዳይ ተድበስብሶ ቀረ:: ውስጥ ውስጡን ግን የማጣራቱ ሥራ እንዲቋረጥ ያዘዙት ኮሎኔል እንደነበሩ ይወራ ነበር::"

ለምን? ... ለምንድነው እንዲቋረጥ ያዘዙት?"

"ያኔ እኔም እራሴ አልገባኝም ነበር:: እንደ ውለታ ነበር የቆጠርኩት:: አሁን ሳስበው ግን አለቃዬ ያደረጉት የነበረው እንደ ፈለጉ ሊቆጣጠሩት የሚችሉት 'እምቢ' ካለም በፈቀዱት ወቅት በቀላሉ እሳት ውስጥ ሊጨምሩት የሚችሉትን የሥጋ ቁራጭ ከእጃቸው ማስገባት ነበር::"

"ተገድጄ ነው ወደ ወንጀል የገባሁት እያልክ መሰለኝ ..." አለ እዮብ ወደ ኋላ ለጠጥ ብሎ::"

"አይደለም:: ..." አለ ተመርማሪው ፈገግ ብሎ "... በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ብዙም ከባድ ወንጀል እንድሠራ አላስገደዱኝም:: ጥቃቅን ጉዳዮችን እንድፈጽምላቸው በትዕዛዝ መልክ ሳይሆን በባለውለታ ለዛ ይጠይቁኝ ነበር:: ለምሳሌ ሰነዶችን ፎቶ ኮፒ አድርጌ እንዳወጣ ጠይቀውኝ አድርጌዋለሁ:: ቀስ በቀስ ግን ወንጀል ውስጥ እየተተበተብኩ መጣሁ:: በመጨረሻ የሐምሌውን የመሳሪያ ስርቆት አቀናጀሁ::"

"እንዴት? "

"በእኚሁ አለቃዬ ትዕዛዝ በጠቅላይ ግምጃ ቤት የሚገኙ አራት መቶ የድምጽ ማፈኛ ያላቸው የብሬታ ሽጉጦች፣ አርባ ስምንት አውቶማቲክ ጠመንጃዎች፣ ጥይቶችና ሲ-አራት ልቁጥ ፈንጂዎች ሌሎችም መሣሪያዎች ወደ ደብረዘይት አየር ኃይል እንዲጓጓዝ በተደረገበት ወቅት ከዱከም ወጣ ብሎ ቀድሞ በተዘጋጀ የወንበዴዎች የደፈጣ ኃይል መሣሪያዎቹ እንዲዘረፉ ከዘራፊዎቹ ጋር ሠርቻለሁ::"

"መሣሪያዎቹ ሲዘረፉ እዛው ነበርክ?"

"አልነበርኩም ... ሆኖም መሣሪያዎቹ ስለሚጓጓዙበት ሁኔታ በቂ መረጃ ስለነበረኝ የዘረፋውን ዕቅድ ዝርዝር ቅደም ተከተል የነደፍኩት እኔ ነበርኩ። ዘረፋውም ሲካሔድ ከዘራፊዎቹ ጋር በአጭር ሞገድ ሬድዮ እየተገናኘሁ ተከታታይ መመሪያ አስተላልፍላቸው ነበር። ከዘረፋውም በኋላ ክትትሉ በተሳሳተ አቅጣጫ እንዲሄድ መረጃዎችን አሳክሬአለሁ።"

"ስለዝርፊያው የተደረገ የማጣራት ምርመራ አልነበረም?"

"ነበር ... ግን የአጣሪው ኮሚቴ ሰብሳቢ እኔ ሆኜ ምርመራው የት እንደሚደርስ ልትገምት ትችላለህ።" አለ ተመርማሪው።

"ቀጥሉስ?"

"በወንጀል ላይ ወንጀል በደራረብኩ ቁጥር አለቃዬ በእኔ ላይ የነበራቸው እምነት ሥር እየሰደደ ሔደ። በሌላ በኩል ደግሞ በጥቂት ወራት ውስጥ ፍጹም አልሜው የማላውቀው ገንዘብ እጄ ይገባ ስለነበር የምሠራውን አላውቅም ነበር።"
"የምን ገንዘብ? "

"በእኚሁ አለቃዬ በኩል በጉርሻ መልክ ይሰጠኛል። እጅግ በርካታ ገንዘብ በአጭር ጊዜ አጠራቀምኩ። ቢሆንም ዋጋ አልነበረውም።

"ለምን? " አለ አቤሰሎም።

"ትፈራለህ? ... " አለ ተመርማሪው አቤሰሎምን እየተመለከተ "... ዓመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ያጠራቀምኩትን ከአራት መቶ ሺህ ብር በላይ የሚሆን ብር እንደልቤ ልመነዝር ቀርቶ ያለችን አሮጌ መኪና ብቀይር እንኳን በዙሪያዬ ያሉ ሁሉ ቀደም ብሎ ተሰረቀ ከተባለው ሰላሳ ሺህ ብር ጋር ያያይዙብኛል ብዬ ስለሰጋሁ የምቀበለውን ገንዘብ እቤቴ ደብቄ ከማስቀመጥ ውጪ ምንም ላደርገው አልቻልኩም ነበር።"

"ይህንን ሁሉ ገንዘብ ስትቀበል በምትኩ ምን ሰርተሃል?"

"አቅሜ የፈቀደውን ሁሉ አድርጌአለሁ። ያልሰራሁት ወንጀል የለም። መረጃዎችን መስረቅ፤ ማስረጃዎችን ማሳከር፣ ሰዎችን ማፈንና መግደል። በተለይ ባለፈው ኅዳር ወር የመከላከያ ሚኒስቴር ከወታደራዊ ደህንነት ጥበቃ ጋር ባለው የውስጥ ግንኙነት አማካኝነት ከኢንተርፖል ጋር ባደረገው ስምምነት ለሁለቱ ድርጅቶች እንደ አገናኝ መኮንን ሆኜ እንድሰራ ከተደረገ በኋላ በርካታ መረጃዎች እጄ ይገቡ ስለነበር ለዕቅዱ መሳካት ብዙ ሰርቻለሁ።"

"በአገናኝ መኮንንነትህ ምንድን ነበር ዋንኛ የሥራ ድርሻህ? "

"እየህ ... ኢንተርፖል ቀጥተኛ ግንኙነት የሚያደርገው ከፖሊስ ሠራዊት ጋር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የወታደራዊ መረጃ ክፍሉ ከኢትዮጵያ ፖሊስ ሠራዊት ጋር ባለው ግንኙነት ከኢንተርፖል ቢሮ ጋር ቀደም ሲልም የመረጃ መለዋወጥ ሁኔታ ነበር። እንግዲህ ይህን ቀጭን መስመር ተጠቅሞ ነው የወንጀል መረቡ የኢንተርፖልን መረጃ መረብ ሰብሮ ለመግባት የቻለው ... ኢትዮጵያ ውስጥ።"

"ግልጽ አድርገው::" አለ አቤሰሎም ጥርሱን ገጥሞ::

"እንዴት መሰላችሁ ..." አለ ተመርማሪው ግንባሩን ፊተግ አድርጎ " ... በመሠረቱ ኢንተርፖል ማንኛውም ወንጀል ላይ የሚረባረብ ይምሰል እንጂ ዋንኛ አትኩሮቶቹ በአንደኛ ደረጃ አለም አቀፍ ሽብርተኞችን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የአደንዛዥ እፅ ዝውውር መስመሮችን መስበር ናቸው::"

"እህ:: " አለ እዮብ በመስማማት እራሱን ነቅንቆ::

"ይህ ማለት ደግሞ ... " ቀጠለ ተመርማሪው:: " ... በአንድ በኩል በኢትዮጵያ ያለው የኢንተርፖል ቢሮ በዓለም ዙሪያ ስለሚካሔደው ፀረ አደንዛዥ እፅ እንቅስቃሴዎች በቀጥታ ከዋናው መሥሪያ ቤት መረጃዎችን ያገኛል:: በአንፃሩም በኢትዮጵያ ውስጥ ያሰባሰበውን ጠቃሚ መረጃ ሁሉ ያለምንም ማዘግየት በኢንተርፖል ማዕከላዊ የመረጃ መረብ የማስገባት ኃላፊነት አለበት:: እንግዲህ እኔ የመከላከያ ሚኒስቴርን ወክዬ በወታደራዊ መረጃ ክፍሉ ውስጥ እንደ አገናኝ መኮንን ሆኜ ስሰራ ወደ እዚህ ማዕከላዊ የመረጃ መረብ የምገባበት የሚስጥር ቁጥር ስለተሰጠኝ ወቅታዊ መረጃዎችን ከተለያዩ ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች በቀላሉ አገኛለሁ::"

"እነማናቸው እነዚህ ድርጅቶች ... የኢንተርፖል ቢሮዎችን ማለትህ ነው?"

"ኢንተርፖል ብቻ አይደለም:: ሌሎች በርካታ ድርጅቶች አሉ:: ዓለም አቀፍ የአደንዛዥ እፅ መቆጣጠሪያና ሕግ አስፈጻሚ ቢሮ፤ የዩናይትድ ስቴትስ ዓለም አቀፍ የአደንዛዥ እፅ መቆጣጠሪያ ፕሮግራም ... ሌሎችም ... በርካታ ናቸው::"

"እና ከእነዚህ ሁሉ መረጃ ታገኝ ነበር ማለት ነው?" አለ እዮብ::

"የይለፍ የሚስጥር ቁጥር እስካለህ ድረስ በቀጥታ ወደ ኢንተርፖል ማዕከላዊ የመረጃ መረብ ገብተህ በደቂቃዎች ውስጥ የፈለከውን መረጃ ማግኘት እጅግ ቀላል ጉዳይ ነው:: ለምሳሌ ናይጀርያዊው የአደንዛዥ እፅ ከበርቴ የጆን አክፓላ ቀኝ እጅ የነበረው ቪንሰንት ሻቲካኖ ከላአስ ተነስቶ በአዲስ አበባ ትራንዚት ወደ ካይሮ እንደሚበር እንደታወቀ የናይጄሪያ ብሔራዊ የአደንዛዥ እፅ መከላከያ የኢትዮጵያን የፖሊስ ኃይል ትብብር በጠየቀበት ወቅት መልዕክት አስተላልፌ ቤጂንግ ላይ መስመር ቀይሮ እንዲያመልጥ ያደረኩት እኔ ነኝ:: የእዚህ ዓይነት በርካታ ሥራዎችን ሰርቻለሁ:: በመሀሉ ግን አንዳንድ ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ እየሆኑ መጡ::"

"ምንድነው ከቁጥጥር ውጭ የሆነው?" አለ አቤሰሎም ጭንቅላቱን ወደ ጎን ዘንበል አድርጎ::

"ልገልፀው በማልችለው መንገድ በጦር ሠራዊቱ ውስጥ የነበሩ የመረቡ አባላት በተለያዩ ቦታዎች ይገደሉ፤ የተቀሩት ይሰወሩ ጀመር:: እርግጥ ተንቀሳቃሽ አባላት በየዕለቱ ያበቃሉ ... ማለቴ ይሞታሉ ... መደበኛ አባላት ግን ... "

"ምን ማለትህ ነው መደበኛና ተንቀሳቃሽ አባላት ስትል?" አለ እዮብ::

ድንገት የድምጽ መቅጃ መሣሪያው የጎረሰውን ክር ሲጨርስ እዮብ 'አቁም' የሚል ምልክት በእጁ ለተመርማሪው ሰጠውና ሌላ ክር ድምፅ መቅረጫው ውስጥ ከቶ -

"ቀጥል::" አለ::

"መደበኛ አባላት የምልህ እንደ እኔ ቋሚ የመረቡ አባላት ናቸው:: ለምሳሌ ከጦር ሠራዊት ውስጥ የተመለመልን ስድስት የመረቡ አባላት ነበርን:: እነዚህን በሙሉ አውቃቸዋለሁ:: በተመሳሳዩ ከፖሊስ ኃይል ከሌሎችም የተመለመሉ ሆኖም የማላውቃቸው መደበኛ አባላት አሉ:: በሌላ በኩል ግን 'ተንቀሳቃሽ' የሚባሉት ተባራሪዎች ናቸው! ተራ የእሳት እራቶች:: አንድ ተንቀሳቃሽ አባል ለአንድ ግዳጅ በገንዘብ ሀይል፣ በማስፈራራት፣ በወሲብ በማባበል በሌላም በሌላም ዘዴ ይመለመልና የተሰጠውን ግዳጅ ዳር ካደረሰ በኋላ ይገደላል::"

"ለምን?" አለ አቤሰሎም ፊቱን አጨማዶ::

"በዝርዝር ግዳጆች ውስጥ መደበኛ አባላት ከተካፈሉ ለአደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ:: ተንቀሳቃሽ አባላት ግን ለአንድ ውሱን ሥራ ብቻ የተመለመሉ በመሆናቸው ቢያዙ እንኳን ለመረቡ ጉዳት የለውም:: ቢሆንም ለደህንነት ሲባል በተለይ ከፍተኛ ወንጀል እንዲፈጽሙ የተደረጉ ተንቀሳቃሽ አባላት ግዳጃቸውን ከፈጸሙ በኋላ ይወገዳሉ::"

"ገባኝ ... ቀጥል::"

"እና እንዳልኩት የእነዚህ ተንቀሳቃሽ አባላት መወገድ የተለመደ አሠራር ነው:: መደበኛ አባላት ግን ... እህ ..." አለ ተመርማሪው ለራሱ ግራ የተጋባ መስሎ "... የምላችሁ በሁለት ሳምንታት ውስጥ ከስድስታችን የጦር ሠራዊት ተመልማዮች ውስጥ ሁለቱ ሲገደሉ አንዱ የገባበት ጠፋ::"

"ማነው ግድያውን የሚፈፅመው?" አለ እዮብ አቋርጦት::

"አላውቅም ... የሁለቱ ሰዎች እሬሳ የተገኘው በአንደኛው ሟች መርሴዲስ የኋላ እቃ መጫኛ ውስጥ ታምቆ ነበር:: ሦስተኛው ግን ጠፋ ... ጠፋ::"

ለአንድ አፍታ ተመርማሪው አይኖቹን በብረቱ ጠረጴዛ ላይ ተክሎ ቆየና በረጅሙ ተንፍሶ ቀጠለ:-

"... ለጊዜው ለደረሰው ግድያና መሰወር የቀረነው ሦስታችን ልንሰጠው የቻልነው ምክንያት አልነበረም ... ብቻ በዚህ ጭንቅ ላይ እንዳለን ሌላ ግድያ በሉት ... ተፈፀመ::"

"የምን ግድያ?" አለ እዮብ::

"ይህኛውን በተቻለ መጠን አደጋ ለማስመሰል ተሞክሯል:: ከቀረነው ከሦስታችን ውስጥ አንደኛው በገዛ ሳሎኑ ውስጥ ቲቪው ላይ እንዳፈጠጠ ፎቴው ላይ ተንጋሎ ደርቆ ተገኘ:: ሐኪሞች 'የልብ ድካም' አሉት ... ለእኔ ግን ያለ ጥርጥር አንድ ተጨማሪ ግድያ ነበር::"

"እና ... ምን አደረግህ? " አቤሰሎም።

"አለቃዬ ቢሮ ገብቼ ጥርጣሬዬን በዝርዝር ገልጬ ነገርኳቸው።"

"ምን አሉ?"

"ፍጹም አልተቀበሉኝም። እርግጥ እንደተደናገጡ ግልፅ ነበር ... ሆኖም ወይ ሁኔታውን በእኔ ፊት ማመኑን ፈርተው ... አለበለዚያም የእርስ በእርስ መጠላለፉ ወዴት እንደሚያመራ ሲያስቡት ዘግንኗቸው ይሆናል ... ብቻ ሀሳቤን አቃልለው ከቢሮአቸው ሸኙኝ።"

"ቀጥሎ ምን አደረግህ?"

"ተሳሳትኩ።"

"ምንድነው ስህተትህ? "

"እርሳቸውንም ... አለቃዬንም ጠረጠርኳቸው።"

"አሁንስ ንፁህ መሆናቸውን በምን አረጋገጥክ? " አለ እዮብ።

"የእዛኑ ማታ በደብረዘይት መስመር መኪናቸው ተገልብጣ በእሳት ተቃጥላ ተገኘ ች። መኪናዋ ከተገለበጠችበት ስትነሳ አልደረስኩም ሆኖም በቦታው ከነበሩ ሰዎች እንደሰማሁት፣ አለቃዬ ሊለዩ በማይችሉበት ሁኔታ ተቃጥለው፣ ከስለው ነበር። ለእኔ ይህ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ነበር። በአጭሩ ከቁጥጥር ውጭ ሆንኩ። እራሴንም ማረጋጋት አቃተኝ። በጥቂት ቀናት እኔንም አንዱ'ጋ እንደሚወሽቁኝ ተረዳሁ ... ትልቁ ችግሬ ግን እራሴን ከማን መጠበቅ እንዳለብኝ አለማወቄ ነበር ... የገዛ ባለቤቴን ሳይቀር በጥርጣሬ አያት ጀመር።"

"እነማናቸው ብለህ ትጠረጥራለህ፤ አሁን?" አለ አቤሰሎም።

"ምንም ፍንጭ የለኝም። አየህ ችግሩ' ገዳይህና አስገዳይህ የተለያዩ ናቸው። የተሳፈርክበት ታክሲ ሹፌር ሊገድልህ ይችላል ወይ ሆቴል ገብተህ ምግብ የምታቀርብልህ አሳላፊ። ማንኛውንም ወገን ወይ በማባበል አለዚያም በማስገደድ የፈለጉትን ሊያስፈጽሙት ይችላሉ። ሆኖም በጥቅሉ ከፖሊስ ኃይል የተወጣጡት ... ወይ መረቡን ከጀርባ የሚቆጣጠሩት የውጭ የአደንዛዥ እፅ ከበርቴዎች ይመስሉኛል ... ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም።"

"እነማናቸው ሰዎቹ ማለቴ በስም ... ወይ ...?"

"አላውቃቸውም። እኔ የማውቀው ከመከላከያ የተመለመልነውን ብቻ ነው።"

"ለምንድነው ፖሊሶችን የጠረጠርካቸው?" አለ አቤሰሎም።

"የወንጀሉ መረብ በጥልቀት የተዘረጋው በጦር ሠራዊቱ ሳይሆን በፖሊስ ውስጥ ነበር። አሁን ወደኋላ ተመልሼ ሳስበው የወንጀሉ መረብ በሦስተኛ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ የፖሊሱ ኃይል የጦር ሠራዊቱን ከጨዋታው አስወጥቶ እንቅስቃሴውን ለብቻው ለመቆጣጠር ያሰበ ይመስለኛል።"

"ምን ማለትህ ነው 'በሦስተኛ ደረጃ' ስትል?" አለ እዮብ።

"ጠቅላላ የወንጀሉን እድገት በሦስት ደረጃ ከፍላችሁ ልታዩት ትችላላችሁ ..." አለ ተመርማሪው ወደ ኋላ ወንበሩ ላይ ደገፍ ብሎ "... የመጀመሪያው ዙር ከሁለት ዓመታት በፊት ተጀምሮ ለስምንት ወራት የቆየ ነበር። በዚህ ጊዜ ማንኛችንም የጦር ሠራዊቱ አባላት በመረቡ አልታቀፍንም። ሆኖም በኋላ እንደተረዳሁት ጊዜው የሙከራና የጥናት ነበር።"

"የምን ጥናት?" እዮብ ጠየቀ።

"ጥያቄዎቹ ... ኢትዮጵያ ዋና ዋናዎቹን የአደንዛዥ እፆች ለማምረት ያላት ብቃት ምን ያህል ነው? በየትኛው አካባቢ ምን ዓይነት እፅ በምን ያህል ስፋት ለመምረት ይቻላል? በተጓዳኙም የሚኖረው የሰው ጉልበት፣ የመገናኛ መስመሮች፣ የደህንነት ስጋትና፣ ሌሎችም ነበሩ።"

"ውጤቱስ?" አለ አቤሰሎም በእርጋታ።

"በውጤቱ ኢትዮጵያ በማምረት አቅሟ ያለ ጥርጥር ከደቡብና ምሥራቅ እስያ እንዲሁም ከላቲን አሜሪካ አገሮች የማትተናነስ እንደውም ልታበቅል ከምትችለው የእፅ ዓይነት ብዛት ከብዙዎቹ የተሻለች ነበረች። የነበረው ዋነኛ ችግር በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ብሎ የተደራጀና እንደ መሣሪያ ሊያገለግል የሚችል የወንጀል ቡድን አለመኖሩ ነበር።"

"ስለዚህ?"

"ስለዚህ ... በጥናቱ መሠረት የእዚህ ዓይነቱን የወንጀለኛ ቡድን ኢትዮጵያ ውስጥ ለማደራጀት የተወሰነ ይመስለኛል።"

"የማይታመን! ..." አለ አቤሰሎም በወንበሩ ላይ እየተቁነጠነጠ "... የት ነው ይህ የወንጀል ቡድን የሚደራጀው ... ሊታመን የማይቻል ነገር ለምን ታወራለህ?"

"ድህነት፣ተስፋ መቁረጥና ውዥንብር ባጠቃው ሕብረተሰብ ውስጥ የወንጀለኛ ቡድን ማደራጀት ያንን ያህል አስቸጋሪ አይምሰልህ። በአስራ ዘጠኝ ዘጠናዎቹ መጀመርያ ላይ በቀድሞዋ ሶቪየት ሕብረት ውስጥ ከምንም አቆጥቁጦ ዛሬ አሉ ከሚባሉት ዓለም አቀፍ የወንጀለኛ ቡድኖች ተርታ የገባውን የሩስያ ማፍያን መውሰድ ትችላለህ። በአመት ከሰላሳ እስከ ሀምሳ ሜትሪክ ቶን ኮኬይን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የሚያስገቡት የኢኳዶር የወንጀል ቡድኖች የኢኳዶርን የዋህ ገበሬ ወደ ተደራጀ የወንጀል ማሕበረሰብነት ለመቀየር የፈጀባቸው ጊዜ ከአስራ አምስት ዓመታት አይበልጥም። ስታስበው ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ምን ልዩ ያደርገዋል?"

"ጥሩ ... እና ይህን የወንጀል ቡድን በኢትዮጵያ ውስጥ ለማቋቋም ነበር የተወሰነው..." አለ እዮብ ተመርማሪው እንዲቀጥል በማበረታታት።

"በጥናቱ መሠረት ..." አለ ተመርማሪው አቤሰሎምን ችላ ብሎ ፊቱን ወደ እዮብ እየመለሰ "... እንዲደራጅ የታቀደው የወንጀለኛ ቡድን በመጀመሪያ መደብ አምራች ገበሬውን፣ በሁለተኛ ደረጃ አቀባባይ የሚሆኑ በተለይ ወጣት ሥራ

አጦችን ይዞ እንዲዋቀር ሲደረግ፤ በሦስተኛ ደረጃ መረቡ በቀላሉ እንዳይጠቃ በቅድሚያ በፖሊስ ኃይል ቀጥሎም በጦር ሠራዊቱ ውስጥ ሠርጎ በመግባት ከፍተኛ ባለሥልጣናትን ጨምሮ እንዲደራጅ ተደረገ:: ይህ ማለት ደግሞ መንግሥት አምራቹንና አቀባባዩን ለመምታት ቢነሳ በቅድሚያ በሦስተኛ ረድፍ የተዘረጋውን መረብ መበጣጠስና ማጥፋት ይኖርበታል::"

"ይህን ሁሉ ከጀርባ የሚያንቀሳቅሰው ማነው?"

"አላውቅም:: በአሁኑ ወቅት ያለው የአደንዛዥ እፅ ንግድ ዜግነት ያለው አይደለም፤ ከሩቅ ምሥራቅ እስከ አላስካ የተዘረጋ ሰፊ መረብ ነው:: በዚህ መረብ ውስጥ ኢትዮጵያ አንድ አነስተኛ ማሳ ነች:: 'እከሌ ነው ከጀርባ ያለው' ማለት አትችልም:: ዓለም ትንሽ መንደር ከሆነች ቆይታለች ... አላውቅም ከጀርባ ያለውን ..."

"እሺ ቀጥል::"

"... ቡድኑ ተደራጅቶ እንዳለቀ በጥናቱ መሠረት የመጀመሪያዎቹ ለምርት ተስማሚ ናቸው የተባሉ የኪስ ቦታዎች ተመርጠው የሙከራ ሥራ ተካሔደ::"

"የት ናቸው እነዚህ አካባቢዎች?" አለ እዮብ አቋርጦት::

"እጅግ በርካታ የኪስ ቦታዎች ናቸው፤ በዝርዝር አላስታውሳቸውም:: ዋና ዋናዎቹ ግን በምሥራቅ የሐረርጌ ከፍተኛ ቦታዎች የጀምስን ቅጠልን ለማምረት፤ በጣና ዙሪያና በደሴቶቹም ላይ አፒየምን እና የኮካ ቅጠልን፤ እንዲሁም በምዕራብ የባሮ ተፋሰስ ካናቢስን ለማምረት የተመረጡ ቦታዎች እንደነበሩ አውቃለሁ:: ሆኖም አንድ ማሳ ከሁለት መቶ ካሬ ሜትር እንዳይበልጥ የተወሰነ ስለነበር ዋናውን ካርታ ካልያዝኩ በስተቀር 'እዚህ-እዚህ' ብዬ መናገር አልችልም፤ በጣም ጥቃቅንና በሺህ የሚቆጠሩ ማሳዎች ናቸው በዕቅዱ የታቀፉት::"

"እሺ::" አለ እዮብ ተመርማሪው እንዲቀጥል በማበረታታት::

"ይህ እንደተጠናቀቀ ሁለተኛው ዙር የምልመላና የትጥቅ ስራን ለማካሔድ የተያዘ ነበር::"

"ምን ማለትህ ነው ትጥቅ ስትል?" አለ እዮብ ግንባሩን አኮሳትሮ::

"የኢትዮጵያ ገበሬ በባሕሉ የጦር መሣሪያ አጠቃቀምን ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው:: ጥያቄው የጦር መሣሪያ ማስታጠቅና ወደ ሽፍታነት መቀየር ብቻ ነበር::"

"በሐምሌ የተቀናጀው የመሣሪያ ዝርፊያ ለእዚህ ነበር ማለት ነው?" አለ እዮብ ፈጠን ብሎ::

"በቀጥታ:: በደፈጣው ቡድን የተሰረቁት አራት መቶ ሽጉጦች፣ አውቶማቲክ ጠመንጃዎችና ሌሎቹም የጦር መሣሪያዎች በሙከራ ወቅት ጥሩ ውጤት ላሳዩና በመቀጠልም የመጀመሪያ ዙር ምርት እንዲያቀርቡ ለተመረጡ ስድስት መቶ ሰማንያ ሁለት ገበሬዎችና ስልሳ ሶስት አቀባባዮቻቸው ተከፋፍለዋል:: የቀሩትም ጊዜያቸውን ጠብቀው የሚከፋፈሉ ናቸው::

"ስድስት መቶ ገበሬዎች አደንዛዥ እፅ አምራች ሆነዋል ነው የምትለው?" አለ አቤሰሎም ቅንድቦቹን ግንባሩ ላይ ሰቅሎ::

"እነዚህ የሙከራውን ጊዜ በውጤታማነት ያለፉት ብቻ ናቸው:: እመኑኝ በጥቂት ወራት ውስጥ በሺህ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ገበሬዎች የአደንዛዥ እፅ አምራች ይሆናሉ::"

ተመርማሪው ለአንድ አፍታ አቀርቅሮ ዝም ሲል እዮብ 'ቀጥል' የሚል ምልክት በእጁ አሳየው::

"እንግዲህ እነዚህ የጥናትና የትጥቅ ደረጃዎች እንደተገባደዱ የሚቀጥለው ስራ የአደንዛዥ እፅ ዘር ወደ አገር አስገብቶ የምርት ሂደቱን መጀመር ነበር:: ወደ አገር ይገባል የተባለው ስምንት ኩዊንታል ዘር እየተጠበቀ እያለ ነው ግድያው የተጀመረው ..."

"ስምንት ኩንታል!" አለ አቤሰሎም ቅንድቦቹን ግንባሩ ላይ ሰቅሎ::

"አዎ::" አለ ተመርማሪው ፈርጠም ብሎ::

"እሺ ቀጥል::"

"... እ ... አሁን ሳስበው ገበሬውን የጦር መሳርያ የማስታጠቁ ስራ ከተገባደደ በኋላ ከመከላከያ የተመለመልነው አባላት ለወንጀሉ መሪዎች አስፈላጊ አልነበርንም:: ለዚህ ይመስለኛል ቀሪውን ሥራ ከፖሊሱ ኃይል ጋር ለመቀጠልና የጦር ሠራዊቱን ለማግለል የተሞከረው::"

"ስለዚህ ከግድያው ጀርባ ያለው የፖሊሱ ኃይል ነው ማለት ነው?" አቤሰሎም ጠየቀ::

"አላውቅም ... መሳምት ነው::" ተመርማሪው ፈርጠም ብሎ መለሰ::

"ይህን የሚያክል ብዛት ያለው የአደንዛዥ እፅ ዘር እንዴት ነው ወደ አገር ለማስገባት የሚቻለው?"

"እንጃ ..." ተመርማሪው ትከሻውን ነቀነቀ::

ከጀርባ ያለው የምርመራ ክፍሉ በር ተንኳኳ:: አቤሰሎም በብረት ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን የድምጽ መቅጃ አቁመና ተነስቶ ወደ በሩ አመራ:: በሩን ከከፈተ በኋላ ከውጭ ካለ ሰው ጋር በሹክሹክታ ሲነጋገር ቆይቶ ተመለሰ::

"ዶክተር ብርሃን ሊያነጋግርህ ይፈልጋል::" አለ አቤሰሎም::"

እዮብ ሰዓቱን ተመለከተ:: ከቀኑ አስራ አንድ ከሃያ::

"ጥሩ ሻለቃ ፀጋዬ ..." አለ እዮብ ፊቱን ወደ ተመርማሪው መልሶ "... የቀረውን ነገ ጠዋት እንቀጥላለን ... ምናልባት የረሳሀቸው ጉዳዮች ካሉ ለማስታወስ ሞክር::"

ሁለቱ መርማሪዎች ከክፍሉ ተከታትለው ሲወጡ በዝምታ ነበር::

ለሁለት ወደሚጋሩት ቢሮአቸው ከገቡ በኋላ እዮብ የድምፅ መቅጃውን መሳርያ የብረት ቁምሳጥን ውስጥ ከተተና:-

"ምን ይመስልሀል?" አለ ፊቱን ወደ አቤሰሎም መልሶ::

"ምን ነካህ እዮብ ... የተጠና ነገር ነው'ኮ የሚተረትርልን::" አለ አቤሰሎም በወንበሩ ላይ ጋለል ብሎ ተቀምጦ::

"ግድ የለም ጊዜ ካገኘን ... እንሰብረዋለን::"

"ካልወሰዱት አይደል ፖሊሶቹ::" አለ አቤሰሎም ተስፋ በቆረጠ ድምፅ::

"እኔ ያልገባኝ ... ፖሊሶች ለእኛ ካልተሰጠን እያሉ የሚጨቃጨቁበት ምክንያት ... ምናልባት ሰውየው እንዳለው ከግድያው ጀርባ ያሉት እነሱው ከሆኑ ..." እዮብ የጀመረውን ሳይጨርስ ተወው::

"አንድ ሳምንት እንኳን እኛ'ጋ ቢቆይ አንድ ፍንጭ ላይ እንደርስ ነበር::" አለ አቤሰሎም::

"ዛሬ ማታ ነው የሚለየው ... ዶክተር ብርሃን ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪ የተጠራሁት ለዚሁ ጉዳይ ነው ብሎኛል::" አለ እዮብ የማስታወሻ ደብተሩንና እስክሪብቶ ከጠረጴዛው ላይ እያነሳ::"

"ለምን ዶክተር የጠቅላይ ሚኒስትሩን አማካሪ እንዲያሳምንና አንድ ሳምንት እንኳን እንዲሰጠን አታግባባውም?"

"እሞክራለሁ ... " አለ እዮብ ወደ በሩ እያመራ "... ከዶክተር ቢሮ ቶሎ ካልተመለስኩ ደህና እደር::"

እዮብ የቢሮውን በር ከውጪ ሲዘጋ አቤሰሎም በተቀመጠበት ወንበር ላይ ለጠጥ ብሎ እንደተቀመጠ ፊገግ አለና ጭንቅላቱን ነቀነቀ::

# ፪

**እምስተርዳም** -

ገሀነመ በረዶ ... ብን-ብን እያለ ይወርዳል:: ቦታ ሳይመርጥ ይከመራል:: የጥር በረዶ:: እምስተርዳም ነጥታለች::

የተሳፈረበትን ታክሲ በር ሲከፍት ጨካኝ የበረዶ ውሽንፍር ፊቱን ገረፈው .. ወደኋላ አልተመለሰም::

የት ይደረሳል?'

የለበሰውን ሱፍ የክረምት ካፖርት ፀጉራም አንገትጌ ሽቅብ ጎተት አደረገና ከታክሲው ወረደ:: ያሶፊን የመንገድ ሻንጣ ቀኝ ትከሻው ላይ አነገበና የራሱን በግራው አንጠለጠለው::

"ፈጠን ሚጪት::" አለ ፌይሰል በታክሲው የኋላ ወንበር ላይ ልጥፍ ብላ የተቀመጠችውን ሴት ልጁን ጎንበስ ብሎ እየተመለከተ::

በቢጫ ጓንት የተሸፈኑ ትናንሽ እጆቿን ሰደድ አደረገችና ጭንቅላቷን የሸፈናትን የቢጫ ካፖርቷን ቆብ በተቻላት ወደ ግንባሯ ቁልቁል ጎተተችው::

ብርድ አትወድም ... ቅዝቃዜ አትወድም ... ጠላቷ::

"ፈጠን በይ እንጂ ሶፊ ... አውሮፕፐላኑ'ኮ ጥሎን ይሄዳል::" ቀኝ እጇን ያዝ አድርጎ ከታክሲው እያወረዳት "አይዞሽ አቅፍሻለሁ::"

ፈጠን ብሎ የታክሲውን ሂሳብ ከከፈለ በኋላ ቁጢጥ ብሎ የቀኝ ክንዱን በወገቧ ዙሪያ ጠምጥሞ ብድግ አድርጎ ታቀፋት::

"እኮ!" በገዛ ትከሻው ላይ ተንጠራርቶ ለሰላሳ ጉንጯን ሳማት::

ሰፊውን የመስታወት በር አልፎ ገባ:: አዳራሹ በተጓዦች ተሞልቷል:: እቃውን ለማስፈተሽ ሰልፍ ያዘና ልጁን ከእቅፉ አወረዳት::

"ባባ ..." አለች በለሆሳስ ትላልቅ አይኖቿን ሰለምለም አድርጋ ሽቅብ እያየችው::

ጎንበስ ብሎ እግሮቿ መሀል የተንጣለለውን ሽንት ሲመለከት አይኖቹን ጨፈነ::

"ምነው! ምነው! ... ሶፊ! ... ሲመጣብሽ ንገሪኝ አላልኩም? "

መልስ አልመለሰችለትም:: 'ምን ታደርገዋለህ?' እንደምትል ሁሉ ትላልቅ ውብ አይኖቿን እያንከባለለች ተጠባበቀችው::

እባትና ልጅ ተፋጠጡ:: አባት ቀድሞ አይኖቹን ሰበረ:: በመሸነፍ መልክ ጭንቅላቱን ነቅንቆ በረጅሙ ተነፈሰ:: ቁጢጥ ብሎ ታቅፎ አነሳትና ኋላና ፊት የተሰለፉትን ተጓዦች ይቅርታ በተላበሰ ፈገግታ እየተለማመጠ ከሰልፉ ወጥቶ ወደ መታጠቢያ ክፍል አመራ::

መተሳሰፊያውና መፀዳጃ ቤቱ ጭር ብለዋል። ፈጠን ብሎ የአንዱን መፀዳጃ ክፍል በር ከፍቶ ገባና ከውስጥ ቆለፈው። ቅደም ተከተሉን እንደ ሶላቱ አጥንቶታል።

"ስለአሳህ ብለሽ ... ሶፊ ... 'ሲመጣብሽ ንገሪኝ' አላልኩም?" ቁስለኛ ጨርቆቿን በላስቲክ ከረጢት ውስጥ እየከተተ።

ፊቷን አዞረችበት 'አትነዝንዘኝ' ማለት እንደፈለገች ሁሉ። በሽንፈት ራሱን ነቀንቀና በቀኝ ክንዱ ታቅፏት ከመፀዳጃ ክፍሉ ወጣ።

"ባባ ..." አለችው ወደ ተንገኮች አዳራሽ ሲገቡ በለስላሳ ቡኒ ፀጉር የተሸፈነ ትንሽ ጭንቅላቷን እዘንብላ አንገቱ ሥር እየተወሸቀች።

"እ?"

"እወድሀለሁ።"

"እጭበርባሪ!" አለ ፈገግ ብሎ ግንባሯን ሳም አድርጎ።

ሻንጣዎቹን አስፈትሾ ወደ መቆያው ክፍል ከገባ በኋላ ወንበር ያዘና በግድግዳው ላይ የተሰቀለውን የበረራ ፕሮግራም የሚያሳየው ስሌዳ ላይ አፈጠጠ።

"እንደማያዘገዩን ተስፋ አለኝ ..." አለ ወፍራም ጉርብርብ ድምፅ።

ዞር ብሎ ተመለከተ ፌይሰል። ነጭ ሙሉ ልብሱ ላይ ጥቁር ባለሰፊ ኮሌታ የክረምት ካፖርት ደርቧል። ፌይሰል ፈተልተል፣ ዘብረቅረቅ ያለውን ፀጉሩን ሲያይ፤ የተቀባው ከባድ ሽቶ ሲሸተው ሰውየው፤ ስራቱ ከመካከለኛው ምስራቅ ነው ብሎ አሰበ። ሪዙ ግርማ ሞገስ የሰጠው በስልሳዎቹ ዓመታት ውስጥ የሚገኝ ደልቃቃ ሽማግሌ።

"ሰረጅም ጉዞ የሚዘጋጁበት አየር አይደለም ..." አለ ሰውየው ፌይሰል ሳይመልስ ዝም ሲል ፈገግ ብሎ " ... ሲሆን - ሲሆን ከቤተሰብ ጋር እሳት የሚሞቁበት እድል ከሰመረም ... ከውብ ኮረዳ ጋር ..." ሰውየው የጀመረውን ሳይጨርስ አቋረጠና ወንዳወንድ ጥቅሻ አከለበት።

ፈገግ አለ ፌይሰል።

"እ ... ልገምት ... ወደ ካይሮ ነህ።" ሰውየው ሲናገር የደስ ደስ አለው።

"ሪያድ።" አለ ፌይሰል።

"አ! እኔ ወደ ካራቺ እልፋለሁ ..." አለ ሰውየው በመቆያው አዳራሽ ውስጥ በተርታ ከተደረደሩት የፕላስቲክ ወንበሮች ላይ ከፌይሰል ጎን እንደተቀመጠ ወደ ኋላ ለጠጥ ብሎ " ... እንተዋወቅ ... ዑመር ሀሰን ቤን ዳሪክ።" በቀኝ እጁ ያጠለቀውን ውድ የቆዳ ጓንት አውልቆ እጁን ለፌይሰል ዘረጋ።

"ፌይሰል ... ፌይሰል አብዱልከሪም።"

ሰውየው አውርቶ የሚጠግብ አይመስልም::

"በምዘዋወርባቸው አገሮች ሁሉ ለባለቤቴ ጥቃቅን ማስታወሻዎችን መግዛት እወዳለሁ ... ውድ መሆን የለባቸውም ... ለማስታወሻነቱ ነው ..." የእጅ ቦርሳውን ጭኑ ላይ አስደግፎ እየከፈተ ንግግሩን ቀጠለ "... ይህችን ሔግ ውስጥ ነው የገዛኋት ..." አለ ትንሽ ቆንጆዬ አሻንጉሊት እያወጣ "... 'ይሄ ሽማግሌ ለአሮጊት ሚስቱ እንዴት አሻንጉሊት ይገዛል?' ብለህ ትገረም ይሆናል:: ለምን መሰለህ? በሱቁ መስኮት ውስጥ የአሻንጉሊቷን ደማቅ፣ ጥቋቁር አይኖች ስመለከት የባለቤቴ ውብ አይኖች ፊቴ ላይ ድቅን አሉብኝ ... ያኔውኑ ሳላወላውል ገዛኋት:: ትክክል አልሰራሁም? ሀ! ሀ! ሀ! ... ታድያ ምን ያደርጋል ከቤቴ ደርሼ ስጦታዬን ለባለቤቴ ሳላበረክት ከባለቤቴ አይኖች የበለጡ ውብ አይኖች ያሏት እመቤት አጋጠሙችኝ!" አለ ከአባታዊ ፈገግታ ጋር ሶፊያን እየተመለከተ " ... ስለዚህ ለባለቤቴ የገዛሁትን ገፀበረከት መንገድ ላይ በውበቷ ለማረከችኝ ኮረዳ ላበረክትላት ቆረጥኩ::" አሻንጉሊቷን የያዘበትን እጁን ወደ ሶፊያ እየዘረጋ::

ግራ የተጋባው ፌይሰል "እ ... እ ..." ከማለቱ ሶፊያ የቀረበላትን ስጦታ ቀልጠፍ ብላ ተቀበለችና ስጦታውን ላበረከተላት የውበቷ ተማራኪ ምስር ምስር የሚያካክሉ ጥርሶቿን ጋበዘችው::

"አስፈላጊ አልነበረም'ኮ ..." አለ ፌይሰል ከብዶት "... መቸገር አልነበረብህም::"

"ሀ! ሀ! ሀ!..." ዑመር ጭንቅላቱን ወደ ኋላ ጥሎ ሳቀ " ... ተመስገን ነው በዚህ መላተቄ! እላህን የምለምነው ግን እነዚህን ውብ ዓይኖች የዛሬ ሀያ ዓመት ድጋሚ እንዳላያቸው ነው:: አየህ .. ያኔ ... እኔ ... የሰባ ዓመት አዛውንት እሷ ደግሞ ... ሀ! ... 'መጥፎ ግጥምጥም' ይሉሀል ይህ ነው ... ሀ! ሀ! ሀ! ... አላህ ይሰውርህ በለኝ ... የኔ ልጅ::"

መተላለፊያውን ተሻግረው ከአውሮፕላኑ በር ሲደርሱ የዑመር ፊት ፌዘኛ ፈገግታውን ተገፎ አባታዊ ርህራሄ ተላበሰ "ልጅህን አላህ ይባርክልህ::" አለ ግራ እጁን ፌይሰል ቀኝ ትከሻ ላይ ጭኖ::

"ቻዎ ካራና ..." አለች የኢጣልያ ሆስቴስ ከተፍለቀለቀ ፈገግታ ጋር ሶፊያን እተመለከተች::

ፌይሰል የሆስቴሷን ፈገግታ በፈገግታ መልሶ ወደ አውሮፕላኑ ዘለቀና ሶፊያን እንደታቀፈ ወንበሩን ፈልጎ ቦታውን ያዘ::

"ካፖርትሽን ላውልቅልሽ?" ቡናማ ፀጉሯን ዳበስ አድርጎ::

አዲሷን አሻንጉሊቷን በወረት ደረቷ ላይ እንደታቀፈች ቀና ብላ አየችውና ራሷን በእሉታ ነቀነቀች::

"ልጅህ ነች?"

ቀና ብሎ ተመለከተ:: ሶፊያ ከተቀመጠችበት ወንበር በስተግራ ተቀምጣለች:: አለቅጥ የወፈረ አካሏ በግራጫ ቀሚሷ ውስጥ ተጨናንቋል:: በስጋ ታምቆ

የተድበሰበሰ ፊቷ፣ ግራና ቀኝ የተንጠለጠሉ ጉንጮቿ፣ ተርታ የተደረደሩ ኩልኩልቶቿ ... አስቂኝ ነጭ አሮጊት አድርገዋታል::

"አዎ ልጄ ናት::"

"እሷን የምታክል የልጅ ልጅ አለችኝ ..." አለች አሮጊቷ ሶፊያን ቁልቁል እየተመለከተች:: የኔዋ አሊስ ትንሽ ከፍ ትላለች፤ ለሚመጣው ሰኔ ስምንተኛ ዓመቷን ትይዛለች::"

"የእኔ አራት ጨርሻ ወደ አምስቱ እየተጠጋች ነው::" አለ ፌይሰል የልጁን ፀጉር እየደባበሰ::

"ውብ አይኖች ነው ያሏት ያንተዋ!" አለች አሮጊቷ በፈገግታ የሶፊያን ጭንቅላት ዳበስ አድርጋ::

ያያት ሁሉ ሳያነሳው የማያልፈው የልጁ የአይን ውበት በተጠቀሰ ቁጥር እናቷ ሶፊያ ትዝ ትለዋለች:: የልጁ አይኖች የእናቷ፣ የሚች ሚስቱ፣ የሶፊያ አይኖች ናቸው::

ሶፊያን እስካየበት ጊዜ ድረስ ፍቅር ሰው ሰራሽ ስሜት ይመስለው ነበር:: ልብወለድ:: ምናልባት አስተዳደጉ ይሆናል:: በዕድሜው በሀያዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ላሳለፈው ልቅ ህይወቱ፤ በተለይ ከሴቶች ጋር ለነበረው ዘልዛላ ግንኙነቱ ምክንያት የሆነው::

ገና የሁለት ዓመት ልጅ ሳለ በካንሰር እንደሞቱ የሚወራለት የእናቱን ፍቅር አለማግኘቱ ብቻ አልነበረም፤ ግድ የለሽ አባቱ ያለእንጀራ እናት የጠየቀውን አሟልተው፣ እንቀባረው ቢያሳድጉትም ከቀን ወደ ቀን የሚኮሰስ የገጠር ትራንስፖርት ንግዳቸውን ከማስታመም አልፈው ከልጃቸው ጋር የሚያጠፉት ጊዜ አልነበራቸውም::

"ከበላ፣ ከጠጣ፣ ከለበሰ፣ ከተማረ፣ የኪስ ገንዘብ ካላነሰው ... ከዚህ በላይ ..."

የመጀመሪያ ዲግሪውን በኢኮኖሚክስ ካገኘ በኋላ በንግድ ሚኒስቴር አዲስ አበባ ውስጥ ለአምስት ዓመታት አገልግሏል:: አምስት ልቅ ዓመታት:: ጭንቅላቱ ሳይሆን አይንና ልቡ በመሩት የፈነጨባቸው፤ ፍፁም መረን የወጣባቸው አምስት አመታት::

የባህር ወንበዴ ነበር ... በሰፊ ባሕር ላይ ያለተቆጣጣሪ የሚቀዝፍ መርከብ ... ለእርሱ ሕይወት ለጥ ያለ የማይናወጥ ሰማያዊ ባህርና የጠራ ሰማያዊ ሰማይ ነበር:: በፈቀደበት ይቀዝፋል ... ባሻው ይንሳፈፋል:: ለእርሱ ወጣት ሴቶች ያማሩና የተሽቆጠቆጡ ወደቦች ነበሩ:: በደረሰበት መልህቁን ጥሎ ጭነቱን ያራግፋል ... ሲያበቃ ... ሲጨርስ መልህቁን ስቦ ወደሚቀጥለው ወደብ ያመራል:: አበቃ::

በግርድፉ የሚያሻምደው ሕይወት ጣዕም የለሽ፣ ተራ ድግግሞሽ፣ አሰልቺ ሆይ-ሆዬ መሆኑ የተሰማው ዘግይቶ ነበር:: እንደ ግድግዳ ሰዓት ቲክ-ቲክ እያሉ የሚያልፉ፤ አንድ አይነት መልክና ፍጥነት ያላቸው ቀናት፣ ሳምንታት፣ ወራትና ዓመታት አንዳቸው ከአንዳቸው የማይለዩ ተራ ድግግሞሽ መሆናቸውን

ቢረዳም እንዴት ከዚህ ሽክርክሪት ውስጥ ስብሮ እንደሚያመልጥ ለራሱም ግልፅ አልነበረም::

ዕድሉ፣ ዕጣው የተቀየረው በአንድ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል አስመጪና ላኪ ማኅበር በወጣ ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ነበር:: ድርጅቱ በኔዘርላንድስ - አምስተርዳምና በፈረንሳይ - ማርሴ ባሉት የቅርንጫፍ ቢሮዎች የሚሰሩ ወኪሎችን አወዳድሮ ለመቅጠር እንደሚፈልግ ነበር ማስታወቂያ ያወጣው::

በአውሮፓ በሚገኙ ከተሞች በወኪልነት ተመድቦ ሲሰራ ሊያጋጥመው የሚችለው በአዳዲስ ገጠመኞች የተሞላ ትኩስ ህይወት በጉጉት ሞላው:: እንደተመኘው ለክፍት የሥራ ቦታው አመልክቶ፣ ውድድሩን አሸንፎ በወፍራም ደሞዝ ለመቀጠር ቢችልም እንደጠበቀው ወደ አውሮፓ ሳይላክ ቀረ በድርጅቱ ባለ አምስት ፎቅ ዋና መሥሪያ ቤት ውስጥ - አዲስ አበባ::

ግድ አልነበረውም:: ሀሳቡ ሌላ ቦታ ነበር::

በድርጅቱ ውስጥ መሥራት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ጠዋት ወደ ቢሮው ሲሔድ፣ ማታ ወደቤቱ ሲመለስ፣ ለሊት አልጋው ላይ ተኝቶ፣ ቀን የቢሮ ጠረጴዛው ላይ ተደፍቶ የሚያስበው በድርጅቱ ህንፃ በአንደኛ ፎቅ ላይ ስለምትሠራው ሴት ልጅ ነበር::

"በጤናዬ ነው ግን?" ይላል ከራሱ ጋር፤ ሀሳቡን ማሰባሰብ ሲያቅተው "... አቤት አይኗ!" ይላል አይኖቹን ጨምቆ ጨፍኖ::

በቀናት ውስጥ ክንዶቹን ሊያንተርሳት ያሰባት ልጃገረድ ማንነት ከተገለጠለት በኋላ ግን ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው ተረዳ:: ሶፊያ የተቀጠረበት ድርጅት ባለቤት የአቶ ዘካርያስ ዩሱፍ ብቸኛ ልጅ መሆኗን ሲሰማ፤ የሚያጠምደው አሳ ከቀጣሪው ጋር ያለውን ግንኙነት ሲረዳ መረቡን ሰብስቦ እያንዳንዷን የክር ቋጠሮ ለመፈተሽ ወሰነ::

ሶፊያን ማጥመድ ቀላል አልነበረም:: አለቅጥ ግደየለሽና ቸልተኛ ነበረች:: በአባቷ ባለ አምስት ፎቅ ፅሕፈት ቤት መተላለፊያዎች ብቅ ስትል ያጋጠሙቻው ጎረምሳ ሁሉ አይን ለመግባት ይጥራል:: ፌይሰልም የተለየ አልነበረም:: እሷም ብትሆን ከማንኛውም ሠራተኛ የተለየ አትኩሮት አልሰገሰችውም:: ሲያስናት ቀማ ትጨብጠዋለች፤ አለዚያም ስስ ፈገግታዋን ሰጥታው ታልፋለች፤ ያላላት ቀን ደግሞ ከፊቷ እንዳለው አየር መኖሩንም ሳታጤን ጥሳው ታልፋለች::

የምታደርገው ሁሉ ቲያትር እንደነበርና ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ መረቡ ውስጥ እንደገባች የተረዳው ግን በአባቷ የግል ድርጅት ውስጥ ከዓመት በላይ ካገለገለና ፍቅራቸውን ከተገላለፁ በኋላ ነበር:: የታፈነውን ስሜት ሲያወጡት ... ያኔ ... አላፊ አግዳሚው አፍ ገቡ ... እያንዳንዱ ሠራተኛ በመሰለው አነበባቸው ... ተረካቸው ...

'እናቱን!' ይላሉ ወጣት ወንድ ሠራተኞች ስሜታቸውን የሚገልፅላቸው የተሻለ ቃል እንዳጡ ሁሉ፤ 'ምን ነካት?' ይላሉ ወጣት ሴት ሠራተኞች ምን እንደነካት እንደማያውቁ ሁሉ፤ 'ምንድን እስኪሆኑ ነው የሚጠብቁት አባትየው?' ይላሉ ጠና ጠና ያሉት ... መጪው እየታያቸው::

"ይቅርታ አንተንም ለመፈተሽ እንገደዳለን ... ፈቃደኛ ነህ?" አለ የመቶ አለቃው ጥግ ቆሞ ፍተሻውን ሲከታተል ቆይቶ ከሁለቱ ሻንጣዎች ውስጥ ምንም እንደሌለ ሲረዳ::

ለአንድ አፍታ ፌይሰል ስጋት ገባው:: ከኪሱ ውስጥ የሚያገኟቸውን እንክብሎች በሌላ እንዳይተረጉሙበት ሰጋ::

"እዚያ ክፍል ግባና ልብስህን አውልቅ::"

ወዳመለከቱት፣ በመጋረጃ ወደተጋረደች ትንሽ ክፍል ራመድ ሲል እግሩ ላይ ተጠመጠመች:: መለስ አለና ግራ ተጋብታ አይኖቿን ከወዲህ ወዲያ የምታንከራትተውን የሴት ልጁን ሁለት ክንዶች ይዞ ሊያባብላት ሞከረ::

አልሆነለትም::

"ይዣት ልግባ?" በልመና መልክ ቀና ብሎ የመቶ አለቃውን እየተመለከተ::

"አይሆንም::" ቁርጥ ያለ ነበር መልሱ::

"መጣሁ ... ሶፊዬ ... አልቆይም::" በተቻለው ድምጹን አለስልሶ አባበላት::

ቀና ብሎ ፊቱን ሲመልስ ድጋሚ ሱሪውን ጭምድድ አድርጋ ይዛ ለቅሶዋን ለቀቀችው::

"ባባ!" በድንጋጤ የገረጣው ፊቷ ለቅሶዋን ተከትሎ ፍም መሰለ::

"ይዣት ብገባ ... ምን ይጎዳል?"

"የምትፈተሸው አንተ ነህ ... በተራዋ እሷም ትፈተሻለች:: ልቀቃትና ግባ::" አለ የመቶ አለቃው እጆቹን ደረቱ ላይ አጣምሮ እንደቆመ ጥርሶቹን ገጥሞ 'ዛሬ አንላቀቅም ...' በሚል አኳኋን "... እይዞህ እዛ ክፍል ደርሰህ እስክትመለስ ሞታ አትጠብቅህም::" አለ የፌዝ ፈገግታ እከሉ::

እጆቿን ከሱሪው ላይ ሊያላቅቅ ጎንበስ ሲል እንባዋን በጉንጮቿ እያዝረበረበች በፍርሀት ኩሬ የሚዋኙትን አይኖቿን አይኖቹ ላይ ተክላ ጥሏት እንዳይሔድ ተለማመጠችው፣ ተንዘበዘበች ... ባላት አቅም ቀጫጭን ክንዶቿን በጉልበቱ ዙሪያ አክርራ ጠምጥማ ምርር ብላ አለቀሰች::

ደረቱ ላይ እጆቹን አጣምሮ የቆመው የመቶ አለቃ ትዕግሥቱ እንዳለቀ ሁሉ ራመድ ብሎ ትናንሽ ክንዶቿን ከአባቷ እግር ላይ መንጭቆ አላቆ ቀና አለና በንዴት ደም የጎረሱ አይኖቹን ፌይሰል ላይ ተከለ::

"ከአሁን ወዲያ ጊዜአችንን እንድታጠፋ አልፈቅድልህም:: ቀጥል::"

ከጀርባው የሚሰማው የልጁ ጩኸት ልቡን ቢሰነጥቀውም ፈጠን ብሎ ከተባለው ክፍል ገባ:: ተከትሎት ከትንሿ፣ በመጋረጃ ከተጋረደችው ክፍል የገባው ፈታሽ ልብሱን አስወልቆ አንድ በአንድ ፈተሸው:: ፌይሰል እንደፈራው ሳይሆን ፈታሹ ከኪሱ ሲገባ ያገኛቸውን እንክብሎች ችላ ብሎ ከኪሱ መለሳቸው::

"ልብስህን መልበስ ትችላለህ::" አለ ወታደሩ የጥፋተኝነት ስሜት ከተቀላቀለው፣ ይቅርታ ከሚጠይቅ ፈገግታ ጋር::

ፌይሰል ንዴቱን መቆጣጠር አልቻለም።

"ምን ነበር የምትፈልጉት? የፈለጋችሁትን ሰው አስቁማችሁ እንዲህ የማንገላታት መብት'ኮ ፍጹም የላችሁም! ወደ ኤምባሲዬ መደወል እፈልጋለሁ። አሁን!" አለ እልህ እየተናነቀው።

ለአንድ አፍታ ከፊቱ የቆመው ፖሊስ አይኖች በፍርሀት የተዋጡ መሰሉ።

ልብሱን ለብሶ እንደጨረሰ ያለበትን ትንሽ ክፍል መጋረጃ ወደ ጎን በርግዶ ከዋናው ክፍል ገባ።

የመቶ አለቃው መሀል ክፍሉ ላይ እግሮቹን አንፈራጦ ቆሟል። አይኖቹ እሳት ይተፋሉ! ጉንጮቹ በቁጣ ይንቀጠቀጣሉ! በተነፈሰ ቁጥር ደረቱ ሽቅብ ቁልቁል ይናጣል።

"ልጁስ?" አለ ፌይሰል በክፍሉ ውስጥ የልጁን አለመኖር ሲያጤን።

"አቶ ፌይሰል አብዱል ከሪም..." አለ የመቶ አለቃው ለደንቆሮ እንደሚያወራ ሁሉ ድምፁን ከፍ አድርጎ "... ይህች የማን ናት?" በቀኙ የያዛትን የሶፊያን አሻንጉሊት ወደፊት ዘርግቶ ይዞ ጠየቀው።

ግራ ተጋባ ፌይሰል።

አሻንጉሊቷ?

"የልጄ።"

የመቶ አለቃው በቀኙ የያዛትን አሻንጉሊት በደረቷ ደፍቶ የለበሰችውን አጭር ነጭ የባሌ ቀሚስ ሽቅብ ገለበና ጀርባዋ ላይ ያለውን የባትሪ ድንጋይ ማስገቢያ በር በረገደው። ከውስጥ አተር አተር የሚያካክሉ እንክብሎች መዳፉ ላይ ተዘረገፉ።

"እነዚህ ምንድን ናቸው?"

ግራ የተጋባው ፌይሰል እንክብሎቹን እየተመለከተ ዝም አለ።

"አታውቃቸውም መሠለኝ ..." አለ የመቶ አለቃው በፌዝ "... እኔ ልንገርህ የ ኤል. ኤስ. ዲ. እንክብሎች ናቸው።

ለአንድ አፍታ የመቶ አለቃው በዝምታ ፌይሰልን አተኩሮ ተመለከተው።

"አቶ ፌይሰል ከዚህ ቀደም አደገኛ የሆኑ የአደንዛዥ እጾችን በድብቅ ይዘው ወደ ሳውዲ አረቢያ ግዛት ሊገቡ የሞከሩ ወንጀለኞች ምን እንደተደረጉ ታውቃለህ? ሳትሰማ እንዳልቀረህ እርግጠኛ ነኝ። አንገታቸው በጎራዴ ተቀልቷል። ልትመከር ይገባ ነበር።

የመቶ አለቃው ወደ ፌይሰል ተጠግቶ ቆመ።

"አቶ ፌይሰል አብዱል ከሪም አደንዛዥ እፅ በድብቅ ይዘህ ወደ ሳውዲ አረቢያ ልትገባ ስትሞክር እጅ ከፍንጅ ተይዘሀል።"

ሰበታ ...

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪ የእረፍት ማሳለፍያ ቤት የንባብ ክፍል ውስጥ እሳት ተቀጣጥሏል::

በቺሚኒው ውስጥ ከተንተረከኩት የግራር ጉማጆች የሚነሳው ነበልባል ድምፁን አጥፍቶ ሲወራጭ፣ ሲንቀለቀል፣ የተወለጋገደ ብርሀኑ ጨለምለም ባለው ክፍል ውስጥ ሲሄድ፣ ሲመለስ ይቆይና ... ድንገት '... ጣ!' ይላል ጥቃቅን የእሳት ፍንጣሪዎች ሽቅብ እየረጨ ...

'... ጣ ... ጣጣ ...'

ጠቆር ብለው ... ቀይ ባለአበባ የፐርሽያ ምንጣፍ ላይ አለፍ አለፍ ብለው ጉብ ጉብ ያሉት ግዙፍ ቡናማ የቆዳ ፎቴዎች እንዴ ደብዘዝ እንዴ ፈካ እያለ በሚውለበለበው የእሳት ወጋገን ውስጥ ሲታዩ የበረሐ ቋጥኞች ይመስላሉ:: በሰፊው የንባብ ክፍል ጥግ ለጥግ ግድግዳውን ታክኮ የተዘረጋው፣ በመጻሕፍት የታመቀው መደርደሪያ ሄድ - መጣ በሚለው የእሳት ብርሃን ውስጥ ሲታይ የተፋፋቀ፣ የተጋጋጠ ጥንታዊ የዋሻ ግድግዳ ይመስላል::

ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪ ፒፓ የሚነሳው ጭስ ክፍሉን አፍኖታል::

"ሁለት ወር ሙሉ በመረጃው ቤት ክሊኒክ ውስጥ ነበር ማለት ነው ... ሰውየው?" አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ የለሊት ልብሳቸው ላይ ጋውናቸውን ደርበው ወፍራም ነጭ የእግር ሹራባቸውን እንዳጠለቁ በአንደኛው የቆዳ ፎቴ ላይ ጋለል ብለው::

ቀጭንና ረጅሙ ሰውነታቸው፣ ከጥቁሩ ነጩ የሚበዛው ፀጉራቸው፣ ስልካካ ፊታቸው ... የፖለቲካ ሰው ሳይሆን የሐይማኖት መሪ አስመስሏቸዋል:: ውስጥ አዋቂዎች ግን ስለእሊሳቸው ሲያወሩ ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው "ሰውየው ..." ብለው መጀመር ይቀናቸዋል:: የፖለቲካ ጡንቻቸውንም ሲያመለክቱ "ጠቅላይ ሚኒስትሩ እሳቸው ናቸው::" ይላሉ በአጭሩ::

"አዎ::" አለ ዶክተር ብርሃን:: ከጆሮዎቹ በላይ መንጣት ከጀመረው ፀጉሩ በስተቀር ጥርት ያለው የቀይ ዳማ ፊቱ፣ ሸንቀጥ ያለ ሰውነቱ የሀምሳ አንድ ሳይሆን የአርባ አንድ ዓመት ጎልማሳ አስመስሎታል::

"በመጀመሪያ ወደ ሆስፒታል የተወሰደው በማን ነበር?" አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ::

"በእኔ ሰዎች ነበር ... በወኪል::" አለ የውስጥ መረጃው ኃላፊ ዶክተር ብርሃን::

"ይቅርታ ... እዚህ ላይ ..." ግዙፉ የፖሊስ አዛዥ አቋርጦ መሀል ገባ "... ምናልባት ጊዜው ስለቆየ ዶክተር የዘነጋው ይመስላል ..." አለ የፌዝ ፈገግታ እያሳየ "... ሰውየውን ከወደቀበት ቦታ አንስተው ሆስፒታል ያደረሱት ተራ

የአካባቢው ነዋሪዎች ነበሩ ... የእኔም ሆነ የዶክተር ብርሃን ሰዎች ስለሁኔታው መረጃ ያገኙት በማግስቱ ጠዋት ነበር::"

የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ መነጽራቸውን በእርጋታ አውልቀው በቀኛቸው እንጠልጥለው ይዘው:-

"እንዴት? ... በአካባቢው የነበሩ ነዋሪዎች ስትል ..." አሉ የፖሊስ አዛዡን እየተመለከቱ::

"ጥቃቱ ሲደርስ የተመለከተችው ሴት ሰውየው ከወደቀበት መንገድ ዳር ካሉ ባለአንድ ፎቅ የሸክላ ቤቶች በአንደኛው ውስጥ የምትኖር ነች:: ሴትየዋ በሰጠችው ቃል መሠረት ማታ ወደ ሁለት ሰዓት አካባቢ ድምፅ ሰምታ ከአልጋዋ ተነስታ መጋረጃዋን ገልጣ ወደ ውጭ ስትመለከት በግምት ሦስት የሚሆኑ ሰዎች ሰውየውን እያባረሩ በኮረኮንቹ ቁልቁል እንደወረዱና ከቤቷ ትይዩ ሲደርሱ ተረባርበው አደጋ እንደጣሉበት መመልከቷን ነው የተረዳነው::" አለ የፖሊስ አዛዡ አሰትጥ ግዙፍ ሰውነቱ የተቀመጠበት ሶፋ የጠበበው ይመስል ቅንጥንጥ ብሎ::

"ጥሩ ... ግን እንዴት ነው እርዳታ የደረሰለት?" የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ጠየቁ::

"ይህችው ሴት ሰዎቹ ተራ ዘራፊዎች ናቸው ብላ በመጠርጠሯ በመስኮት ብቅ ብላ እንደጮኸችና ያንን የሰሙ ሰዎች መደዳ ካሉ ቤቶች ወጥተው እንደደረሱለት ነው ያስረዳችው::" የፖሊስ አዛዡ::

"ስለዚህ..." አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ "... ሰውየውን ወደ ሆስፒታል ያደረሱት የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው ማለት ነው::"

"ትክክል::" አለ የሐምሳ ሦስት ዓመቱ የፖሊስ አዛዥ::

"በጊዜው ስለሰውየው ማንነት አልተረዳችሁም?" አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ሁለቱን ባለሥልጣናት በተራ እየተመለከቱ::

"አደጋው በደረሰ በማግስቱ ጠዋት ስለሰውየው ማንነት ለማጣራት ሰውየው ተወስደ ወደ ተባለበት ሆስፒታል አንድ ቡድን ሄዶ ነበር፤ ሆኖም ያገኘነው መረጃ ቢኖር ጠዋት አንድ ሰዓት ከሀያ ላይ የመረጃ መሥሪያ ቤቱ ሰዎች ሰውየውን ሰርቀው ..."

"ስርቆት አልተካሄደም!" የውስጥ ደህንነት ኃላፊው መሀል አቋርጦ ገባ " ... ሰውየውን የተረከብነው በፎርማ ነው ደግሞም ..."

"ቆይ - ቆይ ..." አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ፒፓ የያዙበትን ቀኝ እጃቸውን አንስተው የደህንነት ኃላፊውን እያቋረጡ "... ቀጥል::" አሉ ፊታቸውን ወደ ፖሊስ አዛዡ መልሰው::

"እንዳልኩት ..." አለ የፖሊሱ አዛዥ የልብ ልብ ተሰምቶት "... የመረጃ መሥሪያ ቤቱ ሰዎች በንዛ ፈቃዳቸው ሰውየውን አፍነው መውሰዳቸውን እንዳረጋገጥኩኝ እኔ እራሴ ወደ ዶክተር ብርሃን ደውዬ ሰውየው የህክምና እርዳታ ወደ

ሚያገኝበት ሆስፒታል በአስቸኳይ እንዲመለስ ብጠይቅም ሰውየው በመረጃው መሥሪያ ቤት ውስጥ ባለ ክሊኒክ ውስጥ አስፈላጊው እርዳታ እየተደረገለት መሆኑንና ወደ ሆስፒታል እንደማይመለስ ተገለፀልኝ:: አሁን ደግሞ ..." አለ የፖሊስ አዛዡ ከፌዝ ፈገግታ ጋር " ... ሰውየው ከተባለው ክሊኒክ እንዲወጣ ተደርጎ ያለምንም ጥፋቱ በእስር ላይ ለመሆኑ በቂ መረጃ አለኝ:: ይህን ደግሞ ተራ አፈና ከማለት ውጭ ምን እንደምንለው አላውቅም::"

"እሺ ዶክተር ... አንተስ?" አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ወደ የአገር ውስጥ መረጃ መሥሪያ ቤቱ ኃላፊ ፊታቸውን መልሰው::

"እ ..." የመረጃው ሰው ትንሽ የተደናገጠ መሰለ " ... እ ... እርግጥ ሰውየው ለሊት ቆስሎ ወደ ሆስፒታል መግባቱን እንደተረዳን ሰዎቼን ወደ እዚያው ልኬ ከሆስፒታሉ አውጥተውት የተሻለ ጥበቃና የህክምና እርዳታ ወደሚያገኝበት የድርጅታችን ክሊኒክ እንዲዛወር አድርጌአለሁ:: ሕክምናውንም ..."

"ቆይ - ቆይ ..." የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ በመሀል ገቡ "... ለዚህ ሰው የተለየ ጥበቃ ማድረግ ያስፈለገው ለምንድነው? ሰውየው በማጅራት መቺዎች ተዘረፈ ወይም ተደበደበ ... ሀኪም ቤት ገባ ... አንድ ሰው በተራ ዘራፊዎች አደጋ ደረሰበት አልደረሰበት ..."

"ይቅርታ ጌታዬ ..." አለ የመረጃው ሰው ከኪሱ ነጭ መሀረቡን አውጥቶ ግንባሩ ላይ ችፍ ያለውን ላቡን እያማጠጠ "... ሰውየው ተራ ሰው አይደለም:: አደጋ የጣሉበትም ቢሆኑ ተራ ዘራፊዎች አይደሉም:: በመጀመሪያ ደረጃ ሰውየው በመረጃው መሥሪያ ቤት ውስጥ በወኪልነት ለአራት አመታት አገልግሏል::"

"ሰውየው ላይ አደጋ የጣሉት ሰዎች 'ተራ ዘራፊዎች አይደሉም' ስትል ምን ማስረጃ አለህ?" አለ የፖሊስ አዛዡ ድንገት::

"ማስረጃው ያለው ባንተ እጅ ነው!" አለ የመረጃው ኃላፊ ፊቱን ወደ ፖሊሱ አዛዥ መንጭቆ ንዴቱን ዋጥ አድርጎ ይዞ::

"አንዴ! አንዴ! ... እረጋ ..." አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ መሀል ገብተው " ... ምንድነው በኮሎኔል እጅ ያለው ማስረጃ ... ልታስረዳኝ ትችላለህ ዶክተር?" ፒፓቸውን አስቀምጠው::

"ሰውየው ጥቃት በደረሰበት አካባቢ ከሚኖሩ በርካታ ሰዎች ባገኘነው መረጃ መሠረት ጠዋት ከአደጋው ቦታ የደረሱ የፖሊስ አባላት ሰውየው አደጋ ደርሶበት ከወደቀበት ቦታ በግምት አስር እርምጃ ራቅ ብሎ ባለ ክፍት ቱቦ ውስጥ አነስተኛ የቆዳ ቦርሳ እንዳገኙ ለመረዳት ችለናል:: በባለቤቱም ላይ የተደረገው ምርመራ ያረጋገጠልን ጉዳይ ቢኖር ጥቃቱ ከመድረሱ ጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ብሎ በሽሽት ላይ እያለ መረጃ የያዘውን የቆዳ ቦርሳ መንገድ ላይ እንደጣለው ነው የሚያስረዳው:: ይህንን መረጃ የያዘ ቦርሳ ነው የፖሊስ ኃይሉ ደብቆ የያዘው ..."

"ሀሰት! ... ፍጹም ሀሰት!" የፖሊስ አዛዡ ሁለት እጆቹን እያወናጨፈ አቋረጠው::

"እረጋ ብለን ብንደማመጥ ጥሩ ነው!" አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ከመሀል የገባውን የፖሊስ አዛዥ በቁጣ:: በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ የተቀመጡ

ባለሥልጣኖቻቸው እርስ በእርስ ሲናከሱ ሲያይዋቸው በስጨት ብለው:: " ... ሁኔታዎችን በስርዓት ብንይዛቸው በጎ ይመስለኛል::"

"ይቅርታ ክቡርነትዎ ..." አለ የፖሊስ አዛዡ በተቀመጡበት እየተቁነጠነጠ " ... ጌታዬ ..." ድምጹን ለስለስ አድርጎ ቀጠለ "... እውነቱ በተባለው ቦርሳ ውስጥ የተገኙት ሰነዶች ሳይሆኑ አንድ የቆሸሸ ሸሚዝና ሁለት ጋዜጦች ናቸው:: እርግጥ ጋዜጦቹ በስውር መረጃ የያዙ ሊሆኑ ይችላሉ በሚል ጥልቅ ምርመራ አድርገናል! ሆኖም ምንም ነገር ልናገኝ አልቻልንም:: ይህ ደግሞ በማንኛውም ወገን ቢጣራ ግልፅ ሆኖ የሚወጣ ነው::"

"ዶክተር ..." አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ፊታቸውን ወደ መረጃው ሰው መልሰው "... በቦርሳው ውስጥ መረጃ ለመኖሩ ምን መነሻ ነጥብ አለህ?"

"ባለቤቱ::" አለ የመረጃው ሰው በአጭሩ "... የሰነዱ ባለቤት ነው የመረጃ ምንጩ:: ሰውየው በአሁኑ ወቅት በመልካም ጤንነት ላይ ነው የሚገኘው:: አደጋው በደረሰበት ማታ ከመሥሪያ ቤቱ በራሱ ተባባሪነት ተካሔደ ስለሚለው ወንጀል መረጃ ይዞ ሲወጣ ነበር አጥቂዎቹ የተከተሉት:: ሆኖም እንደደረሱበት ሲያውቅና ተስፋ ሲቆርጥ መረጃ የያዘውን ቦርሳ መንገድ ላይ እንደጣለው ነው በምርመራ ወቅት የገለፀው::"

"ቀደም ሲል ሰውየው በመከላከያ ሚኒስቴር ዋና መሥሪያ ቤት ውስጥ ነበር የሚሰራው ያላችሁ መሰለኝ በትክክል አዳምጬ ከሆነ?" አሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ለማረጋገጥ ያህል::

"አዎ ጌታዬ::"

"እንግዲያው ዶክተር ... " አሉ ሽማግሌው የመረጃ አማካሪ ጭንቅላታቸውን ዘንበል አድርገው "... ሰውየው አደጋ በደረሰበት ምሽት ከመከላከያ ሚኒስቴር ሰነድ ሰርቆ አውጥቷል ማለት ነው? ቀደም ሲል ደግሞ 'ወኪሉ ነው' ያልክ መሰለኝ ... ካልተሳሳትኩ::"

"ክቡርነትዎ ..." አለ የመረጃው ሰው ወጥመዱ በላዩ ላይ ከመዘጋቱ በፊት በጣቱ እየረገጠ! እያፈገፈገ "ሰውየው በድብቅ ያወጣው ሰነድ በተሟላ መልኩ በእጃችን ቢገባ ለክቡርነትዎ ቢሮ ልናቀርበው የተዘጋጀነው ከፍተኛ የደህንነት ስጋትን በዝርዝር የሚጠቁም መረጃ ነበር::" አፍንጫው ላይ ችፍፍ ያለውን ላብ ሲጠርግ መሀረብ ፍለጋ ኪሱ ውስጥ ገባ::

"ምንድነው ይህ 'የደህንነት ስጋት' የምትለው? ... ግልፅ አድርገው::" የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ትናንሽ አይኖቻቸውን አጥብበው ተመለከቱት::

"ያንን በግልፅ ለማስቀመጥ ለጊዜው አልደፍርም ... ሆኖም ..." የመረጃው ኃላፊ ደንገርገር ያለው መሰለ " ... ቦርሳው በእጄ ቢገባ ሁኔታውን ግልፅ ላደርገው ይቻለኝ ነበር::" አይኖቹን በፖሊሱ አዛዥ ላይ ተከሉ::

"ይቅርታ አድርግልኝና ዶክተር ..." አለ የፖሊስ አዛዡ የፌዝ ፈገግታ ፈገግ ብሎ " ... ቦርሳውን በማንኛውም ሰዓት ልትረከበኝ ትችላለህ::"

"ኮሎኔል ..." አለ የመረጃው ሰው በተራው ፊቱን አሽሟጣጭ ፈገግታ አላብሶ "... እጄ እንዲገባ የምሻው ቀድሞ በቦርሳው ውስጥ የነበረውን መረጃ እንጂ በቦታው የተተካውን ተለዋጭ ሸሚዝና የውስጥ ልብሶች አይደለም::"

"ከአሁን በኋላ በእጅህ ካለው እስረኛ አገኛለሁ የምትለው መረጃ ምንድነው?" አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ የሁለቱን ባለሥልጣናት የቃላት ሽኩቻ ችላ ብለው::

"ያንን በግልፅ ለማስቀመጥ ትንሽ ይከብደኛል::" አለ የመረጃው ሰው::

"ክቡርነትዎ ..." አጋጣሚው እንዲያመልጠው ያልፈለገው የፖሊስ አዛዥ አፈፍ ብሎ ከመሀል ገባ "... ይህ ማለት የመረጃው መሥሪያ ቤት ሰውየውን አፍኖት የሚገኘው ያለ በቂ ማስረጃ ነው ማለት ነው:: በቅድሚያ የተባለውን ሰነድ የፖሊስ አባላት ሰውሩት ከተባለ እንዴት ነው ሰነዱ ለብሔራዊ ደህንነት ስጋት ፍንጭ ሰጪ መሆኑ የተደረሰበት? እሺ ይህም ታወቀ እንበል ... ክቡር ጌታዬ ..." አለ የፖሊስ አዛዡ ድምጹን ረገብ፣ ጎተት አድርጎ " ... ሰነዱ የያዘው ምስጢር ከታወቀ ከእርስዎ መደበቅ ለምን አስፈለገ? ለምን በግልፅ በእርስዎ ፊት አንነጋገርበትም? ይህ የሚያሳየው ሰውየው ታፍኖ የሚገኘው ለእኛ ግልፅ ባልሆነ ሌላ አጀንዳ ነው ማለት ነው::"

የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ በመስማማት መልክ እራሳቸውን ነቀነቁ::

"በመጀመሪያ ደረጃ ..." ቀጠለ የፖሊስ አዛዡ የልብ ልብ እየተሰማው " ... ሰውየው ወንጀል ተፈጽሞበት እንጂ ወንጀል አልፈጸመም ... በአሁኑ ሰዓት ግን ይህ ሰው ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የመዘዋወር መብቱን ተነፍጎ በእስር ላይ ይገኛል:: እንግዲህ ጌታዬ ይህ በመገናኛ ብዙሐን እጅ ቢደርስ ..."

በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ላይ የፈጠረውን ጫና ለማክበድ የፖሊሱ አዛዡ ንግግሩን በመሀል ገታና ወንበሩ ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠ::

"ዶክተር..." የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ በወንበራቸው ላይ ወደ ኋላ ለጠጥ ብለው የሁለት እጆች ጣቶቻቸውን አቆላልፈው የመረጃው ኃላፊ ላይ አተኮሩ " ... ዶክተር ክርክርህ አሳማኝ ሆኖ አላገኘሁትም ... አንደኛ ተገኘ ስለተባለው ሰነድ በቂ መረጃ የለህም ... በእጅህ ካለውም ሰው የምታገኘው ወይም አግኝተህ ነገር ግን ግልፅ ልታደርገው ያልደፈርከው 'ምስጢር' ልበለው ለእንተ ለራስህም አሳማኝ የሆነ አይመስለኝም:: ይህ ደግሞ ፖሊስ በሰውየው ላይ ወንጀል ፈጽመው የተሰወሩትን ግለሰቦች አድኖ ለመያዝ የሚያደርገውን ጥረት እያደናቀፈ ያለ ይመስለኛል::"

የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ መነጽራቸውን በግራ እጃቸው እንደያዙ መወሰን ያቃታቸው ይመስል በቀኛቸው አይኖቻቸውን ያሹ ጀመር::

"ትክክል ጌታዬ! ... በትክክል!" አለ የፖሊስ አዛዡ ሰውየው ለአንድ አፍታ ያወላወሉ ሊመስለው ጭንቅላቱን እላይና እታች እያወዛወዘ፤ እያደፋፈራቸው::

"ስለዚህ ..." አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ በግራ እጃቸው የያዙትን መነጽር በጥንቃቄ አይኖቻቸው ላይ እየሰኩ "... ሰውየውን ያለምንም ማዘግየት ለፖሊስ እንድታስረክብ ይሁን:: እ ..." አሉ ፊታቸውን ወደ ግራ መልሰው "... ኮሎኔልም በትህትና ሰውየውን ከተረከብክ በኋላ ምርመራው በአፋጣኝ ተከናውኖ ዶክተር

የሚፈልገው መረጃ ካለ ቀጥታ ባንተ በኩል ሊያገኝ የሚችልበትን መንገድ አመቻችለት::"

የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ፍጹም በተረጋጋ ሁኔታ ፍርድ ሰጡ::

ባለሥልጣናቱ እጅ ነስተው ወጡ::

የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ገፅታ ድንገት ተለዋወጠ:: መነጽራቸውን ከአይኖቻቸው ላይ መንጭቀው አወለቁና ጠረጴዛቸው ላይ ወረወሩት:: በክፍሉ ውስጥ ካሉት ሦስት ስልኮች መሀል በስተግራቸው ያለውን ቀይ ስልክ ጎተቱና እልህ በተናነቀው እንቅስቃሴ ይደውሉ ጀመር::

"ምን እየሰራህ ነው!" አሉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ከወዲያ ማዶ ስልኩን ያነሳው ሰው ከፊት ለፊታቸው የቆመ ይመስል በወንበራቸው ላይ ወደፊት ተንፏቀው አይኖቻቸውን ፊት ለፊታቸው አፍጥጠው " ... ምን እየሰራህ ነው? ... ዝም ብለህ አዳምጠኝ! ..." አመናጨቁት " ... የመረጃ ሰዎች በጭፍን ነው ያሉት ፖሊሶች እጅ ከገባ ግን ምን እንደሚሆን ታውቃለህ ... ከዚህ በላይ ላዘገየው አልችልም ... የምታደርገውን አድርግ ... ምን ማለቴ እንደሆነ ይገባሃል? ኢታማዦር ሹሙ ያገኙትን ቅንጥብጣቢ መረጃ ይዘው የመረጃ ቤቱ ላይ አጉል ጥርጣሬ አብቅለዋል ... አዎ! ... እሰቀ! ... ተጨማሪ መዝረክረክ አልፈልግም ... ይገባሀል? እሰቀ::" ስልኩን ጆሮው ላይ ዘግተው በገረሜታ ጭንቅላታቸውን ነቀነቁና ፈገግ አሉ:-

"ደደቦች::"

ሁለቱ ባለሥልጣናት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ የማረፍያ ቤት ሲወጡ እንደ ሁለት ጅቦች ጎን ለጎን ነበር:: ሰፋፊዎቹን ነጫጭ የእምነበረድ ደረጃዎች በፀጥታ ሲወርዱ የፖሊሱ አዛዥ በፀጥታው ውስጥ አሸናፊና ተሸናፊው ሳይለይ ይቀራል ብሎ የሰጋ ይመስል ፊቱን ወደ ፊት እንደቀሰረ:-

"ሰዎቼን አሁኑኑ እልካለሁ ... ሁኔታዎች እንዲፋጠኑልኝ ማድረግ ብትችል ..."

"አልችልም ..." የመረጃው ቤት ኃላፊ እልህ በተናነቀው ቃና አቋረጠው " ... በአሁኑ ሰዓት በግቢው ያለው ተረኛ መኮንን ነው:: ጠዋት ልትወስደው ትችላለህ::"

የውስጥ መረጃውን ኃላፊ ብስጭት ሲያጤን የፖሊስ አዛዡ በአሸናፊነት ፈገግ አለ::

ባለሥልጣናቱ ደረጃውን ወርደው እንደጨረሱ ሰላምታ ሳይለዋወጡ ወደ የመኪናዎቻቸው አመሩ::

"እንዲህ ነው!" አለ የፖሊሱ አዛዥ ሹፌሩ ከፍቶ በያዘለት የጥቁር መርሰዲሱ የኋላ በር ገብቶ በሩ ከተዘጋ በኋላ ጭንቅላቱን ከጀርባ አንገት ማስደገፍያው ላይ ጣል አድርጎ::

ሹፌሩ የመኪናዋን ሞተር አስነስቶ ከግቢው ወጥቶ ፊቱን ወደ አዲስ አበባ ሲመልስ ኮሎኔል ሥዩም ከኮቱ የውስጥ ኪስ ውስጥ ተንቀሳቃሽ ስልኩን አወጣ::

'... ማነሽ ... የስኳር መድኃኒቴን ... ማነሽ ... የሙቅ ውሀውን ላስቲክ ...'

መጡበት!

'ወደ ቤት መሄድ?'

'ፍጹም!'

ዛሬ ለሶስተኛ ጊዜ መደዳውን ውጭ ማደሩ ቢሆንም ግድ አልነበረውም።

"ገዛኸኝ ..."

"አቤት ጌታዬ ..." አለ ሹፌሩ በኋላ መመልከቻው መስታወት ውስጥ አለቃውን እየተመለከተ።

"አቤት ደውለህ እንደማልመጣ መልዕክት ተው ... እ ..." አለ ዛሬ ደግሞ የሚሰጠው ምክንያት ጠፍቶት "... እ ... ደብረዘይት ለሥራ ሔጄል በላት።"

"እሺ ጌታዬ።" ወደ አዲስ አበባ የሚጣደፈው ሹፌር ተጨማሪ ትዕዛዝ እየተጠባበቀ። የጠበቀው ትዕዛዝ ሲዘገይበት ሲፈራ ሲቸር "ወዴት እንሂድ ጌታዬ?"

ለአንድ አፍታ ኮሎኔል አይኖቹን በመኪናው ጣርያ ላይ ሰቅሎ አሰበ። የተለያዩ ሴቶች ገፅታ መጥቶ ድቅን አለበት። አንዳንድ ጊዜ ሁሉንም በአንድ ቤት ቢያስቀምጣቸው በወደደ። እንደዚያ ቢሆን እንደ አባቱ ... እንደሚጠላው አባቱ ... በአንድ ጊዜ ከአንድ ሴት ጋር ብቻ ማደር ባልኖረበት ነበር። በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ የኪራይ ቪላዎችና አፓርትመንቶች የቤት እቃ አሟልቶ፤ በየቤታቸው ደሞዝ ቆርጦ ያስቀመጣቸው ቅምጦቹ በርካታ ናቸው።

"አዲሷ'ጋ እንሂድ።" የግድ መምረጥ ነበረበት።

መረጠ።

'አዲሷ ... ፌቨን ...'

ይወዳታል? ይጠላታል? ... እርግጠኛ አይደለም ... ምን ፊልጋ በቋሚነት በተከራየላት ውድ የሆቴል ስዊት ውስጥ ለመግባት ፈቃደኛ እንደሆነች ሲያስብ 'ያንን ጥቁር ዘንፋላ ፀጉሯን ጨምድደህ እነዛን ትላልቅ፤ ጥቋቁር አይኖቿን ጓጉጠህ አውጣቸው - አውጣቸው' ይለዋል። ሲቀርባት ... ሲጠጋት ... ሽቶዋ ሲሸተው ... ገላዋ ሲዳስሰው ... ትንፋሽዋ ሲሞቀው ... ይርበተበታል። ያ ደግሞ ያበሳጨዋል። ፍጹም ሊያገኘው እንደማይችል የሚሰማውን ፍቅሯን ያገኘ ይመስል ሊያባብላት ይጥራል። አንዳንዴ ሲያስበው ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ለእርሷ ያወጣው ወጪ ...

'ህ!'

አፍ አውጥታ "አምጣ" አትለውም ... ግን ለምን እንደሆነ ባያውቅም በገባ በወጣ ቁጥር የሚሰጣት የወርቅና የአልማዝ ጌጣ ጌጦች፤ በየቡናው ጠረጴዛ ላይ

ሥዩምም በየወሩ ከሚቀያየሩ የቤት ሠራተኞችና ጠዋት ወጥቶ ማታ ከሚገባ አባቱ ጋር ተያያዘው - ኑሮውን::

ማታ ማታ ያለማሰለስ የተለያዩ ሴቶችን እየያዘ የሚመጣ አባቱ በሚይዘው ተለዋዋጭ ቁልፉ ሦስት ክፍል ቤታቸውን ከፍቶ ሲገባ ሥዩም ከቤት ሠራተኛዋ ጋር በሚጋራት ኩሽና ውስጥ እንቅልፍ የወሰደው መስሎ ይጋደማል::

አባቱ ከፊተኛዋ ክፍልና ከኩሽናዋ መሀል ካለችው ጠባብ የመኝታ ክፍሉ ሲገባ ሥዩም አቧራ-አቧራ ከሚሸት የብርድ ልብሱ ውስጥ ትንሽ አንገቱን አስግጎ፤ ጭንቅላቱን ብቅ አድርጎ፤ ጆሮዎቹን አቅንቶ ያዳምጣል:: ምን እንደሚባባሉ፤ ምን እንደማያደርጉ ባያውቅም የህፃን የማወቅ ጉጉቱ የሚያዳምጠውን ኮሽኮሽታና ሹክሹክታ እያጣጣመ ይቆያል:: 'ይህ ነው' ብሎ ለመናገር ባይችልም አባቱ፤ ትምህርት ቤት ትልልቆቹ ልጆች የሚያወሩትን 'ባለጌ ነገር' እንደሚያደርግ ደመነፍሱ ይነግረው ነበር::

የዛን 'ባለጌ ነገር' ሀ - ሁ ያስቆጠረችው የአሥራ አንድ ዓመት ልጅ ሳለ የተቀጠረችው አረጋሽ ነበረች:: ሁሌም ትዝ ትለዋለች:: በሰላሳው አጋማሽ ላይ የምትገኝ ድብልብል ያለች ወፍራም፣ ጠይም ሴት ነበረች:: ከአባቱ ቤት ተቀጥራ እንደገባች ሥዩም ከሚተኛበት የምግብ ማብሰያ ክፍል ውስጥ ቀን ቀን ተጠቅልሎ የገዛ ሳጥኗ ላይ የሚኀበር፤ ማታ ማታ ተተርትሮ ከምድጃው ትይዩ የሚዘረጋ ስስ የሳር ፍራሽ በሰባት ብር ተገዝቶላት መኝታ ቤቱን ትጋራው ጀመር::

ጥቂት ሳምንታት እንደቆየች አንድ ማታ አባቱ ያለወትሮው በጊዜ ቤት ገብቶ አመሸ:: አባቱ ቀልድ የማያውቅ፤ ስፊ ዘርጣጣ ፊቱ የማይፈታ ሰው ነበር:: በአንድ ቤት ይኑሩ እንጂ ምግብና መጠጥ ... እንደነገሩ ... ያለውን፤ ልብስም የተገኘውን ገዝቶ፤ ወደ ትምህርት ቤት ልኮ ያስተምረው፣ ያሳድገው እንጂ እንደ ልጅ አጫውቶት አያውቅም::

ያን ማታ አባቱ ከፊተኛው ክፍል እራት እንድታቀርብ አረጋሽን አዘዘ፤ ለራሷም ይዛ እንድትመጣ ተነገራትና ሁሉም በአንድነት እራታቸውን በሉ:: ከእራት በኋላ አባቱ:-

"ሥዩም በል ተነስ ተጣጠብና ተኛ ... ጠዋት ነው የምትነሳው::" ስላለው ሥዩም ወደ መኝታ ክፍሉ ገብቶ አልጋው ውስጥ ገባ::

አረጋሽ ከፊተኛዋ ክፍል እየተመላለሰች ዕቃ ስታነሳሳ ቆየች:: በመጨረሻ ከአባቱ መኝታ ክፍል ገብታ ቀረች:: ሥዩም ጆሮውን አቅንቶ ቢያዳምጥም አለወትሮው ድምፅ ጠፋ::

ከዚያን ቀን ጀምሮ ለጥቂት ቀናት የአረጋሽ የሳር ፍራሽ እንደተጠቀለለ በሳጥኗ ላይ ተረሳ:: አባቱም በጊዜ ይገባ ጀመር:: ይህ ግን ብዙ ጊዜ አልቆየም:: አባቱ እንደ ድሮው እያመሸ የተለያዩ ሴቶችን አስከትሎ ይመጣ ጀመር:: አረጋሽም ሳይፈታ የከረመ የሳር ፍራሿን እያልጎመጎመች ተርትራ፤ እያጉተመተመች ትጋደም ጀመር::

ሁለቱም በተጋደሙበት እንቅልፍ ሳይወስዳቸው ከወዲያኛው ክፍል የሚመጣውን የታፈነ ሳቅና ሹክሹክታ እያዳመጡ ያመሹና መብራቱ ጠፍቶ ፀጥታ ሲሰፍን እረጃጅም ትንፋሻቸውን እየተቀባበሉ ይተኛሉ::

"ነበሩ ... ግን እዚህ አያድሩም ... ቀን ቀን ብቻ መጥተው ማታ ማታ ይሄዳሉ::"

"ብቻህን ነበራ የምታድረው?"

"አዎ::"

"ያኔ 'ሰው ሰምኄ' ብለህ በሩ ላይ ተለጥፈህ ታዳምጥ ነበር ማለት ነው ... አይደል? ... አትዋሽ!"

ዝም::

"ሂ! ሂ! አረጋሽ እንኳን ይቺን ..."

ሌላ ጊዜ እንደምታደርገው መብራቱን ሳታጠፋ ልብሷን ማወላለቅ ያዘች:: ቀሚሷን ከሥር ሰብስባ ከትላልቅ ጡቶቿ ጋር ተናንቃ ባንገቷ አወለቀችውና ወደ ፍራሿ ግርጌ ወርወር አድርጋ በተኛበት ትክ ብላ ተመለከተችው::

አይኖቹን ጨፍኗል፤ ጆርባውን ግን አላዞረም::

"ሥዩም..."

"እ ..." አይኖቹን ሲገልጥ ከፍሉ መሀል በውስጥ ልብሷ ብቻ ቆማለች:: ሽቅብ ግር ብሎት ሲያያት ፈገግ አለች::

"መብራቱን አጥፋው እንጂ::"

"ሌላ ጊዜ አንቺ አይደለሽ የምታጠፊው?"

ናይለን የውስጥ ልብሷን የትከሻ ማንጠልጠያ ቁልቁል ከትከሻዋ አላቃ በድብልብል ወገቧ ዙሪያ እየሳበች ከመሬት ጣለችውና በውስጥ ሱሪዋ ቆመች:: ወዲያው እንደበረዳት ሁሉ "ት-ት-ት" አለችና የብርድ ልብሷ ስር ዘላ ገባች::

"አንተ ሥዩም..."

"አቤት::"

"የኔ ጌታ ስሞትልህ መብራቱን አጥፋው::"

ፈጠን አለና ከአልጋው ተነስቶ እራቁቱን በጣቱ እየረገጠ ከበሩ ጥግ ያለውን የመብራት ማጥፊያ ሊጫን ሔደ:: ቀጭን የህፃን ሰውነቱ ልብሱን አውልቆ ሲታይ ሳር ይመስላል:: አረጋሽ የሳር ፍራሿ ላይ ቁጭ እንዳለች በአይኗ ስትከተለው ቆየችና ከመብራቱ ማብሪያና ማጥፊያ ደርሶ ሲጫነው፤ ክፍሉ በጨለማ ሲዋጥ...

"ሥዩም..."

"እ?"

"ና::"

"አባትህ ልኮህ ነው?" በበሩ ደፍ ላይ ቀኝ እግሯን አስደግፋ ቁልቁል እያየችው::

"አይ ..." አለ እንዳቀረቀረ ቀይ የጥፍር ቀለም የተቀቡ የእግር ጥፍሮቿን እያየ ... የአረጋሽ ጉልድፍድፍ የእግር ጣቶች መጠብበት::"

"ምንድነው ታዲያ ... ከልጆች ተጣላህ?"

ቀና ብሎ አያት::

ጥቁር ሉጫ ፀጉሯ በወፍራሙ ጎንጎን ተደርጎ ከፊት በትከሻዋ ቁልቁል ተጋድሟል ... ትላልቅ፣ ጥቋቁር አይኖቿን ሲያይ አይኖቹን የሚያሳርፍበት ቦታ ግራ ገባውና ቅንጥንጥ አለ::

"አጥሀል እንዴ?" አለች ከደጃፍ ወጣ ብላ ግራ ትከሻውን ያዝ አደረገችና:: የለበሰችው ስስ፣ አጭር፣ ነጭ ቀሚስ ግማሽ ላይ መንገዱን አቋሞ መሰል ብለው የወጡትን ባትና ጭኖቿን አጋልጧቸዋል::

"አንትን ፈልጌ ነበር ..." አለ:: 'ገንዘብ እስከያዘ ድረስ ...'

"ምን?"

ቢገባት ብሎ በኪሱ ውስጥ የወሸቀውን የተጨማደዱ የብር ኖቶች እንደጨበጣቸው አወጣና ዘረጋላት::

ተቀበለችው ... በተን አድርጋ ቆጠረቻቸው::

"አባትህ ነው የላከህ?"

"አይደለም! የራሴ ብር ነው!" ፈጠን ብሎ አረማት::

የጠረጠረችውን ማመን አቅቷት ትክ ብላ ተመለከተችውና ዙሪያዋን ቃኘት ቃኘት አድርጋ በሩን ከፈተችለት::

ገባ::

"ቁጭ በል::" አለችና ከፊት ለፊቱ ሌላ ወንበር ይዛ ተቀመጠች::

"ከየት ነው ያመጣኸው ይሔን ብር?" ብሩን ወደፊት ዘርግታ ይዛ::

"የራሴ ነው ... እማ'ምላክን የራሴ ነው::"

"አትዋሽ ... እውነቱን ንገረኝ ... ከየት ነው የሰረቅኸው?'

"አልሰረቅሁም::"

"አባትህ እንደሰረቅኸው ቢያውቅ ምን እንደሚያደርግህ ታውቃለህ?"

"ከ'ሱ አይደለም የሰረቅሁት!"

"ከማነው ... ከየት ነው የሰረቅከው?" ወደፊት ጠጋ ብላ አጣደፈችው::

# ክፍል ፬

እግዚአብሔር የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ፣ የልቡ አሳብ ምኞት ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየ ...

*ኦሪት ዘፍጥረት ፮፡፭*

ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ ...

በእንፋሎት ከታፈነው የመታጠቢያ ቤት የጠዋት ልብሱን ደርቦ ፀጉሩን እያደራረቀ ብቅ ሲል፣ ሲጣሩ ተሰማው ...

"እዮቤ! ... አንተንኮ ነው!" እናቱ ናቸው::

ራሱን ነቅነቅና ፈገግ አለ:: አሁን ምን አሰበት በሳምንት አንድ ቀን - እሁድን በሰላም ቤቱ መዋል ቢችል::

"እዮቤ!"

"እማዬ መጣሁ አልኩኮ ..." አለ የመኝታ ቤቱ በር ሲበረገድ ፈጠን ብሎ ቁጣ ሳይጀምሩ::

"በመጀመርያ የእግዜሩ ሰላምታ ይቀድማል:: ምን ... አንተ እንደሆንክ እግዜሩንም ትተኸዋል ..." አሉ አይነስውር እናቱ ጥርት ያሉ ነገር ግን የማያዩ አይኖቻቸውን በልጃቸው ድምፅ አቅጣጫ ሰክተው::

"እንደምን አደርሽ እማዬ::"

"በል ቶሎ በል መጋጌጡ ይቅር ... ቤተስኪያን ነው የምንሔደው::" እያልጎምጎሙ በሩን ዘጉ::

ፈገግ አለ::

የእናቱ ነገር አይሆንለትም:: እሳቸውም ይህን አውቀው እሱ ላይ ሲሆን መሞላቀቅ ያበዛሉ:: ከእርሱ ሌላ ሁለት ልጆች አሏቸው፤ የእዮብ የሦስት ዓመታት ታላቅ ሰላማዊት እና የሷ ታላቅ እያሱ:: ሁለቱም አግብተው ቤት አደርጅተው ሳሉ እናትየው ከገዛ ቤታቸው ከባህር ዳር ወደ አዲስ አበባ ከመጡ የሚመርጡት የመጨረሻ ልጃቸውን የእዮብን አፓርትመንት ነው::

እዮብ ገና የሁለት ዓመት ህፃን እያለ የሞቱ አባቱን አያስታውሳቸውም:: በህፃንነቱ ሲሞላቀቅ ያደገው በእናቱ ላይ ነው ... የእርሱ ነገር አይሆንላቸውም ነበር ህፃንም ሆኖ ... አሁን ካደገ፤ ራሱን ከቻለ በኋላ ደግሞ እሳቸው ሲሞላቀቁ እሱ በተራው ያሞላቅቃል::

እዮብ ሁሌም የሚቆጨው የሚያንገበግበው የእናቱ መታወር ነው:: ሀኪሞች ይህ ነው ሳይሉት ገና በሀምሳ ሰባት ዓመታቸው ብርሃን አጡ:: እርግጥ ልጅም ሆነው አይናቸውን 'ታማሚ ነበሩ' ይባላል:: ቢሆንም ለእዮብ እናቱ ገና ሳያረጁ፤ ገና ብዙ ሲቀራቸው ... ታውረው ቤት መዋላቸው ያንገበግበዋል::

"እዮ... ቤ ... አንተ እዮብ!"

"መጣሁ! መጣሁ!"

በእጆቹ ጉርድ ሹራቡ ላይ ቆዳ ጃኬቱን ደረበና የመኝታ ቤቱን በር ከፍቶ ወጣ:: ቀስ ብሎ በጣቱ እየረገጠ ወደ ወጥ ቤት ገባ:: 'ቁርስ ልበላ ነው' ካለ ጉዱ እንደሚፈላ ያውቀዋል::

"እሁድ እርፍዶ በተኛ በወደደ:: ሰው በዚህ ውርጭ! ..." ቢሆንም እናቱ እንዲከፉ አይፈልግም:: ከእርሱ ቤት መጥተው ሲያርፉ በተቻለው ተሽቆጥቁጦ ነው የሚይዛቸው:: ከሁሉ ፀባያቸው የሚያበሽቀው ግን በእሁድ ጠዋት፣ በውርጭ ቤተክርስትያን ካልወሰድከኝ ማለታቸው ነው ... ለዚያውም በእግር ...

"ምነው ... ታወርኩ እንጂ ሽባ ነኝ? ... ደግሞ ከፈጣሪዬ ደጃፍ ለመድረስ ባንተ መኪና ልጫን!"

"እማዬ በመኪና ብንሔድ'ኮ ቶሎ እንደርሳለን::"

"ግድየለም ይቅርብኝ ... ብቻ አንተ ውጣ ... እግር እግዜር ነው ያንተ መኪና አይደለችም ... ብቻ ውጣ አንተ ..."

አይከራከሩቸውም::

ለምን በመኪና መሔዱን እንደማይፈልጉ ግን ያውቀዋል ... 'ለእዚያው ለጭቅጭቋ ጊዜ ለማግኘት ነው ...!'

"እዮቤ ... ተው ... ተው አትናቀኝ ምንም ብርሃን ቢነሳኝ እናትህ ነኝ ... ኋላ እሞትብህና ይቆጭሃል ..." ቀስ ብለው እያስተዛዘኑ፣ እያስፈራሩ ይጀምራሉ " ... ምነው እንዲያ ስትለምነኝ፣ ስትለማመጠኝ 'እሺ ብያት በነበር ... አንድ ልጅ እንኳን ወልጄ አቅፋው፣ ስማው በሞተች ኖሮ ...' ትላለህ ... ተው ..." ከቤተክርስትያን እስኪደርሱ አያቋርጡም::

'እሺ' ... ብሎ ያላደረገው ነገር ቢኖር ያ ብቻ ነው - ትዳር ይዞ ልጅ መውለድ::

"እዮቤ!... አትወጣም ወይ? ... ምን ታደርጋለህ ከዚያ?! ..." ጆሮቻቸውን ወደ ወጥቤቱ መልሰው:: ጠርጥረዋል " ... አንተንኮ ነው!"

"መጣሁ! ... መጣሁ እማዬ!" ፈጠን ብሎ ቅቤ የቀባውን ዳቦ ድምፅ ሳያሰማ እየገመጠ:: 'ሰው በገዛ እጁ ባዶ ሆዱን ሔዶ መራብ!'

አፉን ጠራርጎ ወደ ሳሎን ሲገባ ክፍሉ መሀል ቆመው አገኛቸው:: ጠጋ ብሎ በግራ በኩል ዘረክረክ ያለ ጋቢያቸውን አስተካከለላቸውና " ... በይ እንሒድ::" እለ ግራ እጃቸውን ያዝ አድርጎ::

"ማነሽ ..." አሉ እናቱ የልጃቸውን እጅ እንደ ያዙ "... ታዲያ ወፍራም ቡና ... እ ... ወፍራም ብያለሁ ያንን ሽረሬእችሁን አልፈልግም::"

"ኪርር ... ር ..."

"እንዴ እማዬ ..." አለ እዮብ የእናቱን እጅ ለቀቆ ወደ ስልኩ እየሔደ::

እንደ ክፍሉ ፀባይ እያንዳንዱ የመረጃ ባለሙያ ባልጠበቀው ጊዜና ቦታ እራሱን ሊያገኝ ይችላል:: በጥናት ክፍል ለሚሠራው ለእዮብ ግን በእሁድ ከቢሮ መፈለግ ያልተለመደ ነበር::

"እዎ ... እዎ ... እዮብ ቶሎ ቢሮ እንድትደርስ::" አለ አቤሰሎም::

እዮብ ፊቱን መልሶ ሳሎኑ መሀል ቆመው ወደ ቤተክርስትያን ለመሄድ የሚጠባበቁትን እናቱን ሲያይ! የሚከተለው ጉድ ሲታሰበው አይኖቹን ጨፈነ::

"አቤሰሎም ... ወደ አራት ... አራት ተኩል ላይ ብደርስስ?" አለ እዮብ::

"እዮብ! ... " አቤሰሎም አቋረጠው "... አይሆንም አሁኑኑ ድረስ ..." በስልኩ ውስጥ ያለው ድምፅ ለሰከንድ ያመነታ መሰለ "... እዮብ ትላንት እኔና አንተ የመረመርነው እስረኛ ሞቶ ተገኘ::"

"ሞቶ!" እዮብ ሳያስበው ጮኸ::

እረጋ ብሎ እናቱን ለማባበል አልሞከረም:: "እማዬ ... ይቅርታ ... ምንም ማድረግ አልችልም ... አስቸኳይ ነው ... ከቢሮ ነው ..." እያጉተመተመ ወደ አፓርትመንቱ በር አመራ::

አሳንሰሩ ሲዘገይበት ቁልቁል በደረጃው ተንደረደረ:: '... እስረኛው ሞቶ ተገኘ ...! የማይታመን ...!'

ቁልቁል በደረጃው ...

ከህንፃው ጀርባ ካለው የመኪናዎች ማቆሚያ ቦታ ከያዘችው ቢ ኤም ደብሊው መኪናው'ጋ ሲደርስ ትዝ አለው ... 'ቁልፉ! ... የመኪናው ቁልፍ!' ... የገዛ ጭንቅላቱን በመዳፉ መታና ፊቱን መልሶ የወረዳቸውን አራት ፎቆች ሽቅብ ...

ከአፓርትመንቱ በራፍ ሲደርስ ከበር ላይ የሼል ነዳጅ ማደያ የደንብ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ቆመዋል::

"አቤት ... ምንድን ነበር?" አላቸው በተራ እየተመለከታቸው::

በሩን ያንኳኳ የነበረው የሼል ነዳጅ ሰራተኛ ደንገርገር ያለው መሰለ፣ ወዲያው ፈጠን ብሎ:-

"ነዳጅ ... ማነው ጋዝ እንድናመጣላችሁ ደውላችሁ ..." አለ ከጎኑ ያለውን የቡቴን ጋዝ ሲሊንደር በጣቱ እያመለከተ::

"ይቅርታ ... ተሳስታችኋል ... እኔ አልደወልኩም::" አለ እዮብ የአፓርትመንቱን በር እያንኳኳ::

"አ! ስንተኛ ፎቅ ነው ይሔ ... አምስት አይደለም እንዴ?" አለ ሁለተኛው ሰው::

"አይደለም ... አራተኛ ፎቅ ላይ ናችሁ::" አለ እዮብ ፈገግ ብሎ ተሰናብቷቸው ሠራተኛው ከፍታ በያዘችው በር እየገባ::

"ምንድነው?"

"እባክህ እማዬን አንተ'ጋ ውሰድልኝ ... ትንሽ ..."

"ምነው ደህና አይደላችሁም? ... ሰይጣኗ መጣ?" አለ እያሱ እየሳቀ::

"ኖ-ኖ ደህና ነች ... አሁን ቸኩያለሁ ብቻ ቶሎ መጥተህ አንተ'ጋ ውሰዳት::" አለ እዮብ::

ወንድሙን ተሰናብቶ፤ ከመኝታ ክፍሉ ገብቶ የመኪናውን ቁልፍ ከራስጌ አነሳና ለአንድ አፍታ በጣቁ እየረገጠ ገርበብ ያለውን የእናቱን መኝታ ክፍል ገፋ አድርጎ ጭንቅላቱን አስገባ::

አልጋቸው ላይ ቁጭ ብለው ባዶው አየር ላይ አፍጥጠዋል::

'ምን ጣጣ ነው!'

የአፓርትመንቱን በር ቀስ ብሎ ድምፅ ሳያሰማ ዘጋና ቁልቁል በደረጃው ሮጠ:: 'ግድ የለም ለጊዜው እያሱ ከእርሱ ቤት ወስዶ ያቆይልኝ እንጂ ማታ እግሯ ላይ ወድቄ፣ ተለማምጬ እመጣታለሁ' አሰበ::

ከመኪናው ደርሶ ሞተሩን አስነስቶ ከግቢው ወጣ::

ከመኪና ማቆምያው ስፍራ መጨረሻ ረድፍ የቆመች የአንድ ጥቁር ቸሪኪ ጂፕ ሁለት በሮች በፍጥነት ተከፍተው ሁለት የሼል ኩባንያ የደንብ ልብስ የለበሱ ሰዎች ወረዱ:: ፈጠን ብለው ከጀርባ መኪናዋን ከፍተው የቡቴን ጋዝ ሲሊንደር አውጥተው ለሁለት ተሸክመው ወደ አፓርትመንቱ በር ተጣደፉ::

## ፭

"በመጀመሪያ ልጀን ማየት እፈልጋለሁ!" ፌይሰል በእልህ ተነስቶ ቆመ::

"ቁጭ ብለህ ለምጠይቅህ ..."

"አልቀመጥም! ... ልጀን!"

ከፊት ለፊቱ ያለውን የብረት ጠረጴዛ ከፊፍ ጨምድዶ እንደያዘ በትይዩ ተዝናንቶ ተቀምጦ በእርጋታ የሚመለከተው ሰው ላይ አፈጠጠ::

አእምሮው ጭጋግ ለብሷል:: የሆነው፣ ያለፈው ሁሉ ተቦጣጥሶ፣ ተዘበራርቆ ነው የሚታወሰው::

ከሦስት ወይ ከአራት ቀናት በፊት ... እርግጠኛ አይደለም ... በሪያድ አውሮፕላን ማረፊያ 'የተከለከለ አደንዛዥ እፅ በስውር ይዘህ ልትገባ ስትሞክር ተያዝክ' ብለው ሲያንገላቱት ትዝ ይለዋል:: ተከታትለው የመጡትን ሁኔታዎች ግን አእምሮውን አረጋግቶ ሊያጤናቸው አልቻለም::

በአውሮፕላን ማረፊያው ህንፃ ውስጥ ካለ ጠባብ ክፍል አስገብተው ሲፈትሹት ... የመቶ አለቃው በግራ እጁ የያዛትን የልጁን አሻንጉሊት ቀሚስ፣ ወደ ላይ ገልቦ ... እየተንቀጠቀጠ ... ፊቱ ደም መስሎ ... ሲጮህበት ... እንደ አስፈሪ ቅዠት ትዝ ይለዋል::

በዛች ደቂቃ ሊናገረው የሚፈልገው ብዙ ነገር ነበር ... ጉሮሮው ግን ድምፅ አላወጣልህ አለው ... ከየት መጣ ሳይለው ከመቶ አለቃው ጀርባ የነበረ ፖሊስ ድንገት ተጠግቶ በሁለት እጆቹ ላይ የእስረኛ ካቴና ሲያጠልቅለት ነገሩ ሁሉ ተዘበራረቀበት ... ምንም ሳይናገር የሚመጣውን መጠባበቅ መረጠ::

ከጠባቧ ክፍል እያጣደፉ አውጥተው ወደ መኪና ውስጥ ሲከቱት ያኔ በረገገ፦

"ልጀስ?" ግራና ቀኝ ክንዶቹን የያዙትን ፖሊሶች በተራ እየተመለከተ ጠየቀ "ልጀስ?"

ለጥያቄው መልስ ለመስጠት የሞከረ ግን አልነበረም:: ይሆናል ብሎ ከጠበቀው በላይ ሁሉ ነገር ተፋጠነበት ግራና ቀኝ ጨምድደው ይዘው ፊትና ኋላ ወደቆሙ ሁለት መርሰዲሶች አጣደፉት::

"ግባ!" የመቶ አለቃው ከፊት የቆመችውን መርሰዲስ የኋላ በር ከፍቶ::

"ልጀን የት ወሰዳችኋት?"

"ልጅህ ከኋለኛው መኪና ውስጥ ነች::"

አይኖቹን ልኮ የኋለኛው መኪና ውስጥ ልጁን ፈለገ:: የመኪናዋ የፊት መስታወት ላይ ነጥሮ የሚመለስ የጠራራዋ ፀሀይ ብርሃን ከውስጥ ያለውን መመልከት ከለከለው:: ወደ መርሰዲሱ ሲገባ ግራና ቀኝ እጆበውት የነበሩት

ሁለት የፖሊስ የደንብ ልብስ የለበሱ ሰዎች በሁለቱ በሮች ገብተው ከመሀላቸው ከተቱት:: እንደ ተጣለ በሬ ዙርያውን እየተጣደፉ ሲሻሙት ዘገነነው::

ጉዞው ረጅም አልነበረም:: ወደ አንድ በረጅም አጥር ተከብቦ ሰፊ የብረት መዝጊያ ወዳለው ግቢ ሲደርሱ ተሽከርካሪዋ ፍጥነቷን ቀነሰች:: መኪናዋ ከበሩ ከመድረሷ በፊት በርቀት መቆጣጠሪያ በሩ ወለል ብሎ ተከፈተ:: መርሰዲሷ ሰተት ብላ ገባች:: ሰፊው የብረት በር ከጀርባ በእርጋታ ተዘጋ::

እያጣደፉ ከመኪናዋ ሲያወርዱት ለመጀመሪያ ጊዜ ከጀርባ የነበረችው ልጁ የተጫነችባት ሁለተኛ መርሰዲስ በግቢው እንደሌለች ተረዳ::

"ልጄስ?"

የተከተለው መልስ ግን ፍጹም ያልጠበቀው ነበር:: የመጀመሪያው ቡጢ እምብርቱ ላይ ሲያርፍ ለሁለት ታጠፈ:: አፍንጫው አልደረስ ያለው የገዛ ትንፋሹን እየታገለ፣ እየቃተተ ቀና ሲል በቡጢ የመታው የመቶ አለቃ ፊቱ ላይ ተፋበት:: ምስክር አልነበረም:: ግቢው ወፍ ዝር የሚልበት አይመስልም:: ፍጹም ወና::

"ውሰዱት!"

ግራና ቀኝ እየጎተቱ፣ እየገፈተሩ በግቢው ውስጥ እራቅ ብሎ ወደ ቆመ ባለ አንድ ፎቅ ግራጫ ህንፃ አጣደፉት:: የህንፃውን ዋና የብረት በር እንዳለፉ ወደ ምድር ቤት በሚወስድ እረጅም ደረጃ ቁልቁል አቻኮሉት:: ደረጃውን ሲጨርሱ በተርታ የፍሎረሰንት መብራቶች የተደረደሩበት ረጅም መተላለፊያ ብቅ አለ:: ከኋላ ይከተለው የነበረው የመቶ አለቃ ቀድሞ አለፈና አንድ ሰፊ የብረት መዝጊያ ከፍቶ ገባ:: ተከተሉት::

ጠባብ ክፍል ነች:: ከወለሉ ጋር በትላልቅ ብሎኖች የተያያዘ የብረት አልጋ በስተቀኝ ይታያል:: በስተግራ አነስተኛ የፊት መታጠቢያና የመጸዳጃ ስፍራ አለ:: ከመሀል ሙሉ ነጭ የተቀባ የብረት ጠረጴዛና ሁለት ወንበሮች:: አለቀ::

ያለበት ክፍል የማረፊያ ቤት መሆኑን ሲረዳ ራሱን መቆጣጠር ተሳነው ... 'ሊያስሩት? ... ባላጠፋው ... በማያውቀው ነገር እስር ቤት!'

"እደንዛዥ እጹ የእኔ አይደለም! ... ዑመር ሀሰን ቤን ዳሪክ የሚባል ..." ይለፈልፍ ጀመር::

"ልብስህን ቀይር::" የመቶ አለቃው አቋረጠት፤ ለሌላ ቡጢ ሰበብ የፈለገ ይመስል ጠጋ ብሎ ቆመ::

"ወደ ኢምባሲዬ ስልክ መደወል እፈልጋለሁ ... ወደ ኢትዮጵያ ኢምባሲ!"

በስተቀኝ የቆመው ፖሊስ የፌይሰል ሁለት እጆች ላይ ያለውን ካቴና ፈትቶ በክፍሉ መሀል ጠረጴዛ ላይ ተጣጥፎ የተቀመጠ ደማቅ ቢጫ የእስረኛ ልብስ እንክቶ ደረቱ ላይ ለጠፈለት::

"ቀይር::"

የለበሰውን ልብስ አስወልቀው የለሊት ልብስ የመሰለ ሰፊ ሱሪና ሸሚዝ አስለብሰውት ፍርግርጉን መዝጊያ በላዩ ላይ ዘግተው ከምድር በታች በተሰራው ረጅምና ጠባብ መተላለፊያ ተከታትለው ሲሔዱ እየራቀ፣ እየደበዘዘ የሚሔደው የኮቴአቸው ድምፅ ብቻ በተዘበራረቀ አእምሮው ውስጥ እንደማያቋርጥ ደወል ... ኳ . ኳ . ኳ . ኳ ...

በፍርግርጉ የብረት መዝጊያ ላይ ተለጥፎ፣ እጆቹ የብረቱን ቋሚዎች ጨምድደው ተጠባበቀ:: ሊገልጸው የማይችለው ስሜት እንደ ድፍርስ ጎርፍ ደርሶ እያገለባበጠ፣ እያጣደፈ፣ እያፍገመገመ ይዞት ቁልቁል ሲወርድ እራሱን መቆጣጠር ተሳነው::

'... ልጄን ... ልጄን የት ወሰዷት?' ... ጩኸቷ ... እርር ያለ ለቅሶዋ መልሶ መላልሶ ጭንቅላቱ ውስጥ ይደውልበታል:: ቀጫጭን ክንዶቿን በእግሩ ዙርያ ጠምጥማ ያሰማችው በፍርሀት የሚርገበገብ ስስ እዬዬዋ ... ጆሮዎቹን በሁለት እጆቹ ጥርቅም አድርጎ ይይዝና "ባባ! ..." ሰቀቀኗ ጆሮው ላይ ሲያንጫርር ... ወደኋላ አፈግፍጎ አልጋው ላይ ተቀምጦ ሁለት ጉልበቶቹን በሁለት እጆቹ አቅፎ ... ወዲያው ድንገት ብድግ ብሎ ... ፍርግርጉን በር እየደበደበ ... ባለው ኃይል ይዞ እየነቀነቀ:-

"ልጄን! ... ልጄን!" ይጮሀል::

በታሰረበት ጉረኖ ቀንና ለሊት የለም:: ሁሌም በግ ብለው በረጅሙ መተላለፊያ የተደረደሩት የፍሎረሰንት አምፖሎች የጊዜን ሂደት ሽረው ለዓይን የሚጥበረብር ነጭ አቧራማ ብርሃናቸውን ይነዙታል:: አይመሽም ... አይነጋም::

በፍርግርጉ መዝጊያ ላይ ለምን ያህል ጊዜ ተለጥፎ እንደቆየ ባያስታውስም የተሸከሙት እግሮቹ በድካም ሲብረከረኩ ክንዶቹ ሲዝሉ ከጥግ ካለው የብረት አልጋ ላይ ተመልሶ ተቀመጠና የፈዘዙ አይኖቹን በመዝጊያው ላይ ተከላቸው ... ተጠባበቀ ... በስሆሳስ በሚንቀሳቀሱ ከንፈሮቹ የፈጣሪውን ስም ደጋግሞ እየጠራ እየተለማመጠ ... ተጠባበቀ ...

የመጣ ሰው ግን አልነበረም::

የቀረው እንጥፍጣፊ ድንጋጤ፣ ንዴትና እልህ ትተውት ሲሄዱ የሰውነቱን ስቃይ፣ ትኩሳት ያጥቡለት፣ ያቀዘቅዙለት ይመስል ድምፅ ሳያሰሙ የእንባው ዘለላዎች በጉንጮቹ ላይ እየተከታተሉ ቁልቁል ወርደው በሲሚንቶው ወለል ላይ ተንጠባጠቡ:: ሁሌም አይዞህ የሚለው ሲያጣ፣ የሚወዳት ሚስቱ ፊቱ ላይ ድቅን ስትልበት ደርሰው እሹሩሩ የሚሉት ... ውስጡን የሚያጥቡለት የእንባው ዘለላዎች ደረሱለት::

ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ ትዝ አይለውም ... ምናልባት ለሰዓታት ... ምናልባት ለቀናት ... ግን የብረት አልጋው ላይ እንደተጋደመ ከረጅም ጊዜ በፊት የሰማቸው የሚመስሉ የሰው ኮቴዎች በሩቁ ሲሰሙት እንደ'ረጋ በረዶ በተቀመጠበት የቀዘቀዘ፣ የበደን ሰውነቱ ነፍስ ዘራ::

ከተቀመጠበት ዘሎ ተንስቶ በፍርግርጉ በር ላይ ተለጠፈ::

ተከታትለው ብቅ ሲሉ አራት እንደሆኑ ተመለከተ:: ሦስቱን ያስታውሳቸዋል:: የመቶ አለቃውና በመርሰዲሱ ውስጥ ግራና ቀኝ ያጀቡት ሰዎች ናቸው:: ይሁን

እንጂ ሦስቱም ባለፈው ቀን ለብሰውት የነበረውን የፖሊስ የደንብ ልብስ አውልቀው የሲቪል ልብስ ለብሰዋል:: ጥቁር የእጅ ቦርሳ የያዘው አራተኛው ሰው ግን አዲስ ነበር::

የመቶ አለቃው ከኪሱ ቁልፍ አውጥቶ በሩን ከፈተና አራተኛውን ሰው አስከትሉ ወደ ክፍሉ ገቡ::

"ተቀመጥ::" አለ የመቶ አለቃው በአንድ ጣቱ በክፍሉ መሀል ለመሀል በቆመው ጠረጴዛ ዙርያ ካሉት ሁለት ወንበሮች ወደ አንደኛው እያመለከተ::

ፌይሰል ለሰከንዶች ካመነታ በኋላ አንደኛውን የብረት ወንበር ስቦ ተቀመጠ:: እስካሁን በዝምታ የቆየው፣ ቦርሳ ያንጠለጠለው ሰው ከፌይሰል ትይዩ ያለውን ሁለተኛ ወንበር ስቦ ተቀመጠና ፊቱን ወደ የመቶ አለቃው መልሶ ዘና ባለና የበላይነትን በሚገልፅ ቃና:-

"ውጭ ቆይ::" አለ::

የመቶ አለቃው የመለዮ ሰላምታ ከጎደለው ተጠንቀቅ ጋር ፊቱን መልሶ፣ ከክፍሉ ወጥቶ ፍርግርጉን በር ከውጭ ከቆለፈ በኋላ ከውጭ ቆመው የነበሩትን ሁለት ፖሊሶች አስከትሉ ሔደ::

"አቶ ፌይሰል አብዱል ከሪም ..." አለ ከፌይሰል ፊት ለፊት የተቀመጠው ሰው ፍጹም በራስ መተማመንን በሚገልፅ ቅላፄ "... ሁኔታዎችን በተቻለን መንገድ ለእኛም ሆነ ለአንተ ለማቅለል ትብብርህ እጅግ አስፈላጊ ነው::"

"በመጀመርያ ልጄን ማየት እፈልጋለሁ!" ፌይሰል የሰውየውን ንግግር አቋርጦ ከተቀመጠበት ተነሳ::

"ቁጭ በልና ..."

"አልቀመጥም! ልጄን!"

"አቶ ፌይሰል ቁጣ የትም አያደርሰንም ..." አለ ሰውየው እረጋ ብሎ " ... ቁጭ በልና ለምጠይቅህ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጠኝ::"

"ልጄን ማለት ልጄን ነው! የፈለጋችሁትን ማድረግ ትችላላችሁ!" አለ ፌይሰል በእልህ የሚንቀጠቀጥ ሰውነቱን መቆጣጠር ሲሳነው ከፊት ለፊት ያለውን ጠረጴዛ በሁለት እጆቹ ተደገፈና ተዝናንቶ ተቀምጦ በሚመለከተው ሰው ላይ አፈጠጠ::

"ለምትጠየቀው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆንክ ባለህበት ሁኔታ የክስ ፋይል ከፍቼ ለፍርድ ላቀርብህ እችላለሁ::"

"ቀጥል! ... የፈለግከውን አድርግ!"

"ወንጀለኛ መሆንህ የተዘነጋህ ይመስለኛል አቶ ፌይሰል::"

"ወንጀለኛ አይደለሁም! አደንዛዥ እፁ የእኔ አይደለም ... እምስተርዳም ..."

"አደንዛዥ እፁ የተገኘው’ኮ ..." ሰውየው ከመሀል ገባ::

"ነገርኩህ! አደንዛዥ እፁ የእኔ አይደለም ... አምስተርዳም አውሮፕላን ማረፊያ ያገኘሁት ዑመር ሀሰን ቤን ዳሪክ የሚባል ሰው ነው ለልጁ የሰጣት ... ማስቲ ... አሻንጉሊቷን::"

"አቶ ፌይሰል ..." ሰውየው ድጋሚ አቋረጠው " ... የምትለኝን ለመረዳት ከስር መጀመር አለብን ... ያንን ለማድረግ ደግሞ እራስህን ገዝተህ በእርጋታ መወያየት ይኖርብናል::"

ፌይሰል እያመነታ ሲቀመጥ ሰውየው በስተቀኙ ወለሉ ላይ አስቀምጦት የነበረውን የቆዳ ቦርሳ አንስቶ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠና ከፍቶ አንድ ካኪ የወረቀት ከረጢት አወጣ::

"አቶ ፌይሰል ... ባለንባት ጥልፍልፍና አታካች ዓለም ማንኛውም ነገር ሊፈጸም ይችላል:: እንዳልከው ምናልባት እፁ የአንተ አይደለም:: ያም ሆነ ይህ ከአንተ ጋር በረጋ መንፈስ ለመወያየት እድሉን ካገኘሁ ሁኔታዎች የበለጠ እየተገለጹልኝ እንደሚመጡ ተስፋ አለኝ ... ስለዚህ በጥንቃቄ እየተከታተልከኝ ለምጠይቅህ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ትሰጠኛለህ::"

"በመጀመሪያ ..." አለ ፌይሰል አእምሮው እየሰከነ፤ ያለበትን ሁኔታ እየተረዳ ሲመጣ ሰውየውን አቋርጦ " ... የአገሬ ኤምባሲ ተወካይ እንዲያየኝ እሻለሁ::"

ሰውየው ፈገግ ብሎ ተመለከተው::

"ግሩም:: አሁን ማስተዋል የጀመርክ ይመስለኛል:: ያለህበት እጅግ አደገኛና መፈናፈኛ የሌለው ጥጋት ግልፅ የሆነልህ ይመስለኛል::"

ለጥቂት ሰከንዶች ሰውየው ዝምታ የመረጠ መሰለ:: ወዲያው በወንበሩ ላይ ወደፊት ጠጋ ብሎ ድምፁን ቀንሶ:-

"አቶ ፌይሰል የአገርህ ኤምባሲ ባለሥልጣናት ስለተፈጠረው ሁኔታ እንዲያውቁ ከተደረገ ጉዳዩ በደቂቃዎች ውስጥ ገሀድ ስለሚወጣ በሰዓታት ውስጥ ይፋ ክስ መስርቼ በችሎት ፊት ሳቀርብህ እገደዳለሁ ... ተግባባን?"

"የክሱ መከፈት አያስጨንቀኝም ... እኔ ንፁህ ሰው ነኝ::"

"አቶ ፌይሰል ..." ሰውየው ወደ ኋላ ወንበሩን ተደግፎ ፈገግ አለ " ... ንፁህ ሰው ትሆን ይሆናል ... እኔም የማውቀው ይህንን ነው:: ቢሆንም እስቲ እረጋ ብለህ ለማሰብ ሞክር ... ከአምስተርዳም ተነስተህ ሪያድ ስትገባ በእጅህ ላይ የተከለከለ አደንዛዥ እፅ ተገኝቷል:: እኔ ለተከበረው ፍርድ ቤት የማቀርበው መረጃ ቢኖር ይህንን ነው:: አበቃ::"

"ንፁህ እስከሆንኩ ድረስ ..."

"ወጥመድ ነው! ... አንተ ውሻ ... ወጥመድ ነው ይሔ ሁሉ!"

"እራስህን ግዛ ..." አለ ሰውየው ከተቀመጠበት ሳይንቀሳቀስ በአንገቱ ዙሪያ ሸሚዙን ጨምድዶ የያዘውን የፌይሰልን እጅ ችላ ብሎ "... ራስህን ግዛ ... 'ወጥመድ ነው ወይ?' ላልከው እመነኝ ... ሕይወት በ'ራሷ በእያንዳንዳችን ላይ የተደፋች አስጠሊታና ጨካኝ ወጥመድ ነች:: ዋናው ነጥብ በወጥመድ ውስጥ እንዴት እራስህን ገዝተህ መኖር እንደምትችል መጠበቡ ላይ ነው ... ይህ ካቃተህ የሙት ልጅህን በህሊናህ ቅረፃትና! በማን እጅ እንደሆነች አስታውስ ... በነገራችን ላይ አቶ ፌይሰል ... ትዕግሥት ያለኝ ሰው እመስላለሁ ... ግን ይህ የአሳሳች ተፈጥሮዬ አንደኛው ገፅታ ነው::"

"ምንድነው የምትፈልጉት ... ምንድነው ከእኔ የምትፈልጉት?" አለ ፌይሰል የሰውየውን ሸሚዝ ጨምድዶ የያዘውን የሚንቀጠቀጥ እጁን ሰብስቦ ወንበሩ ላይ ዘፍ ብሎ::

"በጣም ጥሩ ... አሁን ተመሳሳይ ቋንቋ መጠቀም ጀመርን::"

"ወሬውን ተወውና የምትፈልገውን ተናገር!" አለ ፌይሰል ጮሆ::

"ወደ ዋናው ነጥብ ከመግባታችን በፊት ያለንበትን ሁኔታ! እኔ ላቀርብልህ የምችለውን የመፍትሄ ሀሳብ! ሌሎችም አማራጮች እንዳሉ እናጣራ:: እኔ ልሰጥህ ከምችለው የተሻለ አማራጭ ካለ ከወዲሁ አብረን እናፈላልግ በተቃራኒውም የተሻለ አማራጭ እንደሌለ ከተረዳን ... ምንም እንኳን አስቸጋሪ ቢሆንም ያለን አማራጭ ያ ብቻ መሆኑን አውቀን አብረን እንጓዛለን ... ተግባባን?"

"ቀጥል-ቀጥል::" አለ ፌይሰል አእምሮውን አጥርቶ ለማቀየት እየታገለ::

"ጥሩ ... እንበልና ... የእኔን ምክር አልሰማም ብትል ምን ይከተላል?" ሰውየው እርሱ እራሱ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ እንደሚፈልግ ሁሉ ለአንድ አፍታ አይኖቹን ወደ ላይ ሰቅሎ ቆየና ቀጠለ "... ያለ ጥርጥር በሰዓታት ውስጥ ጉዳይህን በይፋ ለአገርህ ኤምባሲ ባለሥልጣናት አሳውቀን የክስ ፋይል እንከፍታለን:: በቀናት በሚቆጠር ጊዜ ውስጥ ችሎት ቀርበህ ሞት ይፈርድብሃል::" አሁንም ሰውየው የተናገረው በፌይሰል አእምሮ ሰክኖ ቦታውን እስኪይዝ ንግግሩን አረገበና የሚያወሩትን ወሬ ሌላ ሦስተኛ ሰው እንዳይሰማ የፈለገ ይመስል ወደፊት ጠጋ ብሎ ድምፁን ቀንሶ በሹክሹክታ ቀጠለ:-

"ይህ ፍጹም ቀላል! ግልፅና ተራ ጉዳይ ነው - ቅደም ተከተሉ:: ሆኖም እዚህ ላይ አንድ አነስተኛ ድራማ ይታከልበታል ... ይኸውም የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ከተፈጸመብህ በኋላ የሳውዲ አረቢያ መንግሥት የሚያውቀው አንድ አቶ ፌይሰል አብዱል ከሪም የተባለ ኢትዮጵያዊ ከአምስተርዳም ተነስቶ ሳውዲ አረቢያ ሲገባ ደብቆ ይዞት ከነበረ አደንዛዥ እፅ ጋር መያዙንና በፍርድ ቤት ውሳኔ አንገቱ በጎራዴ መቀላቱን ይሆናል:: ስለዚህም እሬሳህ ለአገርህ ኤምባሲ ባለሥልጣኖች ይሰጥና ሁሉም የተፈፀመ! ያለፈ! የተረሳ ይሆናል:: ምናልባት ከአንዳንድ የእርጎ ዝንቦች - '... ሟቹ ወንጀለኛ ወደ ሪያድ ሲገባ አንዲት ትንሽ ሴት ልጅ ይዞ ገብቶ ነበር ወይ?' የሚል ጥያቄ ቢነሳ ... በእርግጥ እልሃለሁ ... የሳውዲ አረቢያ መንግሥት የሚሰጠው መልስ 'ፍጹም! ... ሰውየው ወደ ሪያድ የገባው ብቻውን ነበር::' የሚል ይሆናል::"

ፌይሰል "ቀጥል::" ለማለት ጭንቅላቱን ነቀነቀ::

"በጣም ጥሩ! እንግዲህ ከአንተ ወደሚጠበቀው ጉዳይ ስንመጣ ... ትላንት ጠዋት ንብረትነቷ የአንድ ግሪካዊ ባለሀብት የሆነች አንድ መርከብ ተከራይተህ ወደ ጅቡቲ ወደብ በርከት ያለ ዕቃ ልከሃል::" አለ ሰውየው ማብራርያ እንደፈለገ ሁሉ ቅንድቦቹን ግንባሩ ላይ ሰቅሎ::

"አዎ ... የምሰራበት አስመጪና ላኪ ድርጅት የተለያዩ ማዳበርያዎችን ወደ ኢትዮጵያ ያስገባል ... ያንን ነው ከሮተርዳም ወደብ ወደ ጅቡቲ እስጭኜ የላክሁት::"

"ትክክል:: በእጃችን ያሉት ሰነዶች እንደሚያሳዩት መርከቧ ሶስት ሺህ ቶን ዳፕ ማዳበሪያ ጭና በተያዘላት ፕሮግራም መሠረት የሮተርዳምን ወደብ ለቃለች:: በሚቀጥለው ሳምንት ማክሰኞ ከጅቡቲ ወደብ ትደርሳለች::"

ፌይሰል በመስማማት ጭንቅላቱን ነቀነቀ::

"መርከቧ አንተ እንድታደርስልህ ከተኮናተርካት ሦስት ሺህ ቶን ማዳበሪያ በተጨማሪ ንብረትነቱ የእኛ የሆነ ስምንት መቶ ኪሎ ግራም ዕቃ ይዛ ነው ከሮተርዳም የተነሳችው:: በዚህ እንደማትከፋ ተስፋ አለን:: ሆኖም ዋናው ነጥብ ዕቃችን ጅቡቲ ወደብ ተራግፎ ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ አቀድንለት ነጥብ እንዲደርስ ያንተ እርዳታ የሚያሻን ሆኖ አግኝተነዋል::"

"ምንድነው ይህ ዕቃ ... በመርከቧ ላይ የጫናችሁት? ... ማለቴ ..."

"ከሞላ ጎደል 'አንተ ወደ ሳውዲ አረቢያ ይዘኸው ልትገባ ከሞከርከው ዕቃ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው' ብል ከእውነቱ ብዙም የራቀ አይሆንም::" አለ ሰውየው የሁለት እጆቹን ጣቶች በቁንጥ አጠላልፎ ወደ ኋላ ለጠጥ አለና::

"ምንድነው የምትለው ...?" አለ ፌይሰል ተደናግጦ "... አደንዛዥ እፅ በድብቅ ወደ ኢትዮጵያ ይዘህ ግባ ነው? ወንጀል ፈጽም ነው የምትሉኝ?"

"ቆይ - ቆይ ... ያለንበትን እያስታወስን!" አቋረጠው "... የተባለውን ዕቃ ወደ ኢትዮጵያ ይዘህልን ስትገባ ምንም ችግር እንደማይገጥምህ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ:: በመጀመርያ ማዳበርያው የወደብ ኪራይ ሳለመከፈል ሲባል ከመርከቧ ላይ በቀጥታ ሀምሳ-ሀምሳ ኪሎ በሚይዙ የፕላስቲክ ከረጢቶች እንደታሸገ ወደ መኪና ይጫናል:: በዚህ ወቅት ቀደም ብሎ በተዘረጋ ዕቅድ መሠረት የእኛ ዕቃ በጭነት መኪናው ላይ የሚጫነው አንተ፣ እኛና የመኪናው እስጫኝ የወደብ ሰራተኛ ብቻ በምናውቀው መንገድ ነው:: ይህ ከሆነ በኋላ መኪናው ያለፍተሻ ቀጥታ የኢትዮጵያን ድንበር አልፎ ይገባል:: ምክንያቱም አንተም እንደምታውቀው ማዳበርያ የጫኑ ተሽከርካሪዎች በፍተሻ ኬላ ላይ ቆመው አይፈተሹም:: ማዳበርያውንም የመረጥነው ለዚህ ነው:: መኪናው ..."

"ቆይ! ..." ፌይሰል አቋረጠው "... ብያዝስ ... እንደ አጋጣሚ ብያዝስ?"

"አሁንምኮ ተይዘሃል ..." ፈገግ አለ ሰውየው ሁለት እጆቹን ግራና ቀኝ ዘርግቶ "... አደንዛዥ እፅ ይዘው ወደ አገር ውስጥ ለመግባት የሚሞክሩ ግለሰቦችን

በተመለከተ ደግሞ የኢትዮጵያ ህግ ከሳውዲ አረቢያ ህግ የተሻለና የቀለለ ብቻ ሳይሆን በነፃ እንደመለቀቅ የሚቆጠር መሆኑን አንተም ታውቃለህ ... ሀበሾቹ ቢበዛ አንድ ሁለት መቶ ዶላር ይቀጡሀል ... ከከፋም አንድ ስድስት ወር ያስሩህ ይሆናል ... በተጨማሪም እኛ የሰጠንህን ኃላፊነት ለመወጣት ስትሞክር ችግር ላይ ብትወድቅ ቢያንስ ልጅህ በሚቀጥለው አውሮፕላን ወደ አዲስ አበባ! ወደ አያቶቿ ትሔዳለች:: አቶ ፌይሰል እንድታደርግ የምጠይቅህ ጉዳይ ከአደጋ ፍጹም የፀዳ ሳይሆን ይችላል ... ሆኖም አሁን ካለህበት ወስብስብ ሁኔታ ግን በእጅጉ የተሻለ ነው:: አይመስልህም? ስታስበው እኔስ ብሆን አንተን የሚጎዳ ነገር እመክርሀለሁ? ፍፁም!"

ፌይሰል ግራ ተጋብቶ ሰውየውን ይመለከተው ጀመር::

"እንዳልኩት ..." ቀጠለ ሰውየው "... አዲስ አበባ እንደ ደረስክ ተጨማሪ መመርያ ይደርስሀል:: በዚያ መመርያ መሠረት ዕቃውን ለተገቢው ወገን ታስረክባለህ:: አለቀ:: በቃ::"

ፌይሰል በተቀመጠበት ሳይንቀሳቀስ ሰውየውን ይመለከተዋል::

"አ! በነገራችን ላይ ዕቃውን እንዳስረከብክ በተከታይ በሚደርስህ መልዕክት ወደ አዲስ አበባ በሌ አውሮፕላን ማረፍያ ሔደህ ልጅህን ትረከባለህ::" ፈገግ አለ ሰውየው:: "መቼም ከአጭር መለያየት በኋላ ስታገኝህ ሴት ልጅህ እንዴት እንደምትሆን ይታየኛል ... አይ ልጆች! ... ልጅነት ጥሩ ነው!"

ፌይሰል ዝም አለ::

"አቶ ፌይሰል ..." አለ ሰውየው የፌይሰልን ዝምታ እንደ ስምምነት በመውሰድ "መልካም ዕድል::"

## ፮

"መሣርያ ይዘዋል?" አለው ወደ ዶክተር ብርሃን ጸሐፊ ከሚያስገባው በር ውጪ የቆመው የጥበቃ አባል::

እዮብ ጆሮዎቹን ማመን አልቻለም:: የመረጃው መሥሪያ ቤት ባልደረባ ከሆነ ጀምሮ ባለፉት ስድስት አመታት ወደ ዶክተር ብርሃንም ሆነ ወደየትኛውም የሥራ ባልደረባውና አለቃው ቢሮ ሲገባ እንዲህ ጥርጣሬ በሞላው አይን ታይቶ አያውቅም::

'ቀድሞ ነገር ጥርጣሬው ከየት መጣ?! የምን ጥርጣሬ?!'

በእሁድ እቤቱ ድረስ ስልክ ተደውሉለት፤ 'የሥራ ባልደረባው አቤሰሎም ... እስረኛው ሞቶ ተገኘ...' ሲለው እዮብ በመጀመርያ በአእምሮው የተቀረፀበት ሁኔታ ቢኖር ሰውየው እራሱን መግደሉ ነበር:: ሁኔታው ቢያስደነግጠውም መኪናውን አስነስቶ ወደ ቢሮው ሲንዝ ሰውነቱ ተረጋግቶ ዝርዝር ነጥቦችን ሲያጤን አጋጣሚው እርሱ እራሱ ቀደም ብሎ ሊጠረጥረው የሚገባ እንደነበር ተገለፀለት::

"ደደብ!" እዮብ የገዛ እራሱ ጥፋት ወለል ብሎ ታየው::

'እነርሱ አላመኑትም እንጂ እስረኛው በግልፅ ነው የነገራቸው፤ አፍ አውጥቶ "ሟች ነኝ..." ነበር ያላቸው:: "... ፈጠነም ዘገየ ይገድሉኛል ... ከዚህ ከመውጣቴ በፊት ከያሉበት ካልተለቀሙ ... ሟች ነኝ::" ነበር ያለው::

"ምንድነው?" አለ ግራ በተጋባ ሁኔታ ዘቡ ላይ አፍጥጦ::

"ይቅርታ ጌታዬ ማንም ወደዚህ እንዳያልፍ መባሉን ብቻ ነው የማውቀው::" በስተግራ የቆመው የጥበቃ አባል ፈርጠም ብሎ::

እዮብ ትክ ብሎ ተመለከተው:: አያውቀውም:: የግቢውን ጥበቃ አባላት አጣርቶ ያውቃቸዋል::

"አባል ነኝ ... መሳርያ አልታጠቅሁም::" አለ እዮብ በገዛ መሥሪያ ቤቱ እንደ እንግዳ በጥርጣሬ ሲታይ በስጨት አድርጎት::

"ሊፈተሹ ፈቃደኛ ነዎት?"

እዮብ መልስ ሳይመልስ ሁለት እጆቹን ወደ ጎን ዘረጋ::

የመተላለፊያውን በር አልፎ ከዶክተር ብርሃን ልዩ ፀሐፊ ቢሮ ትይዩ ካለው የእንግዳ መቆያ ክፍል ሲገባ መደዳ ተቀምጠው አየ:: አቤሰሎም በስተቀኝ ፊንጠር ብሎ ተቀምጧል:: ከእርሱ ባሻገር በአግዳሚው ጥቁር የቆዳ ሶፋ ላይ የእስር ክፍሉ ኃላፊ ሻለቃ ሞገስ ባየልኝ፣ ሁለት የእስር ቤቱ ጥበቃ አባላትና በግቢው ክሊኒክ ውስጥ የሚሠራ ነርስ ተቀምጠዋል:: እዮብ ሁሉንም በጥቅሉ "እንደምን አደራችሁ::" አለና አቤሰሎም ጎን ተቀመጠ::

"ምንድነው ነገሩ?" አለ እዮብ ቀስ ብሎ ፊቱን ወደ አቤሴሎም መልሶ በሹክሹክታ::

"አላውቅም::" አለ አቤሰሎም:: ፊቱ ገርጥቶ አመድ መስሏል:: ከናፍሩ ደርቀው ሽብሽብ ብለዋል::

"ምን ማለት ነው አላውቅም?" እዮብ አፈጠጠበት::

"እዮብ ..." አለ አቤሰሎም ስሜቱን ለመቆጣጠር እየሞከረ "... ጠዋት ከተረኛ መኮንኑ ቢሮ ተደውሎ 'በአስቸኳይ ዶክተር ብርሃን ቢሮ እንድትደርስ' ተባልኩ:: ግቢ ገብቼ! ከቢሮ ስደርስ በሩ ገርበብ እንዳለ ነው:: ገፋ አድርጌው ስገባ ክፍሉ እንደሌለ ሆኗል:: መሳቢያዎች ተስበው - ተስበው ወጥተው በየቦታው ተጥለዋል! ፋይሎች ወለሉ ላይ ተበትነዋል! የምስጢር ካዝናው በጉልበት ተፈልቅቆ ተበርግዷል ..."

"ምንድነው የምታወራው ..." እዮብ አቋረጠው "... የማን ቢሮ ነው ይሔ?"

"እዮብ ..." አለ አቤሰሎም በተራው ባልደረባው ላይ አፍጥጦ "... የእኔና የአንተ ቢሮ ነው ይሔ:: ወዲያው ተደናግጬ ወደ ተረኛ መኮንን ቢሮ ስሔድ የባሰ ያልጠበቅሁት ዱብ ዕዳ ..."

"የምን ዱብ ዕዳ ... ምንድነው የምታወራው?"

"ትላንት ማታ ካደሩት ሁለት ተረኛ መኮንኖች አንዱ ማታ ጋደም ባለበት እዚያው፣ ሁለተኛው ደግሞ ጠረጴዛው ላይ እንደተቀመጠ፣ የመጀመርያው ጆሮ ግንዱ ስር በጥይት ተመትቶ ሁለተኛው በሽቦ ታንቆ ጠዋት ሁለቱም ደርቀው ተገኙ ተብሎ ..."

"የፈጣሪ ያለህ!" አለ እዮብ የአቤሰሎም ድንጋጤ እየተጋባበት::

"ከዚያ በኋላ እዛው ተረኛ መኮንን ቢሮ ደጃፍ ለተሰበሰቡት የኛም ቢሮ መሰበሩን ተናገርኩ ... ተመልሰን ቢሮአችን ሲታይ ... እህእ ..." አለ አቤሰሎም መናገር አቅቶት::

"ምን ሆነ ... ረጋ ብለህ አስረዳኝ ..." አለ እዮብ በሹክሹክታ የባልደረባውን ክንድ ጨበጥ አድርጎ "... በመጀመርያ ደረጃ የእኛን ቢሮ ሰብሮ የሚገባ ማነው?"

"አላውቅም ..." አለ አቤሰሎም በስጨት ብሎ "... ግን ከአስረኛው ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል ... ማለቴ ..."

"እርሱም ራሱን ገደለ ነው ያልከኝ በስልክ ... ማለቴ ..." እዮብ አቋረጠው::

"እራሱን አልገደለም:: አንደኛው ተረኛ መኮንን በተገደለበት መንገድ በሽቦ ታንቆ ነው የሞተው::"

"ማ ... ማነው ገዳዩ?"

ግእስካሁን ጥያቄ የተደረገላችሁ መሔድ ትችላላችሁ ... አቶ አቤሰሎም 'ይግቡ' ተብለዋል::" አለች::

የእስር ክፍሉ ኃላፊ፣ ሦስቱ የጥበቃ አባላትና በድርጅቱ ክሊኒክ ውስጥ የሚሰራው ነርስ ተከታትለው ከወጡ በኋላ ፀሐፊዋ አቤሰሎምን አስከትላ ወደ ዶክተር ብርሃን ቢሮ ስትገባ እዮብ በመቆያው ክፍል ውስጥ ብቻውን ቀረ::

እዮብ የሆነውን ሁሉ መልሶ መላልሶ አሰላሰለው:: መረጃዎች ሁሉ ወደ እርሱ ሊያመለክቱ እንደሚችሉ ተሰማው:: በመጀመሪያ ደረጃ ምስክሮች ባሉበት ወደ እስረኛው ክፍል በመጨረሻ የገባው እርሱ መሆኑ ...

"እንዴት ነው ነገሩ?" አለ እዮብ ሳያውቀው ድምፁን ከፍ አድርጎ ከራሱ ጋር እያወራ::

እስረኛውን እርሱ ራሱ ካልገደለው እንግዲያው ማን ሊገድለው ቻለ? ሟቹ እስረኛ እንዳለው ሞቱን የሚሹ ምናልባት በፖሊስ ኃይሉ ውስጥ ያሉት የመረቡ አባላት ሊሆኑ ይችላሉ:: ግን ለምን? በማግስቱ ጠዋት የፖሊስ ኃይሉ በይፋ ከተረከበው በኋላ ያለምስክር በቀላሉ የፈለጉትን ሊያደርጉ ሲችሉ የመረጃ ቤቱን አጥር ዘለው፣ ተረኛ መኮንኖቹን ገድለው፣ የእስር ቤቱ ጠባቂዎች ሳይሰሙ፣ ሳያዩ ከእስረኛው ክፍል ገብተው እስረኛውን አንቀው ገደሉ? ...

'የማይታመን!'

እዮብ ለአንድ አፍታ ወደ ኋላ ተመልሶ እስረኛው ባለፈው ምሽት የተናገረውን ለማስታወስ ሞከረ::

"ሻለቃ ፀጋዬ ..." ነበር ያለው እዮብ ወደ እስረኛው ክፍል ገብቶ አንደኛው የጥበቃ አባል ባስገባለት የእንጨት ወንበር ላይ ከተቀመጠ በኋላ "... የምፈልጋቸው ጥቂት ተጨማሪ መረጃዎች ነበሩ ..."

እስረኛው ግራ በተጋባ ሁኔታ አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ ብሎ፣ ሁለት እጆቹን ጭኖቹ ላይ አድርጎ እዮብን ይመለከተዋል:: ቀን ሲመረምሩት ከነበሩት ሁለት ሰዎች መሀል አንዱ ብቻውን ተነጥሎ መጥቶ፣ ከእንቅልፉ አስቀስቅሶ እዚያው ክፍሉ ውስጥ ልመረምርህ ነው ሲለው ግራ መጋባቱን ፊቱ እያሳጣ::

"ሻለቃ ፀጋዬ ... አዝናለሁ ... ግን የመረጃ መሥሪያ ቤቱ ነገ ጠዋት ለፖሊስ ኃይሉ እንዲያስረክብህ ከበላይ ትዕዛዝ ተቀብሏል::"

"! ..." እስረኛው ከተቀመጠበት ዘሎ ተነሳ::

"እንዴ - እንዴ ሻለቃ ፀጋዬ ..." እዮብ የሰውየውን መደናገጥ ሲያይ ሊያረጋጋው እየሞከረ::

"ለምን እዚሁ አትገድሉኝም?! እንዴት አድርጌ ባስረዳችሁ ነው የሚገባችሁ?! በፖሊሶቹ እጅ ከገባሁ አልተርፍም! ልታስገድሉኝ ነው! ለምን እዚሁ አትጨርሱኝም!"

"ለምን?"

"አለቃዬ ..." አለ እስረኛው ከተቀመጠበት አልጋ ላይ ተነስቶ በጠባቧ የእስር ክፍል ውስጥ እየተንጎራደደ "... አለቃዬ ከገመትኳቸው በላይ ጠንቃቃ ነበሩ:: ከቢሮአቸው ገብቼ ስላደረብኝ ጥርጣሬ ከነገርኳቸው በኋላ ወደ ኤታማዦር ሹሙ ቢሮ ሔደው ማንኛውም አደጋ ቢደርስባቸው በማንም እጅ ሊገባ የማይገባ የምስጢር ሰነድ እንዳለና ቢሮአቸው ታሽጎ ኤታማዦር ሹሙ ባሉበት እንዲፈተሽ ጠይቀዋቸው ነበር::"

"ኤታማዦር ሹሙ በመረቡ ውስጥ አሉበት ብለህ ታስባለህ?"

"የሉበትም::" አለ እስረኛው በእርግጠኝነት እራሱን ነቅንቆ::

"በምን እርግጠኛ ሆንክ?"

"በምንም ነገር እርግጠኛ አይደለሁም ... ግን ሰውየው በመረቡ ውስጥ ቢኖሩ አለቃዬ እሳቸው'ጋ ሔደው 'ምስጢር የያዘ ሰነድ አለ' ብለው ባልተናገሩ ነበር:: ብቻ አላውቅም::" አለ እስረኛው ተስፋ በመቁረጥ ዓይነት ተመልሶ በአልጋው ላይ ዘፍ ብሎ ተቀምጦ::

"እሺ ጥሩ ... የአለቃህን ቢሮ እንድታሳሽግ ተነገረህ ... ከዚያስ?"

"ከዚያ በኋላ ፍጹም እራሴን መቆጣጠር እስኪያቅተኝ ድረስ ተደናገጥኩ::"

"ለምን?"

"ምክንያቱም የፈራሁት ነበር የደረሰው:: አለቃዬ የወሰዱት እርምጃ ተራ በቀል ነበር:: በእርሳቸው ላይ አደጋ ከተጣለ በአጠቃላይ የመረቡን እንቅስቃሴ ሊያመክኑት! ሁላችንንም እሳት ውስጥ ሊከቱ ነበር የቆረጡት:: እርግጥ ምን ያህል መረጃ በእጃቸው እንደነበር ማለቴ የመረቡን ዝርዝር እንቅስቃሴ! በውስጡ የታቀፉ አባላትን ማንነት! ሌሎችንም መረጃዎች በምን ያህል ጥልቀት እንዳሰባሰቡ አላውቅም:: ቢሆንም ቢያንስ ቢያንስ 'ቢሮዬ ውስጥ ይገኛል' ካሉት ሰነድ ውስጥ ከሚጠቀሱት ምስጢሮች መሀል የእኔም ጉድ ስለመኖሩ ጥርጥር አልነበረኝም:: ይህ ማለት ደግሞ አለቃዬን ከገደለው ወገን ራሴን መከላከል ብችል እንኳን የአለቃዬ ሰነድ በመንግሥት እጅ ከገባ ካልጠበቅሁት ወገን ወጥመድ ሊዘጋብኝ ሆነ::"

"እና ምን አደረግህ?"

"በመጀመርያ የመጣልኝ ሃሳብ ወደ ጥበቃ ክፍል ደውዬ ሰው እንዲመደብ ከመጠየቁ በፊት እኔ እራሴ ወደ አለቃዬ ቢሮ ገብቼ ሰነዱን መፈለግ ነበር:: ነገር ግን አለቃዬ የተባለውን ሰነድ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ሊገኝ በሚችልበት ቦታ እንደማይደብቁት ሳስበው ሀሳቤን ቀየርኩ::"

"እና ምን አደረግህ?"

"ለምንድነው ታድያ እጅህን ያልሰጠኸው?"

"እንደዛ አይደለም ..." አለ እስረኛው "... ዶክተሩ ወዲያውኑ እጄን ለመረጃ ቤቱ እንድሰጥ አባብለውኝ ሲጨርሱ አድራሻዬን ጠየቁኝ። ግን የመጨረሻው ውሳኔ ላይ መድረስ አቃተኝና እሺም እምቢም ሳልል መልሼ የምደውል መሆኑን ነግሬአቸው ስልኩን ዘጋሁ።"

"መልሰህ ሳትደውል ቀረህ?"

"ደወልኩ። ለበርካታ ሰዓታት አውጥቼ አውርጄ በመጨረሻ የተሻለ ምርጫ እንደሌለኝ ስረዳ ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ መልሼ ደወልኩ። ዶክተሩ በነገሩኝ መሠረት ቢሯቸው ውስጥ እየጠበቁኝ ነበር። እጄን ለመረጃ ቤቱ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን ገልጬ ያለሁበትን ቦታ ነገርኳቸው። ወዲያው መኪና እንደሚልኩልኝና ባለሁበት እንድጠብቃቸው ከአደራ ጋር አስጠነቀቁኝ።"

"እሺ።"

"የተባለችው መኪና በአስር ደቂቃ ውስጥ ከነበርኩበት ደረሰች። መኪናዋ ቆመች። በሹፌሩ ጎን ያለው በር ተከፍተ። የመጀመሪያው ሰው ሲወርድ ተመለከትሁ። እያመነታሁ ወደመኪናዋ ተጠጋሁ። ከመኪናው የወረደው ሰው ወደመኪናዋ ስጠጋ ሲያይ የመኪናዋን የኋላ በር ከፍቶ ያዘልኝ። ተጠጋሁ። ያን ጊዜ ከየት መጣ ሳልለው የተተኮሰ ጥይት ከጎኔ የመኪናዋን በር ከፍቶ የያዘልኝን የመረጃ ቤት አባል ግንባሩ ላይ ሲለው ሰውየው እግሬ ስር ሽብልል አለ። ለአንድ አፍታ በቆምኩበት ደነዘዝኩ ... ሁለተኛው ጥይት ስቶኝ የመኪናዋን የጎን መስኮት ዱቄት አደረገው። ባነንኩ። ወዴት እንደሮጥኩ ትዝ አይለኝም ... ብቻ አንድ ኮረኮንቻማ በሆነ መንገድ ... በጨለማው ውስጥ ስሮጥ ትዝ ይለኛል ... ከኋላዬ ይከተሉኝ ነበር ... ሲተኩስ ..."

የዶክተር ብርሃን ቢሮ ተከፍቶ ፀሐፊዋና አቤሰሎም ሲወጡ እዮብ ከሀሳቡ ተመለሰ። አቤሰሎም ከፀሐፊዋ ነጠል ብሎ ወደ ፊት ራመድ አለና ወደ እዮብ ጆሮ ጠጋ ብሎ።

"ተጠንቀቅ ... እዮብ ተጠንቀቅ ነገሩን ሁሉ እኔና አንተ ላይ እየደፈደፉ ነው ያሉት። ምንም ሀሰት እንዳይወጣህ እኔ እውነቱን ነው የተናገርኩት እለዚያ እርስ በእርሳችን የተለያየ ስናወራ የባለ 'እነሱው ናቸው' ብለው ነው የሚያርፉት ... ተጠንቀቅ!" አለው ክንዱን ጠበቅ አድርጎ ይዞ።

ፀሐፊዋ አቤሰሎም ከክፍሉ እስኪወጣ ድረስ ጠብቀችና ፈጠን ብላ ወደ እዮብ ተጠጋች።

"እዮብ ..." አለችው በተጨነቀ መንፈስ "... ዶክተር ነው የላከኝ ... ውስጥ ስትገባ እንዳትደናገጥ ብሎሀል ... እና ..." አለች ደንገርገር ያላት መስላ "... እዮብ 'ማታ ወደ እስረኛው ክፍል ገብተህ ምርመራ ማካሔድህን እንዳታምን ... ማንም ቢጠይቅህ ፍጹም ካድ' ... ብሎሀል።" አለችው።

እዮብ ግራ ተጋባ።

ለአንድ አፍታ እዮብ ከራሱ ጋር ክርክር ገጠመ:: በአንድ በኩል ፀሐፊዋ የሰጠችው የዶክተር ብርሃን መልዕክት በሌላ በኩል ወደ እስረኛው ክፍል ሲገባ የነበሩ ምስክሮች ...

"ሰምተኸኛል ... ጥያቄዬን?" አለ ሰውየው እዮብን የጎድን እየተመለከተ::

እዮብ አይኖቹን ከሰውየው ላይ ነቀለና ዶክተር ብርሃንን ተመለከተው:: ዶክተር ብርሃን 'ጥያቄውን መልስ' በሚል መልክ ጭንቅላቱን ነቀነቀለት::

"እኔ አይደለሁም ..." አለ እዮብ "... ማለቴ ብቻየን አልነበርኩም ... ከአቶ አቤሰሎም ጋር ነው ገብተን ምርመራውን ያካሄድነው::" እዮብ የገባ ድምፁ ሲጎረንንበት መልሶ ጉሮሮውን አፀዳ::

"ይቅርታ ..." አለ ከአቃቤ ህግ ቢሮ የመጣው ሰው አቋርጦት "... እንዳልከው ቀን ከአቶ አቤሰሎም ጋር ምርመራ እንዳደረጋችሁ እናውቃለን:: ጥያቄው ግን ማታ ..." አለ ሰውየው ጠረጴዛውን በቀሰቡቱ ቀጭ አድርጎ "... ማታ ከመሸ በኋላ ወደ ሁለት ሰዓት አካባቢ ወደ እስረኛው ክፍል ገብተህ ምርመራ አላደረግህም?"

እዮብ ዶክተር ብርሃንን ተመለከተው:: የአለቃው አይኖች ላይ ፍንጭ አጣ:: ለአፍታ ግራ ተጋባ:: ወዲያው የፀሐፊዋ መልዕክት '... ማታ ወደ እስረኛው ክፍል ገብተህ ምርመራ ማካሄድህን እንዳትጠቅስ ... ማንም ቢጠይቅህ በፍጹም ካድ ...' ያለችው ሲመጣበት:-

"አላደረኩም::" አለ የገባ ጥፍሮቹ መዳፉን ሰርስረው እስኪገቡ ድረስ ቡጢ ጨብጦ:: "... ወደ እስረኛው ክፍል አልገባሁም::"

ከፊት ለፊቱ የተቀመጠውን ሰው ጤንነት ቀርቶ ማንነት እንኳን አጣርቶ አያውቅም። እርግጥ እናቱ በውጭ ያለውን የአደንዛዥ እፅ መረብ በአገር ውስጥ ካሉት አባላት ጋር የሚያገናኝ ብቸኛ መስመር ስለሆነ ወደደም ጠላ ያለውን፣ ያዘዘውን ሲፈጽም ቆይቷል ... ግን ... እንደዚህ ያበደ፣ ፍጹም የለየለት የወፈፌ ተግባር ፈጽም ሲለው፣ ምንም የማያውቁትን፣ በገንዘብ ኃይል አባብሎ የመለመላቸውን ሀያ አንድ የፖሊስ አባላት አስጨርስ ሲለው ... እነሱ እንኳን ስራቸው ያውጣቸው ... ግን በገዛ እንገትህ ዙሪያ ገመድ አጥልቅ ሲለው እንዴት 'እሺ' ብሎ እንደሚቀበል ቸገረው። 'እምቢ' ቢል 'አሻፈረኝ' ቢል ... በደቂቃዎች ውስጥ የትኛውን ቅጥረኛ ሊልኩበት እንደሚችሉ ... ማን ያውቃል? ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በመከላከያ ውስጥ የነበረውን መረብ እንዴት እንዳልነበር እንዳደረጉት ሲያስብ ዘገነነው።

ከፊት ለፊቱ እንደተቀመጠ ትክ ብሎ ሲመለከተው፣ የሚያስበውን የተረዳበት ሲመስለው ... ኮሎኔል አይኖቹን ሰበረ።

"ፈራህ እንዴ ኮሎኔል?" አለ ታውበር ቤን ሳውል ፈገግ ብሎ።

'እስስት!' አለ ኮሎኔል በልቡ አይኖቹን ከፊቱ የተቀመጠው ሰው ላይ መልሶ ተክሎ።

"መፍራትን ምን አመጣው? ..." አለ ጭንቀትና ፍርሀቱን በውስጡ አምቆ " ... የንፁህ ሰው ደም እንዳይፈስ ብዬ እንጂ ... የመከላከያ ሰዎችን የት እንዳደረስኳቸው ታውቅ የለ'ንዴ? ... መፍራትን ምን አመጣው?"

ከፊቱ የተቀመጠው ሰው አይኖች ሰርስረውት ሲገቡ በተቀመጠበት ወንበር ላይ ቆነጥነጥ አለ።

ይፈራዋል ... አጥብቆ ይፈራዋል። ማንነቱ የማይታወቅ፣ ከጀርባው ያለው ትስስር፣ ንክኪ ሊገመት እንኳን የማይቻል ሰው ... ይፈራዋል።

ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ አምስት ጊዜ ከአገር ወጥቶ ተመልሶ ሲገባ አምስቱንም ጊዜ የተለያዩ ፓስፖርቶች እየያዘ በተለያየ ዜግነት እንደገባ ያውቃል። ታድያ ስር የሰደደ ትስስር ባይኖረው ይህን ማድረግ ይቻለዋል? ያለጥርጥር ከጀርባው ጠንካራ መተማመኛ አለው። ታድያ የእዚህ አይነቱን ሰው...

ከእርሱ በፊት የነበረውን የምስጢር አገናኝ መኮንን ተክቶ እንደገባ 'ሳላም አባላለሁ' እያለ ነበር እራሱን የሚያስተዋውቀው፣ በተከላተፈ እንግሊዝኛ።

'ሳላም ቤሪ አባላለሁ። የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች አሻሻጭ ነኝ ... ሀ! ሀ! ሀ! አዎ አረብ እመስላለሁ ... ፍጹም ኢራናዊ ነኝ ... ግን የተወለድኩት ያደግሁትም ሊባኖስ ነው ...

"ሀ! ሀ! ሀ! ... አዎ... ሊባኖሳዊ ነኝ ብል እችላለሁ ... አባቴም እዛው ነው የተወለደው ... ሊባኖስ ... በኑዛይ የባህር ዳር ከተማ ተወልዶ በጥረቱ በአገሪቱ አሉ ከሚባሉ ታዋቂ ጠበቆች አንዱ ለመሆን የበቃ ነበር ... አለመታደል ሆኖ የሚወዳት ሊባኖስ መጥፊያው ሆነች ... በ1975 ሚያዝያ ውስጥ ክርስትያኖቹ ፍልስጥኤማውያኖቹን የፈጁበትን ብጥብጥ ተከትሎ የመጣው የሊባኖሳውያን

"ማን ሊገድለው ይችላል ... እራሱን ካልደገለ በስተቀር?"

"ተሳስተሃል ... ሁለት ወር ሙሉ በሰላዮቹ ጉሮኖ በሰላም የቆየ እስረኛ አንተ ልትረከበው አንድ ለሊት ሲቀር ራሱን ገደለ ... ለማመን ያስቸግረኛል::"

"እና ማን ገደለው ነው የምትለው?" ኮሎኔል ሥዩም የምግብ ሳሕኑን ገፋ አድርጎ በተራው ጠየቀ::

"እስቲ እረጋ ብለህ አስበው ... በመጀመርያ ዶክተር ብርሃን ለምን ነበር እስረኛውን ለአንተ አሳልፎ ለመስጠት ያቅማማው? አንድ በል:: ሁለተኛ ግልፅ አድርጎ እያስቀምጠው እንጂ ከእስረኛው ብጥስጣሽ መረጃ ማግኘቱን አልደበቀም:: ሦስተኛውና ዋናው ነጥብ ግን የእስረኛውን አሟሟት ለምንድነው ግልፅ ማድረግ ያልተፈለገው:: ሌላው ቀርቶ እሬሳውን አይተሃል?"

"እሬሳውን አላየሁም ..." አለ ኮሎኔል ሥዩም ዙርያውን ከገላመጠ በኋላ ድምፁን ቀንሶ "... ግን የሰውየው መሞት እንደተገለፀልኝ ወደ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪ ደውዬ እሬሳው ተሰጥቶኝ ምርመራ እንዳደርግ እንዲፈቀድልኝ ጠይቄአለሁ ..."

"እና ...?"

"በመሠረተ ሀሳቡ ተስማምተዋል ..." ኮሎኔል ሥዩም ትንሽ አቅማማና ቀጠለ "... በአስቸኳይ ከፖሊስ ኃይሉና ከመረጃው መሥሪያ ቤት ተውጣትቶ የተደራጀ አንድ ኮሚቴ የሞቱን መንስዔ አስመልክቶ ዛሬውኑ ምርመራውን እንዲጀምር በሚለው ሀሳብ ተስማምተዋል ... ከእርሳቸው ጋር ተነጋግሬ እንደጨረስኩ ሁለት የፖሊስ አባላት ማለት የመረቡን አባላት መርጬ ወደዚያው አስማርቼ ነው ለአንተ ስልክ የደወልኩት:: ቡድኑ ምርመራውን በደቂቃዎች ውስጥ ይጀምራል:: ምናልባትም እስካሁን ..."

"ያንተ ዝይዎች እዚያ እስኪደርሱ ድረስ ያ ነገረኛ እሬሳ ታጥቦ ተተኩሶ ያልቃል ... ብታምንም ባታምንም ያን ጊዜ የመረጃ ቤቱ ሰዎች '... ሰውየው አልሞተም እንደ ኤልያስ ከሰማየ ሰማያት የያህዌ መንኮራኩር ወርዶ ነፍሱን በነጭ ጨርቅ ይዟት አረገ' ቢሉህ ታምናቸዋለህ ... ምርጫ አይኖርህም ... ምን እያልኩ እንደሆነ ይገባሀል? ... ምንም አይነት መረጃ በእሬሳው ላይ አታገኝም!"

"እና ምን አድርግ ነው የምትለኝ ?" አለ ኮሎኔል ሥዩም በተጨነቀ ሁኔታ::

"አንድ ነገር ግልፅ ሊሆንልህ ይገባል ..." ቤን ሳውል በወንበሩ ላይ ወደፊት ፎቀቅ ብሎ ድምጹን ቀንሶ ቀጠለ "... ያለጥርጥር በመረጃው መሥሪያ ቤት ውስጥ ስለ መረቡ ሙሉም ባይሆን ብጥስጣሽ መረጃ ያገኘ ወገን አለ:: ነገር ግን ይህ ወገን ያገኘውን መረጃ በይፋ ሊጠቀምበት አልፈለገም:: ይህ ደግሞ የሚያሳየን ይህ ወገን ያገኘው መረጃ ያልተሟላና አባላቶቻችን ከንድ ላይ ካቴና ለማጥለቅ በቂ አለመሆኑን አለበለዚያ የመረጃ ሰዎች ያገኙትን ብጥስጣሽ መረጃ ተጠቅመው ጥቂት ሰዎችን ወደ ዘብጥያ ከማውረድ ይልቅ በእጃቸው የገባውን መረጃ በትዕግስትና በምስጢር ይዘው ከዚህ ወዲያ መረቡ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በስውርና በቅርብ እየተከታተሉ መቆየትና አመቺ ጊዜና ቦታ ሲያገኙ መላ መረቡን በቀለበት ውስጥ ለማስገባት ማቀዳቸውን ነው::"

"ስለዚህ ...?" ኮሎኔል ሰዩም ዝም ብሎ ማዳመጥ የመረጠ መሰለ::

"በጣም ጥሩ ..." አለ ቤን ሳውል የፖሊስ አዛዡ በእርጋታ ማዳመጥ መጀመሩን ሲያጤን በወንበሩ ላይ እየተመቻቸ "... እንግዲህ እስተውል ... በትድሚያ መረቡ በኢትዮጵያ ውስጥ የተደራጀው የፖሊስና የመከላከያ ኃይሎችን ይዞ የመረጃ ሰዎችን አግልሎ ነው:: ይህ የተደረገው በበቂ ምክንያት ነበር:: የመረጃ ሰዎችን ልትጨብጣቸው አትችልም ... በተለያዩ አገሮች ውስጥ የታየ ነው ... ምን ጊዜም በተሻለ ዋጋ ሊሸጡህ የተዘጋጁ ናቸው:: አሁን ያለንበት ሁኔታ ግን ወደድንም ጠላን በመረጃ ሰዎች ጥርስ ውስጥ መግባታችንን የሚያመለክት ነው:: ለዚህ ነው እነሱ አመቺ ጊዜ ጠብቀው ጥቃት ከመክፈታቸው በፊት እኛ እናጥቃቸው የምለው::"

"እሺ 'በመረጃው መሥሪያ ቤት አባላት ላይ ጥቃት እንክፈት' በሚለው ሀሳብ ላይ በጥቅሉ መስማማት ላይ ደረስን እንበል ... ግን በትክክል ማንን ነው ...?" ኮሎኔል ሥዩም ዐረፍተ ነገሩን መጨረስ የፈራ ይመስል በመሀል አቋርጦ ሁለት እጆቹን አራገባቸው::

"በእርግጥ በአሁኑ ሰዓት ምስጢሩ ላይ ደረሱ የምንላቸው የመረጃ አባላትን 'እከሌ - እከሌ' ብለን በስም መጥራት አለመቻላችን ግልፅ ነው ... ስለዚህ በእርግጠኝነት እከሌ ይታፈን፣ እከሌ ይገደል ለማለት አንችልም:: ለዚህም ነው ያለምርጫ ጥቂት አባላቶቻቸውን በደፈናው እናስወግድ እያልኩኝ ያለሁት ... ቆይ - ቆይ ... " አለ ቤን ሳውል ኮሎኔል ሥዩም ሊያቋርጠው ሲል ቀኝ እጁን ወደፊት ዘርግቶ "... ይገባኛል አንተ የምትለው 'በደፈናው የመረጃ ቤቱን አባላት በየመንገዱ እያረዱ መጣሉ ምን ይጠቅማል?' ነው:: ነገር ግን ማስተዋል የሚገባህ የመረጃው ቤት ሰዎች ፍንጭ በሌለው ሁኔታ አንድ በአንድ በወጡበት ሲቀሩ በመጀመርያ ደረጃ በመሀላቸው አለመተማመንንና ጥርጣሬን ያበቅላሉ:: በሁለተኛ ደረጃ ምስጢሩን የተካፈሉ ግለሰብ የመረጃ ቤቱ አባላት ህይወታቸውን ለማትረፍ ሲሉ እራሳቸውን በሚያጋልጥና ለእኛም ፍንጭ በሚሰጥ ሁኔታ ወዲያና ወዲህ መወራጨት ይጀምራሉ:: ሶስተኛ የመረጃው ቤት በፊናው አባላቶቹን ለማረጋጋትና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ሲል በእጁ የገቡትን ጥቃቅን መረጃዎች ተጠቅሞ በመረባችን ላይ ጥቃት ለመሠንዘር ይገደዳል ... እንደቆሰለ አውሬ እረፋ ደፍቆ ይንጉራል ..."

"በስመአብ ወልድ! ..." አለ ኮሎኔል ሥዩም የመረጃው ቤት እንደተናካሸ አውሬ ከጀርባው እያንፈነፈ ሲያድነው ታይቶት "... በራሳችን ላይ እሳት ለማቀጣጠል ነው እንጣደፍ የምትለኝ?"

"አይደለም ... እየህ የመረጃው ቤት መረቡን ሙሉ በሙሉ ሊያመክን የሚያስችለው መረጃ ጨብጦ ቢሆን ኖሮ ዛሬም እዚህ በሰላም ባልተቀመጥን ነበር:: ስለዚህ የመረጃ ቤቱ የእዚህን ዓይነት መረጃ እጁ ከማስገባቱ በፊት ወደ ጦርነቱ ውስጥ እንዲቀላቀል ስናስገድደው፤ ከዋሻው እፍ ተጠግተን ስንቆሰቁሰው፤ ከጎሬው፣ ከመሸገበት ዘልቀን በጦር ስንሸቀሽቀው ... ያለው አማራጭ ከዋሻው መውጣት ነው፤ ያለችውን የተወሰነች መረጃ ተጠቅሞ ጥቃት መሰንዘር ነው:: እዚህ ላይ ግን አስታውስ የመረጃው ቤት በመረባችን ላይ ሊያደርሰው የሚችለው ጉዳት ቢኖርም አጥፊነቱ ውሱን ስለሚሆን እንደገና እራሳችንን አጠናክረን ለመቀጠል ዕድል ይኖረናል::"

አለፈ:: ከፊት ለፊት አደባባዩን ዞሮ ወደ ጴፖው አመራ:: ከጴፖው እንደደረሰ ግራና ቀኙን አማተረ:: በዙርያው ያሉትን ሰዎች ቃኘ:: በእርሱ ላይ ያተኮረ ሰው ሊለይ አልቻለም:: ፈጠን አለና የቀኝ ጫማውን አውልቆ በአንድ እግሩ ሚዛኑን ለመጠበቅ እየታገለ አራግፎ መልሶ አጠለቀው:: ምንም የለም:: ዙሪያውን ቃኘ::

ድምፅ ሲሰማ ፊቱን መለሰ:: ከጀርባው ከቆሙት የጴፖው ጥበቃ አባላት ውስጥ አንደኛው እጁን እያወናጨፈ ከጴፖው መግቢያ ዞር እንዲል ምልክት ሰጠው:: ፌይሰል አመነታ:: የጥበቃ አባሉ በስጭት ብሉ እጁን እያወናጨፈ በሱማሊኛ እየለፈለፈ ወደ እርሱ ሲመጣ ፌይሰል ፈጠን ብሎ ከቦታው ዞር ለማለት መንገድ ጀመረ::

ፌይሰል ግራ ተጋባ::

ምንድነው ያሉት? '... ወደ ጴፖው እንደደረስክ ... የቀኝ እግር ጫማህን አውልቀህ አራግፍ ... ያን ጊዜ አንድ ሰው ወደ አንተ ቀርቦ ... ወደ እርሱ የመጣ ሰው ግን አልነበረም:: የመጣው ይምጣ በሚል ሁኔታ ፈጠን ብሎ ድጋሚ የቀኝ እግሩን ጫማ አወለቀ ... አራገፈ ...

የጥበቃ አባሉ ይበልጥ ጥርጣሬ የያዘው መሰለ:: ድንገት በትከሻው አንግቦት የነበረውን መሳርያ አውርዶ ይዞ :-

"ከሌኾ ሜሻ! ..." አለ በሱማሊኛ 'ዞር በል ነው'ኮ የምለው' ለማለት "... ጆክሲ መላ ኦጎሉ!" – 'እዚህ መቆም ክልክል ነው!' ሰውየው እጁን እያወናጨፈ፣ እየለፈለፈ ቀረበ::

የጥበቃ አባሉ የሚለው ባይገባውም ከዚህ በኋላ በዚያ ቦታ መቆየቱ የበለጠ ጥርጣሬ ውስጥ ሊከተው እንደሚችል ሲረዳ በቁጣ እየለፈለፈ የሚመጣው የጥበቃ አባል ሳይደርስበት ፈጠን በሉ ጫማውን ለማጥለቅ ተቻኮለ:: የጥበቃው አባል ይበልጥ እልህ የያዘው ይመስል ተጣድፎ ደርሶ ቀኝ ክንዱን ጨመደደው::

"አቶ ዑመር ..." አለ የጴፖው የጥበቃ አባል ጥርት ባለ አማርኛ "... ሴት ልጅህ ሰላምታ ልካልሀለች::"

"ፈሽንዬ ..." አለ ቀደም ብሎ ሳይነግራት እንግዳ መጋበዙ ያስቆጣት ሲመስለው ፈጠን ብሎ "... አስቸኳይ ጉዳይ ስለሆነብኝ ... ማለቴ ቢሮዬ ውስጥ ላገኛቸው ስላልቻልኩ ነው ... ይከፋሻል?" አለ ፊቷን ወደ እራሱ መልሶ አቅፎ ይዟት ጀርባዋን እያሻሸ።

"ለምን ይከፋኛል ... የአንተ እንግዶች የኔ እንግዶች አይደሉ? ... ያልኩት ... የምልህ ... አለ አይደል ...?"

"አ! አ! ... እንግዶች ስልሽ እራት ወይ ሌላ ዝግጅት ያስፈልጋል ማለቴ አይደለም ... ለሥራ ጉዳይ ነው ... አይቆዩም።" እያባበላት።

"ዴግ!" በማፌዝ መልክ ጉንጩን በጣቶቿ ቆንጠር አድርጋ።

'ደሐ ነው' ብላ መናገር ቢያስቸግራትም በአንድ ጉዳይ እንደተረበሸ ፊቱ በግልፅ ይናገራል።

የፊተኛው በር ደወል ሲደወል ከተቀመጠችበት ብድግ አለች።

"ቆይ ፈሽን ..." አለ ኮሎኔል ስዩም የያዘውን የውስኪ ብርጭቆ ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ለድርጎ "... መኝታ ቤት ቆይ እንቺ።" አለ ድንገት ትዕዛዝ በሚመስል ቃና።

ለአንድ አፍታ ልትቃወም የፈለገች ይመስል ትክ ብላ ተመለከተችውና ወዲያው ሀሳቧን እንደቀየረች ሁሉ ወደፊት ራመድ ብላ ጉንጩ ላይ ሳመችው -

"እንዳትቆይ ታዲያ ... ዛሬ አምረኸኛል።" ፈገግ ብላ ወደ መኝታ ቤት አመራች።

"ግቡ።" አለ የክፍሉን የፊት በር ከፍቶ ከውጭ የቆሙትን ሦስት ሰዎች ሲያይ በሩን ከፍት ትቶ ወደ ሳሉን እየተመለሰ።

"ማንም እንዳልተከተላችሁ እርግጠኞች ናችሁ።" አለ ኮሎኔል ሥዩም ጥያቄ ሳይሆን በቀጥተኛ ዓረፍተ ነገር።

"ማንም አልተከተለንም።" አለ ቀድሞ ከፊት የገባው የወንጀል ምርመራው ባልደረባ የመቶ አለቃ ፍቅሬ አበጋዝ። ትናንሽ አይኖቹ ስስ ከናፍሩ ቀጠን አጠር ያለ ሰውነቱ ሰውየውን ፍጹም ጨካኝ መልክ ሰጥተውታል።

"እንዴት ነበር ምርመራው?" አለ ኮሎኔል በተቻለው እልሁን አፍኖ ይዞ በስተቀኙ ወደተቀመጡት የፖሊስ መምሪያው ሰው ወደ ሻምበል ገብረእየሱስ ሀብቴና ወደ አገር ውስጥ መረጃው መሥሪያ ቤት የእስር ክፍል ጥበቃ አባል የአስር አለቃ ዋስይሁን ዓለሙ ፊቱን አዞሮ።

"ግልፅ ነው! የመረጃ ቤቱ ሰዎች ናቸው የገደሉት።" አለ ሻምበል ገብረእየሱስ በስተቀኝ ከያዘው የእጅ ቦርሳ ውስጥ አንድ የወረቀት ፋይል አውጥቶ ለኮሎኔል እየዘረጋለት።

"ያንን አይደለም የምፈልገው ... እሱን ቀድሞ በስልክ ጠቅሰህልኛል።" አለ ኮሎኔል በስጨት ብሎ የወረቀት ፋይሉን ከሻምበሉ እጅ መንጭቆ ጠረጴዛው ላይ እየወረወረው "... በጨለማ ለመጓዝ ጊዜ የለንም። የምፈልገው እስረኛውን

ፈገግ አለች::

"እስካሁን ታስጠብቀኛለህ ... እንደዚያ አምረኸኛል እያልኩህ?"

ጫማዎቹን እርስ በእርስ አፋትጎ አወለቃቸው ... የሱሪውን ቀበቶ ቶሎ ሱሪውን ቶሎ ... ቶሎ ... ቶሎ ...

ሱሪውን እስኪያወልቅ ትዕግስት ያጣች ይመስል አፈፍ ብላ ከአልጋው ወረደች፣ እግሮቹ ስር በርከክ ብላ ዚፑን ቁልቁል በረገደችው ... እጇን ወደ ውስጥ ላከችው ... ጭንቅላቱን ወደ ኋላ ጥሎ ... ጣቶቹን ፀጉሯ ውስጥ ከትቶ ... አጥብቆ ይዟት ...

አ ... አ ... አ ... ቃሰተ ...

"ብስብስ!" አለች መታጠቢያ ቤት ገብታ ጥርሷን እየቦረሸች ... መልሳ መሳልሳ አፏን ተግሞጠሞጠችና ከመታጠቢያ ቤት ወጣች:: አልጋ ውስጥ ገብቶ በደረቱ ተደፍቶ ያንኮራፋል::

"ብስብስ ሽማግሌ::"

ፊቷን መለሰችና ወደ ሳሎን ገባች::

'በካኪ ፖስታ ውስጥ::' ነው ያሏት::

ከፎቴው ላይ ጣል ያደረገችውን ቦርሳዋን አንስታ ከውስጥ ቁልፍና አንድ ትንሽ የፎቶግራፍ ማንሻ አወጣች::

'ካኪ ፖስታ'

ፈጠን ብላ ቁልፉን በኮሎኔል ሥዩም የአዞ ቆዳ ቦርሳ ከተተችና ቦርሳውን ከፈተችው ከውስጥ ያሉትን ሁለት ካኪ የፖስታ ከረጢቶች ስታይ ፈገግ አለች::

"ብስብስ ሽማግሌ::"

ካኪ የወረቀት ከረጢቶቹን ከፍታ ከውስጥ ያሉትን ወረቀቶች አውጥታ ጠረጴዛው ላይ ደረደረቻቸው::የፎቶግራፍ ማንሻውን ከመጀመርያው ወረቀት በላይ ከፍ አድርጋ ይዛ ከጎን ስትጫነው ብልጭ አለ ... ቀጠለች ... እያንዳንዱን ወረቀት ፎቶግራፍ እያነሳች ...

"ኩ ... ር ... ር ..." አለችበት እንደ ድመት አንገቱ ስር ተሸጉጣ::

በእንቅልፍ የከበዱ አይኖቹን የሞት ሞቱን ሲገልጥ እጆቿን በብብቶቹ አሳልፋ እቅፍ አድርጋ ያዘችውና ሽቅብ ሽቅብ አይኖቿን ከብልል ... ልል ...

"እ-እ?" አይኑ ላይ የተንጠለጠለውን እንቅልፍ እየታገለ::

"አልጠገብኩህም'ኮ ... ሥዩም ... ዩ ..."

"እኔም::" ሊላት ፈለገና ... የአይኖቹ ቆቦች ቁልቁል ...

## ፲፪

የፊተኛው በር ደወል ተሰማው ... የእግር ኮቴ ... ለአንድ አፍታ ዝምታ ነገሰ። ሙሉ ልብሱን እንደለበሰ በጆርባው አልጋ ላይ ተንጋሎ አይኖቹን ጨፍኗል። የዶስቶቭስኪ ክራይም ኤንድ ፓንሽመንት ደረቱ ላይ ተደፍቷል። ያለበት ክፍል በር በለሆሳስ ተንኳኳ።

አይኖቹን ገርበብ አድርጎ የተዘጋውን በር ገረመመው።

'ምነው መደበቂያ፣ መሸሸጊያ ቦታ በኖረ! ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ... የገሀነም ምድጃ፣ የጥላሸት ጉድጓድ ... ከዚህ አለም በኖረ ... የሰው ልጅ እራሱን ጆው አድርጎ ቁልቁል ወርውሮ መኖሩን ሳይሆን መፈጠሩንም የሚረሳበት መደበቂያ መቀመቅ በኖረ ... ድጋሚ የሰው ፊት የማያይበት ... ድጋሚ ... 'ለምን?' ብሎ የማይጠይቅበት ...

የተዘጋው የመኝታ ቤቱ በር በቀስታ ተከፈተ።

"እዮብ ..." አቤሰሎም ሲፈራ ሲቸር ጭንቅላቱን ገባ አድርጎ ተመለከተ "... አልተኛህም? ..." በቀጭኑ ገርበብ አድርጎ የያዘውን በር ገፋ አድርጎ ወደ ውስጥ ገባ "ደህና ዋልክ ...?"

እዮብ በጆርባው እንደተንጋለለ ገርበብ ባሉ አይኖቹ ለአፍታ ገረፍ አድርጎት አይኖቹን ሰበረ።

በክፍሉ መሀል የቆመው አቤሰሎም የሚያደርገው ግራ እንደገባው ሁሉ ሁለት መዳፎቹን አሻሸና "... እንዴት ነው ዶስቶቭስኪ ... መጋረጃውን ለምን አትከፍተውም ... በዚህ ጨለማ እንዴት ታነባለህ?" አለ ወደ መስኮቶቹ እያመራ።

"ተወው!"

"እሺ።" አለ አቤሰሎም መሀል መንገድ ላይ ቆሞ። የሚናገረውን ሲመርጥ ከቆየ በኋላ በተቻለው ድምፁን አለሳልሶ "... ለምን ተነስተህ መክሰስ አብረን አንበላም ... እንቁላል ..."

"በቃኝ።"

"እዮብ ..."

"በቃኝ አልኩ ... ተወኝ!"

"ሳትበላ ነው የሚበቃህ?" ድምፁን አለሳለሰ።

"በቃኝ ማለት በቃኝ ነው! ... አሁን ነው ምሳዬን የበላሁት።"

"ምሳህን አልበላህም! ... ቁርስህንም ነካክተህ ነው የተውከው ... ነግራኛለች!" አለ አቤሰሎም በስጨት ብሎ ሰራተኛው ከበሩ የቆመች ይመስል ግራ እጁን በተዘጋው በር ላይ ዘርግቶ።

"ማንን ፈልገው ነው? ... 'አብዩ እርስዎ ኖት ወይ' አልኩ::" አለ ባለሱቁ ደግሞ::

"እዮብ ማለትህ ነው?" ጥርጣሬ ሲገባው ወደ ሱቁ ጠጋ ብሎ::

"እንኩ ..." አለ ባለሱቁ ትንሽ የተጠቀለለች ወረቀት ዘርግቶ ይዞ "... አንድ ሰውዬ አሁን ከዚህ ጠብቆ ሔደ:: ይህን ስጥልኝ ብሏል::"

እዮብ ወረቀቱን ዘርግቶ አያት:: ስድስት ቁጥሮች መልሰው አፈጠጡበት:: ለአንድ አፍታ ግር አሰውና ወዲያው ስድስቱ ቁጥሮች የስልክ ቁጥር መሆናቸውን ሲጠረጥር:-

"ስልክ አለህ?"

"ሀሎ::"

"ሀሎ ... እ ..."

"እዮብ ...?"

"ነኝ::"

"እዝናለሁ ... ለጊዜው ካልኩት ሱቅ ልንገናኝ አልቻልንም::" አለ ከወዲያ የሚሰማው ድምፅ "... ይሰሙኛል?"

"አቤት ... እየሰማኹት ነው::"

"አጠገብዎት ማን አለ?"

"ማንም የለም::" አለ እዮብ ዙርያውን ቃኝቶ::

"ጥሩ ..." አለ ከወዲያ ያለው ድምፅ "... በግማሽ ሰዓት ውስጥ እዚህ እንዲደርሱ እፈልጋለሁ:: በመገናኛ መስመር 'ባርሰነት ሆቴልን' ያውቁታል?"

"አዎ ... አውቀዋለሁ::" አለ እዮብ ፈጠን ብሎ::

"ጥሩ ... ባርሰነት ሆቴል ድረስ መጥተው እንግዳ ተቀባዩን 'ሔለን' ብለው ጠይቁና 'መልዕክት ይዤ ነው የመጣሁት ክፍሉን አሳዩኝ' ይበሏት:: ያገኙኛል::"

"ገባኝ - ገባኝ::"

"አቶ እዮብ ወዲህ ሲመጡ ከጀርባዎ የሚከተልዎት አይን አለመኖሩን ፍጹም እርግጠኛ ይሁኑ ... ለእኔም፣ ለእርስዎም ደህንነት ሲባል::"

ስልኩ ተንኳኩቶ ጆሮው ላይ ተዘጋ::

ዋቢ ሸበሌ ሆቴልን እንዳለፈ ምሽቱ እየገፋ ለአይን እየያዘ መጣ:: በመንገዱ ዳርና ዳር ያሉ መብራቶች በግ - በግ ብለው ታዩት:: መስቀል አደባባይን ተሻገረ:: ከመንገድ ጥግ በቅርቡ ተመርቶ ከተከፈተው ባለአራት ኮከብ ሆቴል ሲደርስ ፍጥነቱን ቀነሰና ወደ ሆቴሉ መግቢያ አመራ::

ከግቢው ውስጥ ግራና ቀኝ በግማሽ ክብ ቅርፅ የተደረደሩትን መኪናዎች የያዘው የእንግዶች የመኪና ማቆምያ ስፍራ በመብራት ተንቆጥቁጧል:: እዮብ የአቤሰሎምን ኒሳን ቦታ አስያዛትና ወረደ::

በሆቴሉ በረንዳ ቁልቁል የተዘረጋው ቀይ ምንጣፍ ደም ይመስላል::

ደረጃዎቹን ወጥቶ ሲጨርስ ከበር ላይ ሙሉ አረንጓዴ የደንብ ልብስና መለዮ ያደረገው የሆቴል በረኛ ሰላምታ ሰጥቶ፤ በሩን ከፍቶ ያዘለት:: የሆቴሉን በር አልፎ ገባና ወደ እንግዳ መቀበያው ጠረጴዛ ተጠጋ::

"ሰላም..."

"አቤት?" አለው እንግዳ ተቀባዩ::

"ሔለንን ፈልጌ ነበር::"

"አንድ ጊዜ ቁጭ ይበሉ:: አለው እንግዳ ተቀባዩ ከጀርባ ወዳሉ ሁለት ጥቋቁር የቆዳ ሶፋዎች እያመለከተው::

እዮብ ይንጎራደድ ጀመር::

"አቤት ...?" ስትመጣ ያላያት፤ ቀጠን፣ ረዘም ያለች ቀይ ወጣት "አቤት ምን ልርዳዎት?"

"ሔለን?" አለ ቀኝ እጁን ለሰላምታ ወደፊት ዘርግቶ::

"ነኝ::" ፈገግ ስትል ነጫጭ ጥርሶቿ ያምራሉ:: ለሰላምታ የዘረጋውን እጁን ችላ አለችው::

"መልዕክት ይዤ ..." ድንገት ሰውየው ተናገር ያለው ዓረፍተ ነገር ቅደም ተከተል ሲጠፋበት እዮብ ግራ ተጋባ::

"ይከተሉኝ::" አለች ልጅቷ በተረጋጋ ሁኔታ ፊቷን መልሳ በስተቀኝ ቁልቁል ወደ ምድር ቤት በሚወስደው ደረጃ እየወረደች::

ተከተላት::

ደረጃውን ቁልቁል ወርደው እንደጨረሱ በስተግራ 'አስተዳደር' የሚል ምልክት የተለጠፈበትን በር ከፍታ ጨለምለም ወዳለ መተላለፊያ ገባች::

ተከተላት::

ጥቂት እርምጃዎች ወደፊት እንደሔደች ፊትለፊት የነበረ በር አንኳኳችና በሩን ሳትከፍት "ይግቡ::" ብላው በሩ ላይ ትታው በመጡበት መተላለፊያ ተመለሰች::

በሩን አንኳኳ:: መልስ የለም:: እንደማመንታት አለና በመተላለፊያው ግራና ቀኝ ገልመጥ ብሎ የበሩን እጀታ ቀልቀል ተጫነው:: በሩ ተከፈተ:: ወደ ውስጥ ገባና ዙርያውን ተመለከተ:: ጨለማ:: እጁን ከበሩ በስተግራ ሰዶ የመብራት ማብሪያውን ዳበሰ ... ተጫነው:: የመብራት ማብሪያና ማጥፊያው 'ቀጭ' ቢልም የበራ አምፖል አልነበረም::

"በሩን ዝጋው::" አለ አንድ ድምፅ በጨለማው ውስጥ::

አመነታ::

"በሩን ዝጋውና ወዲህ ና::" አለ ያው ድምፅ ደግሞ::

ወደ ውስጥ ገብቶ በሩን ዘጋና በድምፁ አቅጣጫ አንድ እርምጃ ተራምዶ ጨለማው ውስጥ ቆመ:: ድንገት ከፊት ለፊቱ አነስተኛ የጠረጴዛ መብራት ቦግ ስትል ከሞላላው ክፍል ጥግ አንድ ጠረጴዛ ተመለከተ::

ክፍሉ ከጠበቀው በላይ ሰፊ ቢሆንም በአንድ ወገን ጥግ ከያዘ ጠረጴዛና ሁለት ወንበሮች፣ ሌላ የሚታይ ነገር ቢኖር በክፍሉ ዙርያ የተደረደሩት ከግድግዳው ውስጥ ተቀብረው የተሰሩት የቁም ሳጥኖች ናቸው::

"ወዲህ ጠጋ በል::"

ወደ ፊት ተራመደ:: ወደ ጠረጴዛው እየቀረበ ሲመጣ ከማንበብያው መብራት በሚወጣው ደብዛዛ ብርሃን ከጠረጴዛው ጀርባ የተቀመጠውን ሰው ተመለከተ ... ሽማግሌ ናቸው:: የተቀመጡትም በወንበር ላይ ሳይሆን በአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪ ላይ ነበር::

"ቁጭ በል::" አሉ ሰውየው ከተቀመጡበት ተሽከርካሪ ላይ ሳይንቀሳቀሱ::

ከፊት ለፊቱ ያለውን የእንጨት ወንበር ስቦ ተቀመጠና ቀና ብሎ ተመለከታቸው::

"አቶ እዮብ ለደረሰብህ ሐዘን የተሰማኝን ፀፀት ብገልፅልህ በወደድኩ .... ግን አግባብ አይሆንም ምክንያቱም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለእናትህ ሞት እኔም ተጠያቂ ነኝ::"

"ማን ኖት እርስዎ?" አለ እዮብ ሰውየውን ትክ ብሎ እየተመለከተ::

"ኮሎኔል ገዳሙ አደፍርስ እባላለሁ::"

"ኮሎኔል ... ኮሎኔል ገዳሙ አደፍርስ? ... ኮሎኔል ገዳሙ?" እዮብ የት እንደሰማው ወዲያው ለማስታወስ ቢቸግረውም ይህን ስም ከዚህ በፊት ለመስማቱ እርግጠኛ ነበር::

ክፍሏ በጠረጴዛዋ መብራት ደብዛዛ ብርሃን ተሞልታለች:: ፈጠን ብሎ ወደ ሽማግሌው ተጠጋ:: ጠረጴዛው ላይ በግንባራቸው ተደፍተዋል:: ጥቁር ቀይ ደም ጠረጴዛው ላይ ተንጣሏል:: በቀኝ እጃቸው ሽጉጥ ጨብጠዋል::

በቀኙ የያዘውን ካኪ ከረጢት ወገቡ ላይ አጥፎ ኪሱ ከተተና ጠጋ ብሎ ሽጉጡን ተመለከተ:: ደነገጠ:: ፈጠን ብሎ ከኪሱ መሀረብ አውጥቶ ከሽማግሌው ቀኝ እጅ ውስጥ ያለውን ሽጉጥ ፈልቅቆ አወጣና አስጠግቶ ተመለከተው::

የገዛ እራሱ ሽጉጥ ነው::

ድንገት ከጀርባው ድምፅ ሲሰማ በፍጥነት ፊቱን ወደ ኋላ ... ወደ በሩ አዞረ::

በሩ ላይ ቆማለች::

"ምንድነው?!" ስትል ተሰማው ወደ ሽማግሌው ክፍል መርታ ያመጣችው ቀይ ሴት::

ሴትዮዋ ከበሩ ጎን ያለውን የመብራት ማብሪያ ስትጫን ክፍሉ በብርሃን ተሞላ::

እዮብ ግራ በተጋባ ሁኔታ እንደ በእጁ የያዘውን ጠፋ የተባለ የገዛ እራሱን ሽጉጥ! እንደ ደግሞ ሴትዮዋን እያፈራረቀ እየተመለከተ ቆመ::

ሴትዮዋ ፊቷን መልሳ ሮጠች::

ወደ በሩ ሮጠ ... በመተላለፊያው አድርጎ በደረጃው ወደ ላይ ሲወጣ ከፊት ለፊት ያለው በር ተከፍቶ ሁለት ሴቶች ብቅ አሉ:: ግራና ቀኝ ገፈታትሯቸው ሮጠ::

"ሰውየውስ? "

ልዑል በስጨት ብሎ የፌይሰልን ግራ ክንድ ጨምድዶ ወደአንደኛው የመፀዳጃ ክፍል ጎተተውና የክፍሏን ትንሽ በር በረገዳት::

የሼል ዴፖው ሠራተኛ ሁለት እግሮቹን ወደፊት ሰተት አድርጎ ዘርግቶ የመጸዳጃ ሳህኑ ላይ ተቀምጧል:: አገጩ ደረቱ ላይ ወድቋል:: በጩቤ ከተወጋው ግራ ደረቱ የሚወርደው ደም እስከ ጭኑ ድረስ አበስብሶታል::

"ይህን ነው ለማየት የመጣኸው?" አለ ልዑል ትርዒቱ ተራ እንደሆነ ሁሉ ዘና ብሎ ጭንቅላቱን ወደ አንድ ወገን ዘንበል አድርጎ::

"ምንድነው የሰራኸው? ... ምንድነው ይሄ?" ፌይሰል ወደኋላ አፈገፈገ::

"ምንድን ነበር ለማየት የጠበከው?"

"ሰው ነውኮ ... የገደልከው!"

"ለመሆኑ አንተ ማነህ? ... " አለ ልዑል ድንገት ቱግ ብሎ "... ለመሆኑ ምን እየሰራህ ይመስልሀል? ... ምን ስታደርግ እዚህ ተገኘህ? ... እስቲ መልስልኝ! እስቲ እራስህን ጠይቀው! ... ህ! 'በምን የተነሳ ይህ ሁሉ ጠባሳ' አለ እሱ ከመንጋው ኋላ ኋላ የሚከተል የዝንጀሮ አውራ!"

"አይገባኝም! ምን አደረገህና ትገድለዋለህ?..." ጮኸ ፌይሰል "... እንዲህ ዓይነት ስህተት ውስጥ አይኔ እያየ አልገባም! "

"አሁን መንገዳችንን ብንቀጥል ጥሩ መሰለኝ:: አትጠራጠር ... በምንሄድበት መንገድ ገና ብዙ ስህተት እንፈጽማለን:: በፀጋ ተቀበለው:: የተሳሳትከው ገና ጥንት ወደዚህ ዓይነቱ ሕይወት ስትገባ መሰለኝ:: ያን ጊዜ ነበር መጠንቀቅ ... 'ዛር ልመና፣ ሳይያዙ፣ ከተያዙ ብዙ ነው መዘዙ' ሲባል ሰምተህ አታውቅም? "

ልዑል ፌይሰልን በቆመበት ትቶት ከመታጠቢያው ክፍል ሲወጣ ፌይሰል ፊቱን እጨማደዶ በደም የተጨማለቀውን የሼል ዴፖ ሠራተኛ ለመጨረሻ ጊዜ መለስ ብሎ ተመለከተና ልዑልን ተከትሎ ከክፍሉ ወጣ::

"እስረኛው በሞተበት ... 'በተገደለበት' ብል ሳይሻል አይቀርም ..." አሉ የደህንነት አማካሪው የፌዝ ፈገግታ ፈገግ ብለው "... በአባላቶችህ ላይ የደረሰ አደጋ ነበረ ... አልነበረም?"

"ነበር::"

"ስንት ሰው ሞተ?"

"ሁለት::"

"በማግስቱ ከአንተና ከፖሊስ ኃይል ተውጣጥቶ የተዋቀረው አጣሪ ኮሚቴ የደረሰበትና ያሳለፈው ውሳኔ ምንድን ነበር?"

"ግድያው የተፈጸመው በአባላት ሊሆን ስለሚችል ..."

"በማን አባል? ግልፅ አድርገው!" ግራ የሌባ ጣታቸውን መልሰው ቀሰሩበት::

"በአገር ውስጥ ደህንነት መሥሪያ ቤት አባላት ... እና ..." ዶክተር ብርሃን ለአፍታ ግራ የተጋባ መስለና ቀጠለ "... በእነዚሁ አባላት ላይ ምርመራ እንዲካሔድ ነበር አጣሪ ኮሚቴው ..."

"ይቅርታ አድርግልኝ..." አቋረጡት "...የአጣሪ ኮሚቴው ሙሉ ሪፖርት እዚህ ውስጥ ተካቷል! ... አንብቤዋለሁ! ዶክተር እኔም የመረጃ ባለሞያ ነኝ:: ኮሚቴው ያስተላለፈው የመፍትሔ ሀሳብ ተጠርጣሪ የሆኑ አባላት በአፋጣኝ በቁጥጥር ሥር ሆነው ... አስታውስ 'በቁጥጥር ሥር ሆነው' ምርመራ እንዲካሄድ ነበር::"

"ትክክል ነው ክቡርነትዎ::"

"ከእነዚህ ሰዎች ውስጥ ስንቱን በቁጥጥር ሥር አድርገህ የመረጃ ማሰባሰብ ሥራ ጀምረሀል?"

"እ...እ ..."

"እኔ ልርዳህ መሰለኝ:: ከተሳሳትኩ ልታርመኝ ትችላለህ:: ማንኛቸውንም በቁጥጥር ሥር አድርገህ ምርመራ አልጀመርክም::"

የደህንነት አማካሪው አይኖቻቸውን ከውስጥ ደህንነት ኃላፊው ላይ ነቅለው 'እናንተ ፍረዱኝ!' ሊሉ የፈለጉ ይመስል በተቀሩት ባለሥልጣናት ላይ አመላለሱና ቀጠሉ::

"እነዚህ አራት 'ከጉዳዩ ጋር የቅርብ ግንኙነት ይኖራቸዋል' ተብለው የተጠረጠሩ አባላት አሁን የት ናቸው? ..." አሉ ወዲያው እራሳቸው ለጠየቁት ጥያቄ እራሳቸው እየመለሱ " ... ከሁለቱ የጥበቃ አባላት አንደኛው ከትላንት በስትያ በመኪና አደጋ ሞቷል ወይም በተቀነባበረ አደጋ ተገድሏል:: ሁለተኛውና የአጣሪ ኮሚቴው በመጀመርያ ደረጃ ያተኮረበት ሰራተኛህ አቶ እዮብ ጌታሁንን በተመለከተ ዝርዝሩን ካንተው ከራስህ ብሰማው በወደድሁ! ጊዜ የለኝም እንጂ!"

"እንግዳው እያወቅህ ነው የምታጠፋው?" ፌይሰል ጆሮዎቹን ማመን እንዳቃተው ሁሉ ፊቱን አጨማዶ ጠየቀ::

"ታውቃለህ?..." አለ ልዑል ፈገግ ብሎ "... ሼክስፒርን የሚያክል ታላቅ ፀሐፊ ዓለምን የትያትር መድረክ፣ እኛን ተዋንያን፣ ሕይወትን ደግሞ አንድ ረጅም ትያትር ብሎ ማለፉ ሁሌም ያስቀኛል:: ፍፁም - ፍፁም የዋህ ትንታኔ! ሕይወት ትያትር በሆነ እንዴት በጣፈጠ! መኖር መተወን በሆነ እንዴት በቀለለ! እውነቱ ግን ... ዓለምም የትወና መድረክ አይደለች፣ እኛም ተዋንያን አይደለን:: ዓለም የመሥዋዕት ገበታ እኛም መሥዋዕት አቅራቢዎች እኛም የመሥዋዕት በጎች ነን::"

"ስለዚህ?" አለ ፌይሰል በማሽሟጠጥ መልክ::

"እረጋ ብለህ ካየኸው ..." አለ ልዑል የፌይሰልን ሽሙጥ ችላ ብሎ "... እውነቱን መሸሽ ካልመረጥክ የሰው ልጅ ይህኛውን ለማግኘት ያኛውን፣ ያኛውን ለማግኘት ደግሞ ይህኛውን መሥዋዕት እያቀረበ የሚውተረተር ምስኪን ፍጡር ነው:: አንዱ ለቤተሰቡ ... ለልጆቹ ሲል እራሱን መሥዋዕት ያቀርባል፣ ሌላው ለአገሩ ሲል ቤተሰቡን ሜዳ በትኖ ይሄዳል፣ ይህኛው ሐይማኖቱን አስበልጦ ... ፅድቅን ሽቶ በመሰል ፍጡሩ በሰው ልጅ ላይ ቅዱስ ጦርነት ያውጃል፣ ጦር ይሰብቃል፣ ያኛው የገንዘብና የወርቅ ጥማቱ ልቡ ላይ ቃር ሆኖበት ስስት እያቀረሸ ፅላት ይቸረችራል ..."

"ቆይ ..." አለ ፌይሰል አቋርጦት "... ይህ ሁሉ 'ሰው መግደሌ ትክክል ነው' ለማለት ነው ... ወይስ ...?"

"ለማለት የፈለግሁት ምንም እንኳን መራራ ቢሆን በሰው ልጅ ጉዞ ይህኛውን ለማግኘት ያኛውን መሥዋዕት ማቅረቡ የነበረ፣ ያለና የሚኖር ብቻ ሳይሆን ልንሸሸው የማንችል ተፈጥሮአዊ ህግ መሆኑን ..."

"አብደሀል?"

"እብደት አልከው? ... አብርሃም አንድ ልጁን ይስሐቅን መሥዋዕት ሊያቀርብ ሲነሳ ... ፈጣሪ ፊቱ ቅጭም አለ የሚል ማንበቤ ትዝ አይለኝም:: እየህ ለአብርሃም የፈጣሪው ፍቅር ስለበለጠበት የገዛ ልጁን በመሠዊያ ገበታ ላይ አጋድሞ ሊያርደው ካራ ሲያነሳ፣ ነፍስ ሲያጠፋ ሲደፍር ፅድቅ ሆኖ ተቆጠረለት ... 'ተው ልጅህን መሥዋዕት አታቅርብ' ብሎ በምትኩ የበግ ሙክት ያቀረበለት አንድዬ ውሎ አድሮ የዓለሙ ፍቅር ቢጠናበት የገዛ ልጁን መሥዋዕት ሊቀርብ አሳልፎ ሰጠው ... ታድያ አዳሜ ለወደደው ያሻውን እያጋፈጠ ሲሰጥ ልዑል ምን ስላደረገ ነው የሚወቀስ? ... በላ ንገረኝ! ... አትሞኝ ሁላችንም የሚበልጥ ሲመጣ ሁሉንም አሳልፈን ለመስጠት እንጨክናለን:: እስቲ ንገረኝ ምንድነው በዙርያችን መሥዋዕት የማይቀርብ ... የማይነካ ... የማይደፈር ... አገር? ሐይማኖት? ቤተሰብ? ... ምን?"

"ስለዚህ ..." አለ ፌይሰል ትክ ብሎ ልዑልን እየተመለከተ "... ስለዚህ አንድ ሰው የፈለገውን መጥፎ ነገር ቢያደርግ ... ጥፋት ሆኖ ሊቆጠርበት አይገባም ማለት ነው::"

"አልወጣኝም:: ... " አለ ልዑል ቀኝ እጁን ከፍ አድርጎ "... ያልኩት 'መጥፎ' የሚባል ነገር ጨርሶ የለም ነው:: ያልኩት 'መጥፎ' የምንላቸውን ነገሮች ለምሳሌ ጥላቻን፣ ክፋትን፣ ሐጢያትን፣ እርኩሰትን ከትልቁ የስነፍጥረት ቀመር ውስጥ ካወጣሀቸው በጎ የሚባሉት ፍቅር፣ ደግነት፣ ፅድቅና ብፅእና ብቻቸውን ሊቆሙ ስለማይችሉ ስነፍጥረት እራሱ ይፈረካከሳል:: የኢትዮጵያ አበው ምን እንዲሉ ታውቃለህ? - 'የሰው ልጅ ቆሞ የሚሄደው በክፋት ነው'::

"ከየት ያመጣኸው ፍልስፍና ነው ይሄ?"

"ብፅእና ያለ እርኩሰት ብቻውን ሊኖር እንደማይችል ምሳሌ ልስጥህ?... " አለ ልዑል ፈገግ ብሎ "... ለምሳሌ እኛ ክርስትያኖች ለሰው ልጅ መዳን የመጨረሻው ተስፋው እየሱስ ክርስቶስ ወደእዚህ ዓለም መጥቶ፤ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ፤ ሞቶ፤ በሶስተኛው ቀን ሞትን ድል ነስቶ መነሳቱ ነው ብለን እናምናለን ... መዳን በዚያ ነውና:: በንፅፅሩም የሰው ልጅ በታሪኩ ከፈፀማቸው ወንጀሎች፣ ሐጢያቶች፣ እርኩሰቶች እጅግ አስቃቂውን ጥሩ ብንባል እኔ ስገምት የሰው ልጅ ደፍሮ የእግዚአብሄር የባህርይ ልጅ የሆነውን፤ ፈጣሪውን እየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ላይ በሚስማር መቸንከሩ ነው እላለሁ:: እንግዲህ አስተውል ... እንደው እንበልና አስቆሮቱ ይሁዳ 'ምን ቆርጦኝ እየሱስን አሳልፌ የምሰጠው ብትፈልጉ በማጅራቱ እረዱኝ' ቢል ኖሮ ወይ ደግሞ አይሁድ አደባባይ ተሰብስበው በጲላጦስ ፊት 'ስቀለው! - ስቀለው!' እያሉ መጮሀቸውን ትተው 'ማርልን! - ማርልን!' ብለው እየሱስን ከእስር አስፈትተውት ቢሆን ክርስትያን ሁላ ምን ይውጣት ነበር? እየሱስ ክርስቶስስ እንዴት መድሀኒዓለም ሊሆን ይቻለው ነበር? በላ ንገረኛ! እንግዳው ይሁዳን እንደ ጥቁር ውሻ! አይሁድን እንደ ነገደ ጊንጥ መጠየፋችን ከየት የመጣ ነው? እኔ ልንገርህ? " አለ ልዑል ቅንድቦቹን ሰማይ ሰቅሎ "... ይህ ሁሉ ጥላቻ የመጣው ... በጎ ስራ ብቻውን ሊቆም አለመቻሉን ካለመረዳት ነው ... ሐጢያትና ፅድቅ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ መሆናቸውን ካለመገንዘብ ነው::"

"ጤነኛ አትመስለኝም::"

"ህ! ጤነኛ መስዬ አልታይ አልኩህ? ... " አለ ልዑል ፈገግ ብሎ "... እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ... ለመሆኑ አንተ እዚህ ከእኔ ጋር ምን ትሰራለህ? እውነት ከእኔ ጋር እየተጓዝክ ያለኸው ከክፉ መንገዴ መክረህ ልትመልሰኝ ይሆን ... ወይስ ... አንተም የምትሻውን ለማግኘት አሊያም የምትፈራውን ለመሸሽ ... መሥዋዕት ለማቅረብ ነው የመጣህ? ... ምንድነው የምትሻው? ... ምን ትሰራለህ እዚህ?"

ፌይሰል መልስ ሳይሰጥ ዝም አለ:: ልጁ ታሰበችው::

ድንገት አንድ ቼሪኪ ጂፕ በከፍተኛ ፍጥነት በጎን አለፈችና በግምት መቶ ሜትር እርቃ እንደሄደች ፊቷን በፍጥነት አዙራ ቆመች::

"ምንድነው? ..." አለ ልዑል ፍጥነቱን ቀንሶ ፊቱን ወደ ፌይሰል መለሰና "... የምታውቀው ነገር አለ? "

"ምን? " ፌይሰል ግራ ተጋብቶ "... ምንድነው የማውቀው?"

"ዑመር! ... " አለ ልዑል በስጨት ብሎ "... ከጅቡቲ ... ከወደቡ ስንነሳ ያነጋገረህ ሰው የሰጠህ መመርያ አለ? ... አስታውስ ... በመንገድ ላይ ይህች መኪና እንደምትጠብቀን ነግሮሀል?"

"አልነገረኝም::"

"እርግጠኛ ነህ?" ልዑል የሚያሽከረክረውን የጭነት መኪና ዳር አሲዞ አቆመ::

"መንገድ ላይ የሚጠብቃችሁ መኪና አለ አላለኝም እርግጠኛ ነኝ::"

"እንግዳው አደጋ ውስጥ ነው ያለነው!" አለ ልዑል ጎንበስ ብሎ ከመቀመጫው ስር ያለውን የላስቲክ ምንጣፍ ገልጦ ታጣፊ መትረየሱን እያወጣ::

ከፊት ያለችው ጂፕ ተንቀሳቀሰች:: በዝቅተኛ ፍጥነት ቀረበች:: ሰላሳ ሜትር ያህል ሲቀራት ቆመች:: የፊት መስተዋቷ ላይ ነጥሮ የሚመለሰው የጠዋቷ ፀሀይ ጨረር ከውስጥ ያለውን ጋርዶታል:: ግራና ቀኝ በሮቿ ተከፍተው ሁለት ሰዎች ወረዱ:: ሁለቱም ሰዎች የያዝዋቸውን መሳርያዎች ለመደበቅ ሳይሞክሩ ጥግ ይዞ ወደቆመው የጭነት መኪና እየተጠጉ መጡ ...

ልዑል መሳርያውን አቀባበለና መጠበቂያውን ለቀቀ -

"አጎንብስ!"

ኮሎኔል ሥዩም ከፊቱ የተቀመጡትን አራት ሰዎች በተራ ተመለከታቸው:: ዛሬ ጠዋት የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ የሰጡትን ትዕዛዝ ተከትሎ የኢንተርፖል ቢሮ በአዲስ አበባ፣ የአገር ውስጥና የውጭ የደህንነት ቢሮዎች 'ምርጥ ባለሙያዎች ናቸው' ያሏቸውን አባላቶቻቸውን አዲስ ለሚቋቋመው አዳኝ ቡድን ልከዋል:: በእርሱ በኩል የተቀሩትን ሦስት ሰዎች ይቆጣጠርልኛል ያለውን ቀደም ብሎ ለአደንዛዥ እፅ መረብ መልምሎ ሲያሰራው የቆየውን የወንጀል ምርመራ አባል የመቶ አለቃ ፍቅሬ አበጋዝን መርጦ መድቧል::

ኮሎኔል ሥዩም ድጋሚ ጎሮሮውን አፀዳና ቀጠለ::

"ይህ ቡድን የተቋቋመው ለከፍተኛ ውጤት ነው:: ይህን ውጤት ደግሞ ከበላይ በተላለፈው ትዕዛዝ መሠረት ቢቻል በሰዓታት አለበለዚያም በጥቂት ቀናት ውስጥ ልንፈፅመው ይገባል:: ..." አለ ኮሎኔል ሥዩም ከፊቱ የተቀመጠውን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ የተቀበለውን ቀይ ጥራዝ አንስቶ ይዞ "... በአጭሩ ኃላፊነታችን ከዚህ ቀደም በአገር ውስጥ ደህንነት መሥሪያ ቤት ውስጥ ሲሰራ የቆየውንና በአሁኗ ሰዓት ከፍተኛና የአገርን ደህንነት አደጋ ላይ ጥሎ በሚገኝ ወንጀል ውስጥ ቁልፍ ቦታ ይዞ ይገኛል ተብሎ የሚጠረጠር፣ ለጊዜውም ተሰውሮ ያለ አቶ እዮብ ጌታሁን የተባለ ግለሰብን በተቻለ ፍጥነት አድኖ ለተገቢው ምርመራና አስፈላጊም ከሆነ ለፍርድ ማቅረብ ነው:: ...

"... ግለሰቡ በመረጃ መሥሪያ ቤቱ ውስጥ በተለያዩ የሥራ መደቦች የሰራ በመሆኑና ሰፋትና ጥልቀት ያለው ልምድ ያካበተ በመሆኑ እራሱን ከህግ አስፈፃሚ አካላት ሰውሮ ለማቆየት፣ አልፎ ተርፎም ህገወጥ የሆነ ማንኛውንም መንገድ ተጠቅሞ እራሱን ከመከላከል የማይመለስ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ክትትሉ ጥንቃቄ የተሞላበትና እጅግ ፈጣን እርምጃዎችን ያካተተ ሊሆን ይገባዋል ...

"እንዳልኩት ጊዜ የለንም:: ይህ ለእያንዳንዳችሁ ግልፅ እንዲሆን እፈልጋለሁ:: ያለንን ማንኛውም አቅምና ልምድ አስተባብረን ይህንን ሰው በሀያ አራት ... ቢበዛ በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ በእጃችን እንድናስገባው እፈልጋለሁ:: ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ እያንዳንዳችሁ ከያላችሁበት ቢሮ ወደዚህ ተዛውራችኋል:: ይህ ሰው በእጃችን እስኪገባ ድረስ ተጠሪነታችሁ ቀጥታ ለእኔ ይሆናል:: ይህን ክትትል እንደ ዕለት ተዕለት ተግባራችን ቀኑን ስንሰራ ውለን ዕለቱ ሲገባደድ ወደ ጎን ብለን ለሚቀጥለው ቀን የምናስተላልፈው አይሆንም ..."

ለአንድ አፍታ ኮሎኔል ሥዩም ንግግሩን አቁሞ በጠረጴዛው ግራና ቀኝ የተቀመጡትን ሰዎች አትኩሮ ተመለከታቸውና ንግግሩን ቀጠለ::

"... ይህ ሰው በእጃችን እስኪገባ ውሎአችሁም አዳራችሁም እዚሁ ግቢ፣ እዚሁ ሕንፃ ውስጥ ይሆናል:: የመኝታ ክፍሎች፣ የመመገብያ አዳራሽ ... አስፈላጊ ነው የሚባለውን ሁሉ እዚሁ ሕንፃ ውስጥ በሦስተኛው ፎቅ ታገኛላችሁ:: ተጨማሪ እንዲሟላ የምትሹት ሁኔታ ካለ ለእዚሁ የተመደበ አባል ስላለ በዚያው በኩል ተፈጻሚ ይሆናል:: ...

"... ቢሯችሁ ለክትትሉ አስፈላጊ ናቸው በተባሉ የመገናኛ እንዲሁም ሌሎች መሣርያዎች የተሟላ በመሆኑ በዚያ በኩል ችግር አይገጥመንም:: ዋናው ቁም ነገር ..." አለ ኮሎኔል ሥዩም የሁለት እጆቹን መዳፎች ፊት ለፊት ጠረጴዛው ላይ ደፍቶ "... ዋናው ቁም ነገር በአስቸኳይ ይህን ሰው አድናችሁ በእጃችሁ ማስገባታችሁ ነው:: ...

"... የመስክ ክትትሉን በተመለከተ እያንዳንዱ የፖሊስ ዘርፍና ጣቢያ ከሰዓታት በፊት በተጠንቀቅ እንዲጠባበቅ ትዕዛዝ የተላለፈ ሲሆን በየትኛውም አቅጣጫ ትዕዛዝ ማስተላለፍ ብትፈልጉ፣ መረጃ ብትሹ ... በየትኛውም የአገሪቱ ከተማ ወይም ገጠር ያለ ኃይላችን አብሯችሁ ለመስራት እየተጠባበቀ ይገኛል:: ...

"... በተረፈ የአስራ ሁለት ሰዓት ሪፖርቶችን ጠዋት በአንድ ሰዓትና ማታ በአንድ ሰዓት ላይ ጠረጴዛዬ ላይ እፈልጋለሁ:: ይህ ሪፖርታችሁ ተጠናቅሮ እያንዳንዱ የሀያ አራት ሰዓት ሪፖርት በቀጥታ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ይላካል:: ጥያቄ ካላችሁ አሁን ወይም በማንኛውም ሰዓት ቢሮዬ ክፍት ነው::"

ኮሎኔል ከተቀመጠበት ተነስቶ ቆመና ሰዓቱን ተመለከተ::

"... አሁን ከምሽቱ አምስት ሰዓት ነው:: ከውጭ እያንዳንዳችሁን ወደ ቤታችሁ የሚወስዷችሁ መኪናዎችና ሹፌሮች ተመድበው ይጠባበቁዋችኋል:: ከአሁን በኋላ እነዚህ መኪናዎችና ሹፌሮች ለዚህ ሥራ የተመደቡ በመሆኑ በማንኛውም ወቅት ልትጠቀሙባቸው ትችላላችሁ:: ...

"... ዛሬ ለሊቱን ወደየቤታችሁ ተመልሳችሁ 'አስፈላጊ ናቸው' የምትሏቸውን የግል እቃዎቻችሁን ማለት የንፅህና እቃዎችን ተለዋጭ ልብሶችን ሌሎችንም ይዛችሁ ጠዋት በየቢሮአችሁ እንድትገኙ እፈልጋለሁ:: ከዚያ ወዲያ ቤቴ፣ ሚስቴ፣ ልጆቼ የሚለውን ለዛ ቢስ መዝሙር መስማት አልሻም::"

ኮሎኔል ለአንድ አፍታ ከፊቱ በጠረጴዛው ዙርያ ተቀምጠው በቆመበት ሽቅብ ፊት ፊቱን የሚመለከቱትን አራት ሰዎች በተራ ቃኘና ...

"በእናንተ በአራታችሁ ችሎታና ልምድ መንግሥት ሙሉ በሙሉ ተማምኖ ይህን ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳስረከባችሁ ተረድታችሁ በሙሉ ልብና ዝግጁነት ውጤት ለማምጣት እንደምትሰሩ ተስፋ አለኝ:: መሔድ ትችላላችሁ:: መልካም ዕድል::"

አራቱ ሰዎች ሰላምታ እየሰጡ ከየተቀመጡበት ተነስተው፣ ተከታትለው ወደ በሩ አመሩ::

"ፍቅሬ ... መቶ አለቃ ፍቅሬ ..." አለ አራቱ ሰዎች በእርጋታ ወደ በሩ ሲያመሩ ከጠረጴዛው ጀርባ ቆሞ ይመለከታቸው የነበረው ኮሎኔል ሰዩም::

"አቤት ጌታዬ ..." የወንጀል ምርመራው መኮንን ከበሩ እንደደረሰ ከጀርባ ሲጠራ ፊቱን መለሰ::

"አንድ ጊዜ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ:: ሌሎቻችሁ መሔድ ትችላላችሁ::"

ኮሎኔሉ የመቶ አለቃውን አስከትሎ ወደ ግል ቢሮ ተመለሰና በቆዳ ወንበሩ ላይ ዘፍ አለ::

"ቁጭ በል::" አለ ኮሎኔል ሥዩም ከኮት ኪሱ ውስጥ ሲጋራ እያወጣ::

የመቶ አለቃ ፍቅሬ ቀልጠፍ ብሎ ከግራ ኪሱ የሲጋራ መለኮሻውን አውጥና ሲጋራውን አያያዘለት::

"ፍቅሬ ..." አለ ኮሎኔል ሥዩም ሲጋራውን በረጅሙ ማግ አድርጎ በለቀቀው፣ በሚደበላለቅ፣ በሚተራመስ ነጭ ጭስ ውስጥ አይኖቹን አጥዞ "... ምን አይነት አደገኛ ሁኔታ ላይ እንዳለን ሳትረዳው የቀረህ አይመስለኝም::"

"ይህን እዮብ የተባለ ሰው ለጊዜውም ቢሆን ማባበል ወይ መግዛት ቢቻልኮ ..." የወንጀል ምርመራው ሰው ጀመረ::

"ያ ነው ችግሩ ..." አቋረጠው ኮሎኔል "... አንደኛ ይህ ሰው ምን ያህል እንደሚያውቅ፣ ምን ያህል መረጃ በእጁ እንዳስገባ፣ አላማውም ምን እንደሆነ የምናውቀው የለም:: በዚህ ሰው ላይ እንድናተኩር የሚያደርገን ትልቁ ነጥብ በአሁኑ ሰዓት መሰወሩ ነው:: ጉዳዩ የሚመለከተው ባይሆን' የሚያሸሸው፣ የሚሸሽገው መረጃ ባይኖር! መሰወርን ምን አመጣው? ለዚህ ነው ይህን ሰው በአስቸኳይ በእጃችን አስገብተን ምስጢሩ ላይ መድረስ አስፈላጊ የሚሆነው::"

"ገባኝ::" አለ የመቶ አለቃ ፍቅሬ::

"አልገባህም ... አልገባህም ፍቅሬ ..." አለ ኮሎኔል ሥዩም ያጋመሳትን ሲጋራ መተርኮሻው ላይ እየደፈጠጠ "... አየህ እኛም ሆንን መንግሥት ይህን ሰው በእጃችን ለማስገባት እንፈልጋለን:: ቢሆንም ዓላማችን ለየቅል ነው:: መንግሥት የሚፈልገው ይህን ሰው በእጁ አስገብቶ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተንቀሳቀሰ ያለውን የአደንዛዥ እፅ መረብ መስበር ነው:: እኛ ደግሞ የምንሻው ይህን ሰው ይዘን በእጁ ያስገባውን መረጃ ለመንግሥት አሳልፎ ሰጥቶ አደጋ ላይ እንዳይጥለን ሰውየውን ለዘለቄታው ማቆም ነው::"

"አልገባኝም ... አንድ ቡድን አይደል እንዴ የተቋቋመው?" አለ የመቶ አለቃው::

"ያንን ነው የምልህ:: ..." አለ ኮሎኔል ጭንቅላቱን እየነቀነቀ "... የእኛ ግብ እንዳልኩህ ወደ ኢትዮጵያ እየገባ ያለው የአደንዛዥ እፅ ዘር ወደታቀደለት ስፍራ እስኪደርስ ድረስ እንቅፋት የሚሆኑበትን ሁሉ ማስወገድ ነው:: የምናደርገውም ይህንኑ ነው:: ይህን የመረጃ ሰው አድኖ እንዲይዝ በተደራጀው ቡድን ውስጥ እንድትገባ ያደረግሁት አንደኛ የቡድኑን አካሔድ ደረጃ በደረጃ እየተከታተልክ እንድታሳውቀኝ ሲሆን እያንዳንዷ መረጃ ወደ መንግሥት አካላት ከመድረሷና ይህም ተፈላጊ ሰው በመንግሥት እጅ ከመግባቱ በፊት በእኛ እጅ የሚቀርበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው:: አስታውስ በዚህ በተደራጀው አዳኝ ቡድን ውስጥ የምትሰራው ለገዛ ነፍስህ እንጂ ለመንግሥት አይደለም:: ምክንያቱም ምስጢራችን ቢወጣ ዘሩ ከታቀደለት ስፍራ ከመድረሱ በፊት ቢደናቀፍ ምን እንደሚጠብቅህ በሚገባ ትረዳዋለህ ብዬ እገምታለሁ:: ...

"ስለዚህ ..." አለ ኮሎኔል በወንበሩ ላይ ተመቻችቶ እየተቀመጠ "... በተቻለህ መጠን ይህ ሰው በመንግሥት እጅ እንዳይወድቅ በተቃራኒው በእኛ ቀለበት ውስጥ እንዲገባ አስፈላጊና አደገኛ መረጃዎችን ቡድኑ ለእኔ ከማቅረቡ በፊት ቀደም እያልክ ሳታዘገይ ታቀብለኛለህ:: እኔ የሰጠኸኝን መረጃ ተጠቅሜ የሚሆነውን አደርጋለሁ::"

የመቶ አለቃው ከተቀመጠበት ሳይንቀሳቀስ መስማማቱን ለመግለፅ ጭንቅላቱን አላይና እታች ነቀነቀ::

"ጥሩ ..." አለ ኮሎኔል እንደዋዛ በስተቀኙ የጠረጴዛውን መሳቢያ ስቦ አንድ የአስር ሽህ ብር እስር አንስቶ ጠረጴዛው ላይ ጣል አድርጎ "... ሁሉን ነቅተህ ተከታተል::"

የቢሮው ጠረጴዛ ላይ ካሉት ሦስት ስልኮች ውስጥ በስተግራ ያለው ጥቁር ስልክ ሲጮህ ኮሎኔል ቀልጠፍ ብሎ አነሳው::

"ሀሎው::"

"ሀሎው ..." አለ የቤን ሳውል የተረጋጋ ድምፅ::

"ኮሎኔል ነኝ::"

"አሁኑኑ እንድትደርስ!"

"አሁን?" አለ ኮሎኔል ሰዓቱን እየተመለከተ::

"አሁኑኑ!" ቁርጥ ያለ ትዕዛዝ::

ኮሎኔል ቢዳከምም ምርጫ አልነበረውም::

ከቢሮው ወጥቶ ወደ ሼረተን ሆቴል ሲያመራ ግን ምን እንደሚጠብቀው ፍንጭ አልነበረውም::

ቤን ሳውል የተከራየውን የሆቴል ክፍል አንኳኩቶ በሩ ሲከፈትለት ... ወደ ውስጥ ሲገባ ... የቤን ሳውልን ፊት ሲመለከት ግን ሌላ ችግር እንደተከሰተ ገባው::

"ምን ተፈጠረ?" አለ ኮሎኔል በጭንቀት::

"ይህ የማን ቦርሳ ነው?"

'ቦርሳ?'

"አው! ..." አለ ኮሎኔል "... የእኔ ነው ትላንት ማታ ተደናግጬ ከመኪናው ውስጥ ስወጣ ትቼው ወጥቼ ነው::" አለ ቦርሳውን ሲቀበል እጁን እየዘረጋ::

"ሹፌርህ ከጠበቅነው በላይ አደገኛ ነበር:: መኪናህን ያፀዱልህ ሰዎች ይህን ቦርሳ ሲያገኙ ጥርጣሬ ስለገባቸው የሰውየውን አሬሳ ሲያነሱ ቦርሳውንም ወስደው መርምረውት ነበር:: ቦርሳው የድምፅ ማስተላለፍያ የተገጠመለት ነው::"

"ቦርሳው!" አለ ኮሎኔል ደንገጥ ብሎ::

"ምነው?" ቤን ሳውል ጥርጣሬ ገባው::

"ቦርሳው ... ቦርሳው ሹፌሬ ... ሹፌሬ አይደለም የሰጠኝ ..." የጀመረውን ሳይጨርስ አቋረጠና ዝም አለ::

"ምንድነው እያልክ ያለኸው?"

"የሴት ጓደኛዬ ... " ኮሎኔል አሁንም የጀመረውን ሳይጨርስ ፊቱን በሁለት እጆቹ ሸፍኖ ቆመ::

## ፳፩

ጠዋት በአራት ሰዓት ከቤቱ ወጣ::

እንደዚያ ነው ያለው እዮብ "... ጠዋት ልክ በአራት ከቤትህ በእግርህ ውጣ ..."

የኮረኮንቹን መንገድ ጨርሶ ከአስፋልቱ ሲደርስ ከአምስተኛ ወደ መርካቶ በሚወስደው አቅጣጫ አራት ብላ ቆማ የነበረች መቶ ሀያ አራት ታክሲ ተሽቀዳድማ መጥታ ፊቱ ድቅን አለች::

አቤሰሎም ይህ የእዮብ ዝግጅት እንደሆነ ገባው::

'... ከዋናው አስፋልት እንደደረስክ የኮንትራት ታክሲ ያዝ ... የሮትማንስ ሲጋራ ማስታወቂያ ያለበትን የላስቲክ ከረጢት ከታክሲው የኋለኛ ወንበር ...'

አቤሰሎም ጎንበስ ብሎ ሹፌሩን ተመለከተው:: ጠይም! ወፍራም! ሞኛሞኝ ፊት::

"የት ነው ጌታዬ::" አለ ሹፌሩ በተረጋጋ ሁኔታ::

"ግዮን ሆቴል::"

"ይግቡ::"

"ስንት ነው?"

"ተከፍሏል::"

አቤሰሎም አላመነታም:: የታክሲዋን የፊት በር ከፈተና ከሹፌሩ ጎን ተቀመጠ:: በቀኙ ያንጠለጠለውን የላስቲክ ከረጢት ዞሮ ከኋለኛው ወንበር ላይ ጣል አደረገው:: እዮብ ያንን ነው እንዲያደርግ የነገረው ...

'... ሁኔታዎች ከተመቻቹልኝ መንገድ ላይ አንተ የተሳፈርክበትን ታክሲ አስቁሜ ከኋላ ወንበር ላይ ያስቀመጥከውን ዕቃ ይዤ... እወርዳለሁ ...'

ባለታክሲው ሞተሩን አስነስቶ በረረ:: ታክሲዋ ለረጅም ጊዜ ማገልገሏ የምታሰማው ኳኳቴ ያሳጣል:: ሹፌሩ ግን የመኪናውን አቅም ያልተረዳ ይመስል ትንሿን ተሽከርካሪ እያንገጫገጨ ይከንፍ ጀመር:: አቤሰሎም የባለታክሲውን ፍጥነት ሲመለከት ስጋት ገባው::

"ወንድም ሌላ ተንኘር ካገኘህ ... ማለቴ ከመንገድ ላይ መጫን ከፈለግህ ትችላለህ::" አለ አቤሰሎም የሹፌሩ ሩጫ እልቀንስ ሲለው እዮብን ከመንገድ ላይ አልፎት እንዳይሔድ እየሰጋ::

"ምንም ችግር የለም::" ባለታክሲው ፍጥነቱን አልቀነሰም::

አቤሰሎም ተመቻችቶ ተቀመጠ:: ከዚህ ወዲያ ያለው አማራጭ ወደ ሆቴሉ ደርሶ እዮብ እንዳለው የላስቲክ ከረጢቱን በመታጠቢያ ቤት የመፀዳጃ የውሀ ማጠራቀሚያ ውስጥ መክተት ነው::

ታክሲዋ አስር ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ግዮን ሆቴል ደርሳ ከፊተኛው በር ስትቆም አቤሰሎም ሹፌሩን አመስግኖ ከጀርባ የመኪናው ወንበር ላይ ያስቀመጠውን የላስቲክ ከረጢት አንስቶ ከመኪናው ወረደ:: የግዮንን ሆቴል የፊት ለፊት ደረጃዎች ቀልጠፍ ብሎ ወጥቶ መታወቂያውን አሳይቶ ሳይፈተሽ ወደ ውስጥ ገባ::

ወደ ግራ እጥፍ ብሎ ወደ ቡና ቤት አመራና ወንበር ስቦ ተቀመጠ:: አስተናጋጇ ስትመጣ 'ቡና' አላት:: ዙርያውን በጥንቃቄ ቃኘ:: በየጠረጴዛው ላይ ከተቀመጡ ሰዎች መሀል በተለይ በእርሱ ላይ አትኩሮት ያላቸው የሚመስሉ ሰዎችን ፈተሸ:: ምንም የለም:: አስተናጋጇ ያዘዛትን ቡና በማቅረቢያ አምጥታ ከፊቱ አስቀምጣለት ስትመለስ ቀልጠፍ ብሎ የስኳር ማቅረቢያውን አስጠግቶ ሁለት ማንኪያ ስኳር ከቡናው ውስጥ ጨምሮ ፉት አለና ብድግ ብሎ የላስቲክ ከረጢቱን ይዞ ወደ መታጠቢያ ቤት አመራ:: ከመታጠቢያ ቤቱ በር ሲደርስ ያልጠበቀው የተንቀሳቃሽ ስልክ ጥሪ ሰማ::

አቤሰሎም ወደ መታጠቢያ ቤቱ ከመግባቱ በፊት እንደማመንታት አለና ቆም ብሎ ከግራ የኮት ኪሱ ውስጥ የያዘውን ተንቀሳቃሽ ስልክ አውጥቶ ተመለከተው በዚህ ስልክ ሊደውልለት የሚችል ሰው አንድ ብቻ ነው::

"ሀሎ?" አለ አቤሰሎም ስልኩን ወደ ጆሮ አስጠግቶ::

"ሀሎ ... አቤሰሎም?" አለ የእዮብ ድምፅ::

"እንዴት ደወልክ ... ስልኩን ከየት ...?" ግራ ተጋባ አቤሰሎም::

"እቃውን አግኝቻለሁ ..." አለ እዮብ ፈጠን ብሎ "... አቤሰሎም በጣም ነው የማመሰግነው በላስቲክ ከረጢት ውስጥ ያስቀመጥክልኝ አስር ሺህ ብር እና ይህን ተንቀሳቃሽ ስልክ አግኝቻለሁ::"

"ከየት? ..." አለ አቤሰሎም ግራ ተጋብቶ አጎንብሶ በገዛ እጁ የያዘውን የላስቲክ ከረጢት እየተመለከተ "... መች ተውኩልህና ... እዮብ ያገኘኸው እቃ እኔ የተውኩልህ አይደለም እቃውን ይዤ ነው የማዋራህ!"

"አይደለም - አይደለም ..." አለ እዮብ አቋርጦት "... ታክሲው ውስጥ ነበርኩ አንተ የያዝከው ከረጢት እኔ በምትኩ በቦታው ያስቀመጥኩትን የላስቲክ ከረጢት ነው::"

አቤሰሎም ሁኔታው ሊገባው አልቻለም:: ለአንድ አፍታ የታክሲውን ሹፌር ገፅታ ለማስታወስ ሞከረ:: እዮብ በምንም መንገድ እራሱን ቢቀያይር ያንን ሹፌር ሊመስል እንደማይችል እርግጠኛ ነበር:: ከእርሱ ከእራሱና ከሹፌሩ ሌላ ደግሞ በዚያች ታክሲ ውስጥ ማንም አልነበረም::

"ታክሲው ውስጥ ነበርኩ ..." አለ እዮብ መልሶ "... ከጀርባ ከእቃ መጫኛው ውስጥ ነበርኩ:: አንተ ወደታክሲው ከገባህ በኋላ የያዝከውን እቃ ከኋለኛው ወንበር ላይ እንድታስቀምጥ ጥቂት ጊዜ ከሰጠሁህ በኋላ መኪናዋ መንገድ

ስትጀምርና የምታሰማው ኳኳቴ እኔ የምፈጥረውን ድምፅ እንደሚሸፍን እርግጠኛ ስሆን ቀድሜ ከታክሲው ሹፌር ጋር ተስማምቼ ብሎትን አላልቼ፣ ፈትቼ ያስቀመጥኩትን የኋላ ወንበር ድጋፍ ከፍ አድርጌ ይዤ ነው ያንተን ላስቲክ አሾልኬ ወስጄ እኔ የያዝኩትን በቦታው ያስቀመጥኩልህ::"

አቤሴሎም የሚሰማው ግራ ሲሆንበት ፈጠን ብሎ በቀኙ የያዘውን የላስቲክ ከረጢት ከፍቶ ወደ ውስጥ ተመለከተ:: መደዳ የተደረደሩ ሦስት የእንግሊዝኛ ልብ ወለድ መጽሐፎች ተመለከተ::

"አቤሰሎም ... ሀሎው!"

"አቤት ... አለሁ ቀጥል::" አለ አቤሰሎም እራሱን አሰባስቦ::

"አቤሰሎም በጣም ነው የማመሰግነው ... ለገንዘቡ ... አንድ ቀን ብድር ከፋይ ያድርገኝ ... ግን ..." አለ እዮብ በተቆራረጠ ድምፅ "... ከገንዘቡ ጋር ያስቀመጥክልኝ ተንቀሳቃሽ ስልክ ምንድነው?"

"እዮብ ..." አለ አቤሰሎም ባልጠበቀው ሁኔታ እራሱን ሲያገኝ የተሰማውን ግራ መጋባት ወደ ጎን ብሎ "... እዮብ ብዙ ላስረዳህ አልችልም ጊዜ የለንም:: እዮብ አንተን አድኖ ለመያዝ አንድ ግብረኃይል ተቋቁሟል:: ግብረኃይሉ ..." በሹክሹክታ ቀጠለ "... ግብረኃይሉ ከፖሊስና ከመረጃው መስሪያ ቤት በተወጣጡ ባለሙያዎች የተዋቀረ ነው:: ያለህበትን ሁኔታ እረጋ ብለህ እንድታጤነው እፈልጋለሁ:: ለተፈፀመው ወንጀል ሁሉ አንተን ተጠያቂ ለማድረግ እየተሞከረ ይመስላል ... እዮብ ... በሌላ እንዳትተረጉመው ግን ከፈቃዴ ውጪ በግብረኃይሉ ውስጥ እንድሰራ ከበላይ ታዝዤአለሁ:: ...

"...ግብረኃይሉ በተቻለው መጠን በጥቂት ቀናት ቢቻል ሰዓታት ውስጥ አንተን ከነነፍስህ ይዞ እንዲያቀርብ ታዟል:: የፖሊስ ኃይሉ ከላይ ከማዘገር እስከታች ነጠላ ጣቢያ በተጠንቀቅ ላይ ነው ... ፎቶግራፍህ እየተባዛ ነው ... ከአዲስ አበባ መውጫ ኬላዎች በሙሉ ታጥረዋል ..."

"እዚህ ግብረኃይል ውስጥ ነው የተመደብከው ... አንተ?!" እዮብ አቋረጠው::

"እይዞህ ..." አለ አቤሰሎም ጓደኛውን ለማረጋጋት እየሞከረ "... እኔ አንተን አሳልፌ የምሰጥ ሰው አይደለሁም:: እዮብ ቢሆንም እራሴንም መጠበቅ አለብኝ በግብረኃይሉ ውስጥ ስመደብ 'አሻፈረኝ' ብዬ በግልፅ መቃወሙ ጥርጣሬ ውስጥ የሚከተኝ መስሎ ስለታየኝ ትዕዛዙን ተቀብያለሁ:: እረጋ ብለህ ካጤንከው ግን የእኔ ከውስጥ መኖር ለአንተ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም ... ማለቴ ... የግብረኃይሉን ዕቅድና እንቅስቃሴ ከስር ከስሩ ቀድሜ ላስጠነቅቅህ ስለምችል ሳታስብ ሊመጣብህ ከሚችል አደጋ እራስህን ልትጠብቅ ትችላለህ::"

"አቤሰሎም ..." አለ እዮብ አቋርጦት "... ከዚህ ወዲያ አንተን አደጋ ውስጥ መክተት አልሻም:: እኔ ..."

"አይደለም! ..." አቤሰሎም አቋረጠው "... እዮብ ምንም አይነት አደጋ ውስጥ አትከተኝም:: ዋናው እንድታስታውስ የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር ፍፁም አደጋ ውስጥ ካልገባህ በስተቀር አንተ ወደ እኔ እንዳትደውል ነው:: ከዛሬ ጀምሮ በግብረኃይሉ ውስጥ እንድንሠራ የታዘዝን ባለሙያዎች በሙሉ ውሎአችንም

አዳራችንም እዚያው ግቢ ውስጥ ስለሆነ እርስ በእርስ የሚኖረው መጠባበቅና መሰላለል ቀላል የሚሆን አይመስለኝም:: እንድታውቀው የሚያስፈልግ ጉዳይ ሲኖር እኔ እራሴ እየደወልኩ አሳውቅሀለሁ::"

"አቤሰሎም ..." አለ እዮብ "... አመሰግናለሁ:: ለጊዜው ያቀድኩት ..."

"ተው! ተው! እቅድህን አትንገረኝ ..." አቋረጠው "... እዮብ አስታውስ ማንንም አትመን ... ትሰማኛለህ? ... ማንንም! ... ቻው እንዳልኩህ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ እኔ እራሴ እደውላለሁ ለአንተም የሰጠሁህ እኔም የያዝኩት ተንቀሳቃሽ ስልኮች የሳተላይት ግንኙነት ማድረግ የሚችሉ በመሆናቸው ከሞላ ጎደል ከአደጋ የፀዱ ናቸው:: ቢሆንም ለጥንቃቄው የምደውልልህ እኔ ብቻ ነኝ:: ደህና ሁን::"

አቤሰሎም ስልኩን ዘግቶ ከኮቱ ኪስ ከተተና በቀኙ የያዘውን የላስቲክ ከረጢት ከፍቶ ከላይ ያለውን መፅሐፍ አውጥቶ ተመለከተው:: የፒተር ራይት 'ስፓይ ካቸር'::

ምፀቱ ፈገግ አሰኘው::

ከቼሪሲ ጂፕዋ የወረዱት ሰዎች በሀያ ሜትር እርቀት ላይ ቆመው ይጠባበቁ ጀመር::

"ውረድ ... " አለ ልዑል ታጣፊ መትረየሱን እንደጨበጠ አይኖቹን ከፊት ለፊት በእርቀት በቆሙበት ሰዎች ላይ ተክሎ "... ውረድና አነጋግራቸው ከጀርባ እሸፍንሀለሁ::"

"... ወርጄስ ... ምን ብዬ ነው የማነጋግራቸው::"

"አትፍራ ... ወርደህ አነጋግራቸው ምን እንደሚሉ ... አደጋ ውስጥ ገብተናል ብለህ ካመንክ ... ምልክት ስጠኝ ... የግራ እጅህን እንስተህ ጭንቅላትህን ዳብስ ... ያን ጊዜ ተኩስ እከፍታለሁ ... አንተ ባለህበት አትነቃነቅ ... ነጥዬ እመታቸዋለሁ::"

"ግን ... " አለ ፊይሰል ስጋት ገብቶት "... እንዳትስት ... እጠገባቸው እንደቆምኩኝ ... "

"ውረድ! ... " አለ ልዑል ፊቱን መንጭቆ ወደ ፊይሰል አዙሮ "... ጊዜ አታጥፋ አለበለዚያ ጥርጣሬ ውስጥ ነው የምንከታቸው ... ተረጋግተህ አነጋግራቸው ምናልባት ምንም ችግር ላይገጥመን ይችላል:: "

ፊይሰል ወረደ:: ወደፊት እለፍ ብሎ ለአንድ አፍታ በሁለቱ መኪናዎች መሀል ወደቆሙት ሁለት ሰዎች ተጠጋ:: ልዑል መሳርያውን እንደያዘ ተጠባበቀ:: ፊይሰል ከሁለቱ ሰዎች ጋር ሲነጋገር ቆይቶ ተመለሰ::

"ምንድነው?" ልዑል የያዘውን መሳርያ እንደጨበጠ ጠየቀ::

"አንተን ነው የሚፈልጉት::"

"እኔን?" ልዑል ጥርጣሬ የገባው መሰለ "... ምንድነው የሚፈልጉት ከእኔ?"

"እኔ እንጃ ... 'እሱን ነው ማነጋገር የምፈልገው' ነው ያሉኝ::"

ልዑል ለአንድ አፍታ ያመነታ መሰለና እንዴ የፊይሰልን አይኖች አንዴ ደግሞ ወዲያ ማዶ መንገዱ መሀል ላይ መሳርያዎቻቸውን እንደጨበጡ የሚጠባበቁትን ሁለት ሰዎች ተመለከተ:: በሩን ከፈተ ...

"ቆይ ... ልዑል ... " አለ ፊይሰል ከእራሱ ጋር ሲታገል ቆይቶ::

"ምን ሆነሀል?" ልዑል ከመኪናው ለመውረድ በሩን ከፍቶ እንደያዘ ፊቱን መልሶ ጠየቀው::

"ሊገድሉህ ነው::" አለ ፊይሰል በተጨነቀ መንፈስ::

"ምን?!"

ቤን ሳውል እንደፈራው ኮሎኔል ረብሻ ሳያነሳ እልሁን ዋጥ አደርጎ ከልጅቷ ፊት ወንበሩ ላይ ተረጋግቶ መቀመጡን ሲያይ ቀና ብሎ ከፌቨን ጀርባ ቆሞ የነበረውን ሰው ጠቀሰው - 'ውጣ'::

"ፌቨን ..." አለ ቤን ሳውል የሚመራውን የወንጀል ጥልፍልፍ አደጋ ላይ የጣለችን ሴት ሳይሆን ተራ ጥፋት ያጠፋችን ታናሽ እህቱን እንደሚያነጋግር ሁሉ እረጋ ብሎ "... ፌቨን ቅድም ለእኔ የነገርሽኝን ሁሉ ከመጀመርያው ጀምረሽ እንድትደግሚልኝ እፈልጋለሁ::"

"የማውቀውን ሁሉ ተናግሬአለሁ ... ሌላ የምጨምረው ነገር የለም::" ኮሎኔልን ማየት የተፀየፈች ወይ የፈራች ይመስል አይኖቿን ቤን ሳውል ላይ ተከለ::

"ድገሚው::"

"ምኑን?"

"ሁሉን ... የተናገርሽውን ሁሉ::" አለ ቤን ሳውል::

አመነታች::

"በመጀመርያ እንዴት መለመሉሽ?" አለ ቤን ሳውል ቀደም ብላ የተረከችለትን ታሪኳን አብሯት እያማጠ::

"አስፈራርተው ነው ... በግድ::" ጀመረች::

"መቼ ነው ወቅቱ ...?" ቤን ሳውል አበረታታት::

"ከአንድ ዓመት በፊት ነው ... አንድ ዓመት ከ...ሁለት ሦስት ወር::"

"በምንድነው ያስፈራሩሽ ... ምን ስታደርጊ ... አነማናቸው?"

"ከጓደኞቹ ጋር ... በቃ ... የምንሰራው ስላልነበር አንድ ቤት እለ ... እዚያ እየሔድን ጫት ... ምናምን እናጨስ ነበር::"

"ምንድነው የምታጨሱት?" ቤን ሳውል አቋረጣት::

"አደንዛዥ እፅ::"

"ምን አይነት?"

"አላውቅም ... ወንዶቹ ናቸው የሚያመጡት::"

"ቀጥይ::"

"እ ... በቃ ... እዚያው እናመሻለን ... ፊልም እያየን ... እና ... አንድ ቀን ያቡን ... ሀሺሽ ስናጨስ ... አንድ ሴት ጓደኛዬና ሁለት ወንዶች ነበርን::"

ወጥተው በወንበሩ ድጋፍ ላይ የተጋደሙትን ቀጠን መለል ያሉ ክንዶቿን ሲመለከት ኮሎኔል ይህች 'እንዲት ፍሬ ነፍስ ያላወቀች ህፃን እንዴት ...' የቀሩትን ሦስት እርምጃዎች ተራምዶ ከፊት ለፊቷ የነበረውን ወንበር ስቦ ተቀመጠ::

"ፌቨን ..."

እንዳልሰማችው ሁሉ ችላ አለችው:: ግራ እጁን ዘርግቶ ቀኝ ትከሻዋ ላይ የተጋደመውን የፀጉሯን ጉንጉን ዳበሰው ... ጣቶቹን ዘርዘር አድርጎ በወፍራሙ የተጎነጎነውን ፀጉር ፈታው ...

"ፌቨን ... ምን በድዬሽ ነው? ... ምን በድዬሽ ነው እንዲህ ..." የጀመረውን መጨረስ ሲያቅተው ጣቶቹን ዘርዘር በፈታው የፀጉሯ ጉንጉን ውስጥ ከተተና ፀጉሯን እንደሚያበጥር ሁሉ ቡናማ ፀጉሯን እየከፈለ የተጋለጠ ደረቷ ላይ በተነው::

'... ተገድጄ ነው እንጂ ... እኔን እወድሀለሁ ...' እስክትለው ተጠባበቀ ... አይኖቿን ፊት ለፊት ግርግዳው ላይ ተክላ ዝም አለች::

"መልሺልኝ ፌቨን ... መልሽልኝ ..." አለ ቀና ብሎ ጥቋቁር አይኖቿ ውስጥ አይኖቹን አስምጦ "... ምንድን ነበር ያጎደልኩት? ... ምንድን አምሮሽ ከለከልኩሽ? ምን ጠይቀሽኝ 'አሻፈረኝ' አልኩ? ... ምን ተመኝተሽ ሳታገኚ ቀረሽ? ... ገንዘብ ... ወርቅ ... አልማዝ ... ሽቶ ... ምን? ... ፌቨን ... ምን?! ...

"ንገሪኝ እንጂ!" አለ ከተቀመጠበት ዘሎ ተነስቶ "... ያጠፋሁት፣ ያጎደልኩት ካለ አስረጂኝ ... ልረዳውና ጥፋቴን አምኜ ልቀበል::"

'ሥዩም እወድሀለሁ! እፈቅርሀለሁ! ... ፊርቼ ለህይወቴ ሰግቼ ነው ... አንተን መሰለሴን፣ ሚስጥርህን አሳልፌ መስጠቴን አትይ ... ያ በግድ ተገድጄ ያደረኩት ነው ... እኔ ግን፣ አቅፈኸው ትተኛ የነበረው ሰውነቴ ግን ፍቅርህን ተቀብሎ ፍቅሩን ሰጥቶህ ይረካ የነበረ ሰውነቴ ግን ... ያኔም አሁንም አንተን ነው የሚለው ... ሥዩምዬ ... ከአንተ ሌላ ወንድ ...' እንድትለው ተጠባበቀ::

ችላ ብላው አይኖቿን በተዘጋው በር ላይ ተክላ ቀረች::

"ፌቨን ..." ሁለት ጉልበቶቿን በሁለት እጆቹ እየደባበሰ ሽቅብ ወደ ጭኖቿ አመራ "... ይገባኛል ... ፌቨን ወደሽ ሳይሆን ተገደሽ እንዳደረግሽው ይገባኛል ... በልብሽ የሚሰማሽን አውቀዋለሁ ..." ሁለት እጆቹን በስሱ ቀሚሷ ስር ወደ ጭኖቿ ውስጥ እየሰደደ ከወገቡ ሳብ ብሎ ፊቱን ወደ ፊቷ አስጠግቶ ... ከንፈሮቹን ወደ ከንፈሮቿ ...

ፊቷን አዞረችበት::

ከተንበረከከበት ዘሎ ተነሳ:: ቁልቁል አፈጠጠባት::

"አ! ... እንዲያ ነው! ... አልገባኝም ነበር ... ለካ የምትቀልጂበት፣ የምታሾፊበት ከጀርባው የምታሽሟጥጪው ወንድ ነበርኩ! ... እንግዲው አንድ ነገር ልንገርሽ ..." አለ ቡናማ ፀጉሯን ከጀርባ ጨምድዶ ፊቷን ወደ ላይ መልሶ አይኖቿ ውስጥ አፍጥጦ "... ጊዜው የእኔ ነው ... አሁን ደግሞ በተራዬ እቀልድብሻለሁ፣ አሾፍብሻለሁ፣ አሽሟጥጥሻለሁ ...!"

ቀበቶውን ፈታና የሱሪውን ዚፕ ቁልቁል ...

## ፳፱

ጊዜው እያለቀ ... ወጥመዱ እየተዘጋ ... ሽምቀቅው እየጠበቀ ነው:: ከዚህ ወዲያ ያሉት አማራጮች ሁለት ናቸው - እጁን ሰጥቶ ማብቃት ወይ ሚቼ የመከላከያ ኮሎኔል በሰጡት መረጃ ተጠቅሞ በጅቡቲ ወደብ አድርጎ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ የታቀደውን የአደንዛዥ እፅ ዘር በእጁ ማስገባት ... ወንጀለኞቹን በቀፈሩት ጉድጓድ ...

ምርጫው ግልፅ ነው:: ነፍሱ እያለች የእናቱ ገዳዮች መጫወቻ አይሆንም:: ቢሆንም ይህንን የወንጀለኞች ቡድን በቀላሉ በቀሰበት ውስጥ ማስገባት ቀላል እንደማይሆን ... ምናልባት የተሻለው አማራጭ የመከላከያ ሚኒስትሩ ሰው እንዳሉት ወደ ኢትዮጵያ የሚገባውን የአደንዛዥ እፅ ዘር በእጁ ማስገባቱ ነው:: ይህ አማራጭ በእርግጥ በወንጀለኛው ቡድን ላይ የበላይነት ይሰጠዋል::

የአደንዛዥ እፁን ዘር በእጁ ማስገባቱ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው:: ግን እንዴት ተደርጎ?

አዲስ አበባ ውስጥ መቆየቱም የሚመረጥ አይደለም:: ልቆይ ቢባልስ የት? ያለ ጥርጥር በሰዓታት ውስጥ እያንዳንዱ የፖሊስ ጣቢያ በከተማው ውስጥ የሚገኙ ትን ሆቴሎች አልቤርጎዎች በሙሉ ይሸፍናል:: የት ነው እራሱን መደበቅ የሚችለው?

ከአዲስ አበባ መውጣቱ አንደኛ አዲስ አበባ የሚደረገውን አደን እንዲያመልጥ ይረዳዋል ... ሁለተኛ በእጁ ለማስገባት ወደሚፈልገው ዘር ያቀርበዋል:: ግን እንዴት ነው ከአዲስ አበባ ወጥቶ በጅቡቲ መስመር በመኪና መንገድ የሚገባን የአደንዛዥ እፅ ዘር የሚያጠምደው?

አቤሰሎም እንዳስጠነቀቀው ከአዲስ አበባ መውጫ መስመሮች ... በየኬላው ላይ ይጠብቁታል:: ምናልባት አቤሰሎም እንዳለው በየአውሮፕላን ማረፍያው፣ በየባቡር ጣቢያው ፎቶግራፉ ተበትኗል ... የፖሊስ ሰንሰለት በተጠንቀቅ ... ይህ ሁሉ እንዴት ተደርጎ ይታለፋል ...?

የሚያጠፋት እያንዳንዷ ደቂቃ አዳኞቹ በአዲስ አበባ ላይ የሚዘረጉትን መረብ እንዲያስፋፉና እንዲያጠናክሩ ዕድል የሚሰጣቸው ነው::

እዮብ አቤሰሎም ያመጣለትን አስር ሺህ ብርና ተንቀሳቃሽ ስልክ በእጁ ካስገባ በኋላ ከዚህ ቀደም ለመረጃው መሥሪያ ቤት በወኪልነት ሲሰራ የሚያውቀው የነበረና ለዚህ ጉዳይ እርዳታ ጠይቆ የተባበረውን የታክሲ ሹፌር ሁለት መቶ ብር ሰጥቶ ከምስጋና ጋር አሰናበተው::

'እንዴት? ... ምን ማድረግ ነው ያለበት?'

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከሕግ ፋኩልቲ እንደተመረቀ የመረጃው መስሪያ ቤት በጥሩ ደምወዝ አባብሎ ወደ እቅፉ ሲያስገባው የጠበቀው ነገር ቢኖር የተሟላ ቢሮ ... የግል ፀሀፊ ...

ፍጹም::

እርምጃ ከጀርባ ማስከተል ... ሁሌም እያባበሉ ... አንድ እርምጃ ብቻ ከፊት ቀድሞ መገኘት::

እዮብ ታክሲ ተሳፍሮ በቦሌ አቅጣጫ ከዚህ ቀደም ወደሚያውቀው የጉዞ ወኪል ሔደ:: የጉዞ ወኪሉ ከመረጃው መስሪያ ቤት ጋር ባለው የውስጥ ስምምነት ለተለያዩ ኦፕሬሽኖች መኪናዎቹን ለመረጃ ሰዎች የሚያከራይና ዳጎስ ያለ ክፍያ በየወሩ የሚያጋብስ ነው::

"ለስንት ቀን ነው?" አለው አጭሩ የጎዞው ወኪል ባለቤት እዮብን ሞቅ ባለ ሰላምታ ከተቀበለው በኋላ::

"አንድ ሳምንት ... በአስር ቀን ያዘው::" አለ እዮብ ዘና ብሎ::

"ዲስከቨሪው ወጥቷል ... እሱን ነው ብዙ ጊዜ የምትወስደው ብዬ ነው ... " አለ አጭሩ ሰው ፈገግ ብሎ ከጀርባ የሚያከራያቸውን መኪናዎች ቁልፍ ወደሚያንጠለጥልበት የእንጨት መደርደሪያ ዞሮ እየተመለከተ "... ጥቁሩ ሬንጅሮቨር ግን አለ::"

"ይሁን::" አለ እዮብ::

"ይህን ፎርም ሙላልኝ::" አለ ሰውየው አንድ ነጭ ወረቀት ለእዮብ ዘርግቶለት "... ሻይ ቡና  አንድ ነገር ልበልህ ..."

እዮብ ቡናውን ጠጥቶ ጥቁሩን ሬንጅሮቨር ይዞ ወጣ:: ክፍያው በወሩ መጨረሻ የመረጃው መስሪያ ቤት የሚሸፍነው ነው:: ተፈላጊው ጉዳይ መኪናውን የተከራየው የመረጃ አባል በተፈላጊው ቅፅ ላይ መኪናውን ለስራ ጉዳይ ለመከራየቱ መተማመኛ ፊርማውን እና የመታወቂያ ቁጥሩን ማስፈሩ ነው - የተለመደ አሰራር ነው::

በፒያሳ አቅጣጫ በረረ::

በተቻለው መጠን ቀልጠፍ ባለ እንቅስቃሴ ወደ አራት ሱቆች እየገባ አንድ ኮንታክት ሌንስ፣ የሴት ዊግ፣ የጥፍር ቀለም ማስለቀቂያ፣ አንድ የሴት ጫማ ... ከመንገድ ላይ ደግሞ አንድ ያገለገለ የወንድ ሙሉ ልብስ ረጅም ከማገልገል ወደማርጀት ያደላ የወንድ ካፖርት፣ ከዘራ፣ ሁለት አነስተኛ ሻንጣዎች ...

ሬንጅ ሮቨሩን አስነስቶ ወደ ግዮን ሆቴል በረረ:: ሰዓቱን ተመለከተ:: ከቀኑ አስር ሰዓት ከሀያ:: ወደ ግራ ታጥፎ አይን ወደማይበዛባቸው መደዳ ወደተደረደሩት የሪቪየራ የመኝታ ሕንፃዎች አመራ:: ቀልጠፍ ብሎ ከመኪናው ወረደና በእግሩ ዙርያውን እየቃኘ ቀጠለ ...

ሕንፃ ቁጥር 15 ... 16 ... 17 ... 18 ...

ገባ::

ምድር ቤት ያለውን ክፍል አንኳኳ ... መልስ የለም ... ቀልጠፍ አለና ደረጃውን ወጥቶ ፎቅ ወዳለው ክፍል መዝጊያ ተጠጋ:: ድምፅ ይሰማል::

አንኳኳ::

በሩ ተከፍቶ ከውስጥ አንድ ወጣት ወንድ ብቅ አለ:: ወጣቱ የለበሰው የጠዋት ልብስ፣ የቤት ጫማና በውሀ የራሰ ፀጉሩ ከባኞ የወጣ መሆኑን ይናገራሉ::

"አቤት?" አለ ወጣቱ:: የለበሰውን የጠዋት ልብስ ኩሌታ እያስተካከለ::

እዮብ ጊዜ አላጠፋም:: ከጀርባ ሻጥ ያደረገውን ሽጉጥ መዝዞ አፈሙዙን ወጣቱ ግራ አይን ላይ ተከለው::

"ድምፅ ብታሰማ አንጎልህን ከአፈሙዜ ላይ ጠራርጌ እወጣለሁ::"

ወጣቱ ሁለት እጆቹን አንሳ የተባለ ይመስል ግራና ቀኝ ከፍ አድርጎ አንስቶ አይኖቹን ጨፈነ::

የልጁን መደናገጥ የተገነዘበው እዮብ ወጣቱን ወደ ውስጥ ገፋ አድርጎ ገባና በሩን ከውስጥ ዘጋው::

"አብሮህ ሰው አለ?" አለ እዮብ የልጁን ግራ እጅ ጨምድዶ ይዞ በእንግዳ መቀበያ ክፍሉ ውስጥ ባለው ፎቴ ላይ ገፍትሮ ጥሎት::

ወጣቱ እንደማመንታት ብሎ ዝም አለ::

"አለ ... የለም?!" አለ እዮብ ሽጉጡን ወደ ወጣቱ ጆሮ ግንድ አስጠግቶ::

"አለ::"

"ማነው?"

"ጓደኛዬ ... ሴት ጓደኛዬ::"

"መኝታ ቤት?"

ወጣቱ ጭንቅላቱን በአሉታ ነቀነቀ - "መታጠቢያ ቤት ገላዋን ..."

እዮብ የወጣቱን ፀጉር ጨምድዶ አነሳውና ከፊት አስቀድሞት የመኝታ ቤቱን በር በርግዶ ገባ:: አልጋው ተመሰቃቅሏል:: በመኝታ ክፍሉ ውስጥ ሰው የለም:: እዮብ ወጣቱን እየገፈተረ ወደ መታጠቢያ ቤት አመራና በሩን ወደ ውስጥ ገፋው ...

"ሃኒዬ!"

"እንዳትጮሂ!"

ከከፍሉ ልትሮጥ እንዳሰበች ሁሉ በደመነፍስ ከውሀው ገንዳው ውስጥ ወጥታ እራቁቷን ቆመች::

"ብትጮሂ ጭንቅላቱን ..." አለ እዮብ የያዘውን ሽጉጥ ወጣቱ እናት ላይ ተክሎ:: "ተጠንቀቂ ... ማንም አይደርስላችሁም ... ሁለታችሁንም እዚሁ ጎን ለጎን አጋድሜ እወጣለሁ::"

ድንገት ጉሮሮዋን የተናነቃት ድንጋጤ ሲያልፍ፣ ፍቅረኛዋ ላይ ሽጉጥ ደግኖ የቆመው ሰው ወንድ መሆኑን ስታጤን፣ በክፍሉ መሀል እርቃኗን መቆሟ ሲሰማት መደበቂያ ቦታ ያጣች ይመስል ሽምቅቅ ብላ ወለሉ ላይ ቁጢጥ አለች::

"ጥሩ ... እንዲህ ከተግባባን ማንኛችሁንም ሳልጎዳ በሰላም እንለያያለን:: ምንም የምተሰጉበት ምክንያት የለም:: ሌባ አይደለሁም:: ጭንቅላቴን አልሳትኩም:: ለጥቂት ሰዓታት ብቻ የምሸሸግበት ቦታ ስለምፈልግ ነው ... ይቅርታ ... ቢሆንም ችግር ከፈጠራችሁ፣ ለደህንነቴ አደጋ ከሆናችሁብኝ ... አማራጭ አይኖረኝም:: ተግባባን?"

ሁለቱም ወጣቶች ምንም ድምፅ ሳያሰሙ የሚከተለውን ይጠባበቁ ጀመር::

"ልብስ ልበሽ::" አለ እዮብ ወጣቱን ልጅ ከጀርባ እየገፋ ወደ መኝታው ክፍል እየተመለሰ::

ሁለቱን ወጣቶች ጎን ለጎን ወንበር ላይ አስቀምጦ አንሶላውን እየቀረደደ፣ እየተለተለ እግርና እጃቸውን አሰሮ፣ አፋቸውን በጨርቅ ጎስጉሶ፣ አይናቸውን ሸብቦ ካስቀመጣቸው በኋላ ፊቱን ወደ በሩ መለሰ::

"እታች ያቆምኩት መኪናዬ'ጋ ደርሼ እቃዬን ይዤ እመለሳለሁ:: እስከዚያው ድረስ ምንም አይነት ድምፅ ብሰማ ... ስመለስ ለምወስደው ማንኛውም እርምጃ ተጠያቂ እናንተው ናችሁ:: በተለይ አንተ እዚሁ እፊትህ እያየህ የዚችን ልጅ ሆድ እቃ እዘረግፍልሀለሁ::"

ወዲያው እዮብ ተንቀሳቃሽ ስልኩን አወጣና አምስት ቁጥሮች ደወለ:: ዘና ብሎ ከወዲያ የሚያነጋግረው ሰው ያለ ይመስል " ... ሀሎው ... እዮብ ነኝ መኪናውን ተከራይቻለሁ ... " ተነጋግሮ ሲያበቃ ዞር ብሎ ወጣቶቹ ላይ አይኖቹን አጉረጠረጠና ከክፍሉ ወጣ::

እራሱን 'እዮብ' እያለ ሲያስተዋውቅ ወጣቶቹ እንደሰሙት እርግጠኛ ነበር ፡ ያንን ነበር የፈለገው:: እቃውን ይዞ እንደተመለሰ ወጣቶቹን ችላ ብሎ ሻንጣውን ይዞ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባ::

ሰዓቱን ተመለከተ:: ለአስራ ሁለት ሀያ ጉዳይ::

ሻንጣውን ከፈተና ኮንታክት ሌንሶቹን አወጣ:: ሁለቱን ሌንሶች ወደ ግራ መዳፉ አጋባ:: የጥፍር ቀለም ማስለቀቂያውን አወጣና የብልቃጡን ክዳን ከፍቶ በውስጡ ያለውን ፈሳሽ የፕላስቲክ ኮንታክት ሌንሶቹን በያዘበት መዳፉ ላይ አፈሰሰው:: የግራ መዳፉን እያንቀሳቀሰ ሁለቱ ኮንታክት ሌንሶች ቀስ በቀስ መስታወት ይመስል የነበረውን ገፅታቸውን እያጡ በምትኩ ወተት የፈሰሰባቸው ይመስል ጉም እየጣለባቸው እስኪመጣ ጠበቀና ውሀውን ከፍቶ አለቀለቃቸው:: ከፊት ለፊት ወዳለው የፊት መስታወት ጠጋ አለና አይኖቹን ሰፋ አድርጎ ከፍቶ አንደኛ ውን ኮንታክት ሌንስ አንስቶ ቀኝ አይኑ ላይ ለጠፈው::

የኮንታክት ሌንስ የለጠፈበትን የቀኝ ዓይኑን አትኩሮ ተመለከተው:: ሞራ እንደዘጋው ሁሉ የዓይኑ ጥቁር ክፍል ከዳር እስከ ዳር ነጭ ሆኖ ተመለከተ:: ግራ ዓይኑን ጨፈነና የኮንታክት ሌንስ ባደረገበት የቀኝ ዓይኑ ለመመልከት ሞከረ:: በድቅድቅ ጭጋግ የታፈነ ቢመስልም ዙርያውን መመልከት

አላስቸገረውም:: ድጋሚ ወደ መስታወቱ ተጠጋና በቀኝ እጁ የያዘውን ኮንታክት ሌንስ ግራ ዓይኑ ላይ ለጠፈው::

በስተቀኝ ካስቀመጠው ቦርሳ ውስጥ የዊግ መላጫውን አወጣ:: ግራና ቀኝ ከጆሮው በላይ ያለውን ፀጉር ትቶ ከላይ መሀል ለመሀል ጭንቀላቱን ላጨው ... ቀና ብሎ ተመለከተ ... ጭጋግ በመሰለው የፊት ማስታወት ፊት አንድ መላጣ አይነ ስውር ተመለከተ ...

እዮብ የአቀደውን አጠናቆ ከመታጠቢያ ቤት ሲወጣ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ከአምስት ነበር:: ስልኩን አንሳና እራት አዘዘ:: የፊት በሩን በቀጭኑ ከፍቶ ተወውና ጥግ ካለ ጠረጴዛ ላይ አንድ የሀምሳ ብር ኖት አስቀመጠ:: ቴሌቪዥኑን ከፍቶ የሳሎኑ ፎቴ ላይ ዘፍ አለ:: በሃያ ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ከበሩ ወዲያ ድምፅ ሲሰማው ተነስቶ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባ::

"ማነው?" አለ በሩ መልሶ ሲንኳኳ::

"እራት ..." ሲል ተሰማው የሆቴሉ አስተናጋጅ ከበሩ ውጭ እንደቆመ::

"ግባ:: ..." አለ እዮብ የመታጠቢያ ቤት የፊት ሳህኑን ውሀ ከፍቶ ወደ መኝታ ቤት ተመለሰና ዘና ባለ ድምፅ:: አስተናጋጁ ወደ ሳሎን ክፍል ሲገባ ሲሰማ ድምፁን ከፍ አድርጎ - "... ገንዘብ በሩ'ጋ ካለው ጠረጴዛ ላይ አስቀምጬልሀለሁ ... መልሱን ያዘው::"

በሩ ከውጭ ሲዘጋ ከመኝታ ቤት ወጣና በሩን ከውስጥ ቀልፎ፤ እራቱ የተቀመጠበትን ማቅረቢያ አንስቶ ከሳሎኑ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠና ሹካና ቢላዋ ለማንሳት እጁን ዘረጋ ... ዳበሰ ... ትንሽ ያስቸግራል:: ቀስ ብሎ አይኖቹ ላይ የለጠፋቸውን ኮንታክት ሌንሶች አነሳ::

እራቱን በልቶ እንደጨረሰ ጫማውን አውልቆ ፎቴው ላይ ጋለል ብሎ የቲቪ ፕሮግራሙን መከታተል ቀጠለ:: እንቅልፍ ሲወስደው ትዝ አይለውም:: ሲባንን ግን ከሰሊቱ አስር ሰዓት ከአምስት ይላል - ሰዓቱ::

ከተጋደመበት ፎቴ ላይ ተነሳና ወደ መታጠቢያ ቤት ገብቶ ገላውን ተለቃልቆ ወጣ:: ሁለቱን ሻንጣዎቹን አንስቶ ከሆቴሉ ክፍል ወጥቶ ወደ መኪናው ወረደ:: ሻንጣዎቹን ከመኪናው ከከተተ በኋላ የብሎን መፍቻ አውጥቶ የተከራየውን መኪና የፊትና የኋላ ታርጋ አውልቆ ወደ አትክልቱ ውስጥ ወርወር አደረገውና ከጎን ቆማ የነበረች የአንድ ቢ. ኢም. ደብልዩ ታርጋ ነቅሎ በተከራያት መኪና ላይ ለካና መኪናው ውስጥ ገብቶ ሞተሩን አስነሳ::

ምሽቱ አብቅቶ ሊነጋ የቀሩት ጥቂት ደቂቃዎች ቢሆኑም ጨለማው ገና አልገፈፈም:: መኪናውን አንቀሳቅሶ ...

በጨለማው ውስጥ ...

ለደቂቃዎች ድንጋጤ ያረበበ ፀጥታ ውስጥ የጭነት መኪናውን ሲያሽከረክር የቆየው ልዑል ድንገት የባነነ ይመስል የመኪናውን መሪ እየደበደበ -

"ለምን ... ምንድነው እየሰሩ ያሉት ... ለምንድነው ሊገድሉኝ የሚፈልጉት ... ምንድነው በትክክል ያሉህ?"

"ላክው ነው ያሉኝ ... 'ወደ ተሽከርካሪው ተመልሰህ ሹፌሩን ላከው' ነው ያሉኝ::"

"ምንድነው የምታወራው ... ሊገድሉህ ነው ነበር ያልከኝ!"

"ልዑል ... " አለ ፌይሰል በድካም ጭንቅላቱን ከጀርባ መደገፊያው ላይ ጣል አድርጎ "... ሰዎቹ የነገሩኝ ዕቅዱ አደጋ ላይ መውደቁን ነው:: 'ዕቅዱ በማይፈለጉ ሰዎች እጅ ገብቷል' ነው ያሉኝ:: ተፈላጊውን ጭነት በተለዋጭ ዕቅድ ለማጓጓዝ መወሰኑን ... ቀደም ብሎ እንደታቀደው ቀጥታ ወደ አዲስ አበባ በማጓጓዝ ፋንታ በወልድያ በኩል ባሕር ዳር ለማምራት ... የተቀረውንም ጭነት ከነመኪናው ለማቃጠል የተወሰነ መሆኑን ነው የነገሩኝ::" ፌይሰል በተሰባበረ አረፍተ ነገር ዘበዘበ::

"አልገባኝም! ... ያልከኝ የነበረው ... በትክክል 'ሊገድሉህ ነው' ነበር::"

"ስታስበው የጭነት መኪናውን የሚያቃጥሉት ሹፌሩን አስወጥተው ይመስልሀል? " አለ ፌይሰል ጭንቅላቱን ወደኋላ ጣል እንዳደረገ አይኖቹን ጨፍኖ "... ልዑል በአንተ አማርኛ የአንተ አስፈላጊነት ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት አብቅቶ ነበር:: ሰዎቹ ያቀዱት ተፈላጊውን ጭነት ወደ ቼሮኪ ጂፕዋ አጋብተው አንተን ከነተሽከርካሪህ መንገድ ላይ አቃጥለው የጭነቱን ዱካ ለማጥፋት ነበር ... ተግባባን?"

"ለምን አስጠነቀቅኸኝ?"

"ምን ማለት ነው 'ለምን አስጠነቀቅኸኝ' ማለት? ... ታድያ ምን ማድረግ ነበረብኝ? ወደሞትህ እባብዬ ልከህ እጄን አጣጥፌ መቀመጥ ነበረብኝ?"

"እነዚህ ሰዎች የነገሩህ ትክክል ከሆነ ... እውነት ዕቅዱ በማይፈለጉ ሰዎች እጅ ገብቶ ከሆነ የእኔን ሕይወት ለማዳን ስትል የወሰድከው እርምጃ ጠቅላላ ዕቅዱን አደጋ ላይ የጣለው መሆኑን ተረድተሀል?"

"እውነቱን ንገረኝ ካልክ በእዚያች ደቂቃ ይህንን ሁሉ አላሰብኩም ... " አለ ፌይሰል ለአፍታ በዝምታ ቆይቶ "... አይኔ እያየ ከመኪናው ወርደህ ስትሄድ አላስቻለኝም::"

"የዋህ እርምጃ ነው የወሰድከው ... በግሌ ግን አመሰግናለሁ ... ብድር እንድመልስ ግን አትጠብቅ::"

"እንዴት?"

"'ምንድነው የማደርገው' ብትል አይሻልም?" አለ ልዑል ፈገግ ብሎ::

"አንተስ ብትሆን ከእኔ በምን ትለያለህ የያዝነውን ጭነት ምንድነው የምናደርገው ... ምናልባት'ኮ ከፊት እየጠበቁን ሊሆን ይችላል?"

"እኔን በተመለከተ ለአገልግሎቴ የሚገባኝን ገንዘብ ተቀብዬ ነው ከቤቴ የወጣሁት ..." ልዑል ቀዝቀዝ ብሎ ጀመረ "... በቀረኝ የሕይወት ዘመኔ በልቼ በማልጨርሰው ገንዘብ ነው ተሸጬ ወዲህ የመጣሁት ... ስለዚህ ወደሚቀጥለው ከተማ እንደደረስን ጥዬህ እሄዳለሁ ... ነፍሴን አድናለሁ ... ገንዘቤን እየበላሁ እኖራለሁ ... ትዳር መስርቼ! ልጆች ወልጄ 'አደራ "አገር ... ሕዝብ" ቢሏችሁ እንዳትሞኙ ለእራሳችሁ እወቁበት ለእራሳችሁ ብቻ ኑሩ!' እያልኩ ልጆቼን እየመከርኩ አንቀባርሬ አሳድጋቸዋለሁ ... አንተ ትቀጥላለህ::"

"ወዴት ነው የምቀጥለው?" አለ ፈይሰል በተጨነቀ መንፈስ::

"ተረጋጋ ..." አለ ልዑል ለአፍታ ፈይሰልን በሀዘኔታ ጨረፍ አድርጎ ተመልክቶ "... ልረዳህ በቻልኩ በረዳሁህ ግን በአሁኑ ሰዓት ሰዎቹ እንደጠላት የሚመለከቱት በአልሞት ባይ ተጋዳይነት የፈረጠጥኩትን እኔን እንጂ አንተን አይደለም ስለዚህ ማድረግ ያለብህ ጅቡቲ ወደቡ ውስጥ እያለን ያገኘነው ሰው በሰጠህ መመርያ መሰረት ወደሚቀጥለው ነጥብ መጓዝ ነው ... ሌላ አማራጭ ያለህ አይመስለኝም::"

"ጅቡቲ ወደቡ ውስጥ ያገኘነው ሰው የነገረኝ የነበረው ሚሌ እንደደረስኩ 'ደንከል' በሚባል ሆቴል ውስጥ ያለች ገንዘብ ተቀባይ የሚቀጥለውን መመርያ እንደምትሰጠኝ ነበር::"

"ያንን ነው ማድረግ ያለብህ ... ሚሌ እንደደረስን እኔ ተለይቼህ እሄዳለሁ ... አንተ ወደተባልከው ሆቴል ሄደህ ሴትየዋን አነጋግራት ... የሆነውን ሁሉ በእኔ ላይ ደፍድፈው ... 'አስገድዶኝ ነው' በላት ... ምን ማድረግ እንዳለብህ ትነግርሀለች::"

"አንተስ?"

"እኔማ እቀጥላለሁ አልኩህኮ ..."

"ወዴት?"

"በጨለማው ውስጥ ..."

# ፳፮

ኮሎኔል ሥዩም በመሰብሰብያው አዳራሽ ውስጥ ባለው ጠረጴዛ እራስ እንደተቀመጠ ቀና ቀጥ ብሎ በግራና ቀኙ የተቀመጡትን የክትትል ቡድኑን አባላት ተመለከታቸው::

"እጅግ የሚያስመሰግን ሥራ ነው የሰራችሁት::" አለ ተራ በተራ እየቃኛቸው::

እንዲህ በቀላል ነገሮች ከፍጻሜ ይደርሳሉ ብሎ አልጠረጠረም ነበር:: ያንን ነገረኛ የመረጃ ቤት ሰው እንዲህ ሁለት ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ቀለበት ውስጥ ገብቶ እየዋለሁ ብሎ አልጠረጠረም ነበር::

ሦስተኛውን የአስራ ሁለት ሰዓት ሪፖርት ለማዳመጥና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የደህንነት አማካሪ በሚልከው የጽሑፍ ሪፖርት ላይ ለመወያየት ቀድሞ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ የአዳኙ ቡድን አጭር ሪፖርት ተነቦ እንዳለቀ ኮሎኔል የተሰማውን ደስታ መደበቅ አልሞከረም::

"እውነት ነው የምላችሁ እራሳችሁን ብቻ ሳይሆን እኔንና ቢሮዬን የሚያኮራና የሚያስመሰግን የከንውን ሪፖርት ነው ... ሁለት ቀን በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ተፈላጊውን በእጃችሁ ማድረጋቹህ ... በቢሮዬ ስም ከፍ ያለ ምስጋና ነው የማቀርበው::"

ግራና ቀኝ የተቀመጡት አራቱ የቡድኑ አባላት ምስጋናውን ለመቀበላቸው ጭንቅላታቸውን አወዛወዙ::

"እ ..." ኮሎኔል ሥዩም በተረጋጋ መንፈስ ፊቱን ወደ አቤሰሎም መልሶ ቀጠለ "... ጠዋት በመጀመርያ ከሆቴል ነበር ማለት ነው ወጥቶ መኪናውን የተከራየው?"

"አይደለም ..." አለ የመቶ አለቃ ፍቅሬ አቤሰሎም ለተጠየቀው ጥያቄ ሊመልስ ሲዘጋጅ ተሽቀዳድሞ "... አይደለም ጌታዬ ... ዛሬ ጠዋት በሦስት ሰዓት ከአምስት ላይ የወረዳው ፖሊስ ከሆቴሉ ጥበቃ አባላት በተደረገለት የወንጀል ሪፖርት መሰረት ወደ እኛ ቢሮ ሪፖርት ሲያደርግ በጊዜው ወደ ሆቴሉ ሔጄ መረጃ ያሰባሰብኩት እኔ ነበርኩ ..."

"የወረዳው ፖሊስ ምንድን ነበር ሪፖርት ያደረገው?" አለ ኮሎኔል አይኖቹን ወደ እራሱ ሰው ወደ የመቶ አለቃ ፍቅሬ አበጋዝ መልሶ::

"ጌታዬ ..." አለ የመቶ አለቃው ኮሎኔል ሥዩም አትኩሮቱን እንደሰጠው ሲረዳ በጥቂት ቀናት ውስጥ ተከትሎ ሊመጣ የሚችለውን የገንዘብ ሽልማትና ሹመት እያሰበ "... በመሠረቱ በመጀመርያ የሆቴሉ ጽዳት ሠራተኞች ጠዋት ሥራቸውን ለመጀመር በተንቀሳቀሱበት ሰዓት ከሪሺየራ የመኝታ ክፍሎች ከቁጥር 18 አካባቢ ጫኸት ይሰማሉ:: ድምፁን ተከትለው ከተባለው ክፍል ሲደርሱ በሩ ሳይዘጋ ገርበብ እንዳለ ያያሉ:: ወደ መኝታ ክፍሉ ሲገቡ ሁለት የሆቴሉ ደንበኞች በወንበር ላይ ታስረው ያገኛሉ:: ..."

ኮሎኔል እያዳመጠ መሆኑ በሚገልፅ ሁኔታ ጭንቅላቱን እላይና እታች አወዛወዘ::

"... በእዚህ ጊዜ ጽዳት ሠራተኞቹ በመደናገጥ ለጥበቃ ክፍል ጥሪ በማድረጋቸው የሆቴሉ ጥበቃ አባላት ወንጀል ወደ ተፈጸመበት ክፍል ደርሰው የወንጀሉን ክብደት በመገንዘብ ወደ ወረዳው ፖሊስ የስልክ ጥሪ ያደርጋሉ ...

"... የወረዳው ፖሊስ ..." አለ የመቶ አለቃው ለአፍታ ምራቁን ውጦ "... የወረዳው ፖሊስ ከስፍራው ደርሶ ሲያጣራ በመኝታ ክፍሉ ውስጥ ታግተው የነበሩት እንግዶች በቅርቡ ከሰሜን አሜሪካ መጥተው የሠርግ ስነ ስርዓታቸውን ሲያከብሩ በዝግጅት ላይ የነበሩ ሁለት ኢትዮጵያውያን መሆናቸውንና የሆቴሉንም ክፍል ላለፉት ሦስት ቀናት ተከራይተው መቆየታቸውን ያረጋገጠ ሲሆን ከዚያ ቀደም ባለው ቀን ወጣቶቹ እንደገለፁት ከቀኑ አስር ወይም አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ነበር ወንጀሉ የተፈጸመው:: ..."

"ቆይ ..." አለ ኮሎኔል አቋርጦት "... በወጣቶቹ ላይ የደረሰ አደጋ ..."

"እርግጥ አደጋ አልደረሰም ..." የመቶ አለቃው ሌላ የቡድኑ አባል እንዳይቀድመው ፈጠን ብሎ ጀመረ "... ግን በወጣቶቹ ላይ ከፍተኛ የማንገላታት ወንጀል ተፈጽሟል:: ዛሬ ጠዋት በስፍራው ደርሶ ሁኔታውን ያጣራው የወረዳው ፖሊስ ከወጣቶቹ መረጃ ሲሰበስብ ወንጀሉን የፈፀመው ሰው ወደ ክፍላቸው ገብቶ በቁጥጥሩ ስር ካደረጋቸው በኋላ ወደ አንድ ቦታ በተንቀሳቃሽ ስልክ ጥሪ አድርጎ 'እዮብ ነኝ ...' እያለ ሲነጋገር እንደነበር በመግለፃቸው የወረዳው ፖሊስም ቀደም ሲል እንደማንኛውም የፖሊስ ጣቢያ ከእኛ ቢሮ ስለዚህ ተፈላጊ ሰው ዝርዝር መረጃና ፎቶግራፍ የደረሰው ስለነበር ጥርጣሬ ውስጥ ይገባል:: በዚህም ጥርጣሬ መሠረት የተፈላጊውን ሰው ፎቶግራፍ ለወጣቶቹ በሚያሳይበት ወቅት ሁለቱም ወጣቶች ያለምንም ማመንታት ወንጀሉ የተፈጸመው በዚሁ ግለሰብ መሆኑን ያረጋግጣሉ:: እንግዲህ በዚህ ጊዜ ነው የወረዳው ፖሊስ ወደ እኛ ቢሮ ሪፖርት ያደረገው::

"ከዚያ በኋላ ነው አጣሪ ቡድን ወደዚያ የተላከው?" አለ ኮሎኔል ጥያቄ ሳይሆን ተራ አረፍተ ነገር በሚመስል ቃና::

"አዎ ..." የመቶ አለቃ ፍቅሬ የቡድኑን ቃል አቀባይነት በስልጣኑ ተረክቦ ቀጠለ "... እኔ እራሴና ሁለት የምርመራ ባለሙያዎች ወደ ስፍራው ተንቀሳቅሰን በአመርቂ ሁኔታ መረጃዎችን ሰብስበናል::"

"ቀጥል::"

"በመጀመርያ ..." አለ የመቶ አለቃው በተቀመጠበት ወንበር ላይ ተመቻችቶ "... በመጀመርያ ወደ ስፍራው እንደደረስን ሁለቱ የምርመራ ሰዎቼን አካባቢያዊ መረጃዎችን እንዲሰበስቡ አድርጌ እኔ በቀጥታ በወጣቶቹ ላይ አተኮርኩ:: በዚህም መሠረት ልረዳ እንደቻልኩት ተፈላጊው ከቀኑ አስር ተኩል አካባቢ ወጣቶቹ ወደ ተከራዩት ክፍል መጥቶ በር እንዳንኳኳና በሩም እንደተከፈተለት ወደ ውስጥ በመዝለቅ ሁለቱንም ወጣቶች በመሣርያ ኃይል በማስፈራራት በወንበር ላይ እንዲቀመጡ በማስገደድ እንዳይንቀሳቀሱ እግርና እጃቸውን በአንሶላ ቅዳጅ አስሮ እንዳቆያቸው ለመረዳት ችያለሁ::"

"ለምን?" አለ ኮሎኔል የተሰጠው ማብራርያ እንዳላረካው በሚገልፅ ሁኔታ "... ምን ፈልጎ ሔደ መጀመርያ?"

"ቀጥል ... የት ነው ያለው አሁን ተይዟል? ሰውየው ..." ኮሎኔል አይኖቹን አቤሰሎም ላይ ተክሎ አደራርቦ ጠየቀ::

"እ ... " አቤሰሎም መኪናዋ በመገኘትዋ ያልተደሰተ በሚመስል ሁኔታ አመነታና "... በቀራ መስመር በሚገኝ አንድ ጋራዥ ውስጥ ነው የተገኘችው መኪናዋ ..."

"ሰውየውስ?" ኮሎኔል አጣደፈው::

"ሪፖርት ያደረጉልኝ የትራፊክ ፖሊስ ጽህፈት ቤት አባላት እንዳሉት ከሆነ የመኪናዋ ባለቤት ከሁለት ቀን በኋላ ረጅም የገጠር ጉዞ ለማድረግ ያሰበ መሆኑን ለባለጋራዦቹ በመግለፅ የመኪናዋን ጤንነት እንዲፈትሹለት ተዋውሎ መኪናዋን አስረክቦ መሔዱንና ነገ ጠዋት መኪናዋን ለመረከብ ተመልሶ የሚመጣ መሆኑን ተናግረዋል::" አቤሰሎም አቀረቀረ::

ኮሎኔል አይኖቹን ባቀረቀረው አቤሰሎም ላይ ተክሎ ከመቀመጫው ተነሳ::

"ጥሩ ..." አለ አይኖቹ የአቤሰሎምን አይኖች እየሸሹ:: ጥርጣሬ ገብቶታል "... ይቅርታ ... ግን በአሁኗ ሰዓት በተቻለን መጠን ምስጢራችንን መጠበቅ አለብን ... ለሌላ ነገር ሳይሆን ሰውየው በእጃችን ከመግባቱ በፊት ይህን አጥር ግቢ ማንኛችሁም ለቃችሁ እንድትወጡ አልሻም ... ተፈላጊውን በተመለከተ በአስቸኳይ አስፈላጊ የሆነውን ኃይል ከዚሁ ከቢሮ ሆናችሁ እንድታሰማሩና ሂደቱንም እንድትከታተሉ:: መሔድ ትችላላችሁ::"

አራቱ የቡድኑ አባላት ተከታትለው እንደወጡ ኮሎኔል ፈጠን ብሎ በአዳራሹ የኋላ በር ወደ ቢሮው ተጣደፈ::

"ሀሎው ..." አለ ከወዲያ ያለው ጎርናና ድምፅ::

"ሀሎው ... እኔ ነኝ ... ክትትሉ ተጠናቋል ... መረጃውን ከትራፊክ ፖሊስ ካሉ ልጆች ውሰድ ... ተጠንቀቅ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፈጽመው::"

ኮሎኔል ስልኩን ዘግቶ ወደ መስኮቱ ሔደና ከአምስተኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘው የቢሮው መስኮት ባሻገር በጨለማው ውስጥ በመብራት ተንቆጥቁጦ የተንጣለለውን የአዲስ አበባ ከተማ ተመለከተ:: ፈገግ አለ::

'... ዛሬ ለሊቱን እዚህ ጨለማ ውስጥ ተደብቆ ይቆይ ... ጠዋት ግን ጉዱ ይለያል ... እንደቀለደበት ... አሻንጉሊት እንዳደረገው ያላሰበው ያልጠረጠረው ጥይት ያንን ተንኮለኛ የእራስ ቅሉን ...

ፈገግ አለ ኮሎኔል::

... ተፈላጊው ነገ ጠዋት መኪናውን ሊረከብ ወደ ጋራዥ ሲያመራ ... ከዚህ ቀደም የማያውቃቸው ፎቶግራፉን በየኪሳቸው አድርገው የሚጠባበቁት ጭልፊቶች ... አቅርቦ ማሳያ መነፅር በተገጠመለት መሳርያ አልመው ...

ይበልጥ ፈገግ አለ ኮሎኔል አይኖቹን በጨለማው በተዋጠው ከተማ ላይ አፍጥጦ ... ሀሳቡ እርቆ ሔደ ...

በጨለማው ውስጥ ...

# ክፍል ፫

እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተፀፀተ፣
በልቡም አዘነ።

*ኦሪት ዘፍጥረት ፮፡፮*

ጆብ ከሔደ ...

የባቡር ጣቢያው ተጨናንቋል::

ከፊሉ መንገደኛ ግራና ቀኝ ሻንጣ አንጠልጥሎ ያለ ሸኚ ባቡሩ መንገድ እስኪጀምር ትዕግስት አጥቶ ይጠባበቃል ... ሌላው በሦስት በአራት ሸኚዎች ተከቦ እየሳቀ እየተጫወተ ወይ ደርሶ የሚተናነቀውን መባባት፤ የመለየት ስቀቀን እየታገለ የባቡሩን መዘግየት ይመኛል ...

የባቡር ትኬቱ ከሚቆረጥበት ትንሽ መስኮት ተነስቶ በሁለት መስመር የተሰለፈው ትኬት አስቆራጭ መንገደኛ ተራውን ይዞ እቃውን እያንፏቀቀ፣ እያስጠጋ፣ ትኬት የቆረጠው እቃውን አስፈትሾ ወደ ባቡሩ ...

"እባክህን እሳቸውን ቶሎ አሳልፋቸው::" አለ ትኬት የቆረጡትን ተጓዦች ወደ ፍተሻ የሚመራው የባቡር ጣብያው ሰራተኛ የሚመራቸውን ህፃን ትከሻ በግራ እጃቸው ይዘው በቀኛቸው አነስተኛ ያረጀ የጨርቅ ከረጢት ያንጠለጠሉ፤ የተቀዳደደ ጥቁር ረጅም ካፖርት ወደ አደረጉ አንድ መላጣ አይነስውር እያመለከተ::

ፈታሹ ቀና ብሎ አያቸው::

ቀጠን ብሎ ስልከክ ያለ ፊታቸው ላይ አይን ቶሎ የሚገቡ ነገሮች ቢኖሩ በመነጽር ያልተከለሉ በሞራ የተሸፈኑ ሁለት ነጫጭ አይኖቻቸው ናቸው::

"ፋዘር ይጠጉ::" አለ ፈታሹ ተራ የሚጠብቁ መንገደኞች ለአይነስውሩ ሽማግሌ ቅድሚያ ቢሰጥ ቅዋሜ እንደማይኖራቸው ተስፋ አድርጎ::

የሽማግሌው እጅ ትከሻው ላይ ያረፈበት ዕድሜው ከአስር ዓመት የማይበልጥ ህፃን ፈጠን ብሎ የሽማግሌውን ግራ እጅ ይዞ እየጎተተ ለፍተሻ ከተሰለፉበት መስመር ወጥቶ ወደፊት አስጠጋቸው:: ወዲያው አይኖቹ ከጆርባ አንድ አነስተኛ ሻንጣ ይዛ ከተሰለፈች ሴት አይን ጋር ተጋጨ:: ሴትየዋ ጠቀሰችው - 'ሂድ ... አትፍራ::'

"ምንድነው የያዙት ... አባት?" አለ ፈታሹ እንደዋዛ የሽማግሌውን የጨርቅ ሻንጣ ዚፕ ከፍቶ እጁን ወደ ውስጥ ተመለከተ::

"ልብስ ነው ልጄ::" ሽማግሌው አንሾካሾኩ::

ፈታሹ ዘምቢል ከምታክለው የሽማግሌው ሻንጣ ውስጥ እየመዘዘ ያወጣቸውን ሁለት ያደፉ ሸሚዞች ይዞ ሻንጣው ውስጥ ተመለከተ:: በስተቀኝ ያገለገሉ ልብሶች፣ የአንገት ልብስ፣ የተቀዳደደ ቀይ ካናቴራ ... ያወጣቸውን ሸሚዞች ከሻንጣው መልሶ ዚፕን ዘጋና የጎን ኪሷን ከፈተ ... የግራ ጆሮ መደገፍያው የተሰበረ መነጽር ...

ፈታሹ ቀና ብሎ ሽማግሌውን ተመለከታቸው:: በነጭ ወፍራም ሞራ የተሸፈኑ ትላልቅ አይኖቻቸው አፈጠጡበት...

"ይለፉ አባት::"

ሽማግሌው እንቅልፍ ወሰዷቸዋል ...

"አባባ!" አለ የባቡሩ ተቆጣጣሪ የሽማግሌውን ትከሻ ነቅነቅ አድርጎ::

"አቤት!" አሉ ሽማግሌው ደንገጥ ብለው ከእንቅልፋቸው ተነስተው ድምፁን ወደ ሰሙበት ፊታቸውን መልሰው "እኔን ነው?"

"አዎ ይቅርታ ..." አለ ሸካራው ድምፅ "... ትኬቶን ያሳዩኝ::"

ሽማግሌው ፈጠን ብለው ከደረቡት የተቀዳደደ ከፖርታቸው የግራ ኪስ ውስጥ ገቡ:: በባቡሩ መስኮቶች ውስጥ የሚታዩት የኤሌክትሪክ ብርሃን ባቡሩ ወደ አንድ ከተማ እንደደረሰ ያስረዳሉ::

"ቶሎ ይበሉ አባባ ..." ተቆጣጣሪው አጣደፋቸው::

ሽማግሌው ከግራ ኪሳቸው ውስጥ የተጣጠፉ ወረቀቶች አወጡ::

"ይቅርታ የእኔ ልጅ ..." አሉ ሽማግሌው ብዥ ብለው ከሚታይዋቸው ወረቀቶች መሀል ለእራሳቸው እና ጎናቸው ለተቀመጠው ልጅ የቆረጡትን ትኬት መርጠው ለተቆጣጣሪው እየዘረጉ::

የባቡሩ ተቆጣጣሪ ሽማግሌውን ችላ ብሎ ግራ በተጋባ ሁኔታ አንዴ ሽማግሌው ከበርካታ ወረቀቶች መሀል ያስችግር መርጠው መዘው ያወጧቸውን ሁለት ትኬቶች አንዴ ደግሞ በወፍራም ነጭ ሞራ የተሸፈኑትን የሽማግሌውን ሁለት ነጫጭ አይኖች ፈዝዞ ሲመለከት ቆየና ድንገት ሽማግሌውን ትቶ ፈጠን ብሎ ወደ ኋላ ተመሰሰ::

ተቆጣጣሪው ወዲያ ማዶ ወደቆመ ሌላ ተቆጣጣሪ ተጠግቶ በጆሮው አንሾካሾከለት:: ሁለተኛው ተቆጣጣሪ እንደ መበርገግ አለና ሽማግሌውን አተኩሮ ተመለከታቸው:: ቀኝ እጁን ወደ ኪሱ ከተተና አንዲት ፎቶግራፍ አውጥቶ አጠናት:: ወዲያው ፈጠን ብሎ የፉርጎውን በር ከፍቶ ወጣ::

ሁኔታውን እየተከታተለ ያንሾካሾካሳቸው የነበረው ሀፃን የሆነውን ሲነግራቸው ሽማግሌው ተረበሹ::

ድንገት ከተቀመጡበት ተነሱ::

"ተነስ ... ወደ መታጠቢያ ቤት ውሰደኝ::"

"ወዴት ነው?" አለ የሽማግሌውን ሁኔታ በጥንቃቄ ሲከታተል የቆየው ተቆጣጣሪ ከጀርባ የሽማግሌውን ትከሻ ያዝ አድርጎ::

"ወደ መታጠቢያ ቤት ነው የእኔ ልጅ::" አሉ ሽማግሌው ድምፁን ወደ ሰሙበት አቅጣጫ ፊታቸው ሳይመልሱ::

"እሺ ይምጡ::" አለ ተቆጣጣሪው "የት ይደርሳሉ?" በሚል መልክ ከፊት ቀድሞ::

"መጥቼስ?"

"ታስረዳቸዋለህ::"

"ይሻላል! ... " አለ ልዑል በገረሜታ "...እነው ሞቼ እነው ቁስ ጠርቼ' አለች ሴትየዋ ... ምን ብዬ ነው የማስረዳቸው? ... መንገድ ላይ እየተታኮሱ ጥሺ ያለፍኩትን'ኮ የእነሱን ሰዎች ነው ... ምንድነው የምላቸው?"

"ወይ የመጣው ይምጣ ... ለመንግሥት እጃችንን እንስጥ::"

"አብደሀል?!" አለ ልዑል ቅንድቦቹን ግንባሩ ላይ ሰቅሎ::

"እሺ ምን ልሁን" አለ ፌይሰል ሁለት እጆቹን በልመና መልክ ወደፊት ዘርግቶ::

ልዑል በረጅሙ ተነፈሰና አይኖቹን ወዲያ ማዶ በተዘረጋው መንገድ ላይ ተከላቸው:: ለአንድ አፍታ ከእራሱ ጋር ሲከራከር ቆየ::

"እ - ፍ! ..." አለ ልዑል በረጅሙ ተንፍሶ የደረሰበት ውሳኔ ትክክል እንዳልሆነ ቢሰማውም ፌይሰልን መንገድ ላይ ትቶት መሄዱ ሲጨንቀው "... ይህን መኪና መንዳት ትችላለህ?"

"አዎ::" አለ ፌይሰል በልዑል ድምፅ ውስጥ ተስፋ ሲሰማው ፈጠን ብሎ::

"ጥሩ ... አንተ ጭነቱን ይዘህ ቀጥል ... እኔ ከጀርባ እከተልሀለሁ ... ወደ ከተማ ከገባህ በኋላ እኔ እስከደርስ ድረስ የግማሽ ሰዓት ጊዜ ስጠኝና ወደ ተባለው ሆቴል ገብተህ ሴትየዋን አነጋግራት ... ሁኔታውን ሁሉ አስረዳት ... ሹፌርህ ጥሎህ እንደሄደና ምን ማድረግ እንዳለብህ ቀጣይ መመርያ እንድትሰጥህ ጠይቃት ... የሚገጥምህ ሁኔታ ሰላማዊ ከሆነ ... እኔም አንተም በየአቅጣጫችን እንቀጥላለን ... ሁኔታው አደጋ ያዘለ ከሆነና ማንኛውም ወገን በአንተ ላይ ጥቃት ለመሰንዘር ከሞከረ ግን ከውጭ እኔ እንዳለሁና ማንኛውም አደጋ ቢደርስብህ እኔ የመኪናውን የነዳጅ ጋን መትቼ ጭነቱን እንደማቃጥለው ገልፀህ አስፈራራቸው ... እኔ በአዚያው አካባቢ ስለምሆን አትጠራጠር ... አንተን ገድለው ለመቀጠል ቢሞክሩ ዛቻህን እፈፅመዋለሁ ..."

"ከሞትኩ በኋላ መኪናውን ብታቃጥል ምን ይጠቅመኛል?" ፌይሰል ፈጠን ብሎ ጀመረ::

"ይቅርታ ከዚህ በላይ ልረዳህ አልችልም ... ላደርገው የምችለው ነገር ቢኖር ሕይወትህ ላይ አደጋ እንዳይደርስ የበኩሌን መሞከር ብቻ ነው:: ከተስማማህ ቀጥል ... የጭነት መኪናውን ይዘህ ወደ ከተማዋ ግባ ከጀርባ እከተልሀለሁ ... አለበለዚያ ግን ..."

"እሺ::" አለ ፌይሰል አማራጭ እንደሌለው ሲረዳ::

ልዑል ከጀርባው የነበረውን የእጅ ሻንጣ አነሳና እግሩ ስር የነበረውን ታጣፊ መትረየስ ከውስጥ ከትቶ ቀና አለ -

"ያወራህልኝ ታሪክ ... ስለልጅህ የነገርከኝ እውነት ከሆነም እግዜር ይርዳህ::" አለ እጁን ዘርግቶ እየተሰናበተው:: "መልካም ዕድል ..."

"በእኔ ይሁንብህ ... እደዘዋለሁ ..." አለ ኮሎኔል ሰዩም ከፊቱ ቆሞ በቁጣ የሚንቀጠቀጠውን ሰው እያረጋጋ "... ከተማዋ ትንሽ ናት በሰዓታት ጊዜ ውስጥ እንደዘዋለን::"

ቤን ሳውል በተቻለው መጠን እራሱን አሰባስቦ ፎቴው ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠና ቀጠለ -

"ኮሎኔል ... ይህ ሰው ከአዲስ አበባ ወጥቶ ለመሸሽግ ቢፈልግ እጅግ በርካታ አማራጮች አሉት:: ከእነዚህ አማራጮች ሁሉ የመረጠው አቅጣጫ የትኛውን እንደሆን አስተውል ..." ቤን ሳውል የተናገረው በኮሎኔል ሥዩም አእምሮ ሰርጎ እስኪገባ ጠበቀና ቀጠለ "... በጅቡቲ ወደብ ተራግፎ! የኢትዮጵያን ድንበር ተሻግሮ የሚገባው አበባ እየተጓጓዘ ያለው በዚህ አቅጣጫ ነው:: ...

"... 'ለምን' ብለህ ጠይቅ ... 'ለምን ይህ ሰው ካላጣው አቅጣጫ ይህን መስመር መርጦ ሩጫ ጀመረ?' ብለህ እራስህን ጠይቅ ... ለመሆኑ አበባውን ወደታቀደለት ስፍራ በሚያጓጉዘው ወገንና በዚህ ሰው መሀል በአሁኑ ሰዓት በምን ያህል እርቀት እንዳለ ታውቃለህ? ከአምስት መቶ ኪሎ ሜትር ብዙ አይዘልም:: ይህ ደግሞ በጥቂት ሰዓታት ሊሸፈን የሚችል እርቀት ነው::"

ቤን ሳውል ከተቀመጠበት ተነሳና ወደ መስኮቱ ሔዶ ውጭ ውጭ ይመለከት ጀመር ...

"ኮሎኔል ..." ቀጠለ ቤን ሳውል "... ይህ ሰው አደንዛዥ እጹን ይዞ እየተጓዘ ወዳለው አካል የሚጣደፈው ለምን ይመስልሀል? ... ምናልባት ለጥቂት ደቂቃዎች ይህን የሀሳብ መስመር ተከትለህ ብትጓዝ እራስህን አሳፋሪ ተወንጃይ ይህን ዛሬ የምታሳድደውን ሰው ደግሞ ብሔራዊ ጀግና ሆናችሁ ታገኛለህ:: እኔ እንኳን ያኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለማልኖር ብዙም ሊያሳስበኝ የሚገባ ጉዳይ አይሆንም:: የሚዘገንነኝ የአንተ እጣ ነው::"

የሰሊቱ ውርጭ እንደ ምላጭ ፊትን ይቀረድዳል ... ከፊት ለፊት እየተከታተለ የሚሽቀዳደመው ንፋስ ፊት ፊቱን ሲለው ጨለማውን እየሰነጠቀ በሚምዘገዘገው የባቡር ጣርያ ላይ በደረቱ ለጥ ብሎ እንደተኛ የቦርሳውን ረጅም የሸራ ማንገቻ ቀኝ ክንዱ ላይ ጠምጥሞ ቦርሳውን ከፊት ለፊቱ ጎለተው::

ያለጥርጥር የባቡር ጣቢያው ጥበቃ አባላት ማንነቱን በእርግጠኝነት አውቀውታል::

ጠባቂዎቹ የባቡሩን መታጠቢያ ቤት በር ሰብረው ሲገቡ፣ መስኮቱ ተከፍቶ ሲያዩ '... ሰውየው ከባቡሩ ላይ በነፍሱ ቀርጦ ዘሏል ...' እንደሚሉ እርግጠኛ ነበር:: ባቡሩ የወለንጪቲን ከተማ አቋርጦ በመለስተኛ ፍጥነት ወደፊት እየተንደረደረ ስለነበር ከባቡሩ ላይ ቢዘል ያንን ያህል አደጋ ላይ የሚጥለው አልነበረም:: የዘቦቹ ጥርጣሬ ይህ እንደሚሆን ስላወቀም ከባቡሩ ላይ ከመዝለል ይልቅ መስኮቱን ከፍቶ ተንጠላጥሎ ጣርያው ላይ ወጣና በደረቱ ተለጥፎ ተኛ::

ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ ለሚቀጥሉት ሰዓታት የአዳኞቹ ወጥመድ በወለንጪቲ ከተማና በዙርያዋ እንደሚሆን እርግጠኛ ነበር::

ሁኔታው ባሳሰበው አቅጣጫ ቢሔድም፣ ባልጠበቀውና ባልጠረጠረው ደቂቃ ድንገተኛ ስህተት ቢፈጽምም ፍጥነቱን ሳይቀንስ ባቀደው አቅጣጫ ወደፊት መቀጠሉ አረጋግቶታል:: ምርጫ የለውም:: ሟቹ የመከላከያ ባልደረባ በስጡት ጥራዝ ውስጥ በተገለፀው ዕቅድ መሠረት አደንዛዥ እፁን የያዘው መኪና ዛሬ ማታ በኢትዮጵያ የጅቡቲ ድንበር ከተማ ከሆነችው ከኤሊዳር እስከ ሚሌ ያለውን ርቀት ሸፍኖ እንደሚያድር በሚቀጥለው ቀን ከሚሌ እስከ ገዋኔ ያለውን እርቀት ብቻ አገባዶ አዳር እንደሚሆን ያውቃል::

ቀደም ሲል የያዘው እቅድ ለሊቱን አዋሽ ደርሶ ማለዳ ተነስቶ አደንዛዥ እፁን የያዘው ተሽከርካሪ ገዋኔ ከመድረሱ በፊት የአደንዛዥ እጹን በእጁ አስገብቶ ... ምን ያደርጋል ... አሁን በሰዓታት እንዲዘገይ ተገዷል:: ቢሆንም ዋናው ጉዳይ እቅዱ አለመጨናገፉ ነው::

የተንጠለጠለበት ባቡር ከመልካ ጂሎ ወደ አዋሽ የሚያደርሰው የባቡር መስመር ከወለንጪቲ ወደ አዋሽ የሚያመራውን የመኪና መንገድ የሚያቋርጥበትን ነጥብ እንዳለፈ ከፊት ለፊት የሚሽቀዳደመውን ንፋስ እንዲያስታግስለት እንደ ጋሻ ከፊቱ የያዘው ሻንጣ ውስጥ ያለው ተንቀሳቃሽ ስልክ ጮኸ::

እዮብ እየተጣደፈ ከቦርሳው ውስጥ ያለውን ስልክ አውጥቶ "ሀሎ!" ግራ ጆሮውን በግራ እጁ ደፍኖ ይዞ ስልኩን ቀኝ ጆሮው ላይ ለጥፎ - "ሀሎ!"

"ሀሎ ... ይሰማል?" አለ ከወዲያ ያለው ድምፅ በደፈናው::

"ይሰማል ... ቀጥል!" አለ እዮብ የጓደኛውን የአቤሰሎምን ድምፅ ሲያዳምጥ ሰውነቱ በደስታ ንዝረት እየተወረረ ... ያ ድምፅ ... ያ እረጋ ያለ፣ በራስ መተማመን የተሞላ ድምፅ 'ሀሎ ... ይሰማል?' ሲል እዮብ ምንም እንኳን በአደጋ ውስጥ ቢሆንም ብቻውን አለመሆኑ ሲሰማው የደስታ ስሜት ጉሮሮው ውስጥ ድንገት እየተሰነቀረበት::

"ከአዲስ አበባ በባቡር መውጣትህን ደርሰውበታል ..." አለ የአቤሰሎም ድምፅ ፈጠን - ፈጠን እያለ "... ወልንጪቲን እንዳለፍክ ከባቡር ዘለህ ማምለጥህን ተረድተዋል:: በአሁኑ ወቅት በወለንጪቲ የሚገኘው የፖሊስ ኃይል በከተማዋ ዙርያ በተጠንቀቅ እየተጠባበቀ ሲሆን ወደ ከተማዋ የሚያስገቡ መስመሮች ሁሉ በስውር ክትትል ተሸፍነዋል ... ምናልባት ከባቡር ዘለህ ወደ ወለንጪቲ በማምራት ፋንታ በእግር ወደ አረርቲ ወይም ወደ በፋ ከተማ ምናልባትም ወደ መኪና መንገዱ ልታመራ ትችላለህ የሚል ጥርጣሬ በመኖሩ በሦስቱ መስመሮች ተንቀሳቅው አሰሳ የሚያደርጉ የፖሊስ አባላት ከዚህ ከአዲስ አበባ በሔሊኮፕተር ወደ ተጠቀሱት አቅጣጫዎች በረዋል::"

"ሀሉ ... ሀሉው!" አለ እዮብ ድንገት ጆሮው ላይ የለጠፈው ተንቀሳቃሽ ስልክ ፀጥ ሲል "ሀሉው!" ስልኩ ተዘግቷል::

እያሳደዱት ነው:: ቢሆንም ከባቡሩ ዘልሎ ሳይወርድ መንገዱን መቀጠሉን አለመጠርጠራቸው አንድ ተስፋ ነው::

ባቡሩ ጡሩምባውን አከታትሎ ለቀቀው:: ባቡሩ ከፊት ለፊት ያለውን ጉብታ አልፎ ወደ ግራ እያደላ ሲመጣ ወዲያ በሩቁ አልፎ አልፎ ጭል ጭል የሚለውን የኤሌክትሪክ ብርሃን ሲመለከት ወደ አዋሽ ከተማ መቃረቡን ተረዳ:: በደረቱ ከተኛበት በጥንቃቄ ቀና ብሎ፤ ሁለት እግሮቹን አንፈራጦ፤ በጉልበቱ ተንበረከከና የቦርሳውን ማንገቻ ፈትቶ ቦርሳውን የገዛ ወገቡ ጋር አሰረው ... በጥንቃቄ እየዳኸ ወደ ኋላ አፈገፈገ ...

ባቡሩ ትንፋሹን እየሰበሰበ፣ እያመቀ ልጓሙን መያዝ፤ ፍጥነቱን መቀነስ ሲጀምር እዮብ በጥንቃቄ ወደተንጠለጠለበት ፋርጎ የኋላ ጫፍ እየተጠጋ፣ እየቀረበ መጣ:: ከፋርጎው ጫፍ ሲደርስ ቀና ብሎ ግራና ቀኝ የመሬቱን ሁኔታ አጠና:: በስተግራው ያለው መሬት ተዳፋት ሆኖ ሲታየው ወደቀኝ አማተረ ... ወሰነ ...

ባቡሩ ወደ አዋሽ ከተማ ከመግባቱ በፊት ከባቡሩ ዘልሎ በስተግራ ያለውን አሸዋማ ሜዳ አቋርጦ ወደ መኪናው መንገድ ወደ አውራ ጎዳናው ተጣደፈ::

'ወደ አዋሽ ሲቃረብ መጠንቀቅ አለበት::' አሰበ::

ከዚያ የሚጠብቀው አደን እንዳለፋቸው ትናንሽ ከተሞች ቀላል እንደማይሆን እርግጠኛ ነበር::

ከመኪናው መንገድ ሲደርስ አረፍ ብሎ ትንፋሹን ሰበሰበ:: ማለዳ ከአዲስ አበባ ወደ ጅቡቲ የሚጓዙ የፈሳሽ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ተሳቢዎቻቸውን እያምዘገዘጉ እንደሚደርሱ እርግጠኛ ነበር::

## ፴፩

ፌይሰል የጭነት መኪናውን እያሽከረከረ የሚሴን ከተማ ሰንጥቆ ገባ:: ከተማዋ ጭር ብላለች:: በዋናው መንገድ ግራ ቀኝ ቆመው ከሚታዩ ጥቂት የጭነት መኪናዎች በስተቀር ውር ውር የሚለው ነዋሪ ጥቂት ነው::

በዝቅተኛ ፍጥነት ቀጠለ ...

'ደንከል ሆቴል' ነው ያለው ሰውየው - '... ሚሴ ከተማ እንደደረሳችሁ ከተማዋን ስታቋርጡ ደንከል የሚባል ሆቴል በአይንህ ፈልግ ... ሆቴሉን እንዳገኘህ ... ከመኪናው ወርደህ ወደውስጥ ግባ ... ወደ ሆቴሉ ገንዘብ ተቀባይ ሄደህ "ወደ አዲስ አበባ የምትልኪው መልዕክት አለሽ ወይ?" በላት:: ተከታዩን መመርያ ትሰጥሀለች::'

ከሆቴሉ ፊት ለፊት እንኳን 'ደህና መጡ - ደንከል ሆቴል' የሚል ምልክት ሲያይ ልቡ በፍጥነት ይመታ ጀመር:: ዙርያውን ገላመጠና መኪናውን አቀዝቅዞ ዳር አሲያዘው:: 'ግማሽ ሰዓት ስጠኝ' ነው ያለው ልዑል:: ሞተሩን ሳያጠፋ ከመኪናው ወረደና ጎማዎቹን እንደሚፈትሽ ሁሉ ተሽከርካሪውን ዞረው:: አካባቢውን ቃኘ:: አይኖቹን እዚህና እዚያ እያማተረ በተለይ እርሱ ላይ አትኩሮት ያለው ሰው ፈለገ ...

ወደሆቴሉ ተጠጋ:: የተቀባው ነጭ ኖራ አረግፏል ... ጭቃ ግርፍ ግድግዳው ተላልጧል ... በረንዳ ላይ በተደረደሩ ወንበሮች ላይ የተቀመጡ ጥቂት እንግዶች ይታያሉ ... ተጠጋ ... ግራና ቀኙን ማተረ ... ከሆቴሉ ውስጥ ሁለት ሰዎች ተያይዘው ሲወጡ ፈጠን ብሎ ወደ ውስጥ ገባ ... ክፍሉ ሰፊ ቢሆንም ጨለምለም ያለ ነው ፊት ለፊት ወደጓዳ የሚያስገባ አንድ በር ይታያል በስተግራ የገንዘብ ተቀባይዋ ባዶ ሳጥን ቆሟል ... ወንበር ሳበና ተቀመጠ::

"ምን ልታዘዝ?"

ቀና ብሎ አያት:: ከላይ እስከታች ድብልብል ያለች በመካከለኛ ዕድሜ ላይ ያለች ሴት::

"ቡና::" አንድ ብር አውጥቶ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠላት::

ቡናው ቢቀርብለትም አልነካውም:: ተጠባበቀ:: ወደጓዳ በሚያስገባው በር አንድ ቀጠን ረዘም ያለች ሴት ብቅ አለችና በክፍሉ መሀል አንድ ጠረጴዛ ከበው ከተቀመጡ ሰዎች ጋር እየተቃለደች ወደ ገንዘብ መቀበያው ሳጥን ሄዳ ተቀመጠች::

ፌይሰል ክፍሉ ውስጥ የተቀመጡትን እንግዶች ሁሉ እርሱን የሚጠባበቁ ይመስል በጥንቃቄ ተመለከታቸው:: ብድግ አለና ወደ ገንዘብ ተቀባይዋ ሄደ -

"ሰላም ..."

"አቤት ...?"

"መልዕክት አለሽ?"

"እ?" አለች ሴትየዋ ግራ በተጋባ መልክ::

"መልሶትን ሳይወስዱ ..." አለች አስተናጋጅዋ ሳንቲሞች ዘርግታለት::

"ያኘው ... ይቅርታ እዚህ አካባቢ ስልክ አገኛለሁ? ... ወደ አዲስ አበባ ለመደወል ፈልጌ ነበር ..."

"ቴሌ ነዋ ... እዚያ ፎቶ ቤትም ያስደውላሉ ግን ውድ ናቸው::"

ሳያወላውል ወደ አመለከተችው ፎቶግራፍ ቤት አመራ -

ያለው አማራጭ እጁን ለመንግሥት ሰጥቶ ... የሆነውን ሁሉ ተናግሮ ... ልጁን የሚያድንበትን መንገድ መፈለግ ነው ... ሌላ ...

"ሀሎው ...?"

"ሀሎው ... እባኮትን አቶ ዘካርያስን ነበር?"

"ይቅርታ ... ከእንግዶች ጋር ናቸው ... ቆይተው ቢደውሉ ..."

"አስቸኳይ ነው በያቸው ... ፌይሰል በይልኝ!"

ስልኩ ጆሮው ላይ ተንጫጫበት::

"ሀሎው ...?"

የአማቹን ድምፅ ሲሰማ ሰውነቱ ተርበተበተበት ... ጉሮሮው ድምፅ አላወጣልህ አለው ...

"ሀሎው ..." ድንገት ደርሶ የተናነቀውን እንባውን እየታገለ "... ሀሎው እኔ ነኝ ፌይሰል ነኝ ..."

"ፌይሰል ..." እረጋ ብለው ጀመሩ አማቹ::

"አቶ ዘካርያስ ..." እንዴት እንደሚጀምር ተማታታበት "... አቶ ዘካርያስ ... ችግር ውስጥ ነው ያለሁት ..." ከየት እንደሚጀምር ግራ ገባው::

"ምን ሆነሀል? ... ደህና አይደለህም ... ሶፊያ ደህና ነች?"

የልጁ ስም ሲጠራ ሆዱ ተገለባበጠ::

"አቶ ዘካርያስ ... ያዳምጡኝ ... ችግር ውስጥ ነው ያለሁት ... ሶፊያ ሪያድ ነች ... እኔ ሚሌ ነኝ ... አደንዛዥ እፅ ይዘህ ካልገባህ ብለው ሶፊያን ሪያድ ላይ ቀምተውኝ ..."

"ምንድነው የምታወራው ...?" ሰውየው ፍፁም ግራ ተጋቡ::

በተቻለው አስረዳቸው ... ወተወተ ... አልገባቸውም ... ቀጠለ ... የሆነውን ... የሚያስታውሰውን ... ዘበዘበ ...

"ፌይሰል ..." አሉ ሰውየው ፌይሰል ከቁጥጥር ውጭ ሲሆንባቸው "... ፌይሰል ... ተረጋጋ ... 'ሚሌ ነኝ' ነው ያልከው? ... አታስብ ለማንኛውም ሁኔታውን ለፖሊስ አሳውቃለሁ ... እዛው ቆይ ..."

ስልኩን ዘግቶ! ሂሳቡን ከፍሎ ከፎቶግራፍ ቤቱ ሲወጣ ከመንገዱ ባሻገር ልዑልን አየው:: መንገዱን በፍጥነት ተሻገረ::

ልዑል ፌይሰል መንገዱን ተሻግሮ ወደ እርሱ እያመራ መሆኑን ሲረዳ ደንገጥ ብሎ ፊቱን አዙሮ ከአንድ የልብስ ሱቅ ዘው አለ:: ፌይሰል ሳያወላውል ተከትሎት ከሱቁ ገባ::

"ምን መሆንህ ነው?! ..." አለ ልዑል ፊቱን ከፌይሰል እያሸሸ በሱቁ መደርደርያ ላይ ከተንጠለጠሉ ልብሶች ውስጥ የሚገዛውን እንደሚያማርጥ ሁሉ አይኖቹን በመደርደርያው ላይ እያንከራተተ "... አብረን ልንታይ አንችልም! ... ምናልባት በከተማዋ መምጣትህን የሚጠባበቁ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ!"

"ማንም የለም::"

"ሞኝ አትሁን እንዲህ አይነት ቁማር አልጫወትም! ... የት ነው ስትደውል የነበረው ... ምን አሉህ ሴትየዋ?" ልዑል ፊቱን እያሸሸ አደራርቦ ጠየቀው::

"ምንም የማውቀው ነገር የለም አሉኝ ገንዘብ ተቀባይዋ ..." አለ ፌይሰል እርሱም ገበያተኛ እንደሆነ ሁሉ ልዑል ጎን ቆሞ::

"እና የት ነበር የደወልከው?" ልዑል አንድ ካኪ ጃኬት ከተሰቀለበት አውርዶ እያገላበጠ እያየ ::

"እማቹ'ጋ ነው የደወልኩት ... አቶ ዘካርያስ::"

"ዘካርያስ? ... የማን ዘካርያስ ነው የምታወራው ... ማናቸው እሳቸው?"

"እማቹ ናቸው ... የምሰራው በእርሳቸው ድርጅት ውስጥ ነው::" ፌይሰል ማብራራቱን ቀጠለ::

"እና ደውለህ ምን አልካቸው?!" አለ ልዑል በረጅሙ ተንፍሶ ጃኬቱን መልሶ በነበረበት እየሰቀለ::

"ነገርኳቸው::"

"ምኑን ነው የነገርካቸው?!" ልዑል ጆሮዎቹን ማመን አቃተው! ጠጋ ብሎ ቆመ::

"ሁሉንም ነገርኳቸው ... ለመንግሥት ... ለፖሊስ ነግረው እንዲደርሱልኝ ..."

"የፈጣሪ ያለህ! ... እራስህን ስተሃል?" አለ ልዑል ድንገት እራሱን መቆጣጠር ያቃተው ይመስል የፌይሰልን ቀኝ ክንድ ጨምድዶ ይዞ:: ወዲያው የሰራው ስህተት ሲታወቀው ፈጠን ብሎ ለቀቀውና "... መኪናውን አስነሳና ከከተማው ወጥተህ ጠብቀኝ ... ነፃ መሆንህን አጣርቼ ከጀርባ እከተልሀለሁ... ሂድ!"

ልዑል ፌይሰል በቆመበት ትቶት ከሱቁ ወጥቶ ሄደ::

በግድ ተረክበው በተለዋጭ መስመር ቢያጓጉዙ ከሁለቱም አቅጣጫ የተደቀነብንን አደጋ ለማምለጥ ይቻለናል::"

"እንዴት አድርጌ ...?"

"አበባው በጅቡቲ ወደብ ገብቶ የኢትዮጵያን ድንበር ካለፈ በኋላ በአዋሽ አድርጎ ቀጥታ አዲስ አበባ እንዲገባ ነው የታቀደው:: ..." ቤን ሳውል ፈጠን ብሎ ቀጠለ "... አሁን የተሻለው አማራጭ አበባውን በሌላ በተለዋጭ መንገድ ማለትም ገዋኒ ከደረሰ በኋላ ወደኋላ መልሶ በሚሌ ወደ ወልዲያ ከዚያም በደሴ በኩል ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ማድረግ ነው::"

"ጥሩ ... ግን ማነው ይህን ግዳጅ ሊወስድ የሚችል?"

"ያንተ ልጆች::"

"እምላኬ! ... እንዴት ነው ...?" ኮሎኔል ድንገት ከተቀመጠበት ተነሳና በቢሮው ውስጥ ይንጎራደድ ጀመር "... አልችልም ... ይቅርታ ግን ይህ ፍፁም ከአቅሜ በላይ ነው::"

"አይሆንም ካልክ ምንም ማድረግ አልችልም:: የሚመጣውን አብረን መጠበቅ ነው ... እኔ የአቅሜንሞክሬአለሁ::" አለ ታውበር ቤን ሳውል ፊቱን ወደ ኮሎኔል መልሶ ቆሞ::

"ምን ማለት ነው 'የአቅሜን ሞክሬአለሁ' ... ነገር ከተበላሸ በኋላ እየመጣህ ... እኔ ምንድነው ማድረግ የምችለው ... ማንን ነው የምልከው?"

"ማንንም ወደዚያ ላክ አልወጣኝም ..." አለ ቤን ሳውል ተረጋግቶ እየቀጠለ "... ገዋኔ ላሉ ሰዎችህ ተለዋጭ ትዕዛዝ አስተላለፍ ነው ያልኩት:: ሁለቱ በቂ ናቸው::"

"ቀደም ሲል ያልነበረ አዲስ ዕቅድ ይዘን ለመንቀሳቀስ ..." ኮሎኔል አቅማማ::

"የምጠይቅህ ጉዳይ እጅግ አስቸጋሪ ነገር እንደሆነ ይገባኛል የተሻለ አማራጭ ግን የለንም::"

"እሺ ተስማማሁ እንበል ግን ምን አይነት ተለዋጭ ትዕዛዝ ነው የማስተላልፈው?"

ቤን ሳውል ወንበሩ ላይ ጣል ወደ አደረገው የእጅ ቦርሳው ተመልሶ ከውስጥ ካኪ ፖስታ አውጥቶ ጠረጴዛው ላይ ጣለለት::

"በአጭሩ ጭነቱን እያጓጓዙ ያሉትን ሁለት ሰዎች ገድለው እቃውን በእጃቸው ማስገባት ... ከዚያ ወዲያ ሊከተሉት ስለሚገባው የጉዞ መስመር ዝርዝሩን ፖስታው ውስጥ ታገኘዋለህ::"

ማለዳ ፀሐይ በስተምስራቅ ያለውን የበረሀ ጥጋት ፍም ስታስመስለው ... ያን ጊዜ ከፊት ለፊቱ ከወለንጪቲ ወደ አዋሽ የሚያመራው አውራ ጎዳና ታየው::

ምንም ተሽከርካሪ አይታይም:: እዮብ ወደ መንገዱ እየቀረበ መጣ:: በስተቀኝ አለፍ ብሎ መንገዱ ቆልቆል ከማለቱም በላይ በስተግራ ሰብሰብ ብለው የበቀሉት ቁጥቋጦች ጥሩ መሸሸጊያ መሆናቸውን ሲያስተውል ወደ ቁጥቋጦቹ ተጠጋ:: ዙርያውን ተመለከተ:: ከወዲያ ከወለንጪቲ አቅጣጫ የሚመጣ የጭነት መኪና እርሱ ከቆመበት ትይዩ ሲያልፍ በአይነ ህሊናው ለመቅረፅ ሞከረ ...

ፈጠን አለና ሦስት ከፍ ከፍ ያሉ ድንጋዮች አንስቶ በአስፋልቱ ላይ አራርቆ አስቀመጣቸው:: እነዚያ ድንጋዮች ከወለንጪቲ እየከነፈ የሚመጣን ተሽከርካሪ መንገድ ዘግተው አላሳልፍ እንደማይሉ ግልፅ ነበር:: ሆኖም የድንጋዮቹን የተወሰጋገደ አቀማመጥ የተመለከተ ማንኛውም ሹፌር የመኪናውን ፍጥነት ለመቀነስ መገደዱ የማያጠራጥር ነው:: የመኪናው ፍጥነት መቀነስ ደግሞ እዮብ መኪናው ላይ ተንጠላጥሎ ለመውጣት የሚያደርገውን ሙከራ ቀላል ያደርገዋል::

በለሊቱ ውርጭ ሲገረፍ ያደረው፣ በቆፈን የተጨማደደው በረሀ ላይ ብቅ ስትል ... ፀሐይዋ የምትጠገብ አትመስልም ነበር:: ማለዳ ላይ ሰውነትን በለሆሳስ እያሻሸች፣ እያባበለች ታሞቅ የነበረች ለጋ ፀሐይ ቀስ በቀስ ማተኮስ፣ ማቃጠል ስትጀምር በረሃው ነፍስ ዘራ::

ችፍርግ ብለው ከበቀሉት ቁጥቋጦዎች ስር እንደተቀመጠ በወለንጪቲ አቅጣጫ እያማተረ ተጠባበቀ:: በባቡር ፉርጎ ጣርያ ላይ ተንጠላጥሎ ያደረ ሰውነቱ እንደተደበደበ ሁሉ ቁስል ሆኗል፣ ከንፈሮቹ ደርቀው ተሰነጣጥቀዋል፤ ለሊቱን በውርጫማው ድቅድቅ ጨለማ ላይ አፍጥጠው ያደሩ አይኖቹ ቀልተዋል፤ ለማረፍ፣ ለማሸለብ፣ ለመተኛት ግን የማይታሰብ ነው::

የመጀመርያው የፈሳሽ ጭነት ተሽከርካሪ ተሳቢውን እያምዘዘገ በሩቁ ብቅ ሲል እዮብ ሽብረክ ብሎ ለመሮጥ ተዘጋጀ::

የጭነት ተሽከርካሪው በአስፋልቱ ላይ ተራርቀው ከተቀመጡት ድንጋዮች ደረሰ ፍጥነቱን ግን አልቀነሰም፤ ድንጋዮቹን በስተግራ ትቶ አለፈ ... ከአይን ራቀ:: ከጥሻ ውስጥ ያለችን ሰስ አድብቶ፣ አስልቶ፣ እመር ብሎ ሲይዝ እንዳሰበ ነብር ሰውነቱ ሁሉ ጡንቻ ሆኖ ለመሮጥ፣ ለመዝለል፣ ለመንጠላጠል አፍታዎች ይጠባበቅ የነበረው እዮብ ሽብረክ እንዳለ ቀረ::

"ድንጋዮቹ!" አለ በብስጭት::

ግራና ቀኝ አጣርቶ አይቶ ወደ መንገድ ሮጠ:: ተጨማሪ ድንጋዮች በአስፋልቱ መንገድ ላይ አሰባጥሮ ኮልኩሎ ወደ ቁጥቋጠው እየተጣደፈ ተመለሰ::

ሁለተኛው ተሽከርካሪ ከወለንጪቱ አቅጣጫ ብቅ ሲል ወደፊት ለመሮጥ ሸብረክ ብሎ የነበረው እዮብ በርከክ አለ:: መኪናው የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ነበር:: ሦስተኛው የፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ግን ለእርሱ በተለይ እንደተላከ ሁሉ በመለስተኛ ፍጥነት መጥቶ ከድንጋዮቹ ሲደርስ ፍጥነቱን ቀንሶ መንገዱን ቀጠለ::

"ማናችሁ እናንተ?" ፌይሰል ከተቀመጠበት ተነሳ::

"ለጠየቅሁህ ጥያቄ አጭር መልስ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ ... ፈቃደኛ ካልሆንክ ሁለታችሁንም እዚሁ ጨርሰን መኪናውን መፈተሽ ይቻላል ... እንድትተባበረን የምጠይቅህ ጊዜ ለመቆጠብ ብቻ ነው ... ከረጢቶቹን ለማሳየት ፈቃደኛ ነህ ወይስ ..."

"ማዳበርያ ነው የጫነው ...?" አለ ልዑል መሀል ገብቶ::

"አንተ ዝም በል!" ከፊት የቆመው ሰው የሽጉጡን አፈሙዝ ልዑል ግንባር ላይ እንደተከለ ትዕግሥቱ ማለቁን በሚያጋልጥ መልክ ጥርሶቹን ገጥሞ አይኖቹን አጉረጠረጠ::

"ዝም ባልል ..." ልዑል ጀመረ::

የድምፅ ማፈኛ የተገጠመለትን ሽጉጥ ልዑል አይኖች መሀል ተክሎ የቆመው ሰው ተኮሰ::

"ድጋሚ እጠይቅሀለሁ ..." አለ ሰውየው በጥይቱ ምት ግንባሩ ሲበታተን ድምፅ ሳያሰማ ወደ ኋላ የተዘረጋውን ልዑልን ፈገግ ብሎ ቁልቁል ሲመለከት ቆይቶ ድንገት እሳት መትፋት የጀመሩ አይኖቹን ፌይሰል ላይ ተክሎ "... እዚህ የተገኘ ነው ምናምንኛ ውይይት ለማካሄድ አይደለም:: እንደነገርኩህ ጊዜ የለንም:: ቶሎ ምርጫህን አሳውቀኝ::"

ፌይሰል ከፊቱ የቆመው ሰው እብድ እንደሆነ ሁሉ አፍጥጦ ተመለከተው::

"ጊዜ እናጥፋ!" ሰውየው አምባረቀ::

"አዲስ አበባ ነው አድርስ የተባልኩት ... ልጄን ..."

"ፈቃደኛ ነህ - ወይስ ..." የሽጉጡ አፈሙዝ ቀዝቃዛ ብረት በአይኖቹ መሀል ሲያርፍ ፌይሰል አይኖቹን ጨፈነ -

"ተኩስ!" አለ ፌይሰል ከፊት ለፊቱ ያለው ሰው የሽጉጡን መደሻ በአውራ ጣቱ ወደኋላ ሲመልስ ለመጨረሻ ጊዜ የሚስቱን የሶፍያን ገፅታ በአይነ ህሊናው ቀረፀና ተጠባበቀ -

ድምፁን ሲሰማ ስሜቱ ተደበላለቀ ... ለቅፅበት ... አይኖቹን ሊከፍት ሞከረና እቃተው ... ጨለማ ... ድጋሚ ተንኳኳ ... አይኖቹን ሲገልጥ ከፊት ለፊቱ ያሉት መሣርያ የጨበጡ ሁለት ሰዎች እንደተደናገጡ ተሰማው::

"አንሳው!" አለ ፌይሰል ግንባር ላይ መሣርያ የደገነው ሰው አንዱ ከጀርባው የቆመው ጓደኛውን እንዴ ደግሞ መሬት ላይ በደም ተጨማልቆ የተዘረጋውን የልዑልን በድን እየተመለከተ::

ወጥመድ ውስጥ ለማስገባት የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ ፈቃደኛ መሆንህ ነው።"

"አደንዛዥ እፁን ልትረከቡኝ ትችላላችሁ ... የጭነት መኪናው ላይ ነው። እኔ የምፈልገው ልጄን ብቻ ነው።"

"ሁሉንም በእርጋታ ነው የምናደርገው። በቅድሚያ እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ታስረዳኛለህ።" አለ እዮብ ከፌይሰል ጀርባ የነበረው ሰው የጣለውን የድምፅ ማፈኛ የተገጠመለትን ሽጉጥ አንስቶ ግራ ኪሱ ውስጥ ከከተተ በኋላ ግድግዳ ተደግፎ የቆመውን ታጣፊ መትረየስ በግራ ትከሻው እያነገበ።

"እኔ አላውቃቸውም ..." አለ ፌይሰል የእዮብ ግራ መጋባት ሲገባው ቀልጠፍ ብሎ "... ሁለት ሆነው ገብተው አደንዛዥ እፁን አሳየን እያሉ ሲያስፈራሩኝ ነው የደረሳችሁት።"

መፍጠን አለበት ...' እዮብ አሰበ '... ቶሎ! ... ቶሎ! ... ሁኔታዎችን ማገናዘብ ... ማነው ከፊቱ ቀድሞ የደረሰው ...?' ወንበሩ ላይ ወደ ተንጋለለው ሰው ተጠጋና መፈተሽ ጀመረ። የገንዘብ ቦርሳውን አውጥቶ ተመለከተ ... ምንም ፍንጭ የሚሰጥ መረጃ የለም ... '... ምናልባት ፖሊሶች ይሆናሉ ...' አሰበ '... ፍጥነት! ... በፍጥነት እርምጃ መውሰድ አለበት ... ምናልባት ተጨማሪ ኃይል በአካባቢው ሊኖር ይችላል ...' ፊቱን ወደ ፌይሰል መለሰ።

"ለማስታወስ ሞክር ... ምንድን ነበር የጠየቁህ?"

"አደንዛዥ እፁን ነው የሚፈልጉት።"

"የት ነው ያለው አደንዛዥ እፁ?"

"መኪናው ላይ ተጭኗል ... ከማጓጓርያው ጋር።"

"የጭነት መኪናው የት ነው ... ቁልፍ አለህ?" አለ እዮብ።

"ሹፌሩ ኪስ ነው ... ገድለው ሬሳውን ደብቀውታል።" አለ ፌይሰል በግራ እጁ የልዑል በድን የተደበቀበትን መታጠቢያ ቤት እያመለከተ።

"የምን ሹፌር?"

"ከጅቡቲ ስነሳ ልዑል የሚባል ሹፌር አብሮኝ ነበር ... እንደገቡ ነው የገደሉት ... መታጠቢያ ቤት ..." ፌይሰል በተሰባበረ ዐረፍተ ነገር ወተወተ።

"የመኪናውን ቁልፍ አምጣ ... ቶሎ በል!"

በሙሉ በእጁ ገብቷል:: የት እንዳለሁ እንደምታውቁ አልጠራጠርም ሆኖም እስካሁን ካልደረሳችሁበት እኔው ልንገራቹህ:: ገዋኔ ነኝ:: ያሰሁበትን የምገልፅላችሁ ከእዚህ በኋላ ምንም ልታደርጉ እንደማትችሉ ስለማውቅ ነው:: የአደንዛዥ እፁን ዘር በእጄ ለማስገባት የሚሻ ወገን በቅድሚያ በኩብ ጠረጴዛ ዙርያ ከእኔ ጋር መደራደር ይኖርበታል:: ይህን ለማድረግ ስምምነት ከጠፋ በማንኛውም ሰዓት ጭንቱ ላይ እሳት እለቅበታለሁ:: ተግባባን?::"

"ሀሎው!" አለ ጎርናና የወንድ ድምፅ::

"ሀሎ!" ፈገግ አለ እዮብ ወጥመዱ ውስጥ ሰተት ብለው እንደገቡለት ሲረዳ::

"እዮብ ..." አለ ጎርናናው ድምፅ ቁርጥ ባለ ቃና "... በአሁኑ ሰዓት የፖሊስ ሰራዊት የመጨረሻውን እርምጃ እንዲወስድ እያስገደድከው ነው ..."

"ፖሊስ?!" አቋረጠው እዮብ "... በእርግጥ ማን እንደሆንክ እርግጠኛ አይደለሁም ... ምናልባት የፖሊስ የደንብ ልብስ አጥልቀህ የሠራዊቱን የመታወቂያ ወረቀት በኪስህ ይዘህ ይሆናል ... ይህ ግን ምንም ማለት እንዳልሆነ ከእኔ የተሻለ አንተ ታውቀዋለህ::"

"አንዴ አዳምጠኝ ..." ሰውየው አቋረጠው "... የፈጸምከውን ወንጀል በሽሽት ልታመልጠው የምትችል ከመሰለህ ጊዜ እያጠፋህ ነው:: ይልቅ እጅህን በሰላም ..."

"አንተ ዝም ብለህ አዳምጠኝ! ..." እዮብ በእልህ ጮሆ በመሀል ገባ "... አሁን እናንተ እኔን የምታስፈራሩበት ሰዓት አይደለም ... የየትኛው ወገን እንደሆንክ አላውቅም ... የየትኛውም ወገን ብትሆን ግድ የለኝም ... በአሁኗ ሰዓት የእኔ የግል ጥያቄ የደህንነት ጥያቄ ነው ... በእናንተ በኩል ደግሞ ከመንግሥትም ሆንክ ከሌላ ፍላጎትህ የአደንዛዥ እጽ ዘሩን በእጅ ማስገባት ነው::"

"ምንድነው የምትፈልገው?" አለ ጎርናናው ድምፅ ቁርጥ ባለ ቃና::

"ገንዘብ ... ገንዘብና ለደህንነቴ ማረጋገጫ ዋስትና ከሰጣችሁኝ ዘሩን መውሰድ ትችላላችሁ::"

"ጥሩ ..." አለ ጎርናናው ድምፅ "... ምን ያህል ገንዘብ ነው የምትፈልገው?"

"ነገ በዚሁ ሰዓት እደውላለሁ! የምጠይቀውን ያህል ገንዘብ እኔ በምፈልገው መንገድ ለማስረከብ ፈቃደኛ ከሆናችሁ የምትፈልጉትን ታገኛላችሁ እስበለዚያ የምትጓጉለት ዘር እሳት ይበላዋል::"

ስልኩን ዘጋና ሂሳቡን ለባለ ሆቴሉ ከፍሎ መንገድ ዳር ወደ እቆማት አነስተኛ የጭነት መኪና ተጣደፈ::

'ነገ የሚያደርገውን የስልክ ጥሪ ሲጠባበቁ ያሰበውን ለማድረግ ጊዜ ያገኛል::' አሰበ::

"እንዴት ነው?" አለ ፌይሰል የእዮብን አይን አይን እያየ::

"አለቃዬን አግኝቼዋለሁ ... መጥፎ ዜና ነው የነገረኝ ...' አለ እዮብ የፌይሰልን አይኖች እየሸሸ "... 'በመንግሥት አካላት ውስጥ መከፋፈል አለ::' ነው ያለኝ '... በተስይ በፖሊስ እጅ እንዳትገቡ ... ወንበዴዎቹ ከጥቂት የፖሊስ አባላት ጋር ተመሳጥረው እያደኗችሁ ናቸው...' ነው የሚለው:: ጥሩው ዜና ደግሞ ..." አለ እዮብ እየሰቀጠጠው "... መንግሥት ልጅህን ከወንበዴዎቹ እጅ ለማውጣት የሳውዲ አረቢያ መንግሥትን ባለስልጣናት ስምምነት አግኝቷል ... የጊዜ ጉዳይ ነው::"

የሰውየው የሽሙጥ ቃና በጠረጴዛው ዙርያ ያሉትን ሁሉ ሲያሸማቅቃቸው ዶክተር ብርሃን ብቻ ዘግይቶ የደረሰ አሽናፊነቱ ፈገግ አሰኘው፡፡ ኮሎኔል ሥዩም ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ከመስጠቱ በፊት በዙርያው ያሉትን ባለስልጣናት አንዴ ገረመመና አይኖቹን መልሶ በደህንነት አማካሪው ላይ ተከላቸው፡፡ ሰውየው በወንበራቸው ላይ ተዝናንተው እንደተቀመጡ አፍጥጠው ሲመለከቱት 'ዛሬ ጉድህን አያለሁ' የሚሉ መሰሉት፡፡

ኮሎኔል ሥዩም ሁኔታዎች ከቁጥጥሩ ውጭ እየሆኑ መምጣታቸው ግልፅ ሆኖ ታየው፡፡ ከዚህ በኋላ ስለአደንዛዥ እፁ ዝርዝር መረጃ እንደሌለው ሆኖ መቅረብ በዙርያው ባሉ ባለስልጣናት ፊት ብቃት የለሽነትን ማመን አለበለዚያም የአደንዛዥ እፁ መረብ አባልነቱን፤ ወንጀለኛነቱን 'ተጠራጠሩ' ብሎ ማለት መሆኑ ሲገባው -

"ክቡርነትዎ ..." በተቻለ መጠን እራሱን አረጋግቶ ጀመረ "... በአሁኑ ወቅት አጅግ አደገኛ የሆነ የወንጀለኛ ቡድን በአገሪቱ ውስጥ የአደንዛዥ እፅ ለማሰራጨት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል ..."

"ተወው-ተወው ይበቃል ..." የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ አቋረጡት "... በእርግጠኝነት ልነግርህ የምችለው ነገር ቢኖር በአሁኗ ሰዓት ይህን ጉዳይ በተመለከተ በቢሮዬ ስር ያቋቋምኩት ቡድን አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ሁሉ በእጁ ማስገባቱን ነው ... በአንተ ወይንም በቡድንህ በኩል ሳገኘው የምችለው ተጨማሪ መረጃ እንደማይኖር እርግጠኛ ነኝ ..." አሉ ሰውየው ሰብሰብ ብለው ተቀምጠው "... በሚከተሉት ቀናት ውስጥ ከአዲስ አበባ ውጭ ባትንቀሳቀስ እመርጣለሁ ... ቢሮህ የታሸገ በመሆኑ ወደእዚያ ለመመለስ አትሞክር፤ ከእቤት ቆይ፡፡ አንድ አንድ መረጃዎችን በመስጠት እንድትተባበር ለሚጠይቁህ ባለሙያዎችም አስፈላጊውን ትብብር እንድታደርግ ይሁን፡፡ መሄድ ትችላለህ፡፡"

ኮሎኔል ሥዩም ያለምንም ተቃውሞ ከመቀመጫው ተነስቶ ሰላምታ ሰጥቶ ወደ ስብሰባ አዳራሹ በር ሲያመራ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ቂም የቋጠሩ የሚመስሉ አይኖቻቸውን አጥብበው ጀርባው ላይ ተክለው ቆዩና ኮሎኔል ከወጣ በኋላ አይኖቻቸውን ወደተቀሩት ባለስልጣናት መለሱ -

"ከአሁኗ ደቂቃ በኋላ ይህን ጉዳይ በቀጥታ የሚከታተለው የእኔው የእራሴው ቢሮ ነው ... የእያንዳንዳችሁ ኃላፊነት ይህን ቡድን መረጃ በማቅረብ እንዲሁም በሌላ በምትጠየቁበት አቅጣጫ መደገፍ ብቻ ይሆናል፡፡ ይህን ቡድን በበላይነት የምመራው እኔው እራሴ ብሆንም ዝርዝር ክንውኖችን ዶክተር ብርሀን ይከታተላል፡፡

ሰውየው ከመቀመጫቸው ተነሱ፡፡

## ፴፰

ከገዋኔ ከተማ ወጥተው በሚሌ አቅጣጫ ተመልሰው በስተግራ ታጥፎ በጭፍራ አድርጎ ወልዲያ የሚያደርሰውን የገጠር መንገድ ሲጀምሩ እዮብ አቅዶ የነበረው ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት ወልድያ ለመድረስ፤ በተከታዩም ቀን ቢችል ደብረታቦር ካልሆነም ንፋስ መውጫ ደርሶ እዚያው ተደብቆ ጊዜ ለመግዛት ነበር::

ከሚሌ መታጠፊያ እስከ ወልዲያ ያለው እዚህም እዚያም የተንደፋፈረውን የጭፍራ አባራማ መንገድ ለማለፍ ግን የጠበቀውን ያህል ቀላል ሆኖ አላገኘውም:: ወልድያ መዳረሻ ላይ መንተፋተፍ የጀመረችውን መኪና እኩለ ለሊት ላይ የፊት ኮፈኗን ከፍቶ በተቻለው አፀዳድቶ መንገድ ቢቀጥሉም ቆንአበ መዳረሻ ላይ ያሉ ትናንሽ ጎጆዎች ሲታዩ አበቃች:: ቆመች::

"ምን ይሻለናል?" አለ ፌይሰል ተረብሾ::

"ውረድ::" አለ እዮብ::

"ወርደንስ?"

"መኪናዋን ትንሽ ከመንገድ ወጣ አድርገን ገፍተን እንደብቃትና እኔ ወደ ከተማ ገብቼ ወይ ሜካኒክ አለበለዚያም ሌላ መኪና እፈላልጋለሁ::"

መኪናዋን ጫካ ውስጥ ከወሸቁ በኋላ እዮብ በእግሩ ወደ ከተማዋ ገባ:: በጨለማው ውስጥ እዚህና እዚያ ከሚሰማው የውሻ ጩኸት በስተቀር ከዋናው መንገድ ግራና ቀኝ የተደረደሩት የተንሳቀሉ ቤቶች ሰው የሚኖርባቸው አይመስሉም::

ወደፊት ቀጠለ::

በስተቀኙ የሚታየውን የግብርና ምርምር ጣቢያ አጥር እንደጨረሰ ከፊት ለፊት የነዳጅ ማደያ ሲያይ ሳያወላውል ተጠጋ::

"ማነህ?" አለ የሽማግሌ ድምፅ በጨለማው ውስጥ::

"እኔ ነኝ!" አለ እዮብ ሳያመነታ ድምፁን ከፍ አድርጎ::

"ማነህ አንተ?" አለ ያው ድምፅ በጨለማው ውስጥ::

እዮብ መልስ ከመስጠቱ በፊት ድምፁ የመጣበትን አቅጣጫ በጥንቃቄ ለየና በጨለማው ውስጥ ወዳለው ሰው ፈጠን ብሎ ተጠጋ::

"እንዴት አመሹ አባቴ ..." አለ በጋቢ ላይ ካፖርት የደረቡ ሽማግሌ አጭር ዱላቸውን እንደያዙ ሲያይ ተረጋግቶ "... ይቅርታ መንገድ ላይ መኪና ተሰብሮብን ነው ... "

"ታድያ ይንጋ እንጂ!" አሉ የነዳጅ ማደያው ዘበኛ በቀኝ እጃቸው ያንጠለጠሉት ዱላ እንዲታይ የፈለጉ ይመስል ወደ ፊት አስቀድመው ይዘው "... በዚህ በውድቅት!"

"እባክዎት ..." አለ እዮብ ድምፁን አለሳልሶ "... የሚያውቁት ሜካኒክ ወይ የገጠር ሹፌር ካለ የድካምዎትን እከፍላለሁ::"

"አይ - ይ ነገርኩህ'ኮ ሲነጋ ሞክር ... በለሊት የሰው ቤት አናንኳኳ!"

ተመለከታቸው:: ሽማግሌ ናቸው:: 'ምንድነው ሊያስደነግጣቸው የሚችል፣ ሊያራራቸው፣ ሊያስበረግጋቸው የሚችል?'

"አባቴ ወድጄ አይደለም የማስቸግርት መንገድ ላይ መቆየት የማይችል ጉዳይ ሆኖብኝ ነው ... እሬሳ ..." አላቸው ድንገት ጠጋ ብሎ ድምፁን ቀንሶ "... ይቅርታ አስቸገርኮት ... እሬሳ ይዘን ነው ... ከአዲስ አበባ ከተነሳን ሁለት ቀናችን ... መኪናዋ ተበላሸችብኝ ... ትራንስፖርት መኪናም ከተገኘ ያሉኝን እከፍላለሁ ..."

"አይ! አይ! ከየት ነው ይርቃል ከከተማው?" በተሰበረው መኪና ላይ የተጫነው እሬሳ መሆኑን ሲሰሙ ሽማግሌው ሽምቀቅ አሉ::

"ከዚሁ ከመዳረሻው ላይ ነው ... አይርቅም::"

"አይ-ይ መጥፎ ሰዓት ላይ ... እንዴት ላድርግህ ይሆን? መኪና እንኳን አይጠፋም ነበር ... ግቢውን ለማን ጥዬ ..."

"የጠየቁኝን እከፍላለሁ ... አላስከፋዎትም:: እባክዎ ይርዱኝ::"

ሽማግሌው የሚጠብቁትን ግቢ ትተው መሄዱን ብዙም ባይወዱትም በአንድ በኩል መኪናዋ ላይ የተጫነው ሁለት ቀን ውሎ ያደረ እሬሳ ... በሌላም በኩል ቃል የተገባላቸው ጉርሻ ...

እያጉተመተሙ በመንደር ውስጥ ለውስጥ ይዘውት ገቡ::

ከተኛበት ተቀስቅሶ ከወገቡ በላይ እራቁቱን ብቻ ያለው ጎረምሳ ሹፌር ግን በቂ ገንዘብ እስኪተከፈለው ድረስ ከእንቅልፉ መቀስቀሱ ብዙም የረበሸው አይመስልም::

"እሬሳ ...?" አለ ወጣቱ ሹፌር "... ብዙ አጃቢ አለ እንዴ ... የኔ መኪና ላንድሮቨር ነች::"

"ይበቃል ... ሁለት ነን ... እኔና ወንድሜ ብቻ ነን::" አለ እዮብ ፈጠን ብሎ::

"እሺ የት ነው የማደርሳችሁ?"

"ሰቆጣ::"

"ኡ! ..." አለ ሹፌሩ ዋጋ የሚያስወድድበትን ሰበብ እያሰበ "... በላይ በወልድያ፣ በኮረም ዞሬ ..."

"አይደለም ... አይደለም በዚሁ ቀጥታ በላሊበላ ..." እዮብ አቋረጠው::

"ኡ! ..." አለ ሹፌሩ አሁንም እየተንገፈገፈ "... በዚህ በጠጠር መንገድ ... የመኪና ፀር!"

"እባክህ የድካምህን ... ያልከኝን እከፍላለሁ ማለዳ ለቅሶኛ ስለሚጠብቁን ነው::"

"እሺ ... መቸስ ምን አደርጋለሁ ... ስንት ትከፍላለህ?..

"ንገረኛ አንተ::"

"ሶስት መቶ ክፈል::"

"እረግ! - እረግ! ... ሌላ መኪና ልትገዛ ነው እንዴ በአንድ ውድቅት ... ተው ጡር ነው!" አሉ ሽማግሌው የብሩን መጠን ሲሰሙ ደንግጠው::

"ግድየለም ከዚህ የሚብስ የለም እከፍላለሁ::" አለ እዮብ ፈጠን ብሎ::

"እ ..." አለ ሹፌሩ እዮብ ሳይከራከር 'እሺ' ሲል ዋጋውን ከፍ አድርጎ አለመጠየቁ እየቆጨው "... እ ... ግን ይሔ ለእሬሳው ነው ለሁለታችሁ ሁለት መቶ ትጨምራለህ::"

"እሺ::"

"ክፍያ በቅድሚያ ነው::" አለ ሹፌሩ ጥርጣሬ ገብቶት::

እዮብ ፈጠን ብሎ ከኪሱ ገባና የተባለውን ገንዘብ አውጥቶ ሰጠው::

"እዚህ ነው ያለው::" አለ ዶክተር ብርሀን ድንገት ከተቀመጠበት ተነስቶ ግድግዳው ላይ ወደ ተለጠፈው ካርታ ተጠግቶ ከንፋስ መውጫ እስከ ወልድያ፣ ከወልድያ እስከ ሰቆጣ የሚያካልለውን አካባቢ በሶስት ጎን ቅርፅ ወፍፍራም፣ ቀያይ እናት ባላቸው ሶስት እስፒሎች እያጠረ "እዚህ ነው ያለው ... ከዚህ ሊወጣ አይችልም::"

አይኖቹ ቀልተዋል፤ ቢሆንም ስለእንቅልፍ የሚያስብበት ሰዓት አልነበረውም:: ከፊት ለፊቱ ተቀምጠው በእንቅልፍ የከበዱ የአይኖቻቸውን ቆቦች የሚርገበግቡ የመረጃ ባለሙያዎች ትክ ብለው ሲመለከቱት እንደተዳከሙ ገባው:: ችላ ብሏቸው ቀጠለ::

"...እዮብን በቅርብ አውቀዋለሁ ... እንዴት እንደሚያስብ በትክክል ይገባኛል ... እስከ አሁን ፖሊሶች ሊይዙት ያልቻሉትም 'ከአሁን አሁን እጃችን ገባ' እያሉ እንዲረጋጉ ከኋላው ፍንጮችን እያንጠባጠበ ከጀርባው በቅርብ እርቀት እንዲከተሉት ስላደረጋቸው ነው:: ይህ በመረጃው አለም ውስጥ የተለመደ የሽሽት፤ እራስን ከጠላት የመሸሸግ ዘዴ ነው:: አንድ ታዳኝ ከጀርባ የሚተወውን መረጃ በጥንቃቄ፣ ጊዜና ቦታን በማገናዘብ የሚያስቀምጥ ከሆነ ተባራሪው በተዘዋዋሪ የአባራሪውን እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል:: ምክንያቱም አዳኙ ከጀርባ የተጣለለትን መረጃ ባገኘ ቁጥር ያንን እያነከ፣ እየዋጠ ሲያዘግም ተፈላጊው ከፊት ለፊት ወደሚፈልግበት ግብ እንዲደርስ ጊዜና እድል ያገኛል::"

"ጥያቄው'ኮ ..." አለ በመረጃው መስሪያ ቤት ከስውር ክትትል ክፍል የመጣው ባለሙያ "... 'የአቶ እዮብ ግብ የት ነው? ... ወዴት ለመድረስ ነው እየሸሸ ያለው?' የሚለው ነው ... ያንን ብናውቅ ዶክተር እንዳልከው ከጀርባ እየተደረገ ያለውን ክትትል በደፈጣ አለበለዚያም በቀለበት ክትትል መቀየር ይቻል ነበር::'

"ይቅርታ አድርጉልኝና ..." አለ አቤሰሎም መሀል ገብቶ "... ቀደም ሲል በነበረው ቡድን ውስጥም ስለሩ ለማስረዳት የሞከርኩ የነበረው፤ አሁንም በተለይ እናንተ የመረጃው ቤት አባላት በቅርብ እንደምታውቁት እዮብ ባልፈጸመው ወንጀል ..."

"እዚህ ላይ! ..." ዶክተር እጁን አንስቶ አቋረጠው "... አሁን እዚህ የምንገኘው የአቶ እዮብን ንፁህነት ወይም ወንጀለኛነት ለማጣራት አይደለም:: የእኛ ኃላፊነት ግለሰቡን በቁጥጥር ስር አውሎ በእጁ ያለው የአደገኛ አደንዛዥ እፅ ዘር በአገሪቱ ተሰራጭቶ ከማንወጣው አዘቅት ውስጥ ከመግባታችን በፊት ..."

"ይቅርታ ..." አለ አቤሰሎም "... የእዮብን ንፁሕነት አንስቼ ለመከራከር ሳይሆን ... ለማሳየት የፈለግሁት እዮብ ባልሰራው ወንጀል ተጠያቂ እየተደረገ በመሆኑ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት የገዛ ነፍሱን ለማዳን ሲል በእጁ ያለውን የአደንዛዥ እፅ ዘር በገንዘብ ለውጦ ከአገር ለመውጣት ማሰቡን ነው::"

"ከአገር መውጣት!" አለ የስውር ክትትሉ ባለሙያ "... ከየት አመጣኸው?"

"እቅዱ ከአገር መውጣት ነው ... ምክንያቱም ያለው አማራጭ ይህ ብቻ ነው:: ..." አለ አቤሰሎም በእርግጠኝነት "... አካሄዱን፣ ሽሽቱን በቅርብ ከተከታተላችሁት ቀስ በቀስ ወደ ጠረፍ እየተጠጋ ነው:: በጥንቃቄ

ብታስተውሉት ከአዲስ አበባ ተነስቶ ገዋኔ ላይ የአደንዛዥ እፁን ዘር በእጁ ካስገባ በኋላ በቅድሚያ ወልድያ ከዚያም ቆንአቦ አሁን ደግሞ በሰቆጣ አቅጣጫ እየሮጠ ነው:: አንድ ጊዜ የሰቆጣን አቅጣጫ ከያዘ በኋላ ወደ ኋላ ካልተመለሰ በስተቀር መድረሻው አድዋ ከተማ ነው:: አድዋ ከደረሰ በኋላ:: "

"ቆይ ቆይ! ..." ዶክተር ብርሃን እጁን አነሳ "... አሁንም የፖሊስ ኃይል የፈፀመው ስህተት ውስጥ እየገባን ነው ... ሰውየውን እንከተል! እዮብ በሰቆጣ አቅጣጫ መንቀሳቀሱን የገመትነው ቆንአቦ ውስጥ ከአንድ ተራ የነዳጅ ማደያ ዘበኛ ካገኘነው የተሰባበረ ሀሳብና '... ወደ ሰቆጣ እንዳያደርሰው ከተዋዋልን በኋላ በላሊበላ አቅጣጫ ጥቂት ኪሎ ሜትሮች እንደተንቀሳቀስን አስገድዶ ከመኪናዬ አስወርዶ፤ ለትራንስፖርት የከፈለኝን ገንዘብ ቀምቶ፤ አይኖቼን በጨርቅ እግርና እጄን በገመድ አስሮ በረሀ መሀል ትቶኝ ሔደ ...' ብሎ መረጃ ከሰጠ አንድ ግለሰብ ነው:: ይህ መረጃ ደግሞ እዮብ እራሱ ከጀርባው ትቶልን የሔደው ማዘናጊያ መረጃ ሊሆን እንደሚችል መጠርጠር ያሻል::"

"ዶክተር ..." አለ አቤሰሎም "... ይህ'ኮ የሚያሳየው እዮብ ሰቆጣ ከደረሰ በኋላ ..."

"ሰቆጣ ከመድረሱ በፊት ወደ'ትም መሔድ ..ይችላል!" ዶክተር ብርሃን መሀል ገባ "... ተመልከት ይህን ካርታ ... የግድ በሰቆጣ አቅጣጫ ስለተንቀሳቀሰ ሰቆጣ ይገባል ማለት አይደለም:: ላሊበላ ከደረሰ በኋላ እንደገና ወደ ቀኝ ታጥፎ ቢፈልግ ወልድያ ... ወደ ፈቀደው መሔድ ይችላል:: ሰቆጣ ገባ ቢባልም የግድ ወደ አድዋ መቀጠል የለበትም:: በቀላሉ በአቧራው መንገድ ወደ ኮረም ተሻግሮ ሊሰወር ይችላል ... ይቅርታ አድርጉልኝ ግን ከአሁን በኋላ እዮብን ከጀርባ መከተል ትክክለኛ ስልት አይመስለኝም:: እንደ እኔ እንደ እኔ አስፈላጊ የሆነው ኃይል ከዚሁ ተንቀሳቅሶ በተባሉት አቅጫዎች በሙሉ በቅድሚያ የቀለበት ከበባ አድርጎ ማለትም አንደኛው አቅጣጫ ·ከሰቆጣ ቁልቁል፤ ሁለተኛው ከቆንአቦ ሽቅብ፤ ሦስተኛው ከቆቦ አግድም በመንቀሳቀስ ላሊበላ ላይ ማጥበብ የተሻለ ይመስለኛል ምክንያቱም በአሁኗ ሰዓት በምንም መንገድ ከዚህ ክልል ሊወጣ አይችልም::"

ስብሰባው ሲያበቃ በስምምነት ያለፈው የክትትል ስልት ዶክተር ብርሃን ያቀረበውን የቀለበት ክትትልን መሰረት አድርጎ የተቀየሰ ነበር::

ከሁለት ሰዓታት በኋላ ከአዲስ አበባ ወደ ላሊበላ ከዚያም ቆንአቦ እና ሰቆጣ የበረረችው ሔሊኮፕተር ውስጥ የተሳፈሩ የመረጃው አባላት በመጀመርያው ረድፍ ተሰማሩ:: የተሰጣቸው መመርያ በሦስት አቅጣጫ ከበባ አድርጎ ከሰቆጣ ቁልቁል፤ ከቆን አቦ ሽቅብ፤ ከቆቦ አግድም ከበባውን በላሊበላ አቅጣጫ ማጥበብ ነበር:: ሁለተኛው ረድፍ ከበባ ሰፋት ባለው ሁኔታ ከምረታ እስከ ወልድያ፤ ከኮረም እስከ ደሴ ባሉ ከተሞች የሚዘረጋ ሲሆን:: በሦስተኛ ረድፍ ምናልባት ተፈላጊው ከመኪና መንገድ ወጥቶ በጫካና በገደላ ገደሉ ለመሸሽግ ወይም ለመሰወር አሰበስዚያም ጊዜ ለመግዛት ሊሞክር ስለሚችል በሁለተኛው ረድፍ ውስጥ ለሚገኙ የወረዳ የፖሊስ ኃይል አስፈላጊው መመርያ ተላልፎ በህብረተሰቡና በአካባቢ ታጣቂዎች እንቅስቃሴ የተደገፈ አሰሳ እንዲደረግ፤ ይህንንም ውጤታማ ለማድረግ የተፈላጊው ፎቶግራፍ በየከተሞቹ መንገድ ላይ እንዲለጠፉ::

በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ሶስቱም ከበባዎች ዙርያ ክብ ገጠሙ::

" ከአገር መውጣት! ... አላደርገውም::" አለ ፌይሰል በስጨት ብሎ::

"ታደርገዋለህ::" አለ እዮብ በተንቀሳቀሰ ቁጥር 'ሲጥ - ሲጥ' የሚለውን የላንድሮቨሯን መሪ ጨብጦ ወደ ንፋስ መውጫ እየተጣደፈ::

ከመምሸቱ በፊት ከንፋስ መውጫ እስከ ምረታ ድረስ ያለውን መንገድ መሸፈን እንዳለበት ቆርጧል::

"እዮብ ..." አለ ፌይሰል በእልህ ጥርሱን ነክሶ "... ምናልባት አልተግባባን እንደሆን ግልፅ ላድርግልህ ... ከዚህ ችግር ውስጥ የገባሁት የገዛ ሕይወቴን ለማቆየት! ለመኖር ስስቼ ከመሰለህ ፍፁም ተሳስተሃል:: ከዚህ ወጥመድ የገባሁት የልጄን ህይወት አተርፍ ብዬ ነው:: አንተ እንደምትለው አላማዬን ከአገር ሸሽቼ በመውጣት ለማሳካት ቢቻለኝ ኖሮ በመጀመርያም ወደ ኢትዮጵያ ባልገባሁ ነበር:: ስለዚህ እዚሁ ከመንገድ ገድለህ ጥለኸኝ ልትሄድ ካሰብህ ያንን ልታደርግ ትችላለህ ... ከነነፍሴ ግን ..."

እዮብ መሪውን ድንገት ወደ ቀኝ ጠምዝዞ ላንድሮቨሯን ዳር አሲያዛትና ሽጉጡን ከቀበቶው ስር አውጥቶ ፌይሰል አይኖች መሀል ተከለው:-

"በእኔ በኩል ችግር የለም 'ተኩስ' በለኝ እዚሁ ጫካ ውስጥ ወሽቄህ መንገዴን እቀጥላለሁ ... ይገባሀል? ... ወይስ ፍፁም ጭንቅላትህ መስራት አቁሟል? ..." እዮብ በእልህ እየተንቀጠቀጠ ቀጠለ "... ይህን ስምንት ኩንታል አደንዛዥ እፅ ይዘን እስከመቼ በአገር ውስጥ ተሸሽገን እንቆይ ነው የምትለው ... ወይስ በአንድ የገጠር ሆቴል ክፍል ተከራይቼ በክብ ጠረጴዛ ዙርያ ከመንግሥት አካላት ጋር እንድደራደር ነው የምትፈልገው?"

"አንተ መንግሥትን ምነው ፈራኸው?"

"ምክንያቱም መንግሥት አንተ እንደምታስበው ለእውነትና ለሀቅ የቆሙ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን ለገንዘብ፣ ለስልጣንና ለዝና የሚሞቱ ... የሚገድሉ እውሬዎችንም ሸሽጎ የያዘ ስለሆነ ነው:: ከመንግሥት ጋር ስደራደር ከማን ጋር እንደምደራደር እንኳን ፍንጭ የለኝም ... አይገባህም ወይ? የምልህ ያለሁት የመንግሥት አካላት ተከፋፍለዋል!"

"ስለዚህ?"

"ስለዚህ መንግሥትን ለድርድር ስጋብዘው 'አይ አልደራደርም ኃይል ተጠቅሜ በእጄ እስገባሀለሁ' ሊል በማይችልበት ቦታ ቆሜ ነው:::"

"የት ነው ይህ ቦታ?"

"መተማን እንዳለፍክ::"

"ሱዳን!" አለ ፌይሰል ጆሮዎቹን ማመን አቅቶት::

"ችግር አለህ ከሱዳን?"

"ሱዳን ሆነህ እንዴት ነው ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የምትደራደረው?"

"ስልክ የሚባል የቴክኖሎጂ ውጤት ከተገኘ ትንሽ ቆየ::"

"ከሱዳን ስልክ ደውለህ የኢትዮጵያ መንግሥትን ... " ፌይሰል ግራ ሲገባው ቅንድቦቹን ሰማይ ሰቀላቸው "... ከዚያ ደውለህ ምን ትላቸዋለህ?"

"የኢትዮጵያ መንግሥትን ብቻ አልወጣኝም:: በእርግጥ በመጀመርያ ደረጃ ከኢትዮጵያ መንግሥት በሁለተኛ ደረጃም ከአደንዛዥ እጹ ባለቤቶች ጋር እደራደራለሁ:: ከኢትዮጵያ መንግሥት ብርን ከወንበዴዎቹ ደግሞ ያንተን ልጅ እጠይቃለሁ ... ሁለቱም 'እሺ' ካሉ እኔም አንተም የምንፈልገውን አገኘን ማለት ነው::"

"በምትኩ ምን ትሰጣቸዋለህ?" አለ ፌይሰል::

"ዘሩን ... የአደንዛዥ እጹን ዘር::"

"አንተ ያለኸው ሱዳን መሰለኝ ... የአደንዛዥ እጹን ዘር ይዘህ ሱዳን ስትገባ ደግሞ ይህች ሱዳን የምትባል አገር የወንበዴዎች ጉረኖ ካልሆነች በስተቀር ዝም ብለው ..."

"ሱዳን እገባለሁ አልኩ እንጂ, 'ዘሩን ይገባ' አልወጣኝም::"

"እና ዘሩን የት ትተወዋለህ?"

"አንተ'ጋ::"

"እኔጋ! ... የት?"

"ሱዳን እንደምገባ እርግጠኛ ስሆን ወይ እዛው መቀመጫ ወይ ወህኒ አለበለዚያም ከወዲሁ አይከል ላይ ከዘሩ ጋር ጥዬህ እሄዳለሁ?"

"አንተ ከሄድክ በኋላ እኔ ዘሩን ለመንግሥት ብሰጥስ?"

"ልጅህን ያገቱ ወንበዴዎች የልባቸውን ይፈፅማሉ::"

"እሺ ... እኔን ከዘሩ ጋር ኢትዮጵያ ውስጥ ጥለህ አንተ ሱዳን የምትገባው ለምንድነው?"

"ምክንያቱም የኢትዮጵያ መንግሥት እጅ እዚያ ሊሻገር ስለማይችል ይህም ሳይሆን ቀርቶ የሱዳን ወይም የኢትዮጵያ መንግሥት አሰበለዚያም ወንበዴዎቼ ቢይዙኝ እንኳን ያላቸው ምርጫ መደራደር ብቻ ስለሚሆን::"

እዮብ የፌይሰልን ተስፋ መቁረጥ ሲረዳ ከጎኑ ያወጣውን ሽጉጥ መጠባበቂያ ጠብቆ መልሶ ከጎን ሻጠውና የላንድሮቨሯን ማርሽ አስገብቶ ወደ ዎረታ ቀጠለ::

ዎረታ ከተማ ሲደርሱ ያጋጠማቸው ሁኔታ ግን ለእዮብ ለእራሱ አስደንጋጭ ነበር:: ለመጀመርያ ጊዜ አዳኙ ከፊቱ ቀድሞ እንደጠበቀው ተረዳ::

የዎረታን ከተማ አልፈው ከመቀጠላቸው በፊት የላንድሮቨሯን የሚንገጫገጭ ሰውነት ለደቂቃዎች አሳርፎ፣ ጎማዎቿን አስፈትሾ፣ ቤንዚን ሞልቶ ለመቀጠል ከነዳጅ ማደያ ሲያቆም ነበር መብረቅ የጣለ ይመስል እዮብ በድንጋጤ በድን የሆነው::

ቤንዚን ቀጅው ወደ ላንድሮቨሯ እየቀረበ መጥቶ ጥቂት እርምጃዎች ሲቀሩት በመኪናዋ ውስጥ የተቀመጠውን የሹፌሩን የተደናገጠ ፊት ሲመለከት ለአፍታ ግራ የተጋባ መሰለና ወዲያው የሹፌሩን አይኖች ተከትሎ ፊቱን መልሶ ወዲያ ማዶ ቀትር ላይ ፖሊሶች መጥተው በለጠፉት ወረቀት ላይ ሲያርፍ እሱም በላንድሮቨሯ ውስጥ የተቀመጠው ሰው ድንጋጤ የተጋባበት ይመስል ባለበት ቆመ:: ወዲያው እንዴ የላንድሮቨሯን መሪ የጨበጠውን ሰው እንዴ ደግሞ ወዲያ ማዶ በማደያው ጣቢያ ግድግዳ ላይ የተለጠፈውን የተፈላጊ ምስል እያፈራረቀ ተመለከተና አንድ እርምጃ ወደኋላ አፈገፈገ::

ድንገት የላንድሮቨሯ ሞተር ተነስቶ የኋላ ጎማዎቿ ከስር ካለው አስፋልት ጋር ሲፋጩ የተሰማውን ሲጥ - ሲጥታ ከጆርባዋ ትታ ስትፈተለክ የነዳጅ ማደያው ጣቢያ ሰራተኛ ከድንጋጤው ባነነ:: ፊቱን መልሶ ወደ ነዳጅ ማደያው ቢሮ ሮጠ -

"ሰውየው! ..." ሌላ ሰው እንዳይቀድመው የፈራ ይመስል የነዳጅ ማደያውን ባለቤት ቢሮ በርግዶ ገብቶ "... ሰውየው! ... አሰፈ ... በዚህ በኩል ... ጠዋት ፖሊሶቹ ... ፎቶግራፉን የለጠፉት ሰውዬ ..."

"ለማለት የፈለግሁት ... የተፈላጊውን እጅ ለመያዝ ብንንቀሳቀስ ምናልባት እንደዛተው ሕጻናቱ ላይ እልሁን እንዳይወጣ ምንም የሚያግደው ነገር የለም::"

"አሀ! ..." ሽማግሌው እስከሪብቶአቸውን እንስተው ጠረጴዛውን እየጠበጠቡ ትኩር ብለው ተመለከቱት "... የምትለው ያለኸው 'ከመኪናው ውስጥ እንዳለ ሕፃናቱ ላይ አደጋ ሊጥል ይችላል ስለዚህ ተፈላጊው ተሽከርካሪው ውስጥ ተደብቆ እኛ ደግሞ ሜካ ውስጥ መሽገን ምጽዓትን እንጠባበቃለን' መሰለኝ::"

"ጌታዬ ..." ዶክተር ብርሃን ግራ ተጋብቶ ጀመረ::

"ጌታዬ - ጌታዬ አትበለኝ! ..." እጃቸውን አወናጭፈው አቋረጡት "... ተጨማሪ ጊዜ እንድታጠፋ አልፈልግም ... ትሰማኛለህ? ... ተጨማሪ ደቂቃዎች እንዲባክኑ አልሻም ... አሁኑኑ አቶ አቤሰሎምን ወደዚያው ላከው ... ከቻለ በሰላም እጁን እንዲሰጥ ሊያግባባው ይሞክር:: አማራጩ ኃይል መጠቀም ከሆነም ጥቃት ከፍቶ ይያዘው:: እኔ አስፈላጊውን ጥቃት ለመሰንዘር ብቃት ያለው ቡድን ከመከላከያ እንዲዘጋጅ አደርጋለሁ በአንተ በኩል ያለውን ዝግጅት በአስቸኳይ አጠናቅቅ:: በዚያ የእፅ ዘር ላይ ምንም አይነት አደጋ እንዲደርስ አልፈልግም ... ያለን ማስረጃ ያ ብቻ ነው::"

"ሕጻናቱ ..." ዶክተር ብርሃን ግራ ተጋብቶ ጀመረ::

"ዶክተር ..." አሉ ሽማግሌው ወንበራቸውን ወደኋላ እንፏቀው ከፊት ለፊታቸው የተበታተነውን ወረቀት ሰብስበው ከአዳራሹ ለመውጣት እየተዘጋጁ "... ሕጻናት ትላንትም ነበሩ ዛሬም አሉ ነገም ይኖራሉ ... ይህ በብሔራዊ ደህንነት ላይ ያንዣበበ አደጋ ነው:: እየሰማኸኝ ነው?"

"እም ጌታዬ::"

የደህንነት አማካሪው ከአዳራሹ ወጡ::

ለሊቱ ፈገግ ሲል ብርዱ እንደ አዲስ ምላጭ ሰውነትን ይሰነጥቅ ጀመር::

ጥቅጥቅ ያለውን ጫካ ሲያልፉ ድንገት ደርሶ ከፊታቸው የተዘረጋውን መጨረሻ የሌለው የሚመስለውን ለጥ ያለ! ሐይቅ ሲመለከት እዮብ በለሊቱ ቆፈን የደረቁትን ጣቶቹን ወደ አፉ አስጠግቶ በትንፋሹ አሞቃቸው:: ወደፊት ሮጥ ብሎ ፊት ፊት ቀድሞ ይመራ የነበረውን አህያ ሲመልሰው ከጀርባ ይከተሉ የነበሩት የአደንዛዥ እፅ የተጫነባቸው አህዮች ችምችም ብለው ቆሙ::

"'ጫካውን ጨርሰን ስንወጣ ሐይቁን እናገኛለን አላልኩም ነበር ወይ ... የታል ጣና?" አለ እዮብ እረኛው ላይ አፍጥጦ::

ባለፈው ምሽት ምረታ ከተማ ሲደርሱ በአንድ የነዳጅ ጣቢያ ግድግዳ ላይ የተለጠፈ የገዛ እራሱን ምስል ሲያይ የተሰማው ድንጋጤ አሁንም የለቀቀው አይመስልም::

ያለጥርጥር መንግሥት አደኑን ይፋ ለማውጣት ደፍሯል:: የእርሱ ግምት አደንዛዥ እጹን ወደ አገር ውስጥ ያስገባው ወንጀለኛ ቡድን ወንጀሉ ገሀድ እንዳይወጣ ሲል በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያለውን መረብ ተጠቅሞ እስከመጨረሻ ድረስ ክትትሉን በስውር ለማድረግ ይገደዳል የሚል ነበር ... የተሳሳተ ግምት::

ምረታ ከተማ ላይ ግልጽ  የሆነለት አስደንጋጭ ሁኔታ መንግሥት ያለምንም ማመንታት ምስሉን በየከተማው፣ በየገጠሩ በመበተን የገባበት ቀዳዳ ገብቶ በእጁ ሊያስገባው መነሳቱ፣ መቁረጡ ነበር:: ይህ ምናልባት መንግሥት የወንጀለኛ ቡድኑ ላይ የበላይነት መያዙንና ይህም አደኑን በገሀድ አውጥቶ ሕብረተሰቡን በመረጃ አቀባይነት እንዲጠቀም እድል የሚሰጠው ነው::

ለጊዜው ከምረታ ከተማ ለመሸሽ ሲሉ ያለ ጥንቃቄ በሐሙሲት አቅጣጫ ቢያመልጡም ከፊት ለፊታቸው የተደቀነው እውነታ ግን ከዚህ ወዲያ ወደየትኛውም ከተማ ሲጠጉ አለመቻላቸው ነበር::

"ፌይሰል ... ከዚህ ወዲያ ዘሩን ይዘን መሸሽ አንችልም::" ነበር ያለው እዮብ ላንድሮቨሩን በጭፍን በሐሙሲት አቅጣጫ እያበረረ::

"ታዲያ ምን ልንሆን ነው?" ፌይሰል ተስፋ በቆረጠ መልክ የጎድን ተመለከተው::

"ያለን ብቸኛ አማራጭ ዘሩን አቃጥለን ..."

"አቃጥለን! ..." ፌይሰል የሚሰማውን ማመን አልቻለም::

"አዳምጠኝ ..." አለ እዮብ ፌይሰል ሲበረግግበት እረጋ ብሎ ያሉበትን አደገኛ ሁኔታ ሊያስረዳው እየሞከረ "... እንዴ አስጨርሰኝ ... ይህን ዘር ይዘን ለመደራደር ብንሞክር ይበልጥ ጥንካሬ እንደሚኖረን ይገባኛል ... ነገር ግን ይህን ስምንት ኩንታል ዘር በመኪና ጭነን የት እንደርሳለን ... ከመኪና ወርደን ተሸክመነው ጫካ ለጫካ እንሸሽግ!"

"እና ብናቃጥለው ምንድነው የሚጨምርልን?"

"ታድያ ምን ልንል ነው? … ዘሩን አምጣ፤ ልጅህን ውሰድ" ሲሉ ምንድነው የማስረክባቸው?"

"ከመጀመርያ 'ልጄን አምጡ ከዚያ በኋላ ዘሩን እሰጣችኋለሁ' ብለህ ብትደራደር የሚከለክልህ ማነው?"

"እሺ እረ … ዘሩ በእጃችን ካልገባ የልጅህን አይን አታይም ብለው ቢደራደሩ የሚከለክላቸው ማነው?"

"እዚህ ላይ ዕድላችንን መሞከር ነው ያለን ምርጫ::"

" 'ዕድላችንን! …" ፊይሰል ቱግ አለ "… ዕድልህን በል እንጂ. አንተ'ማ ነፍስህን አድነህ ጨርሰሃል! የምንደራደረው ኮ በእኔ ልጅ ነፍስ ነው::"

"እሺ …" አለ እዮብ ተስፋ በቆረጠ መልክ "… ሌላ አማራጭ አምጣ … እንዲህ እናድርግ በለኝ::"

"እየው …" አለ ፊይሰል ድንገት አዲስ ሀሳብ ያገኘ ይመስል "… ሚሊ ከተማ እንደደረስን አቶ ዘካርያስ ጋ ደውዬ ነበር …

"ዘካርያስ? … ማናቸው ዘካርያስ?"

"አማቼ ናቸው … የምሰራው በእርሳቸው ድርጅት ውስጥ ነው::" ፊይሰል ማብራራቱን ቀጠለ::

"በእርሳቸው ድርጅት ውስጥ? … የምን ድርጅት? አለ እዮብ ጥርጣሬ በሞላው መልክ አይኖቹን አጥብቦ ፊይሰልን እየተመለከተ::

"በጅቡቲ ወደብ የገባውን ማዳበርያ ያስመጣው ድርጅት::"

"ገባኝ … ማዳበርያውን ያስመጣው አስመጪና ሳኒ …?" አለ እዮብ ጭንቅላቱን ላይና እታች እየነቀነቀ "… ማለት የድርጅቱ ባለቤት … አቶ ዘካርያስ አማችህ ናቸው::" ጥያቄ ሳይሆን በቀጥተኛ አነጋገር::

"ታውቃቸዋለህ?"

"በወረቀት ላይ …" አለ እዮብ ኮሎኔል ነጻሙ አደፍርስ የሰጡት ጥራዝ ውስጥ ያነበበው ትዝ ብሎት "… እና … ሚሊ ስትደርስ ደውለህ ምን አልካቸው?"

"በተቻለኝ ሁሉንም ዘርዝሬ ነገርኳቸው?"

"ምን አድርጉ ብለህ?"

"ጉዳዩን ለመንግሥት አሳውቀው …"

"እንዲደርሱልህ?" እዮብ ፈገግ አለ::

"አዎ::"

የሁለቱ ሰዎች ሁኔታ ያደናገጠው የጣናነሽ ረዳት ወፍራሙን ገመድ በሁለት እጆቹ እንደጨበጠ በወደቡ ዳር ቆሞ ትዕይንቱን ይከታተል ጀመር ...

ከፊተኛዋ ጀልባ ላይ የወረደው ሰው ቀድሞ ደረሰ:: መሳርያውን ወደፊት እንደ ደገነ ከጣናነሽ ተጓዦች ሲደርስ መሳርያውን አቀባበለና አፈሙዙን ረዳቱ ላይ ደገነ:: ከጀርባ ይከተል የነበረው ሰው ሰብሰብ ብለው ወደ ጣናነሽ ለመሳፈር ይጠባበቁ የነበሩትን ተጓዦች ችላ ብሎ ጣናነሽ ላይ ዘሎ ወጣ ... ያለማወላወል በሁለተኛው ደርብ ያሉትን ተጓዦች ግራና ቀኝ እየገፈታተረ አልፎ የመርከቧ ካፕቴን'ጋ ሲደርስ የመሳርያውን አፈሙዝ ሰውየው መሀል ደረት ላይ ተከለ::

"ሀሎው ... እኔ ነኝ ... እንደምን ዋሉ ... አዎ ..."

አቤሰሎም ስልኩ ውስጥ ሲነጋገር ሻለቃው ከመቀመጫው ተነስቶ ቆመ ... እንደመቁነጥነጥ አደረገው::

" ... ዛሬ ጠዋት ... አንድ መርከብ ... አዎ ጌታዬ ..." አቤሰሎም የሆነውን ሁሉ በስልኩ ውስጥ ለሚያነጋግረው ሰው ካብራራ በኋላ መመርያ ጠየቀ ... ለአፍታ ዝም አለና ሲቀጥል "... ጌታዬ ... ሁኔታው አሳሳቢ ስለሆነ የመጨረሻውን አማራጭ ለመጠቀም ቢፈቀድልኝ ..." አለና አይኖቹን ጣርያው ላይ ሰቅሎ ሲያዳምጥ ቆየ "... አዎ ... እዚሁ ነው ያለው::" ፊቱን ወደ ሻለቃው መልሶ "... የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ ሊያነጋግሩህ ይፈልጋሉ::" አለ በአጭሩ::

ሻለቃው ስልኩን ተቀብሎ በተጠንቀቅ ቆሞ ሰውየውን ሲያነጋግር ከቆየ በኋላ "... እሺ ጌታዬ ... ተቀብያለሁ::" አለና ስልኩን ለአቤሰሎም መልሶ አቀበለው::

አቤሰሎም ስልኩን ተቀብሎ፤ ሰውየውን ተሰናብቶ ከዘጋ በኋላ ፊቱን ወደ ሻለቃው መለሰ:-

"ሻለቃ ... እንደሰማኸው ከአሁን በኋላ በእኔ የትዕዛዝ ሰንሰለት ስር ነህ ... ስለዚህ የምሰጥህን መመርያ ያለማወላወል እንድትፈፅም እፈልጋለሁ ..."

"ተቀብያለሁ::" አለ ሻለቃው ፊቱ ላይ መከፋት ሳይታይበት::

"ጥሩ ..." አለ አቤሰሎም ወደ በሩ እያመራ:: ከበሩ ሲደርስ ፊቱን መለሰ "... አሁን ማድረግ የምንችለው ነገር ቢኖር ወደባሕር ትራንስፖርት ሄደን መጠበቅ ነው:: ጠላፊዎቹ እንዳሉት በአምስት ሰዓት የተባለውን ግንኙነት ካደረጉ ማን እንደሆኑ ማረጋገጥና ምን እንደሚፈልጉ ማወቅ እንችል ይሆናል ... ምናልባት ጠላፊው ተፈላጊው ግለሰብ ከሆነ ..." ከክፍሉ ወጣ::

አቤሰሎም "... ቀደም ብዬ የጠቀስኩልህ የመንግሥት አካላት እዛው ድረስ መጥተው ነው ሊያነጋግሩህ የሚፈልጉት::"

"አይሆንም! ..." እዮብ በረገገ "... በፍፁም አይሆንም! ተጠንቀቁ ማንም ወደዚህ ለመቅረብ ቢሞክር ... ለአፍታ አላመነታም! መርከቧን እቃጥላታለሁ! በተሳፋሪዎቿና በጭነቱ ላይ እሳት ለቅቄበት አብሬ እቃጠላለሁ! አቤሰሎም አትጠራጠር አላወላውልም! ማንም እንዳይቀርበኝ!"

"እዮብ ... እዮብ ተረጋጋ! ..." አለ አቤሰሎም ድምጹን በተቻለው ለስለስ አድርጎ "... ማንም የአንተን ይሁንታ ሳያገኝ ወደ መርከቧ አይንቀሳቀስም ... እመነኝ ... እኔ ብቻዬን እመጣለሁ ... አታስብ የመቶ አርባ ዜጎችን ሕይወት አደጋ ላይ የሚጥል እርምጃ አልወስድም::"

"አንተ ምን ልትሰራ ነው የምትመጣው? ..." አለ እዮብ ግራ ተጋብቶ "... ሊያነጋግሩኝ የሚፈልጉ የመንግሥት አካላት እነማን ናቸው?"

"አሁን እየተጠቀምንበት ባለው ሬድዮ ልገልፅልህ አንችልም:: የተሻለ የመገኛኛ መሣርያ ይዤ ነው ወደ አንተ የምመጣው:: መንግሥት የሚያቀርበውን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ የምትስማማበት ሆኖ እንደምታገኘው አትጠራጠር::"

"እስታውስ ... ብቻህን ነው የምትመጣው! ... ተጠንቀቅ የየዋሕ ሰዎችን ሕይወት የማጥፋት ዓላማ የለኝም::"

"እመነኝ! ..." አለ አቤሰሎም መረጋጋት በሞላበት ቅላፄ "... ከመጀመርያው ጀምሮ በተቻለኝ ልረዳህ እንደሞከርኩ አንተም ብትሆን አትረሳውም ... አሁንም አንተን የሚጎዳ ነገር አልመክርህም ... ምንም የሚያስጋህ ጉዳይ የለም ... ይህን ዕድል ስጠኝ ... መገናኛ መሳርያውን ይዤ ልምጣና ከተዝቢው የመንግሥት አካል ጋር በጉዳዩ ላይ ተወያይ ... በሀሳቡ ካልተስማማህ የመረጥከውን እርምጃ እንዳትወስድ ሊያቆምህ የሚችል ኃይል እንደሌለ እኔም አንተም እናውቃለን ... እሺ በለኝ የመገናኛ መሳርያውን ይዤ ልምጣ::"

"ጥሩ ..." አለ እዮብ አንድ ጊዜ ወደ ፌይሰል ተገላምጦ "... አደራ ስህተት ውስጥ እንድገባ እንዳታስገድደኝ ... ብቻህን ነው የምትመጣው ... በጀልባህ ላይ ሌላ ሰው ባይ እንዳታለህ!"

"እመነኝ!" አለ አቤሰሎም በእጭሩ::

እዮብ ሬድዮኑን ዘግቶ ከመቀመጫው ተነሳ:: በተዘጋው በር መስታወት አሻግሮ ፌይሰልን ተመለከተው::

ከህደት መፈፀሙ ግልፅ ሆኖ ታየው:: ከሰዓታት በኋላ ከመንግሥት አካላት ጋር የሚያደርገው ውይይት አሳማኝ ሆኖ ካገኘው፤ የሚቀርብለትን ሀሳብ ለመቀበል ከተስማማ የአደንዛዥ እፁ ባለቤቶች ወጥመድ ውስጥ እንደሚገቡ ግልፅ ነው ... ይህ ደግሞ የፌይሰል ሴት ልጅ መጨረሻ እንደሚሆን ...

'ምንም ምርጫ የለኝም!' አለ ከራሱ ጋር እየተወያየ '... ምንም ማድረግ አልችልም ... አይኔ እያየ የአንድ ሕፃን ልጅ ሕይወት ለማዳን ስል አገርን አደጋ ላይ የሚጥል እርምጃ ልወስድ አልችልም::' ውሳኔው እንደ ድንጋይ ቢከብደውም ጥርሱን ነክሶ ወደፊት ለመቀጠል ወሰነ::

ሶስተኛው የሬድዮ ግንኙነት የተደረገው ከቀትር በኋላ በስምንት ሰዓት ላይ ነበር:: ግንኙነቱንም ያደረገው ባሕር ዳር ከተማ ትራንስፖርት የሬድዮ መገናኛ ክፍል ያለው አቤሰሎም ነበር::

"ሀሎ ... እዮብ ... ይሰማል?"

"ይሰማል ... ቀጥል!"

"እዮብ ከዚህ በኩል አስፈላጊው ዝግጅት ተጠናቋል:: የመገናኛ መሳርያው ከአዲስ አበባ መጥቶአል! ከአንተም ጋር አስፈላጊውን ድርድር የሚያደርጉት ባለስልጣናት አዲስ አበባ እየተጠባበቁ ነው:: ስለዚህ ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ የመገናኛ መሳርያውን ይዤ በባሕር ትራንስፖርት የጥበቃ ጀልባ ወደ አንተ እመጣለሁ::

"አይሆንም! ..." እዮብ የሬድዮ መገናኛውን ተጭኖ ጮኸ "... የምትመጣው በባሕር ትራንስፖርት የጥበቃ ጀልባ አይደለም ... በተራ የአሳ አስጋሪ ጀልባ ነው ... አንድ ነጠላ ጀልባ ላይ ብቻህን ሆነህ ... ከዚያ ውጪ ትልቅ ጀልባ ላይ ተሳፍረህ ብትመጣ ወይም በአሳ አስጋሪ ጀልባህ ላይ ከአንተ ሌላ ሰው ባይ እስካሁን ስታወራው የነበረው ሁሉ ወጥመድ ነበር ማለት ነው ... ሁለቴ አላስብም ... ተጠንቀቅ! "

"ተቀብያለሁ! ..." አለ አቤሰሎም በጥድፊያ "... ምንም ጥርጣሬ አይያዝህ ... እንዳልከው በተራ የአሳ አስጋሪ ጀልባ ብቻዬን እመጣለሁ።"

እዮብ የሬድዮ ግንኙነቱ እንደተቋረጠ ከመርከቧ ካፕቴን ክፍል ወጥቶ የታገቱት ተሳፋሪዎች ወዳሉበት አዳራሽ ገባ::

"ፌይሰል ..." አለ እዮብ የፌይሰልን ክንድ ጨምድዶ ይዞ ከአዳራሹ እየወጣ "... ማንኛውም ችግር ቢፈጠር ... እስታውስ ከዚህ ወዲያ ማወላወል አንችልም ... ጥንካሬ የሚኖረን ስንጨክን ብቻ ነው ... እና ... እንዳልኩህ ችግር ከተፈጠረ እኔ አንድ ጥይት እተኩሳለሁ ... እንዳታወላውል ... የጥይቱን ድምፅ ስትሰማ ጊዜ ሳትወስድ የመርከቧን ነዳጅ በጥይት ..."

"በጥይት! ..." ፌይሰል ተደናግጦ አቋረጠው "... ነዳጁን ነው በጥይት የምመታው? አብደሀል? ነዳጁ ከተቀጣጠለ'ኮ አደንዛዥ እፁ ተቃጠለ ማለት ነው!"

"ፌይሰል ..." አለ እዮብ ለአፍታ አቀርቅሮ ቀና ሲል "... ፌይሰል አዳምጠኝ ... በደንብ አዳምጠኝ ... መርከቧን ለማቃጠል የሚያስገድደን ሁኔታ ይፈጠራል ብዬ አላስብም ... ግን እራሳችንን ለማንኛውም ሁኔታ አዘጋጅተን መቆየቱ ግዴታ ይመስለኛል:: እኔ የምፈልገው ይህ አደንዛዥ እፅ ባልተፈለጉ ሰዎች እጅ እንዳይገባ ነው፤ አንተ ደግሞ ጥረትህ ልጅህን በሕይወት ማግኘት ነው:: ይህ ሳይሳካ ከቀረ ግን ያለን አማራጭ መጨከን ብቻ ይመስለኛል:: መንግሥት

እጃችንን ከነአደንዛዥ እፁ ከያዘ ምን እንደሚከተል ይገባሀል:: አይዞህ ተረጋጋ ሁኔታው የዛን ያህል ይከፋል ማለቴ አይደለም ... አየህ ወዲህ የሚመጣው ሰው የመረጃ ባለሙያ ነው ስለዚህ መሳርያውን ሰጥቶን ሲሄድ በተቻለው መረጃ ሰብስቦ ነው የሚሄደው ... ይህ መረጃ ደግሞ አትጠራጠር ... ከመንግሥት ጋር ስምምነት ላይ ካልደረስን መርከቧን ለማስለቀቅ የሚጠቀሙበት ነው የሚሆነው::"

"ስለዚህ ...?"

"ስለዚህ ..." አለ እዮብ የፌይሰልን ትከሻ ያዝ አድርጎ "... ስለዚህ የመረጃው ባለሙያ ወዲህ ሲመጣ ተገንዝቦት መሄድ ያለበት ጉዳይ መንግሥት ኃይል ተጠቅሞ መርከቧን ለማስለቀቅ ቢሞክር ያለጥርጥር መርከቧን ማቃጠል የምንችል መሆኑን ነው::

ፌይሰል ጭንቅላቱን በመስማማት ነቅንቆ ወደ አዳራሹ ሲመለስ እዮብ ፊቱን መለሰና ወደ መርከቧ የፊተኛ ክፍል አተና ... አይኖቹን በሐይቁ ላይ አርቆ በባህር ዳር ከተማ አቅጣጫ ተከላቸው ... መጨረሻው እንደደረሰ ተሰማው ...

## ፶፱

የከሰዓቷ ፀሐይ ብ-ው ብላ ትነዳለች ... ትንቀለቀላለች ... ንፋሱ እፍ-እፍ እያለ ምሽቱን ይጣራል ... ያለፈው ለሊት ማዕበል አልፎለት ሳጉን የሰበሰበው ሐይቅ ጊዜ ይውሰድ እንጂ መጪው ምሽት ደርሶ ... አረፋ እያስደፈቀ ... እያስጓራ ... የሚያነሳው ... የሚጥለው ... ማዕበል ይመጣ እንዳለው ልቡ የነገረው ይመስል ... ማሕሌት ቆሞ አንዴ ወደፊት አንዴ ወደኋላ ይናጣል ... ይዋልላል ... መጪው መዓት ... መጪው 'ወዮ! ወዮ!' ይታገስለት ይመስል ... ይማልላል ... ሐይቁ ... ቀጣዩ ማዕበል ...

እዮብ በሁለተኛው የመርከቧ ደርብ ፊት ለፊት እግሮቹን እንፈራጦ፣ አይኖቹን መጨረሻ የሌለው በሚመስለው ሰማያዊ ሐይቅ ላይ ያንሳፍፋል::

በሩቁ በባሕር ዳር አቅጣጫ ስትመጣ ተመለከታት ጀልባዋ:: ፈጠን ብሎ ከመርከቧ ካፕቴን ላይ የቀማውን አቅርቦ የሚያሳይ መነፅር አይኖቹ ላይ አደረገ:: አፍንጫዋን ቀና አድርጋ ከጀርባዋ እየሰፉ - እየሰፉ የሚሄዱ ሁለት አረፋማ ፈለጎች እየተወች ... ትፈጥናለች ... ትጣደፋለች ... ጀልባዋ ...

የገዛ ልቡ ሲመታ ተሰማው ... መሳርያውን ጠበቅ አድርጎ ያዘና ሁለት እግሮቹን ፈርጠጥ አድርጎ እንደቆመ ተጠባበቀ ...

ጀልባዋ እየቀረበች መጣች ... ቀስ በቀስ ቅርጽዋ እየለየ ... ነጥብ ታክል የነበረችው ... ጣት ስታክል በነጩ ፋይበር ግላስ አካሏ ላይ ከአፍንጫዋ እስከ ጭራዋ የተጋደመው አረንጓዴ ቀለም ደመቅ ብሎ ለየ ... የአቤሰሎም ቅርጽ ይታይ ጀመር ... ከጀልባዋ ላይ ሌላ ሰው የለም::

ጀልባዋ ወደ ጣናነሽ ስትጠጋ ከጀርባ የሞተሩን መዘውር የያዘው አቤሰሎም ፍጥነቷን ቀንሶ ፊቱን ወደጎን መለሰና የጎድን ተጠጋ::

"እዛው ቁም!" እዮብ መሳርያውን አንስቶ ቁልቁል አቤሰሎም ላይ አነጣጥሮ ጮኸ::

"እዮብ ተረጋጋ!" አለ አቤሰሎም የጀልባዋን ሞተር አጥፍቶ በሐይቁ ላይ በምትዋልለው ጀልባ ላይ እየተንገዳገደ ተነስቶ ቆሞ::

"እዛው በቆምክበት ልብስህን አውልቅ!"

"ምንም አልያዝኩም!" አለ አቤሰሎም ጃኬቱን አውልቆ ሁለት እጆቹን ወደጎን ዘርግቶ::

"የታል የመገናኛው መሳርያ?"

"ጃኬቴ ውስጥ ነው ... የሳተላይት ተንቀሳቃሽ ስልክ ነው የያዝኩት::" አቤሰሎም ባለበት ጮሆ መለሰ::

"ጥሩ ..." አለ እዮብ መሣርያውን ቁልቁል አቤሰሎም ላይ እንዳነጣጠረ "... ስልኩን በጃኬትህ ውስጥ አድርገህ ጃኬቱን ጠቅልለህ ወርውርና ተመለስ!"

"እረጋ በል ... መርከቡ ላይ ወጥቼ ሳነጋግርህ እፈልጋለሁ::" አለ አቤሰሎም በተረጋጋ ገጽታ::

"ያለፈው ስጋት ውስጥ የሚከትህ አይደለም ..." አለ አቤሰሎም ዘና ብሎ "... የሆነው ሆኗል ... በመሠረቱ የወንጀል መረቡ ውስጥ እንዳልነበርክ ለሁሉም ግልጽ ነው ... የፈጸምከው ሁሉ ያልሞት ባይ ተጋዳይ ቡጭርያ ነበር ... ይህን ደግሞ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ ተገንዝበውታል ... እመነኝ ... እጅህን ስጥ ... የአደንዛዥ እፁን ዘር አስረክብ ... ከጨዋታው ውስጥ ውጣ:: ነፃ ሰው ነህ:: "

እዮብ ጭንቅላቱን በእምቢታ ነቀነቀ::

"እሺ ... ምንድነው የምትፈልገው?" አቤሰሎም ትዕግሥቱ ሲለጠጥ በረጅሙ ተንፍሶ ጠየቀ::

"የመደራደርያ ነጥቦቼን ለአንተ አይደለም የማቀርበው! ..." እዮብ በቁጣ ተወራጨ "... እዚህ የመጣኽው ከባለስልጣናቱ ጋር ልታገናኘኝ ነው:: በቃ! ከአንተ ተጨማሪ ንዝንዝ አልፈልግም! "

"ምርጫ የለህም ..." አለ አቤሰሎም ፍጹም በተረጋጋ ሁኔታ ፈገግ ብሎ "... የምትደራደረው ከእኔ ጋር ነው ... ምክንያቱም ይህን ጉዳይ በተመለከተ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ በቀጥታ የተላክሁት እኔ ነኝ:: ብትቀበለውም ... ባትቀበለውም ያለሁት እኔ ነኝ::"

"ምንድነው የምታወራው?"

"አንተ ምንድነው የምትፈልገው? ..." አለ አቤሰሎም ጭንቅላቱን ወደ አንድ ወገን ዘመም አድርጎ "... ለምን እልህ ትጋባለህ? የምትፈልገውን ተናገር ... ዘሩን አስረክብ ... በሰላም ነፃ ሰው ሆነህ ግባ ... 'አይ አይሆንም' ካልክም ወደ ፈለግኸው አገር መውጣት ትችላለህ ... ገንዘብ ነው የምትፈልገው? ... ይሄን ያህል በል ... የጠየከው ይሰጥሀል ... ከዚያ ውጪ ምንድነው የምትፈልገው?"

"ጥሩ ... ግን አንድ ተጨማሪ ጥያቄ አለኝ ..."

"ምን?"

"የአደንዛዥ እፁን ዘር ይዞ ወደ አገር የገባው ሰው ሕጻን ልጅ ሪያድ ..."

"እርሳው! ..." አቤሰሎም አቋርጦት መሐል ገባ "... የአቶ ፈይሰል ሕጻን ልጅ ሪያድ ውስጥ ታግታለች? አዎ ታግታለች:: ይህ ግን አንተን የሚመለከት ጉዳይ አይደለም::"

"የእራሴን ነፍስ አድኜ ይህን ምንም የማያውቅ ሰው ..."

"አትሞኝ! ..." አለ አቤሰሎም ድጋሚ አቋርጦት "... እርሱ የእራሱ ጉዳይ ነው ... እራስህን አድን!"

"አላደርገውም!"

"አላምንም! ... በፍፁም አላምንም! ... ሊሆን አይችልም!"

"እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ... ያንን እስረኛ ... ሻለቃ ፀጋዬን በነበረበት እስር ቤት ውስጥ በሽቦ አንቆ የገደለው ማን ነበር?"

"ምን አይነት ጥያቄ ነው ይሄ? ... እኔ በምን አውቃለሁ?"

"እኔ ግን ልነግርህ እችላለሁ ..." አለ አቤሰሎም እጆቹን ደረቱ ላይ አጠላልፎ ተዝናንቶ እንደቆመ "... እኔ ነኝ ... እኔ ነኝ በተኛበት አንቄ የገደልኩት::"

"ውሸት! ..." እዮብ የሚሰማው ሁሉ ቅርፅ አልይዝልህ ሲለው ጭንቅላቱን ግራና ቀኝ ነቅንቆ "... ሐሰት! ... አንተ በግቢውም አልነበርክ! ምርመራውን ከጨረስን በኋላ እኔ ዶክተር ብርሃን ቢሮ ደርሼ ስመለስ ከቢሮ ወጥተህ ነበር ... በግቢው ውስጥ አልነበርክም::"

"ካስፈለገ ምልክት ብሰጥህስ ..." አለ አቤሰሎም ፈገግ ብሎ "... የመጨረሻ ምርመራ ያደረግህባቸውን የድምፅ መቅጃ ክሮች አስቀምጠህ የነበረው ለብቻቸው በካኪ ወረቀት ውስጥ አልነበረም?"

"የፈጣሪ ያለህ! ..." አለ እዮብ እውነቱ ጭንቅላቱን ሲመታው "... ቢሮአችንን የሰበርክ ... ሽጉጤን ... ምን አድርገህ ገደልከው ሰውየውን?!"

"መሞት ነበረበት ... ምክንያቱም በፖሊሶች እጅ ቢገባ፤ የሚከተለውን ስቃይ የበዛበት ምርመራ መቋቋም ቢያቅተው የመረጃ ቤቱን ምስጢር ለፖሊስ ኃይሉ ሊዘረግፍ ይችል ነበር ... ይህን ደግሞ የመረጃ ቤቱ የሚፈቅደው አልነበረም::"

"እንዴት? ..." አቤሰሎም ይብሱን ሊዘበራረቅበት "... እንዴት ነው ሰውየው የመረጃ ቤቱን ምስጢር ለፖሊስ የሚዘረግፈው ... ምን አውቆ?"

"እዮብ ..." ፈገግ አለ አቤሰሎም "... ተመርማሪው ከመከላከያ ሚኒስቴር ከተመለመሉት አባላት ጋር ይሰራ እንጂ ከጅምሩም በተደራቢነት ለመረጃ ቤቱ የሚሰልል ነበር ... እዮብ እኔና አንተ ያንን ተመርማሪ ደረቅ ወንበር ላይ አስቀምጠን ጥያቄ በጥያቄ ላይ እያደራረብን ስንወተውተው እንውል የነበረው የመረጃ ቤቱ የማያውቀውን ምስጢር ከእስረኛው ፈልቅቆ ለማውጣት አልነበረም ... ምክንያቱም እያንዳንዷን ጉዳይ የሚወጥንም የሚያስፈጽምም ያው የመረጃ ቤቱ ነበር ... ይህን ደግሞ ሻለቃ ፀጋዬ እራሱም ያውቅ ነበር::"

"ታድያ የምንመረምረው ምን ለማግኘት ነበር?"

"አንተን::"

"እኔን?"

"እየሀ ... የመረጃ ቤቱ ዝርዝር እቅዱን ነድፎ፣ ከፖሊስ ኃይሉና ከመከላከያው ቤት ጥቂት አባላትን መልምሎ እቅዱን በእጅ አዙር እየተቆጣጠረ ቢሆንም አንዳንድ በመረቡ ውስጥ ያልታቀፉ ባለስልጣናት በመረጃ ቤቱ ላይ ጥርጣሬ ማብቀል ጀምረው ነበር:: ለምሳሌ እስረኛው ጥቃት በተፈፀመበት ማግስት በፖሊስ እጅ ከመግባቱ በፊት ተሸቀዳድመን ወደ እኛው የድርጅት ክሊኒክ እንዲዛወር ማድረጋችን መረጃ ቤቱን የሚያሳጣ ነበር:: ይህ ደግሞ በብዙዎች ዘንድ ጥርጣሬን ፈጠረ:: ያንንም ተከትሎ የፖሊስ ኃይሉ ሰውየው እንዲሰጠው እና ተገቢውን ምርመራ እንዲያካሂድ እንዲፈቀድለት በተቀናጀ መልኩ በመንቀሳቀስ የበርካታ ባለስልጣኖችን ድጋፍ አግኝቶ ነበር:: ይህ ደግሞ የመረጃ ቤቱ ሰውየውን ደብቆ ለማቆየት የነበረውን ሐሳብ የማይሞከር አደረገው:: የነበረው ምርጫ ሰውየውን መግደል ነበር:: ሰውየው ሲሞት ደግሞ 'ማን ገደለው?' የሚለው ጥያቄ የማይቀር ነበር:: ስለዚህ የመረጃ ቤቱ እራሱን እንደ ድርጅት ከተጠያቂነት ለማትረፍ አንድ ነጠላ አባሉን መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት ... እንደ አጋጣሚ ሆኖ ድርጅቱ አንተን መረጠ:: ስለዚህ ሰውየውን እኔ እንድገድለው ... አንተ ተጠያቂ እንድትሆን ሁኔታዎች በዶክተር ተመቻቹ::"

"ዶክተርም ያውቃል?!"

"ምኑ አትሁን ..." አለ አቤሰሎም "... ሰውየው በተገደለበት ማታ በግቢው ውስጥ ከነበሩት የመረጃው ቤት አባላት መሀል ስለተላለፈው ውሳኔ የማያውቁ ሁለቱ ተረኛ መኮንኖች ብቻ ነበሩ ... ስለዚህም ነው ወደ እስር ክፍሉ ገብቼ እስረኛውን ከገደልኩ በኋላ ወደ ተረኛ መኮንኖቹ ቢሮ ሄጄ ሁለቱንም የጨረስኳቸው::"

"ለምን ገደልካቸው ... ሰውየውን ከገደልክ በኋላ ከግቢው መውጣት ስትችል ..."

"አልችልም ነበር ... ምክንያቱም አንተ በዶክተር ትዕዛዝ ወደ እስረኛው ገብተህ ምርመራ አድርገህ መውጣትህን የእስር ክፍሉ ኃላፊ በስልክ እንዳሳወቀኝ ከግቢው ውጪ ያቆምኳትን መኪናዬን አስነስቼ ወደግቢው ስገባ በዕለት ክንውን ማስፈርያ መዝገብ ላይ ከመሸ ወዲያ ወደ ግቢው መግባቴ ስለሚሰፍር ያንን ዘገባ ማስወገድ ነበረብኝ ... ያንን ለማድረግ ደግሞ በቅድሚያ ሁለቱ ተረኛ መኮንኖች መሞት ነበረባቸው::"

"የኛስ ቢሮ ... የተሰበረውስ በር ... ሽጉጤስ ...?" እዮብ ከቁጥጥር ውጭ መሆን ጀመረ::

"ጥርጣሬዎች ሁሉ ወደ አንተ ማምራት ነበረባቸው ... ከሟቹ የሰበሰብከውን መረጃና ሽጉጥህን ይዤ በሩን ከፍቼ ወጣሁ ... ይህን ሳደርግ ግን ከተረኛ መኮንኖቹ ውጪ ያሉት ሁሉ የማረፊያ ቤቱ ኃላፊ፣ የእስር ቤቱ ጠባቂዎች ሁሉም እረድተውኛል::"

"ሰውየው ከተገደለ በኋላ የተደረገው ምርመራ ሁሉ ... ዶክተር ብርሃን ወደ እስረኛው ክፍል መግባትህን ካድ ያለኝ ... ማለቱ ፀሐፊው ..." እዮብ የጀመረውን ሳይጨርስ አቆመ::

"ያው አነጋግራቸው::" አለ አቤሰሎም እዮብን እየተመለከተ::

"ስልኩን መሬት አስቀምጥና ወደኋላ አፈግፍግ!"

አቤሰሎም ያለማወላወል ስልኩን መሬት ላይ አስቀምጦ ወደኋላ አፈገፈገ:: እዮብ የመሳርያውን አፈሙዝ እንደደገነ ወደፊት ተራመደና አይኖቹን ከአቤሰሎም ላይ ሳይነቅል ስልኩን አነሳው::

"ሀሎው ..." አለ እዮብ ስልኩን ጆሮው ላይ ለጥፎ::

"እዮቤ!"

"ሀሎው?"

"እዮቤ ... እኔ ነኝ ... እናትህ ነኝ::"

"እማማ?!"

"እኔ ነኝ እዮቤ ... እናትህ ነኝ!"

እዮብ አየር መሳብ እንዳቃተው ሁሉ ደረቱን ላይና እታች ናጠ -

"እማዬ ...!"

ሳያስበው በአይኖቹ ሙሉ እምባ ግጥም አለ::

"ሀሎው ..." አለ አንድ ጎርነን ያለ ድምፅ "... አቶ እዮብ እናትህ በበጎ ሁኔታ ላይ ናቸው ... የተሰጠህን ግዳጅ ከዳር አድርሰህል ... መጥተህ እናትህን መረከብ ትችላለህ ..." ጎርናናው ድምፅ ለአንድ አፍታ ተቋረጠና መልሶ ቀጠለ "... ለማንኛውም ማድረግ የሚገባህ በአቶ አቤሰሎም ይነገርሀል ... ጊዜ ሳትወስድ ፈፅመው::"

ስልኩ ተቋረጠ::

እዮብ ቀና ብሎ አቤሰሎምን ተመለከተው:: ሁኔታውን የተረዳው አቤሰሎም ወደፊት ተራመደና እዮብ የያዘውን መሣርያ ተቀበለው::

"እንኳን ደስ ያለህ ... እናትህ በህይወት አሉ::"

እዮብ ስልኩን ለአቤሰሎም አቀብሎት የጨበጠውን ታጣፊ መትረየስ ቁልቁል እንጠልጥሎ ፈዞ ቆመ::

አቤሰሎም ስልኩን መደወል ጀመረ::

"ሀሎ ...ሻለቃ ... መምጣት ትችላላችሁ::"

በአስር ደቂቃ ውስጥ የደረሰችው የባሕር ትራንስፖርት ጥበቃ ጀልባ ከአቤሰሎም ጋር ከአዲስ አበባ ከመጡት የመከላከያ አባላት ውስጥ አራቱን ብቻ አሳፍራ ነበር:: ጀልባዋ ወደ መርከቧ እንደቀረበች በጀልባዋ ላይ የነበሩትን እየመራ የመጣው ሻለቃ ፈጠን ብሎ ከጀልባዋ ላይ ተንጠላጥሎ መርከቧ ላይ ወጣና በተጠንቀቅ ቆሞ ለአቤሰሎም ሰላምታ ሰጠው::

አቤሰሎም የሻለቃውን ሰላምታ ሳይመልስ ችላ ብሎ ፊቱን ወደ እዮብ መለሰ::

"አቶ እዮብ ቀደም ሲል እንደተነጋገርነው ወደ አዳራሹ ገብተህ አቶ ፌይሰል የያዘውን መሳርያ ብትቀበለው::" አለ አቤሰሎም ቅዝቅዝ ብሎ::

እዮብ አሻግሮ ፌይሰልን ተመለከተ:: እንዳቀረቀረ በዝምታ ወደ አዳራሹ አመራ::

"መሳርያህን ስጠኝ::"

"ምነው? ... ሰላም ነው?" አለ ፌይሰል ግራ በተጋባ መልክ አንዴ እዮብን አንዴ ከአዳራሹ ውጪ የቆሙትን ሁለት ሰዎች በእርቀት እየተመለከተ::

ፌይሰል አይን አይኑን ሲያየው እዮብ አይኖቹን አሸሸ::

"ንገረኝ እንጂ! ... ምን አሉ? ተስማማህ? ልጄስ?" ፌይሰል ወተወተ::

እዮብ ቀና ብሎ ፌይሰል አይኖች ውስጥ አፈጠጠ::

"አብቅቷል ... ፌይሰል አብቅቷል ... ልጅህ ተገኝታለች ... አዲስ አበባ ነው ያለችው::"

እዮብ ድንገት በፌይሰል ጉንጮች ላይ ተከታትለው ዱብ - ዱብ ያሉትን የደስታ እንባዎች ሲያይ ፈጠን ብሎ ፌይሰል የጨበጠውን መሣርያ ተቀበለውና ፊቱን መልሶ ከአዳራሹ ወጣ::

በጥበቃ ጀልባዋ ላይ የነበሩት ሶስት የመከላከያ አባላት ከጀልባዋ ላይ እየተንጠላጠሉ መርከቧ ላይ ወጡ:: በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ በመርከቧ ላይ የነበሩትን አስራ ስድስት ከረጢቶች እየተሸከሙ ወደ አነስተኛዋ ጀልባ አጋቡ:: ሦስቱ የመከላከያ አባላት ጭነቱን አራግፈው መጨረሳቸውን የተመለከተው አቤሰሎም ፊቱን ከጀርባው ወደቆመው ሻለቃ መለሰ::

"ጀልባዋ ላይ ጠብቁኝ::"

ሻለቃው በተጠንቀቅ ሰላምታ ሰጥቶ ሶስቱን አባላት አስቀድሞ ከመርከቧ ላይ ተንጠላጥሎ ወደ ጀልባዋ ወረደ::

አቤሰሎም እያመነታ ጎን ለጎን ወደቆሙት እዮብና ፈይሰል ተጠጋ::

"እዮብ ..." አለ አቤሰሎም በጭንቅ "... አዝናለሁ ... ከዚህ ቀጥሎ እንዳደርግ የታዘዝኩትን እንዳልፈፅም መከፈል የምችለው ማንኛውም መሥዋዕት ቢኖር በከፈልኩኝ ... ግን ... መሆን ያለበት ሁሉ የግድ መሆን ይኖርበታል::"

"ምን እያልክ ነው?..." አለ እዮብ የአቤሰሎምን ፊት ሲያጤን ስጋት ገብቶት "... የአደንዛዥ እፁን ነው የምትፈልጉት ... ያንን እስረክቤአችኋለሁ::"

"አዝናለሁ ..." አለ አቤሰሎም የጨበጠውን የመትረየስ አፈሙዝ እያቀና:: ለአፍታ ከፊት ለፊቱ የቆሙት ሰዎች ፊት ላይ ግራ መጋባት ያየ መሰለው ... ወዲያው ... የለቀቀውን እሩምታ ተከስ ተከትሎ እዮብ በጥይት የተበሳሳ መሀል ደረቱን አፍኖ ወደፊት ሲወድቅ ፈይሰል ወደኋላ ተንገዳገደ፤ በመርከቧ የበረንዳ አጥር ላይ ተገልብጦ ባሕሩ ውስጥ ወደቀ::

አቤሰሎም ወደፊት ተራመደ ... ቁጢጥ ብሎ በደረቱ የተደፋውን እዮብን ገለበጠው:: አልፏል:: አቤሰሎም በረጅሙ ተነፈሰና የእዮብን የፈጠጡ አይኖች በዳሰሳ ዘጋቸው::

"እዮብ ይቅርታ ... ይቅርታ አድርግልኝ::"

ቁጢጥ ካለበት ተነሳ:: ከመርከቧ ላይ ተንጠላጥሎ ወደ አነስተኛዋ ጀልባ ተሻገረ::

"እንመለስ::" አለ አቤሰሎም አይኖቹን ተደራርበው በተከመሩት ነጫጭ የላስቲክ ከረጢቶች ላይ ተክሎ::

ጀልባዋ በዝግታ ተንቀሳቀሰች ... ፊቷን ወደ ባሕር ዳር መለሰች ... ወደ ባሕር ዳር የምታደርገው ጉዞ ከአስር ደቂቃ በላይ የሚወስድ ባይሆንም ባሕር ዳር የደረሰችው ዘግይታ ነበር ... ምሽቱ ገፍቶ ለአይን ይሏል ...

ከባህር ዳር ወደብ ጀልባዋን ሲጠባበቁ የቆዩት የመከላከያ አባላት በሩቁ የጀልባዋን ሁለት የፊት ባውዛዎች ሲያዩ ተቁነጠነጡ:: 'ትንፋሻችሁን ያዙ' እንደተባሉ ሁሉ መደዳ በቆሙበት በዝምታ በጨለማ በተዋጠው ባሕር ላይ አፈጠጡ:: ጀልባዋ ከወደቡ ደረሰች::

ጀልባዋ ላይ የነበሩት የመከላከያ አባላት በተራ ወደ ወደቡ ወረዱ:: እያንዳንዱ ፊት ላይ የሚታየው ሀዘን በደቂቃዎች ውስጥ ወደቡ ላይ ተደርድረው ይጠባበቁ በነበሩት ላይ ተጋባ::
አራቱ የመከላከያ አባላት ግዳጃቸውን ፈፅመዋል:: ይህ ወደቡ ላይ ተደርድረው ይጠባበቁ ለነበሩት የመከላከያ አባላት አስደሳች ነበር:: ስሜታቸውን የጎዳ ነገር ቢኖር ከአዲስ አበባ ድረስ አብሮቸው የመጣው የመረጃ ቤቱ ሰው በግዳጅ ላይ መሠዋቱን ሲሰሙ ነበር:: ይበልጥ የቆጫቸው ግን ተፈላጊው ሰው 'ይዞታል' የተባለው አደገኛ እፅ በመርከቡ ላይ ሳይገኝ መቅረቱ ነበር ... ያ ነበር ያንገበገባቸው::

ሔሊኮፕተሯ ተነሳች ... ወደ አዲስ አበባ::

